

# የሶሻሊስታዊ ዕውቀት

# መሠረተ - ሀሳቦች

ትርጉም - በስለሺ አንዳርጌ

Proudly Brought to you
By
www.binyamhk.wordpress.com

# የፖለቲካዊ ዕውቀት

(Fundamentals of Political Knowledge)

## መሠረተ - ሀሳቦች

ትርጉም - በስለሺ አንዳርጌ

አዲስ አበባ

መስከረም - 1971 ዓ. ም.

Proudly Brought to you
by
www.binyamhk.wordpress.com



# ማውጫ


የተርጓሚው መቅድም ........................ 7

መግቢያ ........................ 11

ምዕ. ፩ ሕብረተሰብ እንዴት እንደሚአድግ ...16
፩. የታሪክ — ቁስ አካላዊ አመለካከት ... 18
— ሕብረተሰባዊ ሕልውናና ሕብረተሰባዊ —ንቃተ ሕሊና ........................ 18
— የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች... 22
— የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች አፈጣጠር ጋር ያላቸው ሕብረት (ዝምድና) ...28

፪. የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊ አቀራረጽ 35
— የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊ ሥርዓትና የባሕላዊ — አዕምሮአዊ ኑሮ ........... 35
— የላዕላይ መዋቅር ርዕዮተ—ዓላማዊ ሚና... 38
— የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊ አቀራረጽ ምንድነው ? ........................ 41

፫. መደቦችና የመደብ ትግል ........... 44
— መደቦች ምንድን ናቸው ? ........... 44
— የመደብ መጨቆኛ መሣሪያ........... 46
— የታሪክ አንቀሳቃሽ ኃይል ........... 51
— ሕዝባዊ አብዮት........................ 53

፬. የማኅበረ — ሰብ ታሪካዊ መልኮች ........ 58
— ቤተሰብና ነገድ .................... 58
— ብሔራዊ ቡድኖችና ብሔር ............ 59
— በብሔራዊ ዕድገት ላይ ሁለት አዝማሚያዎች 62
— የቡርዧ ብሔረተኝነትና ወዝአደራዊ ዓለም አቀፍነት ........................... 63

፭. ታሪካዊ አስፈላጊነትና ሰብዓዊ ክንዋኔ ... 66
— ሰዎች እራሳቸው ታሪክን ይሠራሉ ....... 66
— ታሪካዊ አስፈላጊነትና ነጻነት ......... 69
— ብዙኃንና ግለሰብ .................... 71

ምዕ. ፪ — ካፒታሊዝምና የእርሱ መጨማተር ...... 76

፩. የካፒታሊስት ምርት .................. 77
— ሸቀጥና የሸቀጥ ምርት ................ 78
— የጠቀሜታ ዕሴትና የሸቀጦች ዕሴት..... 79
— ገንዘብ .............................. 85
— የዕሴት ሕግ ......................... 89

፪. የጉልበት በካፒታል (ወረት) መበዝበዝ... 92
— ትርፍ ዕሴት ......................... 92
— ካፒታል (ወረት) ..................... 98
— የካፒታል ክምችትና የወዛደሩ ኑሮ እየከፋ መሄድ ............................... 100

፫— ኢምፔሪያሊዝም ....................... 105
— የካፒታሊዝም የመጨረሻ ደረጃ .......... 105





— መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ... 112

፬. የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውሶች
— በካፒታሊዝም ውስጥ የቅራኔዎች መትባት 118
— የካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ደረጃዎች 121
— በእውር ጭፍን (ያለ ሀሳቦች) ............ 125

ምዕ. ፫— ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር... 133

፩. የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ............ 134
— የአጠቃላይ ሕጎች ሁለንታዊነትና የቅርጾች መለያየት ............................ 134
— አዲሱ ዓይነት ዓለምአቀፋዊ ግንኙነት 140
— የዓለም ሶሻሊስት ምጣኔ— ሀብታዊ ሥርዓት ................................ 148
— መሪው አብዮታዊ ኃይል ............ 154

፪. የወዛደሩ አብዮታዊ እንቅስቃሴ
— እያደገ የሚሄደው የኮሚኒስት ፓርቲዎች ተጽዕኖ ................................ 155
— ሠራተኛው መደብ — ለሰላምና ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል መሪው ኃይል ...158
— የወዛደሩ ሕብረት ለድሉ ዋስትና ነው ...164

፫. ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴ
— የቅኝ ገዥነት መጨማተር .............. 166
— የብሔራዊ አርነት አብዮቶች ........... 167
— ትግሉ ይቀጥላል ..................... 169

፮. የጊዜአችን ዋና ጥያቄ ............ 174

— የሰላም ደህንነት የሕዝቦች ኃላፊነት ነው 175

መደምደሚያ ............ 180

— ሰላም ............ 180


— ሥራ ............ 183

— ዕኩልነት ............ 184

— ነጻነት ............ 186

— ወንድማማችነት ............ 187

— ደስታ ............ 188




# የተርጓሚው መቅድም

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በሰፊ አብዮታዊ ማእበል ተጥለቅልቃለች ። ይህን አብዮታዊ ማእበል ጥራት ለመስጠትና ግቡን በትክክል አነጣጥሮ እንዲመታ ለማድረግ የማርክሲዝም-ሌኒኒዝም መስፋፋት የጊዜውና የዘለቄታው አጣዳፊ ጥያቄ ነው ።ብዙሀኑ ሕዝብ በማርክሳዊ ርዕዮተ-አለምንቃተ-ህሊናው ካልበለጸገ ፤ ካልዳበረ ፤ በዚያም እየተመራ ተግባራዊ ድርጊት ካላከናወነ አብዮት አለ ማለት ብቻ ለምንመኘውና ለምናልመው ሶሻሊዝም አያደርስም ። ለዚህ ደግሞ ተቀዳሚው ነገር የመጻሕፍት (የማርክሲስት-ሌኒንስት) ወደ ሃገር ውስጥ መግባት ይሆናል ። በእርግጥ በዚህ አቅጣጫ እየተሟላ ነው ቢባል አሳፋሪ አይሆንም ። ቢሆንም የሚመጡት መጻሕፍት በኢትዮጵያ የሚገኙ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ የሚረዱዋቸው ናቸወይ? አይደሉም ነው መልሳችን ። ታዲያ የነኝህ መጻሕፍት (የእንግሊዝኛው) ጥቅሙ ለምሁራን አካባቢ ብቻ መሆንን ሊያመጣ አይደለም ወይ ? አዎ ነው ። እንግዲያው ሶሻሊዝም ከምሁራን አልፎ ወደ ሰፊው ሕዝብ ሰርጎ ፤ ሰርስሮ እንዲገባ መደረግ ያለበት ተቀዳሚ ነገር ምንድን ነው ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ማንም ሰው ሊመልሰው የሚገባ ጥያቄ በሃገሪቱ ውስጥ ወዳሉት ቋንቋዎች መመለስ ወይንም መተርጎም ሆኖ እናገኘዋለን ።

እስከ ዛሬ (አብዮቱ ከፈነዳበት ከ፷፮ ዓ.ም. ጀምሮ) የተተረጐሙ ወይንም የተጻፉ መጻሕፍት ብዛታቸውና አይነታቸው እጅግ በጣም አነስተኛ ሆኖ ይታያል ። ይህም

ስለሆነ ሰፊው ሕዝብ ሊያገኛቸው እንዳይችል ሆኖአል ።
ሌላው የመጻሕፍቱን አለመዳረስም ያመጣው ነገር ቢኖር
የወረቀትና የመጻሕፍት መወደድ ነው ። ይህን ጊዜ ይፈ
ታው ይሆናል (ከሰዎች ተግባር ጋር) ።

በተለይ መጻሕፍትን በመተርጐም ወይንም በድርሞ
መልክ በማስቀመጥ ለሰርቶ-አደሩ ሕዝብ እንዲቀርብ ለማ
ድረግ ግለሰብ ወይንም የቡድን ሰራተኞች እስከ አሁን ጥረት
ያደረጉ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ ያየነው ነው ። የጥቂት ሰዎ
ችም ስም ብቻ በመጻሕፍቱ ላይ ተጽፎ እና ያለን ። እውቀቱ
አልኖር ብሎ ሳይሆን የመተርጐም (የመመለስ) ልምድ በሃ
ገራችን ውስጥ ስላልተለመደ ነው ። ታዲያ ይህ ደግሞ አን
ድን አብዮታዊ ሰው አብዮታዊ ስሜቱንና ፍላጐቱን እንዲ
ገልጽ ሰፊ ሜዳ የሚሰጠው በመሆኑ ብዙ አንበናል ፤ ጊዜው
ሁኔታው አንቅቶናል ፤ ለሰፊው ሕዝብ እንታገላለን እናታ
ግላለን ለሚሉ ሁሉ ያገለግላል ብዬ ስለማምን የተቻለኝን
ያህል ለመሞከርና ከሙከራዬም ለመማር ጭምር እኔም
ወደዚሁ ማዘንበል ጀምሬአለሁ ።

ባለኝ ዝንባሌ የተነሳ የተቻለኝን ያህል የአማርኛን
ቋንቋ ለመጠቀምና አዳዲስ ቃላትን ለማስተዋወቅ ጥሬአ
ለሁ።ይህን ያደረኩት ዝም ብለን ብቻ የእንግሊዝኛውን ቃል
በቁሙ ብዙ ጊዜ መጠቀሙ ለቋንቋችንም እድገት ቢሆን
መንገድ እንደማይከፍት መረዳት ይኖርብናል ብዬ ስለማ
ምን ነው ። ይሁን እንጂ ፤ ቃላቱን እኔ እንደተመለከትኳቸው
ለእንባቢዎች አርኪ ሆነው ካልተገኙ ለአማራጭነት

እንግሊዝኛውን ቃል ወይንም ሐረግ በዚህችኛዋ መጻሕፍና
ከዚህ ቀደም በወጣችው «የማርክሲዝም መግቢያ» ያቀረ



ብኩ ስለሆነ አብዮታዊ ገንቢ ሂስ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ።
ካንባቢያን የምማረው ነገር ስላለ ብዙ እጠብቃለሁ ።

ሌላው ደግሞ ላስታውስ የምፈልገው በዚች ትርጉም
ውስጥ በእኔ አስተያየት መጤን አለባቸው የምላቸውን ሃረ
ጐች ያሰመርኩባቸው መሆኑ ነው ።ግን አስማመሩ ሌላም
ገጽ አለው ። አንድ አንቀጽ ፤ ወይንም ዐረፍተ ነገር በደንብ
አልታኘከ ላለው ሰው የተሰመረበትን ብቻ አገጣጥሞ (በዚ
ያው አረፍተ ነገር ውስጥ )ቢያነብ ሃሳቡን እንዲረዳውና
ስሜት እንዲሰጠው ሆኖ የተተረጐመ ነው ።


መጻሕፏ በተለይም ለጀማሪ በቀላሉ እንድትገባ ሆኖ
ነው የተተረጐመችው ። በምትተረጉምበት ወቅትም ከሚ
ተረጐመው መጽሐፍ የተደጋገሙ አረፍተ ነገሮችና ሃሳ
ቦች ስላሉ እነኛን ለመዝለል ተገድጃለሁ ። ምክንያቱም
አንባቢን ማሰልቸት ስለሚሆንና ሌላ አዲስ ሃሳብ ስለማይ
ሰጥ ነው ።

ለመጨረሻ ጊዜ የማሳስበው ለዚች መጽሐፍ ጥሩመሰ
ረትና መንደርደሪያ ለማግኘት «የማርክሲዝም መግቢያን»
ማንበቡ የበለጠ መሆኑን ነው ። ይህን የምልበት ምክንያት
አለኝ፡—መጽሐፎቹን,ስናዘጋጅ መሠረታዊ የማርክሲዝምን
ትምህርት በቅደም ተከተል በመስጠት ላይ ያተኩርን መሆ
ኑን በመገንዘብ ነው ። ለወደፊቱም ሙከራችን ይህንኑ
መሠረተ—ትምህርት ለማስፋፋት ስለሚሆን የሚወጡት
ጽሑፎቻችን (ከተቻለ) ተከታታይ እንዲሆኑ ጥረት እና
ደርጋለን ።

---

ማሳሰቢያ ፤

ዓመተ ምሕረቱ በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው ።




# መግቢያ

የትም ቦታ ያሉ የተሻሉ አሳቢዎች ሁልጊዜም ሕብረተሰብ እንዴት እንደሚአድግ ለመረዳት ሞክረዋል ፡— ሁሉም ዓይነት ፍልስፍናዊ ንድፈ—ሀሳቦች ተብራርተዋል ፤ የመቃወሚያ አሳቦች ተቀምረዋል ፤ በፍትህ መንሠራፋት ላይ ሕዝባዊ እምነትን የሚአንጸባርቁ ፤ ሐሳባዊ ሕብረተሰቦች ተገልጸዋል ። ግን ሣይንሳዊ ዕውቀት ያልዳበረ ስለነበረና ካለፈው ምዕተ — ዓመት በፊት የሕብረተሰብ ግንኙነት በቂ ዕድገት ስለሌለው ሕዝቦች ለረጅም ጊዜ የሕብረተሰብን ዕድገት ዕለታዊ ምክንያቶች ለመግለጽ አልቻሉም ነበር ።

ስለተፈጥሮና ስለሕብረተሰብ ሥርዓተ — ለውጥ ሳይንሳዊ ግንዛቤ እስከ ፲፱ኛው ምዕተ — ዓመት ድረስ መሠረቱ አልተጣለም ነበር ። በዚያን ጊዜ ለተነሱት ገጠመኞችናየሕብረተሰብአዊ ሀሳቦች ጥያቄመልስ የሰጡት የማርክስ ትምህርቶች ነበሩ — ማለትም ማርክሲዝም ። የማርክሲዝም ምንጮች ፡— የጀርመን ፍልስፍና ፤ የእንግሊዝ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚና የፈረንሣዊ ተምኔታዊ ሶሻሊዝም ናቸው ።

ለጀርመን ጥንታዊ ፍልስፍና ሁለት ቀንደኛ ሰዎች ሔግልና ፌውርባህ ነበሩ ።

የሄግል ትልቁ አስተዋጽኦው ዲያሌክቲክስ ወይም የዕድገት ንድፈ — ሀሳብ ነው ። ይሁንና ፤ ንድፈ — ሀሳቡ የተወሰነው ለዓለም የመጨረሻው ምክንያትና መሠረት ለሆነው «ፍጹም ሀሳብ» (ABSOLUTE IDEA)
ዕድገት እንጂ ስለተፈጥሮና ወይም ሕብረተሰብ ዕድገት አልነበረም ።

ፈውርባህ ፤ በሌላ በኩል የተፈጥሮ አገላለጽ የሚኖ
ረው በራሱ በተፈጥሮ ውስጥ ነው በማለት ወደተአምራዊ
ና (ገድላዊ) ሳይንሳዊ ያልሆኑ «የፍጹም ሀሳብ» አመለካከ
ቶችን ለመደጋገም መሂድ አስፈላጊ እንዳልነበር ያረጋግ
ጣል ። ግን የእርሱ አመለካከቶችም የተወሰኑ ነበሩ ። ምክ
ንያቱም የሄግልን የዕድገት ንድፈ — ሀሳብ ተፈጥሮንና
ታሪካዊ ክስተትን ለማስተንተን ዋናነቱን አልተገነዘበም
ነበርና ። ቢሆንም የሄግል ዲያሌክቲክስና የፌውርባኽ ቁስ
አካላዊነት ማርክሳዊ ፍልስፍናን ለመቀመር ምክንያታ
ዊና ሳይንሳዊ ሀሳቦች ያሏቸው ናቸው ።

በፖለቲካዊ ኤኮኖሚ መስክ ከማርክስ ቀዳሚ አዳም
ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ ነበሩ ። እነኝህ የሕብረተሰብ ሀብት
ምንጭ የሰው ጉልበት መሆኑን በማሳየት ለሳይንሳዊ
ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ጥርጊያ መንገዱን ከፍተዋል ።

ሄንሪ ቅዱስ — ስምኦን ፤ ቻርልስ ፉርዬና ሮበርት
ኦውን የ፲፱ኛውምዕተ — ዓመት ታላላቅ ተምኔታውያን ሶሻ
ሊስቶች በተባ መንገድ የካፒታሊስት ሥርዓትን በመንቀፍ
ከብዝበዛ ነጻ የሆነ ሃሳባዊ ሕብረተሰብ እንደሚኖር ዕቅድ
አወጡ ። ተምኔታውያን ሶሻሊስቶቹ በዝባገሮችን በማስተ
ማርና ሞራላዊ ውዴታ በማስገባት ሀሳባዊ ሕብረተሰብ
ሊመጣ ይችላል ብለው ሲአስቡ የዋህ ሆነው ነበር ። ይሁ
ንና ሐሳባቸው የማይንሳዊ ሶሻሊዝምን ንድፈ — ሀሳብ
መወለድ አጠናክሮታል ።

ካርል ማርክስና ረዳትና ጓደኛው ፍሬደሪክ ኤንግልስ
ከነሱ በፊት ከነበሩት ሰዎች ይበልጥ ሠርተዋል ። እነኝህን
ሀሳቦችም እንደገና በመገምገም አዲስ ንድፈ—ሀሳብ አዳ
በሩ ።



## የማርክሲዝም የማይነጣጠሉ ሶስት ክፍሎች ፡—

ሕብረተሰብን ለመለወጥ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖር
ያስፈልጋል ። ስለሆነም ፍልስፍና የተፈጥሮን ፤ የሕብረተሰ
ብንና የግንዛቤን ዕድገት የሚገዙ ትን በጣም አጠቃላይ
ሕጎችን የሚነግረን ሳይንሳዊ ምርመር ከማርክሲዝም
ክፍል አንዱና ዋነኛው ነው ።

ግን ፤ አንዱን ሥርዓተ — ማኅበር ሌላው እንዴት
እንደሚተካው ለመረዳት አጠቃላይ ሕጎችን ብቻ ማወቅ
በቂ አይደለም ። ከሁሉም የሕብረተሰብ ግንኙነት ይበልጥ
ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነቶች ወይም የምርት ግንኙነቶች
ይበልጥ ዋናነት እንዳላቸው ማርክስና ኤንግልስ አሳይተ
ዋል ። ስለሆነም ፤ የምርት ግንኙነቶች ዕድገት ሳይንስ
የሆነው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሌላው የማርክሲዝም ዋና
ክፍል ነው ።

ሶስተኛው የማርክሲዝም ዓይነተኛ ክፍል የሳይንሳዊ
ሶሻሊዝም ንድፈ — ሀሳብ የሚባለው ነው ። በሁለቱ ክፍ
ሎች ላይ በመመሥረት — በማርክሳዊ ፍልስፍናና በፖለ
ቲካዊ ኤኮኖሚ — ካፒታሊዝም እንዴት እንደሚዳሽቅ
ያሳያል ። በተጨማሪም ሰው ከራሱ መሰል ሰው ብዝበዛ
ነጻ የሆነበት የሶሻሊስት ሕብረተሰብ እንዴት እንደሚመ
ጣና እንደሚአድግ የሚገዙትን ሕጎች ይመሠርታል ።

እነዚህ ክፍሎች የማርክሲዝም «ቁልፍ» ክፍሎች
ሆነው እንደተገለጹ የተገነዘብን ይመስለናል ። ግን ማር
ክሳዊ አስተሳሰብ እራሱን በፍልስፍና ፤ በፖለቲካዊ ኤኮ

ኖሚና በሶሻሊዝም ንድፈ — ሀሳብ ዕድገት ክልል ብቻ አይገታም ። በተጨማሪም ማንኛውንም የዕድገት መስክ ያሳድጋል ፡— ታሪክንና ሕግን ፤ ክብረ — ሕሊናን (Ethics) የተፈጥሮ ውበትን (Esthetics) ወ.ዘ.ተ. ። በደንብ ለመናገር ፡— እነዚህና ሌሎችም ብዙ የዕውቀት ዘርፎች ሁሉ ዓይነተኛ የሆነ ሳይንሳዊ ጸባይ ያገኙት ማርክሳዊ ሥልትን ከአዋሃዱ በኋላ ነው ። ማለትም ስለሕብረተሰባዊ ክስተት ጥናት ማርክሳዊ አቀራረብን በመያዛቸው ።

ስለዚህ ማርክሲዝም ፤ ተፈጥሮንና ሕብረተሰብን ስለሚገዙት አጠቃላይ ሕጎች ፤ ስለሶሻሊስት አብዮት ድልና ሶሻሊዝምና ኮሚውኒዝም ስለሚገነቡበት መንገድ የሚነገር ተስማሚ የሆነ ሳይንሳዊ አመለካከት ነው ።

ማርክሲዝምን ስናጠና ሁልጊዜ ማስታወስ ያለብን ሁሉም ክፍሎቹ የተዛመዱና የተጣመሩ አንዱ ካንደኛው ተለይተው ሊታዩ የማይችሉ መሆናቸውን ነው ።

ያለፉት አሳቢዎች ያለቀላቸው ፍጹም የሆኑ ንድፈ — ሀሳቦች ለማምጣት አስበው ነበር ። ለሁሉም ጥያቄዎች (ወደፊትም ለሚመጡት — ከተርጓሚው) መጀመሪያውኑ በቂ መልስ አዘጋጅተው ለመጠበቅ ሞክረዋል ። ግን ማንኛውም ንድፈ — ሀሳብ ቢሆን ወደፊት ስለሚነሳው ሁኔታ አስቀድሞ መለየት ይችላልን ? እርግጥ በዙሪያችን ያለው ሕይወት ሳያቋርጥ ያድጋል ፤ የሰው ዕውቀትም እንዲሁ ይስፋፋል ፤ አንድ ንድፈ—ሀሳብ አዲስ ዕውነቶችን ሳይገነዘብ ቢቀርና የቅሬተ — አካላዊ (Fossilized) ሥርዓተ-ቀኖና አድርጎ ቢወስድ እራሱን ከዕውነታ ይገነጥላል ። የሕይወትን ትክክለኛ ሥዕል ስለማይሰጥ ጥቅም የለሽ ከዚያም



አልፎ ጎጂ ይሆናል ። ስለሆነም ንድፈ ሀሳብ በተግባር ላይ መመሥረት አለበት ።

ሁሉንም — ያኸ የሆነ ንድፈ — ሀሳብ ለመገንባት የተደረገው ሙከራ ወደ ጥፋት ወድቋል ። ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ ፤ እነኝህ ዓይነት ንድፈ ሀሳቦች እነሱን ካስገኟቸው ዘመኖች ፤ በዚያውም ጊዜ ከታዩት መደቦችና ከሚአንጸባርቋቸው ፍላጎቶች ጋር አክትመዋል ። በሕብረተሰብ የአሳብ መጋዘን ውስጥ የቀሩትና በአዲስ ንድፈ ሀሳቦች ከፍተኛ ዕድገት የአገኙት — ተግባራዊ ፍላጎትን ለመግለጽ ማለት ነው — በተሟላ ሁኔታ ዕውነታን የእንጸባረቁት ሀሳቦች ብቻ ናቸው ።

በ፲፱ኛው ምዕተ — ዓመት መዳፈያ ላይ ዓለም በታሪክ ውስጥ አዲስ እርከን ያዘ ። በማርክሲዝም መሥራቾች እንደተረጋገጠው የሶሻሊስት አብዮት እየቀረበ መጣ፤የማይቀርም ሆነ ። አስፈላጊው ነገር ማርክሲዝምን በብልሃት ማሳደግ ሆነ ፡ ታዲያ ሌኒን ነው ይህንን ታላቅ ታሪካዊ ተልዕኮ ያጠናቀቀ ።

ሌኒን ማርክሲዝምን ከሕይወት መፋታትና እንደቀዋሚ ቀኖና አድርጎ ማስተናገድን ተቃወመ ። ስለአዲሱ ታሪካዊ ዘመን ጠለቅ ያለ አመለካከት በመውሰድና ዋና ሳይንሳዊ አሰሳዎችን (discoveries) የፍልስፍናዊ ዐይነተኛነት በመገንዘብ የማርክስን ንድፈ — ሀሳብ በአዲስ ሃሳቦች አበልጽጓል ።

የካፒታሊዝምን ከፍተኛ ደረጃ የኢምፔሪያሊዝምን ሕጎች በማጥናት የሶሻሊስት አብዮትን አሳደገ ፤ አዳበረ ።

የዓለም አቀፍ ሠራተኛ መደብን እንቅስቃሴ ፤ ስትራቴጅና
ስለአብዮታዊ ፓርቲ ትምህርት ማለት ነው ። የሶሻሊስት
ለውጦችን መነሻ ገጠመኝ በማስቀመጥ ፤ ሶሻሊዝምና ኮሚ
ኒዝም የሚገነቡበትን ንድፈ — ሀሳብ ሠራ ። ማርክሲዝምን
በማንኛውም መንገድ በማዳበር ወደ አዲስ እርከን አወ
ጣው ። ለዚህ ነው ማርክሲዝም — ሌኒኒዝም እያለን የምን
ጠራው ።

ሌኒን ከሞተ ግማሽ ምዕተ — ዓመት በላይ አልፏል ።
ከዚያ ጊዜ አንስቶ በሰዎች ኑሮ ላይ ትላልቅ ለውጦች ተከ
ናውነዋል ። በትርኢታዊ መልክ የኢምፔሪያሊዝምና የሶ
ሊዝም የኃይሎች ሚዛንከበፊቱ ልዩ ሆኗል ።

አዲስ ብሔሮች ከቅኝ ግዛት ጭቆና ተላቀው ነጻነታ
ቸውን በማግኘት በዓለም መድረክ ላይ ወጥተዋል ። አዲስ
ሁኔታዎች የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ምጥቀታዊ ዕድገት
እየጠሩ ናቸው ፣ — የሰብአዊ ሕብረተሰብን ዕድገት ስለሚ
ገዛው ሕግ የሚመለከተውንና ስለወደፊቱ የዓለም ሁኔታ
ብርሃን የሚረጨውን መሆኑ ነው ። ዛሬ ማርክሲዝም ሌኒ
ኒዝም በመላው ዓለም ባሉት የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓር
ቲዎች ተግባራዊና ንድፈ — ሀሳባዊ ክንዋኔዎች እየበለጸገ
ነው ።

## ምዕራፍ አንድ

## ሕብረተሰብ እንዴት እንደሚአድግ

በዘመናችን ውስጥ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎችና የዜና
ማሠራጫዎች ፈጣን ዕድገት ምክንያት የሰው ልጅ ራሱን
እንዴት እንደሆነ ከውጭ መገንዘብና በሌላ ቦታ ሆና



በአሜሪካ ውስጥ ስላሉት ሰማይ—ጠቀስ ፎቆችና በቬየትናም
ስለሚገኙት የሸምበቆ ጐጆ ዎች በአንዴ መመልከት
ችሏል ። የአንድን ሰው ብልጽግናና የሌላውን ድህነት በማ
ነጻጸር ፤ የአንዳንድ ብሔሮችን ፈጣን ዕድገትና የሌሎችን
ወደኋላ ቀርነት በመገንዘብ እፍኝ በማይሞሉ ጥቂት አሳቢ
ዎች ከመጡ እስከ ጥቂት ጊዜ በፊት ድረስ ብዙ !!ብዙ!!
ሰዎች በመላው ዓለም ራሳቸውን ለምን ይህ እንደሚሆን
ይጠይቁ ነበር ፣ — ለምንድነው አብዮቶች ፤ መፈንቅለ —
አገዛዞች ፤ ጦርነቶች ፤ ግጭቶችና የሀሳቦች ትግል በዓለም
ላይ ሊኖሩ የቻሉት ? እርስ በእርሳቸው ከተለያዩት ፈጣን
የዘመኖች ዕድገት ጋር አንድን ሰው እንዴት ማስተዋወቅ
ይቻላል ? እነዚህ ዕድገቶች በሕግ የሚገዙ ናቸው ወይስ
እንዲሁ በአጠቃላይ በዕድል ላይ ጥገኛ ናቸው ? የሕብረተሰ
ብን ዕድገት የሚገዛውን ሕግ የሚወስነው ምንድነው ? እነ
ዚህ ሕጐች ሊለወጡ ወይም ተጽዕኖ ሊደረግባቸው ይች
ላሉ ? የሚሉትና ሌሎችም ተነስተዋል ።

ለዘመናት ፤ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሞከሩ
ሰዎች በሁለት ዋና ሰፈሮች ተከፍለዋል ፡— ሕሊናውያንና
ቁስአካላውያን በመባል ። ሕሊናውያን ሕብረሰብን የሚ
ገዛውን ሕግ ለመግለጽ የሚፈልጉት ሃይማኖታዊ በሆኑ
ቀኖናዎችና ከሰዎች ግንዛቤ በላይ ነው ብለው በሚአንጹ
ባርቁት «ከሁሉ በላይ ምክንያት» ነው ። ቁስአካላውያን
ደግሞ ሕብረተሰብን የሚገዛውን ሕግ የሚገልጸው ነገር
የሚገኘው በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ፤ በሰዎች መካከል ባለው
ግንኙነትና እንዲሁም በእነርሱ ውስጥና በአካባቢአቸውም
ነው ይላሉ ።

ስለ ሕብረተሰብ ዕድገት ሕግ የሚናገረው ማርክሳዊ
ትምህርት ታሪካዊ ቁስ—አካልነት ይባላል ። ይህ የታሪክን
ነባራዊ የውስጥ ሎጅክ ከመግለጹም ሌላ በጣም አስፈላ
ጊውን ፣ መሠረታዊውንና በጣም ዐይነተኛውን የሕብረተ
ሰብ ክስተት ሸንሸና በማሳየት የሕብረተሰብን መረባዊ
መያያዝ እንድናውቅ የሚረዳን መሠረታዊ ትምህርት ነው ።

## ፩. የታሪክ ቁስ — አካላዊ አመለካከት

### ሕብረሰባዊ ሕልውናና ሕብረሰባዊ ንቃተ — ሕሊና

ተፈጥሮና ሕብረተሰብ የሚዳብሩበት መንገድ መሠረ
ታዊ ልዩነት አለው ። በተፈጥሮ ውስጥ ንቃተ — ሕሊናዊ
ኃይሎች የሉም ። በግብታዊነት ነው ዕድገቱ ። ሕብረተሰብ
ደግሞ ፍጹም ልዩ ነው ። አድራጊና ፍላጐት ያላቸው ንቃተ
—ሕሊና ሕልውናዎች አሉ ። ዓላማዎች ነድፈው ግባቸ
ውንም ለመምታት ይሠራሉ ። ስለዚህ የሰዎች ምክንያት ፣
ሃሳቦችና ግቦች ናቸው የሕብረተሰብን ኑሮ የሚወስኑት
ሊባል ይቻል ይሆናል ።

ለብዙ ዘመናት አሳቢዎች በሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ
ኑሮ መካከል ያሉትን ልዩነቶች አሳይተዋል ። የሰዎችን
«ከፍተኛ» — መንፈሳዊ ኑሮ ከ «ዝቅተኛው»—ቁሳዊ
ኑሮ ጋር በማነጻጸር ላይ የሃይማኖትና የሐሳባዊ አሳቢዎች ፣
ቁሳዊውን ኑሮ የሰዎችን ዋና ፍላጐቶች — ምግብ ፣ ልብስ ፣
መጠለያ ወዘተ . . . በማርካት ደረጃ ብቻ ዝቅ ያደርጉታል ።

እርግጥ ሰው ለመኖር ምግብ ፣ ልብስ ፣ መጠለ
ወዘተ . . . እንዲኖረው ይሻል ። ፈለጋቸውም አልፈለ
ቸው እነዚህ ፍላጐቶች ከተፈጥሮ ጋርና ከሌሎች ሰዎች



ጋር ግንኙነት እንዲአደርግ ያስገድዱታል ። መሬትን ያር
ሳል ፣ ቤት ያንጻል ፣ ልብሶችና መሣሪያዎች ይሠራል ፣ የጉ
ልበቱን ውጤት ምርት ከሌላው ምርት ጋር ይለውጣል ።

ስለዚህ ፣ የሰዎች ቁሳዊ ኑሮ ፣ ሕብረሰባዊ ሕልውና
ቸው ፣ ሰዎች በአካባቢአቸው ላይ የሚሠሩት ውስብስ
ባዊ ሂደት ነው ። እርግጥ እንደ ቁሳዊ ምርት ጥቅሞች ሁሉ
አያሌ ብሎት (much consumption) አይደለም ሰብዓዊ
ሕልውናን የሚወስነው ።

ሕብረተሰባዊ ሕልውና በሕብረተሰቡ ተቀባይነት
ባገኙ ንድፈ — ሀሳቦች ወይም ሀሳቦች ላይ ጥገኛ ያልሆኑ
የራሱ ነባራዊ ሕጐች አሉት ።

በሌላ በኩል ፣ ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት
እንደ እንሰሳ እራሱን ከአካባቢው ጋር በማለማመድ ሳይ
ሆን ግን ፣ በተፈጥሮ ሂደት ጣልቃ እየገባ ተፈጥሮን በቁ
ጥጥሩ ሥር ያውላል ። ሰው ተፈጥሮን ለመለወጥ ያለው
ንቃታዊ ተግባር ከፍላጐቱ ጋር እንዲሰምር አድርጐ አካባ
ቢውን መላመድ ነው ።

የሕብረተሰብ ሕልውና ዋናው ነገር ቁሳዊ ጥቅምን
በማስገኘት ላይ የታለመው ጉልበት ሥራ) ነው ።

* ሥራ ነው ሰውን ከእንስሳት ዓለም ከፍ ያደረገው ።
እንስሳት ምንም ቁሳዊ ምርት አያመርቱም ፡— ዝም ብለው
ብቻ በአካባቢአቸው በተፈጥሮ ተዘጋጅቶ ያገኙትን ነገር
ይጠቀማሉ ፣ ይበላሉ ። ሰው ግን ተፈጥሮን በንቃት ተጽ
ዕኖ ያሳድርበታል ፣ በሥራው ይለውጠዋል ፣ የሚፈልጋቸ
ውን ቁሳዊ ጥቅሞች ይፈጥራል ። በታሪክ ውስጥ በሰዎች

ስለ ሕብረተሰብ ዕድገት ሕግ የሚናገረው ማርክሳዊ
ትምህርት ታሪካዊ ቁስ—አካልነት ይባላል ። ይህ የታሪክን
ነባራዊ የውስጥ ሎጅክ ከመግለጹም ሌላ በጣም አስፈላ
ጊውን ፤ መሠረታዊውንና በጣም ዐይነተኛውን የሕብረተ
ሰብ ክስተት ሸንሸና በማሳየት የሕብረተሰብን መረባዊ
መያያዝ እንድናውቅ የሚረዳን መሠረታዊ ትምህርት ነው ።

## ፩. የታሪክ ቁስ — አካላዊ አመለካከት

## ሕብረሰባዊ ሕልውናና ሕብረሰባዊ ንቃተ — ሕሊና

ተፈጥሮና ሕብረተሰብ የሚዳብሩበት መንገድ መሠረ
ታዊ ልዩነት አለው ። በተፈጥሮ ውስጥ ንቃተ — ሕሊናዊ
ኃይሎች የሉም ። በግብታዊነት ነው ዕድገቱ ። ሕብረተሰብ
ደግሞ ፍጹም ልዩ ነው ። አድራጊና ፍላጎት ያላቸው ንቃተ
—ሕሊና ሕልውናዎች አሉ ። ዓላማዎች ነድፈው ግባቸ
ውንም ለመምታት ይሠራሉ ። ስለዚህ የሰዎች ምክንያት ፤
ሃሳቦችና ግቦች ናቸው የሕብረተሰብን ኑሮ የሚወስኑት
ሊባል ይቻል ይሆናል ።

ለብዙ ዘመናት አሳቢዎች በሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ
ኑሮ መካከል ያሉትን ልዩነቶች አሳይተዋል ። የሰዎችን
«ከፍተኛ» — መንፈሳዊ ኑሮ ከ «ዝቅተኛው»—ቁሳዊ
ኑሮ ጋር በማነጻጸር ላይ የሃይማኖትና የሐሳባዊ አሳቢዎች ፤
ቁሳዊውን ኑሮ የሰዎችን ዋና ፍላጎቶች — ምግብ ፤ ልብስ ፤
መጠለያ ወዘተ . . . በማርካት ደረጃ ብቻ ዝቅ ያደርጉታል ፤

እርግጥ ሰው ለመኖር ምግብ ፤ ልብስ ፤ መጠለ
ወዘተ . . . እንዲኖረው ይሻል ። ፈለጋቹውም አልፈለ
ቸው እነዚህ ፍላጎቶች ከተፈጥሮ ጋርና ከሌሎች ሰዎች



ጋር ግንኙነት እንዲአደርግ ያስገድደታል ። መሬትን ያር
ሳል ፤ ቤት ያንጻል ፤ ልብሶችና መሣሪያዎች ይሠራል ፤ የጉ
ልበቱን ውጤት ምርት ከሌላው ምርት ጋር ይለውጣል ።

ስለዚህ ፤ የሰዎች ቁሳዊ ኑሮ ፤ ሕብረሰባዊ ሕልውና
ቸው ፤ ሰዎች በአካባቢአቸው ላይ የሚሠሩት ውስብስ
ባዊ ሂደት ነው ። እርግጥ እንደ ቁሳዊ ምርት ጥቅሞች ሁሉ
እያሌ ብሎት (much consumption) አይደለም ሰብዓዊ
ሕልውናን የሚወስነው ።

ሕብረተሰባዊ ሕልውና በሕብረተሰቡ ተቀባይነት
ባገኙ ንድፈ — ሀሳቦች ወይም ሀሳቦች ላይ ጥገኛ ያልሆኑ
የራሱ ነባራዊ ሕጎች አሉት ።

በሌላ በኩል ፤ ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት
እንደ እንስሳ እራሱን ከአካባቢው ጋር በማለማመድ ሳይ
ሆን ግን ፤ በተፈጥሮ ሂደት ጣልቃ እየገባ ተፈጥሮን በቁ
ጥጥሩ ሥር ያውላል ። ሰው ተፈጥሮን ለመለወጥ ያለው
ንቃታዊ ተግባር ከፍላጎቱ ጋር እንዲሰምር አድርጎ አካባ
ቢውን መላመድ ነው ።

የሕብረተሰብ ሕልውና ዋናው ነገር ቁሳዊ ጥቅምን
በማስገኘት ላይ የታለመው ጉልበት ሥራ) ነው ።

* ሥራ ነው ሰውን ከእንስሳት ዓለም ከፍ ያደረገው ።
እንስሳት ምንም ቁሳዊ ምርት አያመርቱም ፡— ዝም ብለው
ብቻ በአካባቢአቸው በተፈጥሮ ተዘጋጅቶ ያገኙትን ነገር
ይጠቀማሉ ፤ ይበላሉ ። ሰው ግን ተፈጥሮን በንቃት ተጽ
ዕኖ ያሳድርበታል ፤ በሥራው ይለውጠዋል ፤ የሚፈልጋቸ
ውን ቁሳዊ ጥቅሞች ይፈጥራል ። በታሪክ ውስጥ በሰዎች

ለተፈጠሩት ሁሉም ጥቅሞች ምንጩ ሥራ ነበር ፤ ነውም ።

* የሰው ሥራ ተፈጥሮን ብቻ አይደለም ተጽዕኖ የሚአሳድርበት ፤ ሰውንም ነው ። ከዋና ኃይሎች ጋር ያለው የተጠራቀመ ትግል የሰውን አእምሮ እንዲአስብና እንዲአስታውስ ሲአስተካክለው ፣ ከሌሎች ጋር የሚአደርገውን የመገናኛ ዘዴ አዳበረለት — ከሁሉም በላይ ቋንቋን ።

* የሰው አንጎል ብቻ ሳይሆን ፤ ግን እጆችም ጭምር የሥራ ውጤቶች ናቸው ። የብዙ ምዕተ — ዓመታት ሥራ ቅልጥፍና ያላቸው በመሠረቱ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ለመሥራት ወደሚአስችሉ የሰው አካሎች ለውጧቸዋል ። በሥራ አማካይነት ነው የሰው እጆች በቂ ቅልጥፍና ያላቸው ሆነው የተገኙት ።

ታዲያ ! በሰዎች የሥራ ክንዋኔ ፤ በሕብረተሰባዊ ሕልውናቸውና በአመለካከታቸው ፤ በአስተሳሰባቸውና በፖለቲካዊ ፤ ሕጋዊ ፤ ሞራላዊና ሃይማኖታዊ እምነቶች — በሕብረተሰብ አጠቃላይ መንፈሳዊ ፤ ርዕዮተ — ዓለማዊና ባሕላዊ ኑሮ መካከልና በአጠቃላይ ሕብረ ሰባዊ ንቃተ ሕሊና በሚባለው መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው ? የትኛው ነው ቀዳሚ ነገር ፤ በሕብረተሰብ ኑሮ ውስጥ ዋናው ፤ ለሕብረተሰብ ዕድገት ዐይነተኛ ወሳኝነት ያለው ? ደግሞስ የተከታይ ባሕሪ ፤ የጥገኝነት ፤ የሁለተኛ ደረጃነት ያለውስ ?

ሰዎች በመጀመሪያ ቁሳዊ ፍላጐታቸውን ባያረኩኖር ራሳቸውን በሳይንስ ፣ በፖለቲካዊ ወይም በሥነ ጥበብ ፍላጐት ውስጥ ለማስገባት ባልቻሉም ነበር ።

ስለሆነም ሕብረሰባዊ ንቃተ — ሕሊና ከሕብረሰብእዊ ሕልውና ሊለይ እንደማይችል እንገነዘባለን ።



ከዚህም በላይ የሰዎች ሀሳቦች አፈጣጠር ፤ አኩቶችና አስተያየቶች በምንም መንገድ ይሁን በቁሳዊ ጥቅም የምርት ደረጃ ላይና በሕብረተሰቡ የምርት ሥርዓት ውስጥ እነዚያ ሁኔታዎች በሚይዙት ቦታ ጥገኛ ናቸው ። አንድ ጥንታዊ የሕንድ ተረት ፤ — «በጣም ብሩህ የነበረ አእምሮ እንኳን በማያቋርጥ ሁኔታ እንዴት ዘይት ፤ ጨው ፤ ልብስና ማገዶ እንደሚአገኝ የሚአስብ የድሀ ሰው አንጎል ከሆነ እየሟሸሸ እየቀነሰ ይሄዳል ። » ይላል ።

የዚህ እርግጠኛ ምክንያት ትላልቅ የሕዝብ ቡድኖች በሕብረተሰቡ የአመራረት ሥልት ውስጥ የተለያዩ ቦታ ስለሚይዙና በዚሁ ሕብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ የሕብረተሰብ አመለካከቶችና ንድፈ — ሀሳቦች ስለሚኖሩ ነው ። ለምሣሌ፣—በካፒታሊዝም ውስጥ ሁሉም የቡርገዞዋውና የሶሻሊስቱ ርዕዮተ — ዓለሞች አሉ ። የመጀመሪያው የካፒታሊስትን ሥርዓት ያጠናክራል ። የሚአንጸባርቀው የካፒታሊስቱ መደብ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚይዘውን ቦታና የእርሱን ፍላጐት ነው ። ካፒታሊስቶች ሠራተኞችን ይበዘብዛሉ ፤ ሥልጣኑን ይወስዳሉ ፤ ስለዚህም የኑሮን ጥቅሞች ሁሉ ይደሰቱባቸዋል ። የካፒታሊስቱን ፍላጐት የሚአብራሩት ንድፈ — ሀሳቦች ካፒታሊዝምን በጣም ትክክለኛና እርግጠኛ የሕብረተሰብ ሥርዓት አድርገው ያውጃሉ ።

በሌላ በኩል ፤ የሶሻሊስት ርዕዮተ — ዓለም የሚበዘበዙትን የሕብረተሰብ ክፍሎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ሲአንጸባርቅ ፤ የካፒታሊስት የእድገት ሕጐችን ያጠናል ፤ የተጨቆኑ መደቦች አብዮታዊ የመደብ ትግልን ተግባር ይቀምራል ፤ እናም ካፒታሊዝም የሚወድምበትንና

ወደሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ መንገዶችንና ዘዴዎችን
ያብራራል ።

የምንመረምረው ምንም ዓይነት የሕብረተሰብ ንድፈ
— ሀሳብ ይሁን ፤ በማያጠራጥር ሁኔታ በሕብረተሰብ የሕ
ልውና አድማስ ላይ ሥር የሰደደ ነው ፡— እንበልም በሕብ
ረተሰብ የቁስአካላዊ ኑሮ ሁኔታ ላይ ። ስለዚህ የሕብረተሰብ
ዕድገት እንቅሳቃሽ (ገፋፊው) ኃይል መታየት ያለበት በሕ
ዝቡ ንቃተ—ሕሊና ውስጥ ሳይሆን ፤ ግን በሕብረተሰብአዊ
ሕልውናቸው ፤ በቁሳዊ ጥቅም የምርት ደረጃ ላይ ነው ።

## <u>የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች</u>

በመጀመሪያ ምርት ምን ማለት እንደሆነ መሠረቱን
እንጣል ። አንድን ነገር ለማምረት ለመሥሪያ የሚአገለ
ግሉ ቁሳቁሶች አስፈላጊ ናቸው ። እነኝህም ለምሣሌ ፡—
እህል ፤ ፍራፍሬ ፤ የጉማ ዛፍ ያልተጣራ ብረት ፤ የድንጋይ
ከሰል ፤ የተፈጥሮ ዘይት ፤ ወዘተ . . . ናቸው ። በሌላ አነጋገር
ሰው ተግባሩን የሚአውልበት (የተፈጥሮ) ማንኛውም ነባሪ
የምርት መመንጫ ነው ። ሰው በባዶ እጁ ቁሳዊ ጥቅሞቹን
ሊአመርት አይችልም ። እጅግ በጣም ቀላሉን ሥራ እንኳን
ለመሥራት ብዙውን ጊዜ መቆፈሪያ ወይም ማርቴሎ ወይም
መጥረቢያ ወይም ካራ ያነሳል ። እናም ዘመናዊ እንዱስት
ሪያዊ ምርት ሁሉንም ዓይነት የማሺን መሣሪያዎች ፤ ዕቃ
ዎች እና ዝግጅቶች ይፈልጋል ። ሰዎች በምርት መመንጫ
ዎች ላይ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ፤ ሜካኒካዊ ፤ አካላዊና
ኬሚካላዊ ኃይሎች የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ይሰ
ኛሉ ። ማርክስ የእነዚህን ዋናነት አጽንኦት ሲሰጥ «የአንድ
የምርት ሥርዓት አጥንትና ጡንቻ ናቸው ።» ብሏል ።



ከተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ሌላ ፤ ማንኛውንም
ነገር ለማምረት ሰው እጆች ፤ የፋብሪካ ሕንጻዎች ፤ መጋዘ
ኖች ፤ የባቡር ሐዲዶች ፤ መስኖዎች ፤ ወዘተ . . . ሊኖሩት
ይገባል ። እነኝህ ከተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ጋር አን
ድነት በመሆን የማምረቻ መሣሪያዎችን ያስገኛሉ ። የም
ርት መመንጫዎችና የማምረቻ መሣሪያዎች ባንድነት የም
ርት መገልገያን ይፈጥራሉ ፤ ከምርት የሚለዩ ነገሮች አይ
ደሉም ።

በመጨረሻም ምርት የሰዎች በትክክል መሥራትን
ይጨምራል ። ያለሰው ማሺኖች (መኪናዎች) ሕይወት
የላቸውም ፤ ቁሳዊ ሀብትን ማምረት አይችሉም ። የቁሳዊ
ሀብት አምራቾች በምርት ውስጥ በጣም ዋናና ዐይነተኛ
ናቸው ።

የሕብረተሰብ የምርት መገልገያዎች እነሱን ለመጠ
ቀምና ለማንቀሳቀስ ዕውቀቱና ልምዱ ካላቸው ሰዎች ጋር
በመሆን የምርት ኃይሎችን ያስገኛሉ ። በተፈጥሮና በሕብ
ረተሰብ መካከል ያለውን ቁሳዊ ግንኙነት ያንጸባርቃሉ ።
የዕድገታቸው ደረጃ የሚአሳየው ሰው ምን ያህል ተፈጥሮን
እንደተቆጣጠረ ነው ።

* የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች የምርት ኃይሎችን
ደረጃ ለመገምገም የሚአስችሉን ዋና መለኪያዎቻችን
ናቸው ። የራሳቸው የሆነ ታሪክ አላቸው ፡— ከእንጨትና
ከድንጋይ መሣሪያነት ዛሬ እንደምናያቸው ሰውን አሰራራ
ቸውንና የማስተካከሉን ቁጥጥር ብቻ እንዲአካሄድ ትተ
ውለት አሁን እስከ አውቶማቲክና ውስብስብ ወደሆኑ መገ
ልገያዎች ተራምደዋል ፤ አድገዋል ። የተግባር መገልገያ

ዎች ባደጉ ቁጥር የዚያኑ ያህል የሚመረተው ቁሳዊ ሀብት
መጠን እያየለ ይሄዳል ። አንድ ሰው አንድን ዛፍ በደንጋ
ምሣር ለመቁረጥ ሙሉ ቀን ይወስድበት ነበር ። አሁን ግን
የሞተር መጋዝ በጥቂት ሰከንዶች ይከውነዋል ። አንድ
ትልቅ አፈር ጋፊ መኪና በሰባት ሰዓት ውስጥ አንድ ሺህ
በአካፋ የሚገፉ ሰዎች የሚሰሩትን ያህል አፈር ይገፋል ።

* ሌላው የምርት ኃይሎችን ደረጃ መለኪያ የሚሆነው
አንድን ነገር ለመሥራት የሚአስፈልገው ሥልጠት
(ጉልበት) (power) ነው ። ለብዙ ሺህ ዘመናት ለሥልጠት
ሁሉ ምንጩ የሰው ልጅና የለማዳ እንስሳት የጡንቻ ኃይል
ነበር ። አሁን ግን የሥልጠት ምንጮች ግዙፍ የኤሌክትሪክ
አስተላላፊ መኪኖች ናቸው ። የሚአመርቱት የሥልጠት
ደረጃ ከሰው ልጅ ጡንቻ ብዙ ሚሊዮን ጊዜ ዕጥፍ ነው ።

* ሌላኛው የምርት ኃይሎችን ደረጃ ዋና መለኪያ መልክ
የማምረት ገጠመኝ ነው ፤ ማወቁና ልምዱ ። ከመቶና ሃምሣ
ዓመታት በፊት ካለው ሲወዳደር የዛሬው የምርት ኃይሎች
የሚመዘኑት በጣም በመጠቁት የተግባር መገልገያዎች
ብቻ ሳይሆን ፤ ግን በሠራተኞች የትምህርት ደረጃና ልምድ
ብቁነት ጭምር ነው ። ዛሬ ምርት ራሱ ቀጥታ የምርት ኃይ
ል ከሆነው ሳይንስ ውጭ ሊታለም የማይችል ነገር ሆኗል ።

ለሕልውናው የሚአስፈልገውን ነገር ሁሉ ብቻውን
ለማምረት የሚችል ምንም ሰው የለም ። መናኝ እንኳን
በራሱ ጥረት ዋና ፍላጐቶቹን ለማግኘት ቢመኝ በሕብረ
ተሰቡ በተሠሩና በተሻሻሉ መሣሪያዎች መጠቀምና የብ
ዙ ትውልዶችን ገጠመኝ ማግኘት አለበት ። የማምረቻ
መሣሪያዎች የምርት ገጠመኝና የጉልበት ውጤቶች ሁሉ



የሰዎች የተባበረ ጥረት ውጤቶች ናቸው ። ሰዎች ባንድነት
ሲሰሩ እርስ በእርሳቸው ተሳስረው በምርት ግንኙነቶች
ውስጥ ይገባሉ ።

አንድ ሰው ምንም ዓይነት የተለዩ ሥራ ቢሠራ ጉል
በቱ፡ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን የሕብረተሰቡ ጉል
በት አካል ብቻ ነው የሚሆነው ። ስለሆነም ፤ በአንድ ቤተ
ሰብ ውስጥ ባል ምግብ ያቀርባል ፤ ሚስት ደግሞ ታበስላለች
በሕብረተሰብ ውስጥ ገበሬ ባለእጆችንና ሠራተኞችን በም
ግብ ምርት ይደግፋል ፤ በተራቸው እነሱ የተግባር መገል
ገያ መሣሪያዎች ያቀርቡለታል ። ይህ የእርስ በእርስ ጥገኝ
ነትና መረዳዳት ለሕብረተሰብ ምርት አስፈላጊ ሁኔታ ነው።
ይሁንና ፡ በቤተሰብ አባላት መካከልም ይሁን ወይም በሕ
ብረተሰብ አባላት መካከል እኩልነትን አያመለክትም ።
በገጠር ለምሣሌ ፡— ባለ እኩል ገበሬዎች እና ሲሶ አራሾች
የመሬት ከበርቴውን እንዲሀበትም ሲረዱት እርሱ ግን በሕ
ይወት እንዲኖሩ ብቻ «ይረዳቸዋል» — (ዕርዳታ ከተባለ !
ከተርጓሚው) ። «እርስ በእርስ መረዳዳት» በኩል እኩል
አለመሆን እንዳለ ግልጽ ነው ። ይህን ዕኩል አለመ
ሆንን ያመጣው ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ቀላል
ነው ፡ — የመሬት ባለቤትነት ።

* ሰዎች እራሳቸው የሚአስገኙአቸውን ቁሳዊ ሀብቶች
ካልወሰዱ ለመኖር አይችሉም ። እነሱንም በመውሰድ
በንብረት ግንኙነት ውስጥ ይገባሉ ወይም የባለቤትነት
ግንኙነት ውስጥ ። በታሪካዊ የቁሳዊ ጥቅም አያያዝ ስልት
አቀራረብ እንደተረዳነው ምርት ያለ አንድ ባለቤትነት
መልክ ሊገኝ አይችልም ።

* የቡርዦዋ ኤኮኖሚስቶች እንደሚአናፉት ንብረት የሚወክለው ሰው በነገሮች ላይ ያለውን የመቆጣጠር ኃይል ነው ይላሉ ። ይሁንና እርግጥ አንድ ነባሪ ንብረት የሚሆነው ሰዎች እርስ በእርሳቸው በሕብረተሰብ ግንኙነት የምርት ሂደት ውስጥ ሲገቡና ሲተሳሰሩ ነው ።

* አንድ ገበሬ ማሳውን ዘርቶ በመሬት ላይ ስላለው ኃይል አይደለም የሚአስበው ፤ እንዲአውም የሚአስበው የትኛውን የወደፊት ሰብል ሊጠበቅ እንደሚችልና ምን ያህሉን ድርሻ ለዕዳ ፤ ለግብር ፤ ለኪራይ እና ለሌሎችም ግዳጆች እንደሚከፍል ነው ።

* ንብረት ከቋንቋ ጋር ሊወዳደር ይችላል ። ቋንቋ የአንድ ሰው ውጤት ነው ተብሎ ከተወሰደ ብኩንነት ነው ፤ ምክንያቱም በዚያ ዓይነት መንገድ ሰውየው የራሱ ቋንቋ ብቻ ነውና ያለው የሚአናግረው ሰው የለውም ማለት ነው ። ልክ በዚህ መንገድ ምርትም ከሕብረተሰብ ግንኙነት ውጭ ሕልውና የለውም ።

ታዲያ ! የምርት ግንኙነቶች ምንድን ናቸው ? በጥንታዊ ሕብረተሰብ ውስጥ የጐሣዊ ሕብረተሰብ አባሎች በሕብረተሰቡ ምርት ላይ እኩል ቦታ ነበራቸው ። ለመኖር የሚአስችሉ ምርቶችን ለመጠበቅ ባንድነት ይሠራሉ ፤ እርስ በእርሳቸው ይረዳዳሉ ፤ እና በአንድነትም ሆነው የአመረቱትን ወይም የማረኩትን ይመገባሉ ። ይህ ሊሆን የቻለው የምርት መገልገያዎች ለሁሉም የሕብረተሰቡ አባሎች ንብረት በመሆናቸው ነው ።

በባሪያ አሳዳሪው ፤ በመልከኛውና በካፒታሊስቱ ሕብረተሰብ ውስጥ በሕዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት ፍጹም



ልዩ ሆን ። የሕዝቡ የተለያዩ ክፍሎች በምርቱ ሥርዓት ውስጥ የተለያየ ቦታ በመያዝ አንዳንዶቹ ሌሎችን መበዝበዝ ጀመሩ ። ስለዚህ ፤ የሕብረተሰቡ የሥራ ውጤት ትክክል ባልሆነ መንገድ ይከፋፈላል ። እፍኝ ሙሉ በዝባዦች በሌሎች ጉልበት የተገኘውን ከፍተኛውን ድርሻ ሲወስዱ ሠፊው ሕዝብ ግን ተጨቁኖ በድህነትና በእርዛት ይሰቃያል ። ይህ የሚሆነው ምክንያቱም ሰዎች በሙሉ የምርት መገልገያዎችን ስለሚአዝዙባቸው ነው ።

ከሶሻሊስት ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነት ሽግግር ጋር እንደገና ሁኔታቸውን ይለውጣሉ ። የሕብረት ሥራዎች ይሆናሉ ፤ የጋራ ምርቱም ለሥራው በተደረገው የጥረት መጠንና ተሳትፎ መሠረት ነው የሚከፋፈለው ። ይህ ተግባር ሊከወን የቻለው ምክንያቱም በሶሻሊዝም ውስጥ ዋናዎቹ የምርት መገልገያዎች በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ስለሚያዙ ፤ ስለሚታዘዙ ነው ።

ስለዚህ በግልጽ ፡— የምርት ግንኙነቱን ዓይነት ለመወሰን የምርት መገልገያዎችን ማን እንደሚአዝባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው ። የምርት ግንኙነቶች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የንብረት ግንኙነቶች ናቸው ።

የምርት ግንኙነቶች የግል ባለቤትነት በብዝበዛ ግንኙነት ሲከሰቱ ፤ የሕዝብ ንብረት መሆናቸው ደግሞ የሕብረት ግንኙነትን ያሳያል ። የዚህ ባለቤትነት መልክ ሁሉንም በምርት ውስጥ የሕብረተሰቡን ክፍል ደረጃና የጉልበት ውጤቶች የሚከፋፈሉበትን መንገድ ይወስናል ።

አሁን፤ እንዴት ነው የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች በይነግብር የሚአካሂዱት (የሚወሳሰቡና የሚወራረሱት) ?

## የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች አፈጣጠር ጋር ያ
## ቸው ሕብረት (ዝምድና)

ሰብዓዊ ሕብረተሰብ ከታየበት ጊዜ ጀምሮ ሰዎች
ቁሳዊ ጥቅሞችን ፈጥረዋል ። ምርት ሲቆም ሕብረተሰቡ
ወደያውኑ ያለውን መጠባበቂያ ይጠቀምበትና ይጨርሰ
ዋል ። እንዲህ ዓይነት ነጥቦች እንደአካባቢ ለውጦችና የሕ
ዝብብዛት ዕድገት የመሳሰሉት ምርትን እንዲጨምርና
እንዲሻሻል እንደሚአስገድዱት ታሪክ አሳይቶናል ። ይህም
በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች ለውጦች ተካበ
ነው የሚታየው ።

* ሰዎች ከድንጋይ መጥረቢያና ጦር በኋላም ከቀስትና
ፍላጻ — (የምርት ዋና መሣሪያዎቻቸው) በቀር ሌላ በለ
ቸው ጊዜ የሕብረተሰቡ የምርት ኃይሎች ደረጃ በጣም
ዝቅተኛ ነበር ። ዝቅተኛ ፍላጐታቸውን ለማሟላት ቢአስ
ተናግዱና ቢአከናውኑም በከፍተኛ ችግር ነው ። ሊኖሩ
ችለዋል ፤ ምክንያቱም በሕብረት ይሠሩ ስለነበር ። በእው
ነቱ ፤ በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት የሥራ ፍሬና የምርት
መገልገያዎች በሙሉ የሕብረተሰቡ እንጂ የግለሰቦች አል
ነበሩም ። አንድ የጐሣዊ ማኅበረ — ሰብዕ አባል ብቻ
ውን ራሱ ለመሥራት የሚችልበት ሁኔታ ስለሌለ በዝቅተኛ
ደረጃ ያሉት የምርት ኃይሎች የግል ንብረት እንዳይሆኑ
አግደዋል ። ብዝበዛም አልተቻለም ፤ ምክንያቱም እያንዳ
ንዱ አባል ራሱን ከሚመግበው በላይ ለማምረት አይችልም
ነበርና ። የጐሣዊ ማኅበረ — ሰብዕ የኖረው በቡድን ሥራ
ነው ፤ ስለዚህም አባሎች ሁሉ እኩል ነበሩ ። የምርት ግ
ኙነቱ ካለው የምርት ኃይል ደረጃ የተጣማ ነበር ።



* ከዚያ ፤ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ የምርት ማምረቻዎች ተሻ
ሻሉ ። ብረታ — ብረት የተግባር መገልገያዎች ታዩ ፤ የግ
ልበት አምራችነትም ጨመረ ። አሁን ሕብረተሰቡ ከዋና
አስፈላጊ የቀን በቀን ፍላጐቶች በላይ ማምረት ችሏል ።
ትርፍርፍ ምርት ለማምረት በቅቷል ።

* በሕብረተሰቡ ውስጥ የሥራ ክፍፍል ታዩ ። እህላ
እህልን ከማብቀል ሌላ ሰው እንስሳትን ማርባትና የእጅ
ሥራዎችን መሥራት ያዘ ። የሥራ ክፍፍል ወደ ምርት መለ
ዋወጥ አመራ — እህል አብቃዩ የእንስሳት ውጤት ሲአስ
ፈልገው ከብት አርቢው ደግሞ እህል ያሻዋል ። እያንዳንዱ
ፍላጐቱን የሚአረካው በመለዋወጥ ብቻ ነው ። ስለዚህ
የጥንታዊ ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነት ጸባይ ፤ ሰውን በጐ
ሣዊ ማኅበረ — ሰብዕ ክልል ውስጥ የወሰነው ፤ ከምርት
ኃይሎች ጋር መጣማት አቆመ — ምክንያቱም የሥራ ክፍ
ፍልንና የምርት መለዋወጥን ስለሚአግድ ወይም ስለሚ
ጐተት ነው ።

* እነዚህ ግንኙነቶች ምርት እድገቱን እየቀጠለ ሲሄድ
ፈራረሱ ። ከተግባር መገልገያ መሣሪያዎች መሻሻል ጋር
የምርት መጠንም በሚአስደንቅ ሁኔታ ጨመረ ፤ እነዚህን
ለማምረት በአጠቃላይ የማኅበረ — ሰቡ መሳተፍ አስፈላጊ
አልነበረም ፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ቤተሰብ ይከወን
ነበርና ፤ ቀስ በቀስ እነዚህ ቤተሰቦች የምርት መገልገያዎች
ባለቤትነትን ያዙ ። በቤተሰቡ ኃላፊ በንብረት ላይ ያለው
ቁጥጥር በዝምድና ደረጃ ላይ በመመሥረት ፤ በቤተሰቡ
አባላት መካከል በሚአከፋፍለው ማለት ነው ፤ የግል ንብ

ረት አዛዥነት መሠረት ተጣለ ፤ ከዚህም ጋር የምጣኔ ሀብት
አለመመጣጠን መጣ ። ይህ ያለመመጣጠን ደግሞ እያደ
ሄደ ፤ ምክንያቱም የጐሣ አለቆችና የዕድሜ ታላላቆች የ
ዙትን ቦታና ሥልጣን ለመበልጸጊያ ተጠቀሙበት ። አዲስ
የማምረቻ መገልገያ እያንዳንዱን ቤተሰብ ለመኖር ከሚ
ስፈልገው በላይ ለማምረት አስቻለው ።

* ትርፍ ምርት ለልውውጥ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሠራተ
ኞችን በመቅጠር ምርትን ለማስፋፋትም ይውላል ።

* ስለሆነም አንድ ሰው ሌላውን እንዲበዘብዝ ዕድል
ሰጠው ። ሀብታሙ ድሀውን ጨቆነው ። የጦርነት እስረኞች
ወደ ባሪያነት ተለወጡ ። የጥንታዊው ጐሣዊ ሥርዓት
በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ተተካ ።

* በዚህ ሕብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች የ
ሪያ አሳዳሪው ንብረት ነበሩ ። በተጨማሪም ሠራተኛውን
ባሪያውን — የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች ቅጣያ የነ
ረውን ያዝዛሉ ። በመጀመሪያ የባሪያ አሳዳሪ ሕብረተሰብ
የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ጋር ተጣሙ ፤ ተስ
ማሙ ። ከምርት ኃይሎች ዝቅተኛነት ደረጃ ሲነጻጸር ፤ ቁሳ
ዊና ባሕላዊ ዕድገት የብዙኃን ባሪያዎች ጭካኔ የተመላበት
ብዝበዛ ተካሄደ ። የሕብረተሰቡን የሥራ ክፍፍል ጥልቀት
በመስጠት እና ባሕልን በማሳደግ ደረጃ ከላይ ያየነው ነበር
ምርትን ከፍ ለማድረግ ዋና ግፊት የሆነው ። በዚያን ጊዜ
ነበር የጉልበት ሥራ ከአእምሮ ሥራ የተለየው ። ምሁራን
ገጣሚዎች ፤ የቅርጽ ጠራቢዎችና ፈላስፎች ከጉልበት ሥ
ተላቀው ራሳቸውን ወደ ምሁራዊና አእምሮአዊ ሥ
ውስጥ አስገቡ ።



* ሳይንስ ሥር እየሰደደና እያደገ ሲሄድ ፤ የምርት ኃይሎች መሻሻላቸው ቀጠለ ። እህል ማብቀል ውጤታማ እየሆነ ፤ በብረታ ብረት ምርትና በብረት ዕቃዎች ትልቅ ዕድገት ተፈጠረ ። የእጅ ባለሙያዎች ልምዳቸውን ይበልጥ አመጠቁ ። በዚህ ሁኔታ የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የምርት ግንኙነቶች ቀስ በቀስ የምርት ኃይሎችን መጉተታቸው ቀጠለ ። ባሪያው ለሥራው ምንም ፍላጐት አልነበረውም ። ይሠቃይ ፤ ለብዙ ጊዜ ይሠራ ነበር ፤ ምክንያቱም በጌታው ጅራፍ ሥር ስለነበር ፤ ውጤቱም ዝቅተኛ ነው ። ባርነት ቀስ በቀስ ለመልከኞችነት (ለፊውዳሊዝም) መንገድ ሰጠ ።

* በመልከኛው ሕብረተሰብ ዋናው የምርት መገልገያ «መሬት» አብዛኛው በመልከኛው መኳንንት ነበር የተያዘው ። ሠራተኛው ሕዝብ ፤ ገበሬዎች ፤ ትናንሽ መሣሪያዎችን ብቻ ነው ያላቸው ። እናም የራሳቸው የሆነ መሬት ስለሌላቸው የመልከኛው መኳንንት ሁኔታውን ተጠቅመው ወደ ገባርነት ለወጧቸው ። የመልከኛው መኳንንት፤ገባሮችን እንዲሠሩበት ወይ ቁራጭ ማሣ ይሰጧአቸውና ከምርቱ ውስጥ የዐይነት ክፍያ እንዲከፍሉ ወይም በኩዳዶቻቸው (Estates) ላይ እንዲሰሩ በማድረግ — የመሬት ኪራይ መሆኑ ነው — ወይም በአጠቃላይ ሕብረተሰቡን ግዳጅ በማስገባት ይበዘብዛሉ ።

* በመጀመሪያ አዲሶቹ የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ደረጃ ጋር ተጣሙና ለአንዳንድ ዕድገቶች መንገዶችን ከፈቱ ። ገባሩ የሥራው ውጤት ከሆነው እህል የተወሰነው ክፍል ለእርሱ ስለሚሰጠው አንዳንድ የመሥራት ፍላጐቶች አሉት ። ስለዚህ በሥራው የበለጠ ትኩረት ኖሮ

ት ፤ የተግባር መገልገያዎች ይበልጥ ውጤት እንዲአስገኙ
ይጠቀምባቸዋል ።

*   ይሁንና ፤ ከጊዜ በኋላ አዲስ የምርት ኃይሎች በመል
ከኛው ሥርዓት ውስጥ ታዩ ። የከተሞችና የእጅ ሥራዎች
ዕድገት ነበር ። የሥራ ክፍፍል ጨመረ ፤ ልውውጥ መስፋ
ፋቱን ቀጠለ ፡— ብሔራዊ ገበያዎች ቀስ በቀስ ተከሰቱ፡
እና የሸቀጥ ገንዘብ ግንኙነት የቀድሞ የመልከኛ ሥር
ዓት መሠረትን ተጫነው ። በኋላ ፋብሪካች ብቅ አሉ ።
የእጅ ባለሙያውን (እራሱ በራሱ መሣሪያ ሠርቶ አደሩን)
ማስወገድ ጀመሩ ። የጡንቻ ኃይል በማከታተል በንፋስ
ኃይል ፤ በውሃና በመጨረሻም በእንፋሎትና በኤሌክትሪክ
ተተካ ።

*   ማሺኖች ከገባርነት ነጻ የወጡና ይበልጥ ልምድ ያላ
ቸው ሠራተኞች አስፈለጓቸው ። መልከኝነት ለሕብረተ
ሰብ ዕድገት እንቅፋት ሆነና ለካፒታሊዝም በውስጡ ክፍል
ለመተው ተገደደ ።

*   በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያ
ዎች የካፒታሊስቶች ንብረት ስለሆኑ ፤ ሠራተኞች የጉል
በት ኃይላቸውን ለካፒታሊስቶቹ እንዲሸጡ ይገደዳሉ ።

*   የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች ለምርት ኃይሎች
እድገት ሰፊ እድል ይሰጣሉ ። በካፒታሊዝም ውስጥ የቴክ
ኖሎጂ እርምጃ ከዚህ በፊት ከሆነውና ከተፈጠረው ሁሉ
ይበልጥ መጠቀ ። ግን የምርት ኃይሎችን ከዚህ ደረጃ በማ
ሳደግ ፤ ካፒታሊዝም ደግሞ የራሱን መቃብር ይቆፍራል ።
ከዚህም በላይ ትብ ቅራኔዎችን ያመጣል ። ወደ ሶሻሊዝም
መሸጋገርም የማይቀር ይሆናል ።



የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ታሪክ በመካከ
ላቸው ውስጣዊ መተሳሰር እንዳለ ያሳያል ፡— በተወሰነ
ደረጃ ላይ ያሉ የምርት ኃይሎች ከራሳቸው ጋር የሚስምሩ
የምርት ግንኙነቶች ን ይጠይቃሉ ። በአንድነት ስንመረም
ራቸው ብቻ በአንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ ሰዎች እንዴት
እራሳቸውን እንደሚአኖሩና ቁሳዊ ምርትን እንደሚአመ
ርቱ፡ ሊገባን ይችላል ። በሌላ አነጋገር ፡— የምርት ኃይሉ
ችና የምርት ግንኙነቶች ባንድነት የሕብረተሰቡን ቁሳዊ
ሀብት የሚመረትበትን ሥልተ — ምርት ይመሰርታሉ ።

የምርት ኃይሎች ከሥልተ — ምርቱ አካል ውስጥ
ይበልጥ ተንቀሳቃሽና አዳጊ ናቸው ። የዚህም ምክንያት
ቁሳዊ ጥቅምን በማምረት ሂደት ውስጥ ሰዎች ሳያቋርጡ
የበለጠ ዕውቀትና ገጠመኝ ስለሚአተርፉ እና ይህም
በተራው ያሉትን የምርት መሣሪያ ዎች ስለሚአሻሽል ፤ አዲ
ሶች እንዲፈለሰፉ ስለሚአደርግ ነው ። ስለሆነም የምርት
ኃይሎች ወደፊት ማደጋቸውን ይቀጥላሉ ።

ዕድገታቸው ከምርት ግንኙነቶች ፍጹም ልዩ ነው ።
የባለቤትነቶች መልክ — ማለትም ከትውልድ ወደትውልድ
በውርስ ከሚተላለፈውና ከሃይማኖታዊ ግብረ — ገብነቶች
ጋር ከተያያዙትና በሕግ ከተደገፉት — ከተግባር መገልገያ
መሣሪያዎች ይበልጥ ለመለወጥ በብዙው አስቸጋሪ ናቸው።
ከምርት ኃይል ሲነጻጸሩ በዕርጋታ ላይ ናቸው ። በጥንታዊ
ሕብረተሰብ የምርት መገልገያዎች የጋራ ባለቤትነት ለብዙ
መቶ ሺ ዘመናት ቆይቷል ፤ ባሪያ አሳደሪነት ጥቂት ሺ ዓመ
ታት ወስዷዋል ፤ መልከኝነት ቁጥጥሩን ከአንድ ሺ ዓመ

ታት በላይ ጠብቋል ፤ እና ካፒታሊዝም ለብዙ ምዕተ — ዓመታት ሕልውናውን አሳይቷል ።

የሥልተ — ምርት ሁለቱ አካሎች ባልተመጣጠነ መንገድ ስለሚአድጉ ፤ የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ኋላ ቀር ይሆኑና በመጨረሻ ቅራኔ ይፈጥራሉ ። ኋላ ቀር የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ዕድገት ይጐትቱታል ፤ እናም ግጭቱ አርጌው የምርት ግንኙነት ከምርት ኃይሉ ጋር በሚሠምር አዲስ የምርት ግንኙነት እስካልተተካ ድረስ መፍትሔ ሊአገኝ አይችልም ። አዲሶቹ የምርት ግንኙነቶች ለምርት ኃይሎች ዕድገት ይበልጥ ሰፊ ሜዳ ይሠጧቸዋል፤እንዲያውም በመጀመሪያ ዕድገታቸውን ያሽጋግሩታል ። ግን በኋላ የምርት ኃይሎች እንደገና ወደፊት ያድጉና ከምርት ግንኙነቱ ክልል ይወጣሉ።በሥልተ—ምርቱ ሁለት አካሎች መካከል አለመጣጣም ይከሰትና እንደገና ታሪክ በዕድገቱ ውስጥ ሌላ እመርታ ይወስዳል ።

ስለዚህ የሥልተ — ምርት ሁለቱ ክፍሎች የተወሳሰቡ መሆናቸውን እናያለን ። የምርት ግንኙነቶች ለምርት ኃይሎች ጥገኛ ሆነው የምርት ዕድገት በሚጠይቀው ሁኔታም ከነሱ መዛመድ አለባቸው ። ወዲያውኑ መጣጣማቸው ሲአቆም በሥልተ ምርቱ ውስጥ ቅራኔዎች ያድጋሉ ። በምርት ግንኙነቶች ውስጥ ያለው ለውጥ አጣዳፊ ይሆናል ።

ይህ ነው በምርት ግንኙነቶችና በምርት ኃይሎች አፈጣጠር ውስጥ ያለው የዝምድና ሕግ ባሕሪ ። ይህ ሕግ ለታሪካዊ እርምጃ ዋና አዘላይ ሽቦ ነው ።

ታሪክ እራሱን ለተመልካች እንደዘመኖች ኃያል ሞገድ ማለትም ከፍተኛ የመንግሥት ተጠሪ ፤ ገዥዎች ፤



ዲፕሎማቶችና ወታደራዊ መሪዎች ስሜቶች በማያቋርጥ መንገድ የሚጋጩበትና የሚፈነዱበት አድርጎ ይቀርባል ። ለአንድ በድንገት ለሚመለከት ሰው እነዚህ ግለሰቦች እራሳቸው ታሪክን የሚሠሩት ይመስለው ይሆናል ። የሥልተ ምርትን ዕድገትና በተጨማሪም የምርት ኃይሎችንና የምርት ግንኙነቶችን በይነ ግብር በሚገዙት ሕጎች አሠራር የሚወሰኑ ጠለቅ ያሉ ታሪካዊ ሂደቶች እንዳሉ እንኳን አይጠራጠርም ። እነዚህ ሂደቶች እና ሂደቶችን የሚያካሂዱት ሰዎች ናቸው እውነተኛ ታሪክ ሠሪዎች — ማለትም ሰዎች (ሕዝቦች) ሥራቸውን በሚሠሩበት ጊዜ ታሪክ እየተገነባ ይሄዳል ።

## ፪ — የሕብረተሰብ — ምጣኔ ሀብታዊ አቀራረጽ

## የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ ሥርዓትና የባሕላዊና አእምሮአዊ ኑሮ

ወደ ሕብረተሰብ ሕልውና ግንዛቤ በመመለስ — የኑሮ ቁሳዊ መልክ — የሕብረተሰብ ንቃተ ሕሊናን ፤ ባሕላዊና ምሁራዊ ኑሮን እንዴት እንደሚወስን እንመልከት ። የሕብረተሰብን ንቃተ — ሕሊና በመቅረጽ ወሳኝ የሆነው — አዳጊዎች የምርት ኃይሎች ወይም በብዛት ዕርጋታ ላይ ያሉት የምርት ግንኙነቶች እንደሆኑ — የሥልተ ምርት የትኛው ክፍል እንደሆነ ማወቅ ዐይነተኛ ነገር ነው ።

እስቲ ከምርት ኃይሎች እንጀምር፡— የምርት መገልገያዎች ሲሻሻሉና የምርት ገጠመኝ ሲጠራቀም ፤ የሰዎች ስለተፈጥሮ ያላቸው ሳይንሳዊ ዕውቀት ይጨምራል ። ይህ

በሰዎች ስነ — ልቡና (psychology) እና አስተሳሰብ
ውስጥ ዱካ በመተው በማያጠራጥር ሁኔታ የማይን
ሳዊ አሳቦችንና ንድፈ — ሀሳቦችን አመሠራረት ተጽዕኖ
ያሳድርባቸዋል ። ግን ፍልስፍናዊ ፤ ክብረ — ሕሊናዊ ፤ ወይ
ም ሃይማኖታዊ ሀሳቦችን ሌላው ይቅርና ፖለቲካንና ርዕ
ዮተ — ዓለምን በቀጥታ ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር ለማ
ጠቃለልና ለመደምደም መሞከር ጅልነት ነው ። ስለእው
ነት ከሆነ ዛሬ ሁሉም ሶሻሊስትና ካፒታሊስት አገሮች
በምርት ላይ አንድ ዓይነት መሣሪያ ይጠቀማሉ ፤ ይሁንና
ፖለቲካዊ ሥርዓታቸው ፤ ርዕዮተ ዓላማቸው ፤ እና ክብረ —
ሕሊናዊ መርሆዎች በመሠረቱ ይለያያሉ ።

የሕብረተሰብ ንድፈ — ሀሳቦችን ፤ ፖለቲካዊ ሥርዓ
ትን እና የክብረ — ሕሊናዊ ግንኙነቶችን መሠረት በም
ርት ኃይሎች ውስጥ ለመፈለግ መሞከር ወይ በስህተት
ወይ ጥያቄውን ለማወናበድ ሆን ተብሎ የተደረገ ጥረት ፤
በሕብረተሰቡ ግን ኙነት ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች ለመደ
በቅ ፤ በዛሬው ዓለም ውስጥ ባሉት ሁለት ርዕዮተ — ዓለ
ሞች መካከል ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ ለማለሰለስና ለማ
ጨለም የሚደረግ ነው — በሶሻሊስትና በቡርዧ ርዕዮተ
ዓለም መካከል ያለውን ቅራኔ መሆኑ ነው ።

የምርት ግንኙነቶች የሕብረተሰብን ንቃተ — ሕሊና
እንዴት እንደሚቀርጹ የሚጫወቱትን ሚና ደግሞ እንገን
ዘብ ፡— ለምሣሌ የካፒታሊስት ሕብረተሰብን እንውሰድ ።
ይህ ሕብረተሰብ በግል ንብረትና በካፒታሊስቶች የሠራተ
ኞች ብዝበዛ ላይ የተመሠረተ የካፒታሊስት የምርት ግን
ኙነት የገነነበት ነው ። ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ
ከነኝህ ግንኙነቶች ይሠምራል ፡— የካፒታሊስቱ መደብ



(ቡርዦዋው) የፖለቲካ ሥልጣንን በመያዝ ምጣኔ—ሀብቱን
ይቆጣጠራል ። የቡርዦዋው ሞራል የንግድን ወደፊት የመ
ቀጠል መንፈስና የንግድ ሥራን በአጠቃላይ ያንጸባርቃል ፤
የምርት ዓላማው በሌሎች ድካም ሀብታም መሆንን እስከ
ተቻለ ድረስ በትርፍ ማግኘት የታለ መውን ገዥ የምርት
ግንኙነትም ያንጸባርቃል ። በመጨረሻ ትንተና ፡— የቡር
ዦዋው ፍልስፍናዊ እና ፖለቲካዊ ንድፈ — ሀሳቦች የካፒ
ታሊስቱን ፍላጎት ይጠብቃሉ ። ተራማጅ ንድፈ — ሀሳቦ
ችም የሠራተኛውን መደብና የሌሎች ተራማጅ ኃይሎችን
ፍላጎት እያንጸባረቁ በካፒታሊዝም ውስጥ ይኖራሉ እንል
ይሆናል ። እርግጥ ነው ። ግን ከምንም ነገር አይደለም
የሚነሱት ፤ እንዲያውም ፤ የካፒታሊስት ሥልተ — ምር
ትን ቅራኔዎች ነው የሚአንጸባርቁት ።

አሁን የካፒታሊስትንና የሶሻሊስትን ሕብረተሰቦች
እናነጻጽር ። ከሶሻሊዝም ድል ጋር በሕዝብ ንብረትነት ላይ
የተመሠረቱ አዲስ ዓይነት የምርት ግንኙነቶች ይከሰታሉ ።
እነኝህ አዲሶች የምርት ግንኙነቶች የሕብረተሰቡን ባሕላ
ዊና አእምሮአዊ ኑሮ ፤ ለፖለቲካዊና ርዕዮተ — ዓለማዊ
ክፍሎች ሥር ነቀል ለውጥ እንዲሰጡ ያደርጋሉ ። በሰዎች
መካከል ያለ ግንኙነት በኮሚኒስት ሞራል ላይ የተመሠረተ
ነው ። የሕብረተሰቡ ርእዮተ—ዓለም የሰፊውን ሠራተኛ
ሕዝብ ክፍል ፍላጎት ያንጸባርቃል ።

ስለዚህ የሕብረተሰቡን የምጣኔ—ሀብታዊ ሥርዓቱን
የሚአስገኙት የምርት ግንኙነቶች የባሕላዊና አእምሮአዊ
መሠረቱንም ይይዛሉ ። የሕብረተሰቡ ምጣኔ — ሀብታዊ
ሥርዓት በላዩ ላይ ላዕላይ መዋቅሩ የሚዋቀርበትን መሠ
ረት ያስገኛል ። ላዕላይ መዋቅሩ—የሕብረተሰቡን አስተሳ

ሰቦችና ንድፈ — ሀሳቦችን ፤ የተለያዩ የርዕዮተ — ዓለም
ግንኙነቶችንና ፖለቲካዊ ፤ ሕጋዊና ባሕላዊ ተቋሞችንና
ድርጅቶችን የሚአጠቃልለው ነው ።

## የላዕላይ መዋቅር ርዕዮተ — ዓለማዊ ሚና

እርግጥ የተለያዩ ዓይነት አመለካከቶች አሉ ፤ — ግን
ተራማጅ አስተሳሰቦች የሕብረተሰብን ዕድገት ወደፊት
ሲአራምዱ አድሃሪዎቹ ደግሞ ዕድገቱን ይጻረራሉ ።

በአንዳንድ ሀሳቦች ምክንያት ሰዎች እርስ በእርሳቸው
ርዕዮተ — ዓለማዊ መተሳሰርን ይፈጥሩና በሕብረተሰቡ
ምጣኔ — ሀብታዊ ኑሮ ላይ ተጽዕኖ የሚአሳድሩ የተለያዩ
የሕብረተሰብ ተቋሞችንና ድርጅቶችን ያቋቁማሉ ።

* ለምሣሌ፡— በማደግ ላይ ያሉ ለዕድገታቸው የሶሻሊ
ስትን መንገድ የመረጡ ሀገሮች ከፍተኛ ዋናነት የሚሰጡት
መንግሥታዊ ክበቡን በኢንዱስትሪ መገንባትንና በእርሻ
ውስጥ የሕብረት ሥራን ለማራመድ ባላቸው ዓላማ የመ
ራትን ይዞታ ማሻሻል ነው ። በማደግ ላይ ያሉ አገሮች
መንግሥታት—በካፒታሊስት ርዕዮተ—ዓለም ላይ የሚን
ተራሱ—በማንኛውም መንገድ ምጣኔ—ሀብታዊ ክበብን
ለማራመድ እና በሀገራቸው ውስጥ የካፒታሊስት የምርት
ግንኙነቶችን በተቻለ መጠን ለማቋቋም ይታገላሉ ።

ርዕዮተ — ዓለማዊው ላዕላይ መዋቅር በትክክል ያለ
ምንም እንከን በምጣኔ — ሀብት መዋቅሩና በእርሱም የማ
ካሄደውን ለውጥ አያንጸባርቅም ። እርግጥ በምጣኔ ሀብቱ
ላይ ንቃታዊ ተጽዕኖ ያከናውናል ፤ እናም በሕብረተሰቡ



ዙሪያ — ገባ ዕድገት ( Over - all Development )
ውስጥ በደምብ ገብቶ ይገኛል ። ታሪክን እንደ ምጣኔ
— ሀብታዊ ርምጃ ብቻ አድርጎ ለመውሰድ ማሰብ
ሲፈ የተለያዩና ውስብስብ የሕብረተሰብ ኑሮን ከማርከ
ሲዝም ምንም ግንኙነት በሌለው ደረቅ ዕቅድ እና ስለ
ሕብረተሰብ ክስተት እንዳናውቅ በሚአግደን ነገር በማ
ይቀር ሁኔታ መተካት ይሆናል ።

በእርግጥ ግን እንዴት ፤ የጋንዲን ትምህርት ወይም
የኔሕሩን ፤ የናስርን ፤ የንክሩማህንና የሌሎችን በእስያና በአ
ፍሪቃ የብሔራዊ ነጻ አውጭ እንቅስቃሴ መሪዎችን ፖለ
ቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት ከንጹህ ምጣኔ ሀብ
ታዊ ደረጃ መለየት ይቻላል ? ለምሣሌ ፡— ምርጫቸው
ለሶሻሊስት መርሆዎች ዕድገትና ሙሉ በሙሉ የአገሮቻቸው
ምጣኔ — ሀብታዊ እውነተኛ ሁኔታ ነጸብራቅ ነው ብሎ
መግለጽ ይቻላል ? እርግጥ አይቻልም ። ኋላ ቀሩ ሥልተ —
ምርት ዕድገቱ በሕንድ ፤ በግብጽ ፤ በጋና እና በሌሎች በእ
ስያና አፍሪቃ አገሮች ለብዙ ዓመታት በኰሎኒያሊስቶች
ሰው ሰራሽ ዕገዳ ታግዶ የነበረው ፤ የሶሻሊስት ሕብረተሰ
ብን ርዕዮተ — ዓለም የራሱን በራሱ ዕድገት የሚአበረታታ
ምክንያት አልነበረም ። የአብዛኞዎቹ የብሔራዊ እርነት
እንቅስቃሴ መሪዎች አመለካከት ተቀርጾ የነበረው በዓለም
የሶሻሊስትና የኮሚኒስት እንቅስቃሴዎች ተጽዕኖ ነው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሶሻሊስት ማኅበ
ረሰብ ገጽታና ሶሻሊዝምን በመደገፍ በዓለም መድረክ ላይ
የኃይሎች ሕብረት መቀያየር ፤ በብሔራዊ የእርነት እንቅ

ሲቃሴ ርዕዮተ — ዓለምና ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ የለውጥ ውጤ
ት አስገኝቷል ።

በሌላ በኩል ፣— የእሲያና የአፍሪካ የብሔራዊ — አርነት
ዕንቅስቃሴ መሪዎች አስተያየትና ትምህርት ሁልጊዜም
ቢሆን በሃይማኖታዊ እምነቶች ፤ በዘር ውርሶች ፤ (Traditions)
ልምዶች እና በሕዝቦቻቸው ጥንታዊ ባሕል ተጽዕና
የተማረኩ ናቸው ።

ይሁንና እንዲህ ዓይነቱን እንደ ብሔራዊ የአርነት
እንቅስቃሴ ያለውን ውስብስብ እና ብዙ ገጽታ የያዘውን
ክስተት በማስተንተን ላይ በምንም መንገድ ቢሆን አንድ
ሰው ምንጩ ያለው የምጣኔ — ሀብታዊ ጭቆናን በመታገል ፣
የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የቅኝ ግዛቶችን የግልጽ
ዝርፊያ በመቃወም ላይ ነው ወደሚል መደሚያ ይደርሣል፡
በተበዝባገዮቹ የአፍሪቃና የእስያ ሕዝቦች ከበዝባገዮቻቸው
ጋር ያለው ትግል (ከአውሮጳውያን ኢምፔሪያሊስቶች
ጋር) የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ የታየበትን ፖለቲካዊ
ላዕላይ መዋቅርና ርዕዮተ — ዓለሙ የተመሠረተበትን
መሠረት አመጣ ።

ወይም ሌላ ምሣሌ እንውሰድ ፣— በሰዎች ታሪክ ላይ
የማዕዘን ድንጋይ የሆነው የጥቅምቱን የሶሻሊስት አብዮት
እንመልከት ። አብዮቱ በትክክል የምጣኔ — ሀብታዊ ዕድ
ገትና የምርት ኃይሎች ልማት ውጤት ነው ብሎ ማሰብ
ስህተት ይሆናል ።

በጥቅምቱ አብዮት ጊዜ ሩሲያ በምጣኔ — ሀብት በኩል
ዋና ከነበሩት የካፒታሊስት አገሮች በብዙ መንገድ ኋላ
ቀር ነበረች ። የሶሻሊስት አብዮት መሠረታዊውና አንቀሳ



ቃሹ ኃይል — ወዝአደሩ ፤ ከአብዛኞች የአውሮጳ መንግሥ
ታት ወዛደሮች ሲወዳደር አነስተኛ ነበር ። ግን የመጀመሪ
ያውን የሩሲያ የ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. አብዮት በማካሄድ ብዙ ገጠ
መኝ ስለነበረው ጥብቅ የሆነ ፖለቲካዊ ሕብረት ከገበ
ሬው ጋር ወስዷዋል። የወዝአደሩ አብዮት ድል ማድረግ ወዝ
ደሩን በትግሉ ተሳትፎ ላይ በመራውና የአብዮቱ ዋና መም
ሪያ በሆነው ያለቦልሼቪክ ፓርቲ ሊታለም የሚችል ነገር
አልነበረም ። እርግጥ በመጨረሻ ትንታኔ ላይ የጥቅምቱ አብ
ዮት የምጣኔ — ሀብት ፍላጎትን ገልጿል ፤ ግን ይህ ፍላጎት
ተንጸባርቆ የነበረው በመደቦች ፖለቲካዊ ትግል ፤ በፓ
ርቲው ከንዋኔና በሌኒን መሪነት ቀኝ ክንፎችንና «ግራ»
ክንፍ አድርባይነትንና በአጠቃላይ የቡርገዞዋውን ርዕዮተ
— ዓለም የመዋጋት የርዕዮተ — ዓለም ፍትጊያ ላይ ነው ።

ስለዚህ የሕብረተሰብ ዕድገት የሚከናወነው በምጣኔ
— ሀብት ፤ በፖለቲካ ፤ በርዕዮተ — ዓለምና በሌሎችም
የኑሮ መስኮች ሁሉ በሚደረገው ባይነግብር (Interaction)
ነው ። ቢሆንም ፤ ሁልጊዜም የሕብረተሰቡን ዕድገት
የሚገዛውን ሕግ ለመረዳት እንዲቻል ያን በይነግብር
ሊአሰምር የሚችለውን ምጣኔ — ሀብታዊ መሠረት መገ
ንዘብ አስፈላጊ ነው ።

## የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጽ ምን ድነው ?

እሁን የሕብረተሰብን የሕይወት መዋቅር በአጠቃ
ላይ እንመልከት ። ከእንግዲህ ወዲያ እንደ እውነቶችና
ወቅቶች ወይም ምስቅልቅሉ እንደወጣ የሕዝብ ክንዋኔ
ሆኖ አይቀርብልንም ። የምርት ግንኙነት ሥርዓት ሕብረተ

ሰቡን በአጠቃላይ ቀጥ አድርጎ እንደሚይዝ አጥንት ሊቆጠር ይችላል ። የሰዎች ርዕዮተ — ዓለማዊ ግንኙነት ፤ ባሕላዊ ክንዋኔዎች ፤ አመለካከቶች ፤ ፖለቲካዊ ዝንባሌዎችና ግብረ — ገባዊ ሀሳቦች በሕይወትና በማደግ ላይ ላለ ሕብረተሰባዊ አካል ሥጋና ደሙን ይመሠርታሉ ።

የምጣኔ—ሀብታዊ ሥርዓትን ሕብረትና ርዕዮተ—ዓለማዊውንና ፖለቲካዊውን፤ላዕላ ዊመዋቅሩን የሚአጠቃልለውን ይህን ዓይነት ሕብረሰብአዊ አካል ማርክሲስቶች ሕብረሰባዊ — ምጣኔ ሀብት አቀራረጽ ብለው ይጠሩታል ።

ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጾች ዘላለማዊ አይደሉም ። በእራሳቸው ይመጣሉ ያረጃሉ ፤ ይጠፋሉ ።

የሕብረተሰብ ታሪክ የሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብት አቀራረጽ ዕድገትና ለውጥ ታሪክ ነው ። ይህ ሂደት የሚገዛው በሕዝቦች ምኞት ወይም ንቃተ — ሕሊና ጥገኛ ባልሆኑ ፤ ነባራዊ ሕጎች ነው ። ከዚህም በላይ እነዚህ ሕጎች የሕዝብን ምኞትና ንቃተ — ሕሊና ይወስናሉ ።

በሥልተ — ምርት ውስጥ ያለ ለውጥ የሚአመለክተው በሕብረተሰብ የምጣኔ ሀብት መዋቅር ላይ ያለውን ለውጥ ነው ። ከዚህም በማስከተል ፤ ይነስም ይብዛ ጠቅላላው ርዕዮተ — ዓለማዊው መዋቅር በፍጥነት ይለወጣል። ሕብረተሰብ ከአንዱ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጽ ወደ ሌላኛው ይተላለፋል ።

በምርት ኃይሎችና እንደየሕብረተሰብ እርምጃ መለኪያ በመሆን ከነርሱም በሚሠምሩት የምርት ግንኙነቶች የዕድገት ደረጃ ላይ በመንዝ ማርክስ አምስት ዓይነት የሕብ



ረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጽ አሳይቷል — ጥንታዊው ጋርዮሽ ፤ የባሪያ አሳዳሪ ፤ የመልከኛ ፤ የካፒታሊስትና የኮሚኒስት በማለት ። እያንዳንዱ ተከታታይ አቀራረጽ በሰዎች ታሪክ ላይ አዲስ ደረጃን ያስመለክታል ።

በቡርዧ ሶሲዮሎጂ ውስጥ ታሪክን እንደተከታታይ ዙር — መልስ (Cyclical) እንደ ማያቋርጥ ዙረት አድርገው የሚመለከቱ ንድፈ — ሀሳቦች አሉ ። እያንዳንዱ ዙር መልስ ዙረት ቀድሞ የሆነውን መልሶ የሚደግም ነው እንጂ በአጠቃላይ ዕድገት የለም ብለው ያምናሉ ።

እርግጥ ይህ ትክክል አይደለም ። በተለያዩ አቀራረጾች (Formations) ውስጥ ያሉ የምርት ኃይሎች ደረጃ ሲነጻጸር ከአንዱ አቀራረጽ ወደሌላው በተሸጋገረ ቁጥር ያአድጋል ። ሊካድ የማይችልም ባሕላዊ ዕድገት አለ ።

* እርግጥ ፤ «የባሕል ባለበት የመቆም» ሌላው ይቅርና ወደኋላ የሚሄድበት ጊዜ ነበር ። ለምሣሌ ፡— በአውሮጳ የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት በመልከኛው በተተካበት ወቅት ፤ አዲሱ ሕብረተሰብ በመጀመሪያ ላይ በባሕልና በሥነ — ጥበብ ሊረሳ የማይችል ማሽቆልቆል ደርሶበት ትንደነበር አይዘነጋም ። ይህ እንደገና የሚአረጋግጠው በምጣኔ — ሀብታዊ ሥርዓቱ ላይ አውቶማቲክ የሆነ የሕብረተሰብ ንቃተ — ሕሊና ጥገኝነት እንደሌለ ነው ። ይሁንና ፡— የባሕልን ተከፋፋይ መልኮቹን ሳይሆን በአጠቃላይ ዕድገቱን ብንመለከት ፤ እናም የተለያዩ የታሪክ ዘመኖችን ሳይሆን የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊን አቀራረጽ ብናነፃፅር ፤ እያንዳንዱ ባሕልን በሚመለከት ረገድ ከቀድሞው ይልቅ ወደፊት የመግፋት ደረጃ ነው ያለው ።

የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብታዊ አቀራረጽ የመተካካት ትንታኔ የሚአሳየው ፤ ከዙር — መልስ እንቅስቃሴ ባሻገር ሁልጊዜም ቢሆን ሰብዓዊው ሕብረተሰብ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እያደገ የሚሄድ መሆኑን ነው ። ይህ ነው የሕብረተሰብ ዕድገት መንገዱ ።

## ፫ — መደቦችና የመደብ ትግል

### መደቦች ምንድን ናቸው ?

እያንዳንዱ ሕብረተሰብ ፤ ከጥንታዊው ጋርዮሽ በስተቀር ፤ በምጣኔ ሀብት በኩል አንዱ ባንዱ ላይ ጥገኛ በመሆንና እያንዳንዳቸው በተለያዩ ዋና ባሕሪዎች በመለያየት በትላልቅ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተከፍለዋል ። በማርክሲስቶች አባባል እንዲህ ዓይነቱ አከፋፈል እንደ ባሪያና ባሪያ አሳዳሪ ፤ የመልከኛ መኳንንትና ገበሬ ፤ ካፒታሊስትና ሠራተኞች ያሉት መደቦች ናቸው ።

ዋናዎቹ የመደብ ገጽታዎች (ባሕሪዎች) ምንድን ናቸው ? የከበርቴውን ሕብረተሰብ እንውሰድና በሠራተኞችና በካፒታሊስቶች መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት እንመርምር ። በኑሮ ሁኔታቸው ፤ በአለባበሳቸውና በሥነ — ሥርዓታቸው (Manner) ይለያያሉ ። እነዚህ ባሕሪዎች ዋና ናቸው ግን መሠረታዊ የመደብ ልዩነቶችን እያነጥሩም ። አይገልጹም ፤ ለምን ? ለምሣሌ ፦— ሠራተኛውና ካፒታሊስቱ የተለያዩ አመለካከቶችና የኑሮ ዘዴዎች አሏቸው ። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ካፒታሊስቱ ከፍተኛ ገቢ ስላለው ነው ብንል ወደ እውነቱ እየተቃረብን ነው ፤ ማለትም ወደ መደቦች መሠረታዊ ልዩነት እየተዳረስን



ስለሆነ — ምጣኔ ሀብት አድማስ ላይ በተመሠረቱት ምክንያቶች መሆኑ ነው ። ይበልጥ ትብ ( Incisive or Sharp ) የሆነው ትንታኔ ሠራተኛውና ካፒታሊስቱ የተለያየ ገቢ እንዳላቸው ብቻ አይደለም የሚአሳየው ። ይህን ገቢ እያንዳንዱ ፍጹም በተለያየ መንገድ ነው የሚአገኘው ፤ እናም ይህ ለምን ካፒታሊስቱ የሕብረተሰቡን ከፍተኛውን ሀብት ከሠራተኛው ይበልጥ ያገኛል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳናል ። መልሱ ፦— ምክንያቱም ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎችን ስለያዘ ነው የሚለው ይሆናል ። ይህ ባለቤትነት ካፒታሊስቱ ምጣኔ ሀብቱን እንዲገዛና ሠራተኛውን እንዲበዘብዝ የላቡንም የሥራ ፍሬ እንዲአጋብስ ይረዳዋል ።

ስለዚህ ፤ አንድን መደብ ከሌላኛው መለያው ጸባይ ከምርት መገልገያዎች ጋር ያለው ግንኙነት ነው ። ሌሎች ጸባዮች ከዚህ በማስከተል ይመጣሉ ። በሕብረተሰብ የምርት ሥርዓት በሕብረተሰብ የሥራ ድርጅት ሚና ፤ የሕዝብ ንብረት የሚበዘበዝበት መንገድና የዚህን ንብረት አንጻራዊ ድርሻ እያንዳንዱ መደብ የሚደስትበት ፤ ከዚህም በተጨማሪ የመደቦች ፖለቲካዊና ግብረ — ገባዊ ፤ ሥነልቡናዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ገጽታና ጸባይ የሚገኝበት ቦታ እነኝህ ናቸው ፦— የምርት መገልገያዎች ።

በእርግጥ ፦— መደቦች ሊኖሩ የሚችሉት የሕዝብ ክፍሎች ከምርት መገልገያዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተለያዩ ደረጃ በሚይዙበት ሕብረተሰብ ብቻ ነው ። የግልንብረት ባልነበረበት የጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ መደቦች አልነበሩም ። ይሁንና መደቦች ዘላለማዊ አይደሉም ።

ከግል ንብረት ጋር ነው የተከሰቱት ፤ ስለዚህም ይህ ዓይነት የንብረት አያያዝ ሲጠፉ ቀስ በቀስ ይጠፋሉ ።

## የመደብ መጨቆኛ መሣሪያ

በዝባዥ መደቦች የምርት መገልገያዎችን ከያዙ ጊዜ ጀምሮ ፍላጐታቸውን ወደ ሕብረተሰቡ ውስጥ ለማስገባት የሚጠቀሙበትን ሰፊ ምጣኔ — ሀብታዊ ኃይል ተጠቅመዋል ። የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነትና ብዙኃኑን ለመበዝበዝ የጥቂቶችን መብት የሚያረጋግጠው ሥርዓት ወዲያውያ ዓይነት ሕብረተሰብ ሲመሠረት ነው የታወጀው። የበዝባገሮችን ፍላጐት ተጻራሪ የሆነ ማንኛውም ክንዋኔ ሕገወጥ እንደሆነ ተገልጿል፤ እናም ተረግጠ ተይዟል ። በመደብ ሕብረተሰብ ውስጥ ሕብረተሰባዊ ግንኙነቶች የሚገዙት የገዥውን መደብ ፍላጐት በሚገልጹ ሕጋዊ መልኮችና ደንቦች ነው ። አጠቃላይ መጠሪያቸው «ሕግ» ነው ።

ግን ለምንድነው ሕብረተሰብ የገዥውን መደብ ፍላጐት መታዘዝና ለሕጐችም ታማኝ ጠባቂ የሚሆነው ? የዚህ ምክንያቱ የገዥው መደብ ፖሊስን፤ ጦር ሠራዊትን፤ ፍርድ ቤቶችን ፤ እሥር ቤቶችንና ሌሎችንም ሕግ አጠናካሪ አካሎችን ስለሚቆጣጠር ነው ። በአንድነት ሲጠቃለሉ ፣ እነዚህ አካሎች ተግባሩ ተበዝባዥ መደቦችን መጨቆን የሆነውን ፖለቲካዊ መዋቅር — «መንግሥት» የሚባለውን ይፈጥራሉ ። በማንኛውም የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብት አቀራረጽ :— በብዝበዛና በግል ንብረት ላይ በተመሠረተ — መንግሥት በተበዝባገሮች ላይ የበዝባገሮች የመደብ መጨቆኛ መሣሪያ ነው ።



መንግሥት የታየው ሕብረተሰብ በመደቦች ሲከፋፈል ነው ። እስከ አሁንም ድረስ ሁሉም ሰው ሕብረተሰባዊ ሁኔታዎችን በሕብረት አካሂዷል ። ሥልጣን ከሰዎች አልተለየም ነበር ። የዕድሜ ታላላቆችና የጐሣ አለቆች ሥልጣን የተመሠረተው በግለ — ሰቦች ጠባይ ላይ ነው ፣ እንደ ገጠመኝ ፤ ጀግንነትና ፤ ጥበብ ባሉት ። ግን ከግል ንብረትና ብዝበዛ መከሠት ጋር ፤ ባለንብረት ክፍሎች ምንም እንኳ ጥቂቶች ቢሆኑ ፤ ቀስ በቀስ በሕብረተሰቡ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን ጨበጡ ። ይህን አስከትሎ ፤ ሥልጣን ከሕዝቡ ተለየና ወደ በዝባገሮች መንግሥታዊ ኃይል ተለወጠ ፤ ዋና ተግባሩም የብዙኃን ተጨቋኞችን መቋቋም መሰባበር ሆነ ።

የሕብረተሰብ — ምጣኔ ሀብት አቀራረጽ በሚለወጥበት ጊዜ የመንግሥት መደባዊ አፈጣጠርም እንዲሁ ይለወጣል ። ሶስት ዓይነት ዋና በዝባዥ የመንግሥት ዓይነቶች እናያለን :— የባሪያ አሳዳሪ ፤ መልከኛ እና ካፒታሊስት ።

ይሁንና በዓይነት ብቻ ሳይሆን መንግሥት በሌላም መንገድ ልዩነት ሊኖረው ይችላል ። እስቲ ብዙ የዳበሩ የካፒታሊስት መንግሥታት ላይ እናተኩር :— ለምሣሌ :— እንግሊዝ ሕገ—መንግሥታዊ (Constitutional—monarchy) ዘውደኛ ስትሆን ዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ ፕሬዚዳንታዊ አገዛዝ አላት ። ይሁንና በቅርጽ ቢለያዩም ሁሉም አንድ ዓይነት መንግሥታት ናቸው ። የመንግሥት ቅርጽ ጥገኛ የሚሆነው በአገዛዝ ቅርጽ ላይ እና ሁለተኛ ደግሞ የበላይነቱን በያዘው የፖለቲካ ገዥ ነው ። ሁለት ዓይነት ቅርጽ ያላቸው አገዛዞች አሉ :— ዘውደኝነትና ሬፑብሊክ የሚባሉ ።

*    ዘውደኝነት (Monarchy) በዘር በሚተላለፍ መብት
የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት ነው ። ዘውደኛው
(ንጉሥ ፤ ዛር ፤ ንጉሠ — ነገሥት) የሚወክለው የገዥውን
መደብ ነው ። የእርሱ ድርጊቶች ወይም ዓላማው ከገዥው
መደብ ጋር ከተጋጩ ፤ የኋለኛው ክፍል አጐብዳጅ ዘውደኛ
በሆነ ሌላ ሰው እርሱን ለመተካት ዘዴዎችን ይፈልጋል ፤
ወይም በሕገ — መንግሥትና በፓርላማ ድጋፍ በመጠቀም
ካለው ሥልጣን ያግደዋል ።

*    ሬፑብሊክ የሚለው ቃል የመጣው ከላቲን ቋንቋ
«ሬስ ፑብሊክ ፡— የጋራ ምክንያት ወይም መንስኤ »ከሚ
ለው ሆኖ የሚአመለክተው በተመረጡ አካሎች (ሰዎች)
የሚከናወንን የአገዛዝ መልክ ነው ። ለየት ያለ አንደኛው
ን መደብ በሌላው የመጨቆኛ መልክ ነው ።

የፖለቲካ ገዥ የአገዛዝ ዘዴዎችን ይወስናል ። በሕብ
ረተሰቡ የመደብ ኃይሎችና በፖለቲካዊ ግንኙነት ላይ በመ
መርኮዝ ፤ የገዥውና የበዝባዡ መደብ የተጨቆኑት መደ
ቦች እንደተረገጡ እንዲቆዩ ሽብርን በማስፋፋት (በማሠ
ራጨት) ይጠቀምበታል ። ከዚህም በላይ የከፋፍለህ ግዛውን
ፖሊሲ (A Stick-and-Carrot Policy) በተግባር ለማዋል
ሁሉንም የሕዝብ ክፍሎች በተለያዩ መጠን (ደረጃ)
ይጠቀምባቸዋል ።

ይሁንና የዚህ ወይም የዚያ የፖለቲካዊ ገዥ ምርጫ
ሙሉ በሙሉ የገዥ ክፍሎች ተግባር ነው ብሎ ማሰብ ስህ
ተት ይሆናል ። የፖለቲካ የበላይነትን በማሸነፍ ፤ ማንኛ
ውም በዝባዥ መደብ ሁልጊዜም ሙሉ የሥልጣን ቁጥጥር
ለማግኘት ይታገላል ። ከሌሎች መደብ ከሁሉም በላይ



ከብዙሃን ሠራተኛ ሕዝቦች በሚገጥመው ቅዋሚ ሕዝባዊ
እንቅስቃሴ እንዳይነሳ አስቀድሞ ለመከላከል ስምምነቶች
እንዲአካሂድ ይገደዳል ። ቢሆንም እንዲህ ዓይነት ስም
ምነቶች ጥቂት ቢገፉም እንኳ እስከመጨረሻ አይዘልቁም ።
በመጨረሻ የገዥው መደብ የመጨረሻ (መውደቂያ) የበላ
ይነት ተግባር የሆነውን ሥልጣኑን ከፊሉን ይሰጣል
(ያከፋፍላል) ።

አሁን ፤ በጣም ዋና ጽንስ — ሀሳብ የሆነውን ዲሞክ
ራሲን ለማብራራት ጊዜው ደርሷል ። ዲሞክራሲ የአገዛዝ
ሥልት የሆነ የብሔሩን ሁኔታ ለማካሄድ በአጠቃላይ
የሕዝብን ተሳትፎና የግለሰቡን ነጻነት የሚአረጋግጥ ነው ።
በሌላ አባባል በዲሞክራሲ ሥር ዜጐች ፖለቲካዊ መብታ
ቸውን በሕግ ፊት እንደ እኩልነት ፤ የመናገር ነጻነት ፤ የመ
ሰብሰብ ነጻነት ፤ የጽሑፍ ነጻነት ፤ የቤት አለመደፈር የመ
ሳሰሉትን ለመለማመድ (ለመጠቀም) መቻል ማለት ነው ።

*    በብዝበዛ ላይ በተመሠረቱ ሕብረተሰቦች ውስጥ ዲሞ
ክራሲ ከመገደብ (ከመታገድ) በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም ።
በባሪያ አሳዳሪው ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊኮች ፤ እንደ አቴና
ወይም ጥንታዊ የሮማ ግዛት በመሰሉትና ለብዙ ሺ ዓመታት
የዲሞክራሲ ሞዴል ሆነው በአገለገሉት ፤ አብዛኛው ሕዝብ
— ባሮች — ከማንኛውም ሰብዓዊ መብት የተገለሉ ነበሩ ።

*    ሀብታም የባሪያ ጌቶች ዋናውን ነገር — የባሪያ ሥር
ዓትን ለማቆየት ሲባል ብቻ — ገበሬዎችንና ነጋዴዎችን
ነጻ ለማውጣት ከፍተኛ የሥልጣን ክፍያ ሰጡ ። ዲሞክራሲ
ነጻ የሆኑ ሰዎች ባሮችን ለመጨቆን እንዲችሉ አንቀሳቀሰ ።

*    በመካከለኛው ዘመን በኢጣሊያ እንደ ቬኒስእና ፍሎ
ሬንስ ፤ በሩሲያ ኖቭጐሮድ የመሳሰሉት የከተማ መንግሥ

ታት (ሬፑብሊኮች) ይገዙ የነበሩት በሀብታም ነጋዴዎች
በሕብረት — ሥራ ባለቤቶች ነበር ። በጊዜው የነበሩ ም
ራባውያን ዲሞክራሲዎች አጠቃላይ ምርጫ ቢኖራቸው
ም ፣ ሁሉንም ምጣኔ ሀብታዊ ኃይላቸውን የዜና ማሠራጫ
መንግሥታዊ ወኪሎቻቸውን ፣ ሠራተኛው ሕዝብ በመንግ
ሥታዊ መዋቅሩ ውስጥ እንዳይሳተፍ ለመከልከል ለጉበ
ለማታለያና ለመዋሸት በሚጠቀሙበት በካፒታሊስቶች
ነው የሚገዙት ። ይህ የሚአሳየው ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች
በራሳቸው የመንግሥትን መደባዊ ይዘት ሊለውጡት እንደ
ማይችሉ ነው ።

በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ ሕብረተሰብ ውስጥ ፣ መን
ግሥት በመሠረቱ የበዝባዦችን የበላይነት መጠበቂያ
(ማቆያ) መሣሪያ ሲሆን ፣ ዲሞክራሲ ደግሞ የዚህ የበላይነት
አንደኛው ገጽ ነው ።

ግን ፣ በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ ሕብረተሰብ ውስጥ
ዲሞክራሲ ምንም ያህል የተወሰነና ሕጋዊ ይሁን በዚያ ዓይ
ነት ሕብረተሰብ ወይም ሁኔታ ውስጥ ለሚኖሩ ሠራተኛ ሕዝ
ቦች ሲሆን (ሲደረግ) ከሚገባው ሁሉ ይበልጥ ተቀባይነት
ያለው የአገዛዝ መልክ ዲሞክራሲን የያዘው ነው ።

* ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች ሕዝቦች ለብዙ መቶ ዓመ
ታት ለመብታቸው ባደረጉት የመብት ትግል ከገኙዋቸው
መደቦች የሚሰጡ ናቸው ።

* በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ በዛሬው ዘመን ሕብረተሰብ
ውስጥ የቡርዦዋ ዲሞክራሲ የራሱን መደብ ወሰን በመለ
በቅ ሠራተኛ ሕዝቦች ሁኔታቸውን ለማሻሻል ለትግላቸው
አመች ሁኔታ በሚፈጠርላቸው ጊዜ ይቋቋማቸዋል ወይ



ይዋጋቸዋል ። በሕገ መንግሥቱ ላይ በታወጀው ፖለቲካዊ ነጻነት በመንተራስ ፣ ሠራተኛው ሕዝብ በገጠርና በከተማ ከገኘው መደብ አዲስ ፖለቲካዊና ምጣኔ — ሀብታዊ ስጦታዎች ብቻ ሳይሆን ፣ በመንግሥት የሚረዳ ትምህርትና የጤና አገልግሎት እንዲሁም ለራሳቸው የፖለቲካ ፓርቲ ለመሥራት ፣ ለትክክለኛ ተወካዮቻቸውና ለፍላጎቶቻቸው ተዋጊዎች (ተሟጋቾች) ሁሉ ለመታገልና ጥያቄ ለማቅረብም ይችላሉ ። በተለይም ፣ የካፒታሊስቱ መደብ ፣ እያየለ የሚሄደውን አብዮታዊ ንቅናቄ በመፍራት ዲሞክራሲያዊ መልክ ያለውን አገዛዝ ለማፍረስና በምትኩ ምሉዕ — በኩልሄ በሆነ አምባገነንነት ለመተካት ይፈልጋል ። በእዚህ ዓይነት ሁኔታ ሠራተኛውን ሕዝብ ፊት ለፊት የሚገጥመው ቁልፍ የሆነ ተግባሩ ያገኘውን መብት ለማስጠበቅና የነበረውንም ለማስፋፋት የሚደረገው ትግል (ውጊያ) ነው ።

ሆኖም ዓይነተኛውና (ዋናው) ዲሞክራሲ ፣ መርሆው የሕዝብ አገዛዝና የግለሰብና የብዙሃኑ ነጻነት የሆነው ሊኖር የሚችለው ብዝበዛ ሲጠፋና በዝባዡ ሲደመሰስ ነው ።

## ታሪክ አንቀሳቃሽ ኃይል

ሰብዓዊ ታሪክ ፣ ተበዝባዦች ለብዙ ጊዜ በበዝባዦቻቸው ላይ የአካሄዱትን ጦርነት የመዘገበ ነው ። የጥንት የምዕራብና የምሥራቅ የባሪያ አሳዳሪ መንግሥታት ብዙ ጊዜ በባሪያ አመጾች ጡጫ ይንቀጠቀጡ ነበር ።

ለምሳሌ በቻይና ትልቅ ስፋት ያለው የገበሬዎች ጦርነት ፣ በመካከለኛው ዘመን የመልከኛ መንግሥታት ውስጥ የመደብ ተጻራሪነት ምን ያህል ትብ እንደነበር አሳይቷል ። በከበርቴ አገሮችም በወዝ — አደሩ የተካሄዱት የመደብ ትግ

ሎች ከ፲፱ኛው ምዕተ — ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ ኃይሉ
እየጨመሩ ቀጥለዋል ።

ለምንድነው የመደብ ትግል የሚኖረው ፤ እናስ በሕብ
ረተሰብ ታሪክ ውስጥ ምን ዓይነት ሚና ይጫወታል ?

የተጨቋኝ መደቦች በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው
ቦታና በጨቋኞቻቸው የሚደርስባቸው የውርደት ሥቃይ
ወደአብዮታዊ ድርጊት ይገፋፋቸዋል ።

የቡርዡዋ ፈላስፎች (ርዕዮተ—ዓለማውያን) የተቃራ
መደቦች ፍላጐት ሊታረቅ የሚችል ነው ብለው ይለፍ
ፋሉ ። ግን ፣ እንዴት ጨቋኝና ተጨቋኝ ሊታረቁ ይችላሉ
በዝባዦች ነጻ ፍላጐታቸውን ለማግኘት የሚጠቀሙበት
ወታደርና ፖሊስ ለመበታተን ፤ የመሬት ፤ የፋብሪካ እ
ሌላም የምርት መገልገያ ባለቤት እንዲሆኑ የሚከላከል
ቸውን ፍርድ ቤትና ዳኞችን ለማጥፋትና መሬትን ለገበ
ዎች ፤ ፋብሪካዎችን ለሠራተኞች ለማዞር ኃይል መጠቀ
ያስፈልጋል ። ከዚህ በኋላ ሀብታቸውን ሁሉ አጥተው በ
ባዥነታቸው ያከትማል ። በመደብ ትግል ብቻ ነው የምር
መገልገያዎች ከነእርሱ ሊነጠቁና ብዝበዛ ሊወገድ የሚ
ችለው ።

ቀደም ብለን እንዳወሳነው ፤ የሕብረተሰብ — ምጣ
ሀብት አቀራረጾች በአዲስ የምርት ኃይሎችና አርጅተው
በአረጁ የምርት ግንኙነቶች ግጭት ምክንያት ለአዲስ
መንገድ ይከፍታሉ ። ግን በዝባዥ መደቦች ፤ በአለው አ
ራረጽ ገዥ የሆኑቱ ፤ እነዚያ የአረጁ ግንኙነቶች እንዲጠ
ፈቃደኛ አይደሉም ። ሆን ብለው ከእነርሱ ጋር የሙጥ
በማለት ሀብታቸውንና ኃይላቸውን እንዳለ ለማስቀረ



ይዋጋሉ ። በጣም ረጅም ጊዜ አይደለም ፣— በተለያዩ የእ
ስያ አገሮች የጉሣ አለቆችና መልከኛ ገዥዎች ፍጹማዊ
ኃይላቸውንና ጥቅሞቻቸውን በሚገዟቸው ገበሬዎች ንብረ
ትና ኑሮ ላይ ለማቆየት በኃይል እንደተዋጉና በምን ያህል
ጥንካሬ የመሬት ማሻሻያን በተግባር እንዳይውል እንደተ
ቃወሙ ማስታወስ ይቻላል ። ለካፒታሊስቱ ሥርዓት በራ
ሳቸው ፍላጐት ይሰጣሉ ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው ። እንዲ
ያውም ተግባራቸው ሥርዓታቸውን እስከመጨረሻው መራ
ራ ፍጻሜ ድረስ የሚዋጉለት መሆናቸውን ያሳያል ።

ማኅበራዊ ሥርዓት በሌላ ይበልጥ ተራማጅ በሆነ
ሥርዓት የሚተካው በግብታዊነት አይደለም ። ይሁንና አሮ
ጌዎቹ የምርት ግንኙነቶች ለዕድገት እንቅፋት ይሆናሉ ።
ለእነኝህ ግንኙነቶች የሚዋጉትን የአድሃሪ መደቦች መቋ
ቋም ፤ መሰባበር አስፈላጊ ይሆናል ። በተጨቋኝ መደቦች
የተካሄደው አብዮታዊ ትግል ታሪካዊ ትርጉሙ ይህ ነው ።
የሕብረተሰብን ዕድገት ለመገደብ አድሃሪ መደቦች የሚአስ
ቀምጡትን እንቅፋት ጠራርገው ይጥላሉ ። በማንኛውም
በብዝበዛ ላይ በተመሠረተ ሕብረተሰብ ውስጥ የታሪክ
አንቀሳቃሽ ኃይል የመደብ ትግል ነው ። ያለዚህ ተጻራሪ
በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ ዕድገት የለም ። ይህ ትግል የመ
ጨረሻ ነቁጡን የሚደርሰው በሕዝባዊ አብዮት ወቅት ነው።

## ሕዝባዊ አብዮት

በታሪክ ውስጥ የቀስ በቀስ ዕድገትና አጠቃላይ የሕብ
ረተሰብ ሥርዓት ሥርነቀልና የድንገተኛ ለውጦች መካከል
ባሉት ዘመኖች ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ ።

* ከሮማውያን ግዛት ውድቀት በኋላ የመካከለኛው
ዘመን «ችክ ያሉና የጭካኔ ዘመናት» በአውሮጳ መጡ ።
የቤተ መንግሥት መፈንቅለ — መንግሥቶች ታቀዱ ፤ አን
ደኛው ንጉሣዊ ቤተሰብ ሌላውን ተካ ፤ ጦርነቶች ድብልቅ
ሊቃቸው ወጣ ! የመልከኛ ይዞታዎች እንደገና ተቀረጹ ።
ግን ከነዚህ ወቅቶች አንዳቸውም እንኳ የመልከኛውን
ሥርዓት ባሕሪ አልለወጡትም ። ከጊዜ ወደጊዜ የገበሬ
አመጽ ነበልባሎች የፊውዳልን መኳንንትንና ዘውደኞች
ጠርጐ ለመጣል ሁሉንም አገሮች እንዲሳተፉ አደረጉ ።
ሆኖም የገበሬዎችን የዋህነት በመጠቀም መሣፍንቱ ሥልጣ
ናቸውን በመከፋፈል አመጹን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ
አዳፈኑት ።

* ግን በኋላ ታላቅ የሕብረተሰብ የአጣዳፊ ለውጦች
ዘመን መጣ ። በ፲፮ኛው ምዕተ — ዓመት በሆላንድ ፤ በ፲፯
ኛው ምዕተ — ዓመት በእንግሊዝ ፤ እና በ፲፰ኛው ምዕተ —
ዓመት በፈረንሣይ ይህ ሁኔታ ተፈጽሟል ። በሶስት
ምዕተ — ዓመት ውስጥ በአውሮጳ መሪ አገሮች የሕብረተ
ሰብ ሥርዓቶች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ተደርጓል — መልከ
ኛው ሥርዓት በካፒታሊዝም ተተክቷል ።

* ተመሳሳይ የሆኑ ታሪካዊ የዕድገት ዝንባሌዎች በእ
ስያ አገሮች ውስጥም ሊጠቀሙ ይቻላል ። ለምሣሌ በቱርክ፤
አርጅቶ ያፈጀው የመልከኛ የምርት ግንኙነት ፤ በሕብረ
ተሰብ ዕድገት ላይ ጐታች የነበረው — በነጻነት ጦርነት ጊዜ
(፲፱፻፲፱ — ፳፪) ዓይነተኛ ወታደራዊ መሪና የፖለቲካ
ሰው ኋላም የሀገሪቱ የመጀመሪያ የቱርክ ሬፑብሊክ ፕሬዚ
ዳንት በሆነው በጀኔራል ሙስጠፋ ከማል መሪነት የቱርክ
ሕዝብ ባካሄደው የቡርዥዋ ብሔራዊ አብዮት ወሳኝ የሆነ



ጡጫ ቀምሷል ። ለውጡን የአስተዋወቁት ከማልና ረዳ
ቶቹ መልከኛን ሥርዓት ከመጀመሪያውኑ ሲአጥላሉ የነ
በሩት ፤ ለአንድ ሺ ዓመት ያህል የመልከኛ ወጐችን ሲአ
ስጠብቅና ዘብ ሆኖ የኖረውን ሙሉ ኃይል ያለው ሆኖ ያገ
ለግል የነበረውን ቤተክርስቲያን ከመልከኛ መኳንንት በመ
ንጠቅ ነው ። ይሁንና ያ ሕዝባዊ አብዮት ፤ በሰፊው ሠራተ
ኛ ንቁ ተሳታፊነት የተካሄደው ፤ በአጠቃላይ ተራማጅ የነ
በረው ፤ ለሁኔታቸው (ለኑሮአቸው) ወደሚአገለግል መሠ
ረታዊ መሻሻል አልመራቸውም ። እንዲያው ብቻ መልከኛ
በዝባዦችን በካፒታሊስት በዝባዦች ተካና አረፈው ።
በሌላ አነጋገር ፤ አንድ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ሕብረተ
ሰብ በሌላው ተተካ ።

ስለዚህ ፡— በሕብረተሰብ ሥርዓት ውስጥ የሚታይ
ሥር — ነቀል ለውጥ ፤ አንድ የሕብረተሰብ ምጣኔ—ሀብ
ታዊ አቀራረጽ በሌላው የመተካቱን ውጤት የሚአስገኘው
ሕዝባዊ አብዮት ተብሎ ይጠራል ።

በምጣኔ — ሀብታዊ አባባል ፤ በምርት ኃይሎችና በም
ርት ግንኙነቶች መካከል ከሚነሳው ግጭት ነው የሚመነ
ጨው ። የሕብረተሰብ ተራማጅ ክፍሎች ቅራኔውን ለመፍ
ታትና አሮጌዎቹን የምርት ግንኙነቶች ለማስወገድ ይሻሉ ።
ይሁን እንጂ ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ ለማስቀረት
በሚታገሉ አድኃሪ መደቦች መቋቋም ይገጥማቸዋል ። የገ
ዥው መደብ አብዮታዊ እንቅስቃሴን ለመምታት የመንግ
ሥትን ኃይል ይጠቀማል ። ስለዚህ የሥልጣን ጥያቄ ለማን
ኛውም አብዮት ዋናውና ተቀዳሚው ጥያቄ ነው ። አንድ
ጊዜ አብዮታዊ መደብ ሥልጣን ከጨበጠ ፤ ይህን ሥልጣን

አሮጌውን ሥርዓት ለመጠራረግና አዲሱን ለማስተዋወቅ
ይጠቀምበታል ።

ማንኛውንም የሥልጣን መጨበጥ ፤ ማንኛውም የአ
ሠራር ለውጥ ፤ ሕዝባዊ አብዮት ነው ተብሎ አይወሰ
ድም ። አርጅተው ያፈጁ የምርት ግንኙነቶች ያለሕዝቡ
ሰፊ ተሳትፎ ሊሰባበሩና ይበልጥ ተራማጅ በሆኑ አዲስ
ግንኙነቶች ሊተኩ እንደማይችሉ እውነት ነው ።

አለበለዚያ ማንኛውም የሥልጣን ለውጥ ፤ ማንኛውም
የአሠራር ለውጥ ፤ ምንም ያህል ተራማጅ ይሁን ፤ እንዲሁ
መፈንቅለ — መንግሥት ነው የሚሆነው ፤ ምንአልባት
በአንዳንድ አመቺ ሁኔታዎች ምክንያት ብቻ እና የሕዝቡ
ንቁ ድጋፍ ከተሰጠው ወደ ሕዝባዊ አብዮት ሊአድግ ይች
ላል ።

ታሪክ አብዮት በትእዛዝ የማይሠራ ('ሠ' ይጠብቃል)
እንዳልሆነ ያሳያል ። በመጀመሪያ አብዮታዊ ሁኔታ መፈ
ጠር አለበት ። ይህ ሊሆን የሚችለው የገዥ መደቦች በድ
ሮው መንገድ ሊገዙ እንደማይችሉና ተጨቋኞችም በዚያ
መልክ ለመኖር ፍላጎት እንደሌላቸው የሚአሳይ ሁኔታ
ላይ ሕብረተሰቡ ሲደርስ ነው ።

እንዲያም ቢሆን ማንኛውም አብዮታዊ ሁኔታ ወደአ
ብዮት ያድጋል ማለት አይደለም ። አብዮት እንዲፈጠር
ለተግባር የተዘጋጁ ሕዝባዊ የፖለቲካ ኃይሎች እንዲኖሩ
ያሻል ። እነኝህ ኃይሎች ሊመጡ የሚችሉት ያለውን ሥር
ዓት ለመገልበጥና አብዮቱን ወደ ድል ለመምራት የመሸ
ከም ፍላጎት ካላቸው ፤ እንበልም የአብዮቱ እንቀሳቃሽ
ኃይል ከሆኑት መደቦች ነው ። እነዚህን ኃይሎች ለማገ



ላቀስ አብዮታዊ መደቦች የመደብ ትግል ገጠመኝ እንዲ
ኖራቸው ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ድርጅቶችን እንዲመሠ
ርቱ ፤ እና ለአብዮታዊው መንስኤ (ምክንያት) መስዋዕት
የሚሆኑ መሪዎችን ለማስገኘት ቆራጥ ተግባር ለመውሰድ
ችሎታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ።

ተጨቋኝና ተበዝባዥ መደቦች በሕዝባዊ አብዮት
ውስጥ ልዩ የሆነ ንቁ ሚና ይጫወታሉ ። የጀግንነት ትግላ
ቸው የአሮጌውን ሥርዓት መሠረት ድራሽ አባቱን ያጠ
ፉል ። የአድሃሪ መደቦችን የሥልጣን ጠንካራ ይዞታዎች
ለማጥቃት የአብዮቱን ተዋጊ ኃይሎች ይመሰርታሉ ። በማ
ከታተልም ፤ አብዮታዊ ድሎችን ከጸረ — አብዮተኞች
ድርጊት በቆራጥ ነት ይከለከላሉ ።

ሕዝባዊ አብዮቶች ከተግባራቸው ሲነጻጸሩ አፈጣጠ
ራቸው ለየት ይላል ። አንድ አብዮት የቡርዧ ወይም የካፒ
ታሊስት ግንኙነቶችን ከአስተዋወቀ ፤ የቡርዧ አብዮት
ነው ። የሶሻሊስት ሥርዓትን ከአስተዋወቀም ፤ የሶሻሊስት
አብዮት ነው ።

የታላላቅ አብዮቶች ሁሉ ዋና እንቀሳቃሽ ኃይል ተጨ
ቋኝ መደቦች ነበሩ ። ናቸውም ። በፖለቲካዊ ኑሮ የብዙኃኑ
ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ምክንያት ሁኔታዎች በጣም በፍጥነት
አደጉ ። ሕዝባዊ አብዮት እንደ አውሎ ነፋስ ነው ። ለመተን
ፈስ እንዲአስችል በማድረግ አየሩን ያጸዳል ። አብዮቶ
ችም ከማኅበረ — ሰቡ ርምጃ ፊት ለፊት የተደቀኑ እንቅፋ
ቶችን ይጠራርጋሉ ፤ በዚህ ጥሩ ምክንያት ነው ማርክስ
«የታሪክ አሽከርካሪዎች » ናቸው ያለው ።

## ፩. የማኅበረ — ሰብ ታሪካዊ መልኮች ፣

### ቤተሰብና ነገድ

ሕዝቡን በሕብረተሰብ ቡድኖች ከሚከፋፍሉ መደብችና ሌሎች ልዩነቶች ሌላ ፣ ወደ ሰው ጥንታዊ ኑሮ ራቅ ብለው የሚሄዱ የማኅበረ — ሰብ ታሪካዊ መልኮች ኖረዋል ።

ከነኝህ ውስጥ የመጀመሪያው ከደም ዝምድና የሚገኘው ቤተሰብና ነገድ ነው ። ሁሉም ሕዝቦች በሥጋ ዝምድና ወይም ከአንድ አያት በመወለድ ፣ በአባትም ይሁን በእናት ምክንያት የተባበሩ አድርገው ራሳቸውን ቆጥረው ነበር ። ማኅበረ — ሰብ በመሆን አንድነት ኖረዋል ። ይህን እንደ ድንገተኛ ምኞት አይደለም የሚሠሩት ፣ ወይም ደግሞ ምክንያቱም «ከውሃ ደም ይወፍራል» በሚል (በዝምድና ወይም በሥጋ ቆጠራ አይደለም — ከተርጓሚው) ። ለማደን ፣ ወይም ከብት ለማርባት ዝንባሌ ፣ ወይም መሬትን ለማረስ ፣ እና ሌላ ሥራ ለመሥራት ሕጻናትን ከመንከባከብ ጋር ሕዝቦች በሥራ እንዲተሳሰሩ ተገደው ነበር ።

እንዲህ ዓይነት ማኅበረ — ሰቦች ሲአድጉ ፣ ብዙ ፣ ብዙ ቡድኖች ከእነርሱ እየተለዩ መጡ ። ግን ሁሉም ዝምድናቸውንና ምጣኔ—ሀብታዊ ግንኙነታቸውን የቤተሰቦች ወይም የነገዶችን ሕብረት ለመፍጠር ይጠብቁታል ። ብዙውን ጊዜ ነገዶች በመቶ ወይም በሺ የሚቆጠሩ ነበሩ ። አባሎቹ የሚኖሩበትና የሚአድጉበት አንድ የተወሰነ አካባቢን ይይዛል ። የነገድ ሰዎች አንድ ዓይነት ቋንቋ ይናገራሉ እና አንድ ዓይነት ልማድ ፣ የበዓል አከባበርና የባዕድ አምልኮ ነበራቸው ። የአንድ ቤተሰብ ወይም ነገድ ኑሮ በግብታዊ ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነበር ። ቤተሰብ በአዋቂዎች በተመረጡ ታላላቆች (በዕድሜ) ነበር የሚመራው ። ነገዶች የሚገዙት በነገዳዊ ስብሰባዎች በሚመረጡ ቆንሲሎች ነው ።

በኋላ በጐሣ የተያያዙ ነገዶች ሕብረት ለመፍጠር ጀመሩ ። የዚህ አስፈላጊነት የተመራው በምጣኔ ሀብታዊና ወታደራዊ ግንዛቤዎች ነው ። ይሁንና የሥጋ ዝምድና ዋና አያያዥ መሆኑን ቀጥሎ ነበር ።

ከሥራ መከፋፈል መቀጠል ጋር የኤኮኖሚ ዕድገትና የግጦሽ መሬት በአዳኝ ነገዶች መካከል ማከፋፈሉ የግዛታዊ ርቀትና ቅርበትን ሚና በመጨመር በጐሣ ዝምድና የተያያዙ ነገዶችን ወደ የግዛት አንድነት አመራቸው ። ቀስ በቀስ የሥጋ ዝምድና ዓይነተኛነትን ዝቅ እያደረገ የግዛታዊ መተሳሰርን ጨመረ ።

### ብሔራዊ ቡድኖችና ብሔር

የነገዶች ሕብረት በተወሰነ የጊዜ ርዝመት በዝምድና ደረጃ ብቻ የሚኖር በጣም ሠፊ ድርጅት ነው ። ምጣኔ — ሀብታዊ መተሳሰሮች ሲአድጉ ምንም እንኳ በዝምድና ደረጃ ያልተዛመዱትን ሁሉ ቢአያይዙም ፣ የግዛታዊ መጠን ዓይነተኛነት እየጨመረ ነገዶች በአንድ ግዛት ውስጥ መኖራቸው እውነት ነው ። ስለዚህም አንድ ዓይነት ምጣኔ ሀብታዊ ዝንባሌዎችና መተሳሰሮች እንዲሁም ባሕላዊ ግንኙነቶች ወደመቀራረብና ወደ መጨረሻው አንድነት እንዲሁም አንድ ዓይነት ቋንቋ እና ልማድ ወደ መመሥረቱ ገፉፉቸው ። የጋራ ታሪካዊ መዳረሻቸውን በመወሰን ፣ አንድ

ዓይነት የሥነ — ልቡና ወዘናቸውንና ባሕላቸውን ቀረጹ ።
ይህ ዕድገት ለብሔራዊ ክፍል (ቡድን) የመከሰትን መነሳ
ሳት መንገድ ሰጠ ።

የብሔራዊ ቡድኖች በባሪያ አሳዳሪና በመልከኛው
ሕብረተሰብ ታዩ ።

* በእሲያ የብሔራዊ ቡድኖች አብዛኛው ክፍል ነገዳዊ
ማኅበረ — ሰቡ ወደባሪያ አሳዳሪና መልከኛው መንግሥት
በተሸጋገረበት ጊዜ ቀስ በቀስ አደጉ ። ስለዚህ የላአ ሉም፣
የላልቴንግ እና የላአሱን ነገዶች የላአ ብሔራዊ ቡድንን መሠ
ረቱ ፤ የኔቫርና ኩርግሃ ነገዶች የኔፓልን ብሔራዊ ቡድን
ያዙ ፡— ወዘተ ........ ።

የብሔራዊ ቡድን ከሌላው አንጻር የላላ ዘራዊ ማኅበረ
— ሰብ ነበር ። ብዙዎቹ ጥንታዊ ብሔራዊ ቡድኖች ተከፋ
ፈሉ ፤ ሌሎችም ወደ ብሔርነት አደጉ ። ብሔራዊ ቡድኑን
ም በአንድነት አስተሳሰረው የያዙት ሁኔታዎች በአንጻሩ
ነዋሪ አልነበሩም ፤ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ማኅበረ —
ሰብ ለራሱ የሆነ (ነጠላ) ምጣኔ — ሀብት አልነበረውምና።

ብሔራዊ ቡድን የያዙት የዘራዊ — ግዛት ቡድኖች
በአንጻሩ እራሳቸው በሚያመርቱት ምርት የራሳቸውን ፍላ
ጐት ለማርካት በመሞከር ከሌሎች ተገልለው ኑሮአቸውን
ገፉ ። ከምርት ኃይሎች ዝቅተኛነት ሲነጻጸር ቀዋሚ የሆነ
የዕቃዎች መለዋወጥን የሚአሟላ በቂ ትርፍ ምርት ለማ
ምረት አላስቻላቸውም ። በጋራ ባሕል ውስጥ የአካባቢ
ልዩነቶች ለብዙ ጊዜ ድረስ ይነበቡ ነበር ፤ እንዲሁም
የጋራ ቋንቋው የቅላፄ ፤ የአነባበብ እና ሌላም ክፍልፋዮች
ታይተውበታል ።



ወደ መልከኛው ሥርዓት መጨረሻ ዘመን ብሔራዊ
ቡድን በያዙት ዘራዊ ግዛቶች መካከል የዕቃዎች መለዋ
ወጥ በአዲሶ የምርት ኃይሎች ላይ በመመሥረት ጨመረ ።
ምርት ለንግድ ፤ ማለትም በተለይ ለገበያ ማደግ ጀመረ ።
በተለያዩ ቡድኖች የሕብረተሰብ የሥራ ክፍፍል ይበልጥ
በጣም ግልጽ እየሆነ የአንዱ በሌላው ላይ ጥገኝነትም አደገ።
ለምሣሌ ጥጥ አብቃይ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች ሩዝና ሌላም
የምግብ ሸቀጦችን የሚለውጡባቸውን የጥጥ ውጤቶች
በመሥራት ሠለጠኑ ።

ብረት በማውጣትና በማቅለጥ የተሠማሩ ነገዶች የጥጥ
ውጤቶች ወይም እህላ እህሎች በማምረት ጊዜን ከማጥ
ፋት ይልቅ በለውጥ ማግኘት የተሻለ መሆኑን መረጡ ።

ትላልቅ የመለዋወጫ ማዕከሎች ፤ ገበያዎች ፤ ታዩ ።
ቀስ በቀስ ቤተሰቦችን ፤ ነገዶችና ብሔራዊ ቡድኖችን በጠ
ንካራ ምጣኔ ፤ — ሀብታዊ መተሳሰሮች ሕብረት የፈጠረው
ብሔራዊ ገበያ ተመሠረተ ።

በመጨረሻ ፤ ግዛታዊ ሕብረት በምጣኔ — ሀብታዊ
ሕብረት ተደገፈ ። ይህ አንድ ዓይነት የሆነ ብሔራዊ ባሕ
ልና ብሔራዊ ንቃተ — ሕሊና ለማሳደግ መሠረት ጣለ ።
እንግዲህ ብሔር ፡ --- የሕዝቦች የጸና ማኅበረ — ሰብ ሆኖ
የምጣኔ ሀብታዊ ፤ ግዛታዊ ወሰን ፤ ቋንቋ ፤ ባሕላዊና ሥነ
ልቡናዊ መተሳሰሮች ያለው ነው ።

በብሔሮች መካከል ያሉ ግንኙነቶች በሕብረተሰብ
ውስጥ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ። እራሳቸውን በምጣኔ —
ሀብቱ ፤ በፖለቲካውና በባሕላዊ እድማሱ ውስጥ እንዲሰሙ
ያደርጋሉ ።

## በብሔሮች ዕድገት ላይ ሁለት አዝማሚያዎች

በብሔሮች የዕድገት ግንኙነቶች መካከል ሁለት ልዩ የሆኑ አዝማሚያዎች አሉ ። የመጀመሪያው የብሔራዊ ኑሮ (ሕይወት) መንቃትና የብሔራዊ ነጻነት ፍላጐት ነው ። ሁለተኛው በብሔሮች መካከል ያለ ግንኙነትን የማስፋት፣ በመካከላቸው ያለውን ድንበር የማጥፋትና ሕብረተሰብን ዓለም አቀፋዊ የማድረግ ዝንባሌ ነው ።

በመሠረቱ ፤ የዓለም ሥልጣኔን ስለሚአበለጽጉ ሁለቱም ዓይነት አዝማሚያዎች ተራማጆች ናቸው ።

የመጀመሪያው አዝማሚያ በብሔሮች ዕድገት የመነሻ ደረጃ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል ። ወደ ሕልውና በመምጣት ላይና እሱነቱን ለማሳወቅ ነጻ የሆነ ምጣኔ — ሀብታዊና ባሕላዊ ዕድገቱን እንዲሁም መብቱን ለማስከበር የሚታገለው ብሔር ትግሉ ፣— እራሱን ከከበበው የመልከኛ ሕብረተሰብ ወይም ወደ ብሔርነት ደረጃ አድጐ በወጣለትና ስለዚህም ቀድሞውኑ ጠንካራ ከሆኑ ብሔሮች ጋር የሚመራ ይሆናል ። በዚያ ደረጃ ዋና ተግባሩ ብሔራዊ መንግሥትን የመገንባቱ ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ ፤ ይህ አዝማሚያ በተለይ ወደብሔርነት በሚአድጉ አንዳንድ ብሔራዊ ቡድኖችና በተለይም በእሲያና አፍሪቃ የአውሮጳውያን የቀድሞ ቅኞች ግዛት ላይ ጠንካራ ቅዋሜ በመፍጠር ትብ የሆኑ ብሔራዊ ግጭቶችን ያመጣል ። የጨቋኝ ብሔሮች የገዥ መደቦች ለብሔራዊ እርነት ያለውን መገፋፋት ይቋቋሙታል ። ይህን ለማሸነፍ ያለው አንድ አማራጭ መንገድ ቆራጥ የሆነ ትግል ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ በብሔሮች መካከል ያሉት ግንኙነቶች የሚአድጉት ተጻራሪ በሆነ መንገድ



ነው ። የአንዳንድ ብሔሮችና ብሔራዊ ቡድኖች ለሌሎች ባሪያ በመሆን ይሆናል ።

ሁለተኛው አዝማሚያ በተለይ ግልጽ የሚሆነው በገዥ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች ሁኔታ ውስጥና በብሔራዊ መንግሥት መመሥረት ላይ ነው ። ግን እንዲህም ሆኖ እንኳን በቡርዧ ብሔራዊ መንግሥት ውስጥ የብሔራዊ መከፋፈል መወገድ ማለት ውጤቱ የአነስተኛና የደካማ ነገዶች ፤ ብሔራዊ ቡድኖችና ብሔሮች በትላልቆችና በተጠናከሩ ብሔሮች የምጣኔ ሀብት ባርነትና የባሕል መነጠቅ ነው ።

የተጨቆኑ ሕዝቦች ለነጻነትና ለብሔራዊ ንቃት የሚአደርጉት ትግል ፤ ከካፒታሊስት ጭቆና ለመላቀቅ የዓለም አቀፍ የሠራተኛ መደብ ለሰው ልጅ ሕብረሰባዊ ነጻነት ከሚአደርገው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ጋር በቅርብ የተገናኘ ነው ።

ይህ መንገድ ብቻ ነው ሁሉም ብሔሮች እውነተኛ ነጻነት የሚአገኙበትና ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ለማሳደግ የተሟላ ሰፊ ዕድል የሚሰጣቸው ። ከዚያ በኋላ በሁሉም ብሔሮች መካከል የተደጋጋፊነት ሁኔታ ይፈጠራል ።

## የቡርዧ ብሔረተኝነትና ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት

ካፒታሊዝም ሲመጣ ብሔሮች እንደሚከሰቱ ይታወሳል ። በመሠረቱ ፣ ቡርዧው — ብሔራዊ እንቅስቃሴውን የሚመራው — ከመጀመሪያውኑ የብሔራዊ ንቃተ — ሕሊናና የብሔራዊ ስሜትን መገንፈል ለራሱ መደብ ዝንባሌ

ሊጠቀምበት ይታገላል ። ለራሱ ጥሩ የሚሆነው ነገር ለብ
ሔሩም ጥሩ እንደሚሆን ይለፍፋል ። በመጨረሻም ፤ «እን
ንድ ብሔሮች ከሌሎች የበላይ ናቸው ።» የሚለው ሀሳቡ በገ
ዜው ተቀባይነት ይኖረዋል ። የቡርዧ ፈላስፎች የሕዝብን
አእምሮ በብሔረተኝነት ለመመረዝ ይሞክራሉ ፤ ስለዚህም
በወዝአደሮች መካከል የመደብ ንቃት እንዳይኖር በተለያዩ
ብሔረሰቦች ባሉ ሠራተኛ ሕዝቦች መካከል አለመግባባትን
ይዘራሉ ።

እርግጥ ብሔረተኝነት በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ባለው
ጠባይ መገምገም ይኖርበታል ። ከኢምፔሪያሊዝም ጋር
የሚዋጋ የተጨቆነ ብሔር ብሔረተኝነት የዲሞክራሲያ
ዊና ፤ የተራማጅ ነት ትርጉም አለው ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ
የብሔረተኛነት ሀሳቦችና ስሜቶች ኢምፔሪያሊዝምን የመ
ቃወም መልኮች ናቸው ። ግን እነዚህ ተራማጅ ገጽታ
ሊሸጋገሩ የሚችሉት የሠራተኛው መደብና ሌላውም የሠ
ራተኛው ሕዝብ ክፍል ፤ የብሔሩ አብዛኛው ክፍል ፍላጐት
የተስማማ መሆኑ ሲታይ ነው ። ይህ የመደብ ጥቅማቸውን
ለማስጠበቅ ሲሉ የብሔር ነጻነትን ሁኔታዎች ለመከዳት
ከማያወላውሉት አድሃሪዎች ፍላጐት ጋር ሲነጻጸር ተጻራሪ
ነው ።

ሠራተኛው መደብ ግን ፤ ወዝአደራዊ አለም አቀፍነ
ትን «ብሔረተኛነት ማድረግ» ይቃወማል ፤ በአንጻሩ የሁሉም
ብሔሮች ዘሮች ሠራተኛ ሕዝቦች የካፒታል ገዥነትን
በመቃወምና ከማንኛውም የሕብረተሰብና የብሔር ጭቆና
ነጻ ለመውጣት ለሚያደርግ ትግል የመደብ አንድነትን (ሕብ
ረትን) ይደግፋሉ ። «የሁሉም አገር ሠራተኞች ተባበሩ!»



የሚለው የታወቀው መፈክር የዓለም አቀፍ ወንድማማችነ
ታቸው መግለጫ ነው ።

ወዝአደራዊ ዓለም አቀፍነት የሚመጣው በካፒታሊ
ስት ሕብረተሰብ ውስጥ ከሠራተኛው መደብ ከመጀመሪያ
የኑሮ ሁኔታ ነው ። በካፒታል ዓለም አቀፋዊ ኃይል ነው ። ካፒ
ታል (ወረት) ዘር ወይም ብሔር ሳይለይ ሠራተኞችን ይበዘ
ብዛል ። ወደባለጸጐች ካዝና የሚፈሱ ትርፎች በተለያዩ አገ
ሮች ውስጥ ባሉ የሠራተኞች ጉልበት የሚሠሩ ናቸው ።
ዓለም አቀፍ ካፒታሊዝምን ለመደምሰስ የሁሉም ወዝአደ
ሮች ፤ የሁሉም ሠራተኛ ሕዝቦች ዓለም አቀፋዊ ሕብረት እን
ዲኖር ያስፈልጋል ። ማርክሳዊ — ሌኒናዊ ፓርቲዎች የሠ
ራተኛው መደብ አብዮታዊ ግምባር ቀደም መሪዎች ፤ ወዝ
አደራዊዓለም አቀፋዊነት መርሆን ለተግባራቸው እንደ
መሠረት አድርገው ወስደውታል ።

በጥንቱ ዓይነት መልክ ወዝአደራዊ — ዓለም አቀፍ
ነትን መተርጐም — (ከብሔረተኝነት ጋር በማነጻጸር) — መ
ጥፎ ስህተት ይሆናል ።

ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት የብሔሮችን እውነታ
ዎችና ልዩ ልዩ ባሕሪዎችንና እንዲሁም ባሕላቸውንና ብሔ
ራዊ ክብራቸውን ከማይገነዘበው ብሔረተኝነት ጋር ምንም
ግንኙነት የለውም ።

ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በሙሉ ብሔራዊ ዝን
ባሌን መከዳት ማለት አይደለም ፤ ግን ትክክለኛ ግንዛቤና
ሠራተኛው ሕዝብ የመደብ ዝንባሌ ጋር ማዋሃድ ማለት
ነው ።

የቡርዧ ብሔረተኝነት ግን ለብሔራዊ ዝንባሌዎች
የከንፈር ድርጎ ( Lip Service ) እየሰጠ ፤ በተግባር
እነዚህ ዝንባሌዎችን ይዳምጣቸዋል ። ይህ ዓይነት ብሔ
ረተኝነት ወይም ትምክህተኝነት ለብዙ ብሔሮች እየ
ገኛ ሥቃይ የአመጣባቸውንና ድል የሆነውን የኢምፔሪያሊ
ስት ጦርነት ከአንድ ጊዜ በላይ ለማቀጣጠል ረድቷል ።
ለምሳሌ ፥— ናዚዝም ካለው የጀርመን ዘር የበላይነት አመ
ለካከት አንጻር — ለጀርመኖች ለራሳቸው ከፍተኛ ጥፋት
አድርሶ ላለቀው — ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሰውን
ልጅ ማገዶታል ። በሕዝቦች መካከል ጠላትነትና ጥላቻን
በመዝራት ፤ የቡርዧ ብሔረተኝነት ጭቁኖችን ሊከፋፍ
ቸው ይሞክራል ።

ወዝአደራዊ ዓለም አቀፍነት ሠራተኛውን ሕዝ
የሕብረተሰብ ነጻነት በመስጠት (የወደፊቶቹን ብሔሮች
ያስተሳስራል ። የእያንዳንዱን ብሔር የፈጠራ ኃይሎች
ለማንቃት በመታገል ፤ በዓለም አቀፍ የአንድነት — ዕኩልነ
ላይ በመመሥረት የብልጽግናን ሰፊ መልክ ይከፍታል
የዓለም ሠራተኛን መደብ የጋራ ዝንባሌ በማስጠበቅ
በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ — የዛሬውን መሪ ኃይል ማለ
ነው — ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት የሁሉንም ብሔሮ
እውነተኛ ዝንባሌ ያገለግላል ።

## ፩. ታሪካዊ አስፈላጊነትና ሰብዓዊ ክንዋኔ

### ሰዎች እራሳቸው ታሪክን ይሠራሉ

እንደተፈጥሮ ሁሉ ፤ ሕብረተሰብም ነባራዊ ሕጎች
በመከተል ስለሚአድግ ፤ ሰዎች በታሪክ ውስጥ ምን ሚ



እንደሚጫወቱ፡ መጠየቅ አስፈላጊ ነው ። ሰው ለታሪካዊ
አስፈላጊነት ደንባራ መሣሪያ ነውን ?

* የቡርዧ ርዕዮት — ዓለማውያን የማርክሲዝም — ሌኒ
ኒዝምን «ሀሰተኛነት» ለማሳየት ሲሞክሩ ፤ የዕድል እምላኪ
ነት ተአምርን ነው የሚናገረው በማለት ይለፍፋሉ ። ይህን
የሚሉት የታሪካዊ ከዊን — ነገሮች ድርጊት ቀድሞ በታ
ለመ (በተወሰነ) ሁኔታ ይፈጸማል የሚል አመለካከት ነው
ያለው የሚል ግንዛቤ ወስደው ነው ። ሌላው ምክንያት ፤
ለምንድነው ታዲያ የታሪክ ሕጎች በራሳቸው በማይቀር
ሁኔታ ወደኮሚኒዝም የሚመሩ ከሆነ ፤ ለሶሻሊዝምና ኮሚ
ኒዝም ትግል የሚአስፈልገው ? የሚለው ነው ። የበጋ
ወይም የጥቢ ወራት እንዲመጣ ጦርነት (ትግል ) መች
ተደርጎ ያውቃልና ይሉናል ።

ይሁንና ፤ በታሪክና በተፈጥሮ ሕጎች መካከል ያለው
መሠረታዊ ልዩነት ፤ በመጀመሪያው ሕጎች በተግባር የሚ
ውሉት በሰዎች ክንዋኔ መሆኑ ነው ። ታሪካዊ አስፈላጊ
ነት እራሱን እንደማይቀር አድርጎና ከሰብዓዊ ክንዋኔ
ተጽኖ በላይ ግልጽ አድርጎ አይቀርብም ። እንዲያውም፤
እራሱን ግልጽ የሚአደርገው የምርት እንቅስቃሴ ሲገፋና
በሕብረተ — ሰቡ ውስጥ የሕዝቡን ሰፊ ክፍል በአንድ በተ
ወሰነ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ የሚገፉፉ አዲስ ቁሳዊ ፍላ
ጎቶች ሲነሱ ነው ።

የመልከኛው ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ወደ ኋላ
በጐተቱበት ጊዜ ፤ እነዚህን ግንኙነቶች ጠርጎ ለመጣል
ተግባራዊ አስፈላጊነት ታዩ ። ይህ አስፈላጊነት የመልከ
ኛው ግንኙነቶች ከባድ ሸክም በሆነባቸው ፤ በቡርዧዎችና

ገበሬው አብዮታዊ ክንዋኔ ውስጥ እንዲለጽ አስፈለገ ። የእነኝህ መደቦች አብዮታዊ ትግል የመልከኛውን ሥርዓት ጠራርጐ ጣለው ።

የአዲስ የምርት ኃይሎች በቅኝ ግዛቶች ውስጥ ማደግና የብሔራዊ ቡርዧ ፤ የምሁራንና የሠራተኛው መደብ በዚያው ውስጥ መከሰት የቅኝ ግዛታዊ ግንኙነት መጥፋት እንዳለበት ጠየቀ ።

ግን እንግሊዞች ፤ ፈረንሳዮች ፤ ደቾችና ሌሎችም ቅኝ ገዥዎች ያለጦርነት የቅኝ ገዥነታቸውን አልለቀቁም ። ስለዚህ የሕንድ ፤ የበርማ ፤ ኢንዶኔዥያ ፤ ማላያ ወዘተ . . . . . ሕዝቦች ለነጻ ብሔራዊ ዕድገት መብታቸው በመራራና በተራዘመ ትግል በመታገል መከላከል ነበረባቸው ።

የቅኝ ግዛት ሕዝቦች የብሔራዊ — አርነት ትግል ታሪክ ፤ ሕይወታቸውን ለሀገራቸው መብትና ነጻነት ያሳለፉ ጀግኖች ግለኛ ያልሆኑ አርበኞችን አርአያ አሳውቋል ።

የታሪክ ሕጐች ከመ — ቅጽበት ፈንድተው አይከናወኑም ። ሕዝቦች እራሳቸው የራሳቸውን ታሪክ ይሰሩታል ፤ ግን እሠራራቸው አውቀውት አይደለም ፡— በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጽዕኖ መሠረት ሥራቸውን ሲአከናውኑ ነው ፤ የዚህ ዓይነተኛው የመሪ መደቦችና የሕብረተሰብ ቡድኖች ዝንባሌን የሚአንጸባርቀው የምጣኔ — ሀብት ፍላጐት ነው ።

ይህ ፍላጐት የሚገኘው ዝንባሌአቸውን ከፍ አድርገው ለማሳየት ተግባራቸውን በሚአከናውኑና በዚያው ይነስም ይብዛ ለሕብረተሰቡ ዕድገት አጣዳፊ ፍላጐት የሆነውን በሚአዩት ሰዎች ነው ።



ሌኒን ፤ ለሶሻሊዝም እና ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚደረገውን ሚና ፤ የአብዮታዊ ንድፈ — ሀሳቦችንና በዚህ ትግል ውስጥ የማርክሲስት ፓርቲ የሚፈጽመውን ንቁ አብዮታዊ ትግል ዋናነት የሚአኮስሱ አድርባዮችን በጽኑ ተቃውሟቸዋል ። አዲሱን ሥርዓት የማቋቋምን ፍላጐት የተገነዘቡ አብዮታዊ ኃይሎች ግልጽ እየሆኑ በመጡ ቁጥር፤ የዚያኑ ያህል ለዚያ ፍላጐታቸው ለመዋጋት የበለጠ ንቁ ይሆናሉ እናም የሕብረተሰቡ ዕድገት እርምጃም የፈጠነ ይሆናል ።

## ታሪካዊ አስፈላጊነትና ነጻነት

የቡርዧ ርዕዮተ — ዓለማውያን ማርክሲዝምን ሲነቅፉ ብዙውን ጊዜ የሚለፍፉት ፤ ታሪካዊ አስፈላጊነትን መቀበል ማለት የነጻነትን ምርጫ መቃወም ወይም አለመቀበል ነው ይላሉ ። «ነጻነት» የሚለው ቃልም ለእያንዳንዱ ሰው ከፍተኛ ስበት አለው ። ዓላማው ነጻነት ለማግኘት መሆኑን የማይናገር ምንም ዓይነት ፖለቲካ ወይም ርዕዮተ — ዓለም የለም ። በቬየትናም የዩናይትድ ስቴትስ ወራሪዎች እንኳን የሚዋጉት ለቬየትናም ሕዝቦች ነጻነት እንደነበር ለፍፈዋል ። እርግጥ የቬትናም አርበኞችና የዩናይትድ ስቴትስ ወራሪዎች «ነጻነት» የሚለው ቃል ፍጹም በተለያዩ መንገድ ገብቷቸዋል ። ታዲያ ነጻነት ምንድነው ፤ እናስ መቼ ነው አንድ ሰው ፤ አንድ ብሔር በእርግጥ ነጻነት የሚሰማው ?

የሚከተሉትን ምሣሌዎች እንገንዘብ ፡— ሁለት ሰዎች በጫካ ውስጥ ሲሄዱ መንገድ ጠፍቷቸዋል እንበል ። ከሁለቱ አንደኛው ፤ በገጠር አካባቢ የአደገው ፤ ለራሱ ወዳያ

ሙት የሚያገኝበትን ዘዴ ይሞክራል ። አንድ ትልቅ ዛፍ ላይ
ይወጣና በጸሐይ አቅጣጫ ችፍግ ባሉ ዛፎች አማካይነት (ምል
ክት) ወዘተ . . . አቅጣጫውን ይማትራል ። ይወርድና ጓደ
ኛውን ጨለማ ከመምጣቱ በፊት መጠለያ ሲያገኙ ወደሚች
ሉበት ቦታ ለመሄድ በቶሎ እንዲከተለው ይነግረዋል ።

* ግን ሌላው ፤ በከተማ ውስጥ ያደገው ፤ ከማንም ሰው
ትዕዛዝ እንዲቀበል አይፈልግም ። የቤቱን መንገድ የሚያ
ውቀው አድርጐ በማሰብ ጓዱን መከተል ይቃወማል ። ስለ
ዚህ የመጀመሪያ መንገዱን ያለምንም ዓላማ ይወስዳል ።
በማንኛውም ጊዜ አቅጣጫውን መለወጥና ሌላ መንገ
መያዝ እንደሚችል በማመን ራሱን ያጽናናል ። ለሰዓታት
ከዞረ በኋላ ብቻና መንገዱን ለማወቅ እንዳልቻለ ሲረ
የምርጫ «ነጻነቱ» (የእርሱ) ተምኔታዊና ባዶ እንደ ሆ
ይገነዘባል ። እርግጥ ፤ ነጻ አይደለም ፡— በአካባቢው ባሉ
ነገሮች ቁጥጥር ሥር ነው ፤ እናም ያስፈራሩትና ወደተሰ
መቁረጥ ይገፋፉታል ።

* የመጀመሪያው ሰው ፤ አቅጣጫውን ከአዩ በኋላ ወ
መረጠው አቅጣጫ ለመሄድ የመንቀሳቀስ ነጻነቱን ወሰ
አስፈላጊነት አውቆ የተቀበለው እና መቀመጥና እረፍ
መውሰድን በመቃወም ከመጨለሙ በፊት ከደኑ ውስ
ለመውጣት የተጣደፈው ብዙ አደጋዎችን በማስወገ
ከደኑ በሰላም ወጣ ። ሌላኛው ሰው ፤ አስፈላጊ ከሚሆነ
ሁኔታ ጋር በማዛመድ ነጻነቱን ለመወሰን የተቃወመው
በጨለማ የደኑ ምርኮኛ ሆነ ።

ለሰዎች የታሪካዊ ክንዋኔ ን ነጻነት የሚሰጣቸው የ
ባራዊ አስፈላጊነት ዕውቀት ነው ። የዚህ ምሣሌ የሚሆነ



በኮሚኒስት ፓርቲው የተመራው የሶቪየት ሕዝቦች ሥራ
ነው ። ፓርቲው የሕብረተሰቡን ዕድገት በሚገዙት ሕጐች
ዕውቀት የታጠቀ ነበር ። ከታሪካዊው አስፈላጊነት እን
ጻር በማዛመድ የሰዎችን ክንዋኔ ያደራጃል ፤ ይህም አስፈላ
ጊነት ወደኮሚኒዝም ይመራቸዋል ። ውጤቶቹ በደምብ
የታወቁ ናቸው ፡— በሶቪየት ሕብረት የኮሚኒስት ፓርቲ
ፕሮግራምና ፤ በፓርቲው ኮንግሬስ ውሣኔዎች በመመራት ፤
በታሪክ ሕጐች መሠረት በተተለመው መንገድ ለመራመ
ድና የወደፊቱ ኑሮአቸው ምን እንደሚሆን እርግጠኛ ናቸው ።

* እርግጥ ፤ የሶሻሊስት ሥርዓት በራሱ በምጣኔ ሀብ
ታዊ አያያዝ ሁኔታዎች ውስጥ ፤ በፖለቲካ ፤ በባሕል ወይም
በርዕዮተ ዓለም ውስጥ ስህተቶችን አይከለክልም ። ስለዚህ
ማርክሲስት — ሌኒኒስቶች የሚአምኑት ነባራዊ ሕጐችን
በጥንቃቄ ማጥናት አስፈላጊ እንደሆነና አንድን ክንዋኔ
በሕብረተሰቡ ፍላጐት መሠረት ለማካሄድ ዓይነተኛ ጥን
ቃቄ እንደሚአስፈልገው ነው ።

ስለሆነ ፤ የአንድ ነገር አስፈላጊነት ነጻነትን አይከለከ
ልም ፤ እንደዚሁም ፤ ነጻነት አስፈላጊነትን አያስወግድም ።
ነጻነት አስፈላጊነትን በመቀበል የተሞላና በተግባራዊ
ጥቅም ላይ እንዲውል የሚአደርግ ነው ።

## ብዙሃንና ግለሰቡ

የታሪክን መጽሐፍ ገጾች በማገላበጥ ፤ አንድ ሰው
በሕብረተሰቡ ኑሮ ውስጥ ጠለቅና ሰፋ ያለ ፈለግ ያላቸው
የብዙ ሰዎችን ስም ያገኛል ። እነሱም ታላላቅ ሳይንቲስ

ቶች ፤ ጀኔራሎች ፤ የአብዮታዊ እንቅስቃሴ አሳቢዎች
መሪዎች ናቸው ።

• ንቁ ግለሰቦች በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ (ዓይነተኛ) ሚ
እንደሚጫወቱ አጠራጣሪ አይደለም ። ለምሣሌ ፤ በሕን
ታሪክ ውስጥ ጋንዲ የተጫወተው ሚና አይካድም ። ግ
የእርሱ ጥንካሬ የሚገኘው የት ላይ ነው ? ክንዋኔው ፤ ንግ
ሩና መጽሐፎች ላይ ቀረብ ያለ ትኩረት ካለ የሚአብራራ
ቅኝ ግዛትን በመጸረር የሕንድ ሰፊ ሕዝብ የእንቅስቃ
ፍላጐት እንደሆን «ግልጽ» ያደርጋል ። ለዚህ ነው ሕዝ
መሪው እንዲሆን የመረጠውና የረዳው ።

የእንግሊዝ ጨቋኞችን የሚቃወሙ በሕንድ ውስ
በፊት ብዙ ተራማጅ ምሁራን ነበሩ ። እነሱ ተገርፈዋል
ታስረዋል ። ግን እነኛ ጀግኖች ግለሰቦች የሆኑ ፤ ከሰፊ
ሕዝብ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያልነበራቸው ነበሩ ። በዚ
ምክንያት ክንዋኔአቸው የፈለጉትን ፍሬ አላስገኘም
የንቁ ግለሰቦች ጥረት በምንም ዓይነት መልክ ከሰፊ
ሕዝብ ጋር ካልተያያዘ ፤ የሕብረተሰቡን ዕድገት አጣ
ፍላጐት ካልገለጸ መውደቁ ፤ ብኩን መሆኑ አይቀርም

እስቲ እናጢን ፤ — ይህ ወይም ያ ትልቅ ሰው በመ
ረክ ላይ ባይታይ (በይመጣ) ኖሮ ታሪክ ምን ይደርስበ
(ይሆን) ነበር ? ለምሣሌ — ከማል በአንድ አጋጣሚ በሕ
ንነቱ ቢሞት ኖሮ በቱርክ ውስጥ የቡርዧ አብዮት አይ
ርም ማለት ነው ? በግልጽ ፤ አብዮቱ በምንም ዓይነት መ
ገድ ይሁን ይኖር ነበር ። ምክንያቱም ታሪክ የሚወስነ
የሕብረተሰብን ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጾች ዕድገት በ
ገዙት ነባራዊ ሕጐች ነውና ። በቱርክ የቡርዧዊው አብዮ



ታሪካዊ አስፈላጊነት ነበረው ። ከማልም ባይኖር ይህንኑ ለመከወን የሚችሉ ሌሎች ሰዎች ይኖሩ ነበር ። ምናልባት ፤ ብዙ ከዊን — ነገሮች ሌላ መንገድ ተከትለው በሌላ ጊዜ ሊፈጸሙ ይችሉ ይሆናል ፤ ግን የዕድገቱ ዋናው ዝንባሌ አንድ ዓይነት ሆኖ ነበር የሚቀረው ።

ታሪክን በመገንባት ደረጃ የግለ — ሰቦችን አስፈላጊነት ማርክሲዝም አይክድም ። ግን የጊዜውን የሕብረተሰብ ፍላጐት ከሌሎች ይበልጥ ለማየት ፤ ቁርጥና ግልጽ ባለ መንገድ ለመግለጽ ፤ ከዚያም ተራማጅ ኃይሎችን ለማደራጀትና ፍላጐታቸውን ለማግኘት የሚአደርጉትን ትግል ለመምራት አንድን ሰው ትልቅ የሚአሰኘውን ችሎታውን የሚሠራው ምን እንደሆን ያጤናል ።

በተለያዩ ዘመናት የንቁ ግለሰቦችን ጥናት እንደሚአሳየው የክንዋኔአቸው ታሪካዊ ዋናንት ሁልጊዜም ቢሆን የተወሰነው እነሱ በሚወክሉት የሕብረተሰቡ እንቅስቃሴ ስፋት ነው ። ከማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ይበልጥ የወዛደሩ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ተወዳዳሪ በሌለው ሁኔታ ታላቅ ከሆን ጀምሮ ፤ በተለይም በመሪዎች ላይ ከፍተኛ ደረጃን (የሥራ) ይጠይቃል ።

የማርክሲዝም — ሌኒኒዝም መሥራቾች — ማርክስ ፤ ኤንግልስ ፤ እና ሌኒን — ከሌሎች ለየት ያለ ንቁ ችሎታ ነበራቸው ፤ — ሊረሳ የማይችል ሳይንሳዊ አመለካከት ፤ የአብዮታዊ ንቅናቄዎችን ገጠመኝ በድርም የማስቀመጥ ችሎታና ንድፈ — ሀሳብን ከተግባር የማዋሃድ ብቃት ነበራቸው ፤ የድርጅት ችሎታ ፤ ሊጐብጥ የማይችል የማሸነፍ ፍላጐት ፤ ድፍረት እና ተወዳጅነትን አትርፈዋል ።

ዋናውን አቅጣጫና የሕብረተሰብን ዕድገት ሕጐች ሲወስኑ ፤ የማርክሲዝም — ሌኒንዝም መሥራቾች ለማንኛውም ክስተት የፈጠራ ዝንባሌና ግምገማን አቅርበዋል ፤ ጠይቀዋል ። ትምህርታቸው የተመሠረተው ፤ በሰዎች የምክንያት እምነት ላይና የሰው ልጅ የወደፊት ብሩሃዊ ኑሮ በሚንተራስበት በማንኛዎቹም ታምራዊ ፤ ሊታወቁ በማይችሉ ኃይሎችና ሕጐች ሳይሆን ፤ ግን ከማንኛውም ዓይነት አካላዊና መንፈሳዊ ጭቆና የሠራተኛ ሕዝቦች ጥንታዊ ነጻነት ላይ በሚአተኩረው ጠለቅ ያለ የእውነቶች ጥናት ነው ።

የማርክሲዝም — ሌኒኒዝም መሥራቾች የሰውን ልጅ ከብዝበዛና ከጭቆና ነጻ የማውጣት ትግል ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሁሉንም ሰዎች ምስጋናና አክብሮት ተቀብለዋል ።

የንቁ ግለሰቦች በታሪክ ውስጥ የተጫወቱት ሚና ምንም ያህል ትልቅ ቢሆንም ፤ ያን ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል የሚያደርገው ምንም ነገር የለም ። የማንኛውም ታላቅ ሰው ክንዋኔ ታሪካዊ ቢጋር (Frame - Work) የሚወሰነው በዘመኑ ባለው የሕብረተሰብ ፍላጐት ነው ። በሳይንስ ፤ በባሕልና በኪነት እንኳን ፤ በተለይ ችሎታ (የአእምሮ) ዋና በሚሆንበት ፤ በመጨረሻ ትንታኔ ላይ ባሕላዊ እድገት በሕብረተሰብ ፍላጐት ነው የሚወሰነው ። ታላላቅ ሳይንቲስቶች አንዳንድ ነገሮችን የአገኙት (የፈለሰፉት) ከነሱ በፊት በሌሎች ሰዎች ተግባሮች መንገዱ ስለተጠረገላቸው ነው ። እንደዚሁም ታላላቅ ሠዓሊዎችና ቀራጺዎች በሥራቸው



የሚአንጸባርቁት በዘመናቸው የነበረውን ሕብረተሰብ አመለካከት ነው ።

ንቁ ግለሰቦችን እንደሚአስገኘው የሕብረተሰብ ፍላጐት ሁሉ ፤ በመጀመሪያ ደረጃ በምርት አድማስ ውስጥ ባለው የዕድገት ውጤት ነው የሚታዩት ። ሁኔታው ይህ ከሆነ ጀምሮ ዋጋንና (እሴትን) ሀብትን በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚአስገኙት ሠራተኞች በታሪክ ውስጥ ቁልፍ የሆነ ሚና ይጫወታሉ ብሎ መደምደም ሎጂካዊ ነው ።

ወደ ፖለቲካ በመዞር ፤ አንድ ሰው እርግጠኛ በመሆን ሰፊው ሕዝብ ወሳኙን ሚና እንዳይጫወት የሚከለክለው አንድም እንኳን መታጠፊያ ነጥብ የለም ለማለት ይቻላል ። በሕዝባዊ አብዮቶችና የነጻነት ጦርነቶች ውስጥ የመጨረሻው አባባል የሚአርፈው በሕዝቡ ላይ ነው ። በሰላም ጊዜም ቢሆን ፤ የገዥ መደቦች ሰፊውን ሕዝብ ከፖለቲካ ለማለያየት ሲአስቡ ፤ በምንም ዓይነት መንገድ አንዳንድ ተጽዕኖዎችን ያሳድራሉ ። ንጉሦች ፤ ፕሬዚዳንቶችና ሚኒስትሮች ፤ የበዝባዥ መደቦችን ዝንባሌዎች ለመጠበቅ ሲሉ ፤ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን እንዲጠኑ አድርገዋል ። በትግል ወቅት ሠራተኛው ሕዝብ የገዥ መደቦችን ፍላጐት በመገደብና ብዙ ጊዜም ድርድሮች እንዲአካሂዱ በማስገደድ ድል አድርጓል ።

በመጀመሪያ ስንመለከት ፤ በምሁራን አካባቢ የሰው ልጅ ያገኛቸው ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ በንቁ ግለሰቦች፤ ሳይንቲስቶች ፤ ሃይማኖታዊ መሪዎች ፤ ጸሐፊዎች ፤ ገጣሚዎች ፤ ሠዓሊዎች (ቀራጺዎች) ሙዚቀኞች ላይ ጥገኛ በመሆን ይመስላል ። የታላላቅ ስሞች ሙሉ ሊስት አለ ። ግን ፤

ከየት ነው ታላላቅ ሰዎች ሃሳቦቻቸውንና የሰዎችን የመፈ
ጠርና የመሥራት ችሎታ የሚአንሳሱትን መገፋፊያዎች
የሚአገኙት ? እንደሚታወቀው ሁሉ ፤ ሳይንስ የሚዳብ
ረው በተግባራዊ ከንዋኔና በምርት የዕድገት ርምጃ መሠረት
ነው ። ሳይንሳዊ ሀሳቦች የቁሳዊ ጥቅሞች የብዙ ትውልድ
አምራቾች ውስጥ በደለበ የምርት ገጠመኝ መጋዘን በጥል
ቀት ሥር ሰደዋል ፡— በሠራተኛ ሕዝቦች ።

በኪነት ውስጥ አንድ ሰው ሊአስታውስ የሚገባው
ተረትማ ወጎች ፤ ሕዝባዊ መዝሙሮች እና የግጥም ስንኞ
ችን ነው ። እያንዳንዱ ብሔር በሕዝቡ መካከል ታላላቅ ገጣ
ሚዎች ፤ ሠዓሊዎች ሙዚቀኞች አለው ። እውነተኛ ሠአ
ሊዎች ሀሳቦቻቸውንና ነፀብራቆቻቸውን (Images) ሁል
ጊዜም የሚወስዱት ከሕዝቡ ኑሮና ልማዳዊ እምነቶች ነው።

ሕዝቦች ወሳኝ ሚና የማይጫወቱበት የሕብረተሰብ
ከንዋኔ አድማስ የለም ፤ እናም ታሪክ ሲአድግ ይህ ሚና
ጠንከር ባለ መንገድ ይጨምራል ።

## ምዕራፍ ፪

## ካፒታሊዝምና የእርሱ መጨማተር

በዋና ሥራው ፤ ካፒታል ፤ ማርክስ ሲጽፍ ፡— «በእ
ሁኑ ሥራ ላይ የኔ ጥናት ርዕስ የካፒታሊስት ሥልተ — ምር
ትና ከዚያ ተጣምተው ስለሚሄዱት የምርት ግንኙነቶችና
ልውውጥ ነው ።» ብሏል ። በካፒታሊዝም ውስጥ ምርትንና
የሀብት አከፋፈልን የሚገዙትን ሕጎች ግልጽ በማድረግ
የማይቀረው የካፒታሊዝም መጨማተርና የሶሻሊዝም
ድል ማድረግ የሚመጣው ከኑሮ ምጣኔ — ሀብታዊ ሁኔ
ታዎች እንደሆነ ማርክስ አሳይቷል ።



## ፩. የካፒታሊስት ምርት

የካፒታሊዝም ባሕሪያዊ ገጹ የሸቀጥ ምርትን ሙሉ
በሙሉ መግዛቱ ነው ። በሸቀጥና በሸቀጥ ልውውጥ ሂደት
ውስጥ የካፒታሊስት ሕብረተሰብ ቅራኔዎች ተጠራቅመ
ዋል ፤ ደልበዋል ።

የሸቀጥ ልውውጥ ከካፒታሊዝም ቀደም ብሎ የኖረ
ቢሆንም ይነስም ይብዛ ቅድመ— ካፒታሊስት አቀራረጾች
ተፈጥሮአዊ ምጣኔ ሀብት ነበር ያለው ። እያንዳንዱ መል
ከኛ ምጣኔ — ሀብታዊ ክፍል የራሱ የሆነ ኑሮ (ሕይ
ወት) ነበረው ። ገባር ገበሬዎች (Serfs) እና የእጅ ባለሙያ
ዎች በመልከኛውና ባገልጋዮቹ ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ
ትን ብዙዎችን ነገሮች ማምረት ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ ፤ አን
ዳንዴ ከውጭው ዓለም ጋር በልውውጥ ውስጥ ገብቶ
ነበር ።

ገበሬዎች በተፈጥሮ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ይቀጠሩ
ነበር ። እህል ያበቅላሉ ፤ ከብት ያረባሉ ፤ ይሸምናሉ ፤ መጫ
ሚያ ይሠራሉ እና ሁሉንም ዓይነት የሥራ መሣሪያዎች ።
እርግጥ ፤ በተፈጥሮ ምጣኔ — ሀብት እንኳ አንዳንድ ምር
ቶች፤ እንደጨው ፤ ብረት ፤ ቅመሞችና የድሎት ዕቃዎች በገ
በያ ውስጥ እንደሸቀጥ ሆነው ይለዋወጡ ነበር ። ግን ይህ
ዓይነት ልውውጥ ሁለተኛ ደረጃ ነው ፤ ምክንያቱም የምር
ቱን አነስተኛ ድርሻ የያዘ በመሆኑ ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ፋብሪካዎችና የእርሻ ውጤቶች
በመጀመሪያ ደረጃ ለሽያጭ ናቸው ። የሸቀጥ — ገንዘብ ግን
ኙነቶች ማንኛውንም ዓይነት ኑሮ ስለሚገዙ ፤ የሸቀጦች
የማያቋርጡ ልውውጦች አሉ ።

## ሸቀጥና የሸቀጥ ምርት

የሸቀጥ ምርት ፣ በአምራቶች በራሳቸው ለፍጆት
(ለብሎት) ከሚውል ይልቅ ምርቶች ለሸያጭ የሚሠሩ
በት የሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ ድርጅት ነው ።

የጉልበት ምርቶች ሸቀጦች ለመሆን ፣ በመጀመሪያ
ደረጃ አንድ ሰው ለራሱ ብሎት የሚአስፈልገውን ማንኛ
ውንም ነገር የሚያመርትበትና ግን እራሱን በአንድ ዓይነት
ሙያ የሚአሰለጥንበት የሥራ ክፍፍል እንዲኖር አስፈላጊ
ነው ። ሁለተኛ ፣ የምርት መገልገያዎች በግለሰቦች ወይም
በቡድን ግለሰቦች መያዝ አለባቸው ።

እነኝህ ሁለት ሁኔታዎች ሲኖሩ ፣ የሸቀጦች መሸጥና
መገዛት — ምጣኔ ሀብታዊ አስፈላጊነት ይሆናል ።

ሶስት ዓይነት የሸቀጥ ምርቶች አሉ ። ቀላል የሸቀጥ ምርት
በትናንሺ ነጻ በሆኑ አምራቾች የሚመረት — በባለ እጆችና
በገበሬዎች ፣ የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት — የተቀጠረ
ጉልበት በሚበዘብዙ ካፒታሊስቶች የሚካሄድ ፣ እና የሶሻ
ሊስት ሸቀጥ ምርት — በሶሻሊዝም ውስጥ የሚኖረው
ናቸው ።

ቀላል የሸቀጥ ምርት ከማንኛውም ልዩ ከሆነ የሕብረ
ተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ አቀራረጽ የተዛመደ አይደለም ፣
በተለያዩ ሥልተ — ምርት ውስጥ ይኖር ነበር ። ብትንትን
በነበረው ጥንታዊ ጐሣዊ ሥርዓት ውስጥ ወጥቶ ፣ የባሪያ
አሳዳሪንና መልከኛ ሥርዓትን አገልግሎ ፣ እናም በካፒታ
ሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ መኖር ቀጠለ ፤ ያም ብቻ አይደ
ለም ፤ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ ዘመ
ላይም እንኳን ይኖራል ።



የካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት ብቅ ያለው በመልከኛው
ሥርዓት ውስጥ ነው ። በእጅ ሥራዎችና በእርሻ ፣ በከተማና
በገጠር እየጨመረ ከሄደው መከፋፈል ጋር ፣ የመልከኛው
ምጣኔ — ሀብት በገበያ ግንኙነቶች ውስጥ ይበልጥ እየገባና
በገንዘብ ቁጥጥር ሥር እየሆነ ሄደ ። ስለዚህ የሸቀጥ ግንኙ
ነቶች ዕድገት ለመልከኛው መጨማተር መንገድ ጠረገ ።
የካፒታሊስት ሸቀጥ ምርት መልከኛነት በሚፈራረስ ጊዜ
ከቀላል ሸቀጥ ምርት ወጣና አደገ ።

አሁን ፣ የቀላልና የካፒታሊስት ሸቀጥ ምርትን ዋና
ገጾች እናወዳድር ። በሁሉም ዘንድ ነዋሪ የሆነው ነገር
በሥራ ክፍፍል እና የምርት መገልገያዎችና የጉልበት ውጤ
ቶች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው ። ግን
የእጅ ባለሙያዎችና የገበሬዎች ቀላል የሸቀጥ ምርት ከካ
ፒታሊስት ዓይነት ምርት የሚለየው የመጀመሪያው የጉል
በት ውጤቶች የአምራቾች ንብረት መሆኑ ነው ። በካፒታ
ሊዝም ውስጥ የጉልበት ውጤት ምንም እንኳን እነዚያን
ምርቶች ለማምረት አንድ ብጣቂ ሥራ ባይሠራም የምርት
መገልገያዎች ባለቤት ለሆነው ንብረት ነው ። ይህ ነው በካ
ፒታሊስት የሸቀጥ ምርትና በቀላል የሸቀጥ ምርት መካከል
ያለው መሠረታዊ ልዩነት ።

## የጠቀሜታ ዕሴትና የሸቀጦች ዕሴት

ሸቀጦች ለልውውጥ የሚሠሩ የጉልበት ውጤቶች
ናቸው ። እንዳንድ ፍላጐቶችን ማሟላት እንዳለባቸው ፣
በዚህም ሆነ በዚያ ጠቃሚ እንደሚሆኑ ፣ ግልጽ ነው ፤ ያለ
ዚያ ማንም የሚገዛቸው የለም ። የአንድ ምርት ለሰዎች
ጠቃሚነት፡ በዚህም ሆነ በዚያ የጠቀሜታ ዕሴት ተብሎ
ይጠራል ።

የሥጋ ወይም የተከ
የዳቦ ፣ የስኳር ፣ የቅቤ ፣ የወተት ፣ እነዚህ ምርቶች የሰውን የም
ተፈ ሥጋ ጠቀሜታ ዕሴት ፣ እንዲያሟሉ በውስጣቸው እንደሚይዙ ያሳያል ።
ግብ ፍላጐት እርካታ በውስጣቸው እንደሚይዙ ያሳያል ። የሰዎችን የእግር መላበሻ ተፈላ
የሚግ የጠቀሜታ ዕሴት የሰዎችን የእግር መላበሻ ተፈላ
ጊነትን ማሙያ ይዟል ። ከጉልበት ውጤት በተጨማሪ የሰ
ዎችን ግላዊ ፍላጐት ለማርካት የሚውለው ፣ ቁሳዊ ሀብት
ለማምረት የሚአገለግለው የምርት መገልገያም የጠቀሜታ
ዕሴት አለው ።

ሰዎች ሸቀጦችን የሚወስዷቸው በሚገዟቸው ጊዜ ለግል ሲጠቀሙባቸው ነው ። ልዩ ልዩ ሸቀጦች በአንድ ዓይነት የገንዘብ መጠን ሊገዙ ይችላሉ ። ሁሉም ሸቀጦች የጋራ የሆነ ገጽ አላቸው ፡— ሁሉም የሰዎች የጉልበት ውጤቶች ናቸው ። ይህ ነው ተመጣጣኝ (በአንድ ዓይነት ሁኔታ ሊለኩ ወይም ሊታዩ የሚችሉ) የሚአደርጋቸው ። ሸቀጦችን አንዱን ካንደኛው ለመገመት በምናወዳድር ጊዜ ፣ በትክክል የምናወዳድረው በውስጣቸው የጠፋውን የጉልበት መጠን ነው ። በሸቀጥ ውስጥ የገባው ጉልበት የሸቀጡን ዕሴት ይወስናል ። እራሱ ጉልበት (ሥራ) ዕሴት አይደለም ። ጉልበት ዕሴት ሊይዝ የሚችለው ሸቀጦች ለልውውጥ ሲመረቱ ብቻ ነው ።

የዕሴትን ባሕርይ ለመረዳት እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም ፤ ምክንያቱም ማርክስ እንደጠቀሰው ፣ ዕሴት በእራሱ የአካልነት ቅንጣት የለውምና (Value in it Self has not a grain of Substance) ። አሁን የዕሴትን ጽንሰ ሀሳብ ደረጃ በደረጃ ለመተንተን እንሞክር ።

ዕሴት ፣ በሸቀጥ ውስጥ የፈሰሰ ጉልበት ነው ማለት ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ፣ ዓይነተኛነቱ የሚንተራሰው ይህን ሸቀጥ



ለመሥራት በጥቅም ላይ በዋለው የጉልበት መጠን ነው ። ይህ መጠን ሊለካ የሚችለው በሥራ ሰዓቱ ርዝመት ነው ። ለማጠቃለል ፣ ይህ ሰዓት (ጊዜ) የጉልበትና የዕሴት መለኪያ እንደሆነ እናጢን ። የሥራ ሰዓት ራሱ በሰዓት ፣ በቀን ወዘተ . . ይለካል ።

አንድ ሸቀጥ ለማምረት የበለጠ ጉልበት ባስፈለገ መጠን የዚያኑ ያህል ዕሴቱ ይንራል ። ነጥቡን ለማብራራት ቀላል ምሣሌ ይኸውና ። አንድ ማዕድን አውጭ ፲ ብር የሚአወጣ ያልተጣራ ብረት አወጣ እንበል ። ከዚያው ላይ ብረት አንጣሪው ፴ ብር የሚአወጣ አራት ማዕዘን ያለው ብረት አነጠረለት ። አራት ማዕዘን ያለው ብረት ፺ ብር የሚአወጣ የአረብ ብረት ለመሥራት በጥቅም ዋለ ። ይህ የአረብ — ብረት ፫፻ ብር የሚአወጣ የወረቀት መርፌዎች ወይም ለታጣፊ ሴንጢዎች ምላጭ ፱፻ ብር ለሚአወጡ ወይም ፻ ሺ ብር ለሚአወጡ የሰዓት ሞላዎች ለመሥራት አገለገለ ። በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ የዋለው አንድ ዓይነት መጠን ያለው የአረብ ብረት ነው ። ታዲያ ለምንድነው ምላጮች ከወረቀት መርፌዎች መብለጥ ያለባቸው ፣ እና ሞላዎች ከምላጮች ይበልጥ ውድ የሆኑት ? ምክንያቱ ፣ አንዳንድ ዕቃዎችን ለመሥራት የሚጠይቀው የጉልበት ኃይል መጠን ሌሎች ለመሥራት ከሚጠይቀው ይበልጥ ስለሚአይል ነው ።

ሸቀጦችን የሚአመርቱ ሰዎች የሚሰሩት በተለያዩ ሁኔታ ነው ፣ የተለያዩ የሥራ መሣሪያዎች ይጠቀማሉ ፤ የተለያዩ ልምድም አላቸው ፤ አንድ ዓይነት ሸቀጦችን ለማምረት የተለያዩ የሰዓት መጠን ያጠፋሉ ። ይሁንና ፤ በገበያ አንድ ዓይነት ሸቀጦች አንድ ዓይነት ዕሴት ነው

ያላቸው ። ለመደምደም ፤ የአንድ ሸቀጥ ዕሴት በምርቱ
ግላዊ ገጽ ወይም በአምራቹ ላይ ጥገኛ አይሆንም፤ግን የሚወ
ሰነው ሰፍና በታየው የአሠራር ሁኔታ ነው ፡— በሕብረተ
ሰቡ አስፈላጊ (ተቀባይነት ባገኘ) የሥራ ሰዓት ነው ።

አሁን ፤ የዕሴትን ጽንሰ — ሀሳብ መግለጽ እንችላለን፡
ዕሴት — አንድን ሸቀጥ ለማምረት የጠፋው የሕብረተሰቡ
ተፈላጊ ጉልበት ነው ።

የሕብረተሰቡ አስፈላጊ ሰዓት አንድን ሸቀጥ ለማም
ረት የሚጠይቀው የማይለወጥ ሆኖ አይቀርም ። የምርት
ኃይሎች ፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፤ ወዘተ . . . . ባደጉ ቁጥር
እያጠረ ይሄዳል ።

ለምሣሌ ፤ በ1784 ዓ. ም. በእንግሊዝ ውስጥ 0.37
ኪሎ ግራም የሱፍ ክር ዕሴቱ ፩፻፴ ፔንስ* ነበር ። በ፲፰፻፴
ወደ ፲፩ ፔንስ አሽቆለቆለ ። ነጥቡ ከአጠንጣኝ ማሺኖች
መፈልሰፍና በሰፊው መስፋፋትና መተዋወቅ በኋላ ፤ የሱፍ
ክር በአብዛኞቹ ፋብሪካዎች ይሠራ ስለነበርና ዕሴት ደግሞ
በማሺን ምርት ይወሰን ስለነበር ነው ። የሕንዳዊ ሸማ
ዎች ፤ ማጠንጠኛ አሽከርካሪዎች ይጠቀሙ የነበሩት ፤ የሱፍ
ክር ለማምረት ከፋብሪካዎች ይበልጥ ሰዓት ያጠፉ ነበር
ማሺን የሠራውን የሱፍ ክር እንግሊዝ ወደ ሕንድ መላ
እንደጀመረች ፤ በእጅ የተሠራው የሱፍ ክር ዕሴት ፋብሪ
ከሠራው ጋር አሽቆለቆለ ። ውድድሩን ለመቋቋም ባለ
ቻል ሕንዳውያን ሸማኔዎች ጠፉ ።

* ከ 1971 ዓ. ም. ጀምሮ ፤ ፔኒ አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ
ነው — ከተርጓሚው



ይህ ምሣሌ የሚአሳየው የአንድ ሸቀጥ ዕሴት በእያን
ዳንዱ ክፍለ-ጊዜ (በአንድ ሰዓት ወይም አንድ ቀን) በሚመረ
ተው የዕቃ መጠን በሚለካው የጉልበት አምራችነት ላይ
ጥገኛ መሆኑን ነው ። ከሁሉም በላይ ፤ ጥገኛ የሚሆነው
በሥራ መሣሪያዎችና በቴክኒካዊ ደረጃቸው ላይ ይሆ
ናል ። ማሺኖች በተሻሻሉ መጠን ጉልበትም የዚያኑ ያህል
ያመርታል ። አምራችነት ማሺኖችን ለመጠቀም ሠራተ
ኞች ባላቸው ልምድና ችሎታ ላይም ጥገኛ ይሆናል ።
የሳይንሳዊ ዕድገትም ከፍተኛ ዋናነት አለው ። በሳይንስ
የሚገኙት ነገሮች በተፋጠኑ ቁጥር የጉልበት አምራችነት
መጠንም ይንራል ። በመጨረሻም ፤ የጉልበት አምራችነት
በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ላይ ጥገኛ ነው ። ለምሣሌ ፡— በእ
ርሻ ሁኔታ ላይ ፤ የአፈር ለምነትና አመች የአየር ንብረት
ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ። በማዕድንና በዘይት ምርት ኢን
ዱስትሪዎች ውስጥ ብዙው ጥገኛ የሚሆነው ባልተጣራው
ብረት ወይም ዘይት ክምችት ብዛት ነው ።

የጉልበት አምራችነት በሁሉም የካፒታሊስት ድር
ጅቶች ውስጥ በአንድ ዓይነት ሁኔታ ተሟልቶ እያድግም ።
እንደ ሕግ ሆኖ ፤ በመጀመሪያ በአንዳንዶቹ በቴክኒክ ደረጃ
መጠቅ ባሉትና በጣም ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ሲሉ በአ
ዲሱ የአሠራር ሥልት በሚገለገሉት ከፍ ይላል ። ከዚያ እነ
ስተኛ ድርጅቶች ለመኖር ሲሉ ምርት ለማሻሻል የሚገደ
ዱት ፤ ሥራቸውን ሠራተኞችን ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ
በመበዝበዝ በሚአካሂዱት ፤ ይቀጥላል ።

የጉልበት አምራችነት ለማንኛው አቀራረጽ ምጣኔ —
ሀብታዊ አስፈላጊነት ነው ፤ ለሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብ
ታዊና ባሕላዊ ዕድገት ዋና ቅድመ — ዝግጅት ከሆነበት

ማለት ነው ። አዲሶቹን የምርት ኃይሎች ደ
ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው ። አዲሶቹን የምርት ኃይሎች ያንጸባርቃል — ግ
ጀና የምርት ግንኙነቶችን አሠራር ያንጸባርቃል — ምርት ባ
ጃና የምርት ግንኙነቶችን አሠራር — ምርት ባ
ትም ሥልተ — ምርቱንና የዚህን ሥልተ — ምርት ባ
ርይና እርምጃ ።

ማንኛውም ወራሽ የሆነ ሥልተ — ምርት ከቀድሞ
ይበልጥ የጉልበት አምራችነትን በመጨመር ይታያል
ለሕብረተሰቡ የበለጠ ምርትና ትልቅ ሀብት ያቀርባል
ከአሮጌው ይበልጥ አዲሱ ሥርዓተ — ማኅበር የበለ
ጠቃሚ መሆኑን ግልጽ የሚአደርገው የጉልበት አምራችነ
ዕድገት ነው ።

ሌኒን ሲጠቁም «በመጨረሻ ትንታኔ ፤ የጉልበት አ
ራችነት በአዲሱ ሕብረተሰብ ሥርዓት በጣም አስፈላገ
ዋና ነገር ነው ። ካፒታሊዝም በገባርነት ዘመን ያልታ
ውን የጉልበት አምራችነት አስገኝቷል ። ካፒታሊዝም መ
በሙሉ ሊጠፋና ድል ሊሆን የሚችለው አዲስና ይበለ
የናረ የጉልበት አምራችነት በሚአስገኘው በሶሻሊ
ነው ።» ብሏል* ።

ስለዚህ የአንድ ሸቀጥ እሴት ጥገኛ የሚሆነው
ልበት አምራችነት ላይ ነው ። የጉልበት አምራችነት
ይል ፤ አንድ ሸቀጥ ለማምረት አነስተኛ ሰዓት ከመ
ዱም ሌላ ዝቅተኛ ዕሴት ይኖረዋል ።

ዕሴት ፤ የሸቀጥ ምርት ጸባይ የሆነ ታሪካዊ ፈርጅ ነ
የጉልበት ውጤቶች የልውውጥ ሸቀጦች በመሆን ሲወ
ብቻ ነው ሊኖር የሚችለው ። በተፈጥሮ ምጣኔ — ሀብ
ምርቶች ለገበያ በማይውሉበት ፤ እንደ እሴት ላለ ፈርጅ

* ሌኒን ፤ ጠቅላላ ሥራዎች ፤ ቅጽ 29 ፤ ገጽ 247



ረተሰባዊ አስፈላጊነት የለም ። ወይም በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ውስጥ ይህ አስፈላጊነት አይኖርም ፤ ምክንያቱም ከዚያ ጀምሮ የሸቀጥ ምርት ይከስማልና ። ለማጠቃለል ፦ ዕሴት የነገሮች የተፈጥሮአዊ ባሕሪ አይደለም ። እንዲአውም ፤ በአምራቾች መካከል የሕብረተሰብ ዝምድናን መግለጫ ነው ።

## ገ ን ዘ ብ

ሸቀጦችን በሚለዋወጥ ሕብረተሰብ ውስጥ ገንዘብ ሊወገድ የማይችል ነው ።

ገንዘብም ሸቀጥ ነው ፦ የሌሎችን ነገሮች ዕሴት መግለጫ ሸቀጥ የሆነ ፤ የሁለንታዊ አኳያነትን ሚና ለመጫወት ከሌሎች ብዙ ነገሮች ተለይቶ የወጣ ነው ። ገንዘብ በመድረክ ላይ (ገበያ) በታዩ ጊዜ ፤ ለሚወስዱት (ለሚአዘ በት) ሰዎች ሀብትና ሥልጣን በመስጠት የአዲስ ምጣኔ — ሀብታዊ ኃይል መድረስን አመለከተ ።

ወርቅ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያለው የሸቀጥ ገንዘብ ሆነ ። ባለፈው በተፈጥሮአዊ ባሕሪዎቹ ምክንያትና የገንዘብን ሕብረተሰባዊ ግልጋሎት በመስጠት ወርቅ ከሁሉም በላይ አመች ነገር ነበር — ነውም ። በቀላሉ ሊከፋፈልና ተመልሶም ያለምንም ጉድለት ሊገጣጠም (አንድ ሊሆን) ይችላል ። ስለማይዝግ ፤ ያለምንም ችግር ሊቀመጥ የሚችል ነው ። በተጨማሪም ከክብደቱ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ይዘት አለው ፤ የዚያኑም ያህል ከፍተኛ እሴት ።

ገንዘብ ብዙ ግልጋሎቶችን ይሠራል ። ከሁሉም በፊት እንደ እሴት መለኪያ ያገለግላል ፤ ማለትም የሌሎችን ሸቀጦች ሁሉ እሴት ለመለካት እንጠቀምበታለን ።

የአንድ ሸቀጥ ዕሴት በገንዘብ አባባሉ ተመን ( Price)
ተብሎ ይጠራል ።

የአንድ ሸቀጥ ዕሴት በአንድ የተወሰነ የወርቅ መጠን
የአንድ ሸቀጥ ዕሴት በአንድ የተወሰነ የወርቅ መጠን
ከተገለጸበት ጊዜ ጀምሮ የመለኪያ ደረጃ መወሰን አስፈላጊ
ነው ። ወርቅን በሚመለከት ረገድ ክብደት ሎጅካዊ የሆነ
የመለኪያ ደረጃ ነው። በገንዘባዊ መልኩ በአንድ ሀገር ውስጥ
ተቀባይነት ያገኘውና የማንኛውንም ሸቀጥ ተመን ለመወ
ሰን የሚአገለግል ክብደት ያለው የወርቅ መጠን ፤ የተመን
መለኪያ ይባላል ።

ዕሴታቸው በገንዘባዊ መልክ የሚገለጸው የዕቃዎች
ተመን ፣ ተጠያቂነትና ቀራቢነታቸው (ለሕዝብ) እኩል
የሆኑት ፤ በሁለት ሁኔታዎች ላይ ይንተራሳል ፦ በራሳ
ቸው የሸቀጦች ዕሴትና የወርቅ ዕሴት ላይ ። የሸቀጡ ዕሴት
ዝቅ ሲል ፣ ተመኑም ይወርዳል ፤ ይለዋወጣሉ ማለት ነው ፤
በሌላ በኩል ደግሞ ፤ የወርቅ ዕሴት ዝቅ ሲል ተመኑ ከፍ
ይላል ፤ እንደዚሁ ይለዋወጣል ። ስለዚህ ፤ የዕቃዎች ተመን
የሚለያየው ከዕሴታቸው ቀጥታ በመመጣጠን ሲሆን
ከወርቅ ዕሴት ጋር ግን ተቃራኒ መመጣጠን ይኖራቸዋል ።

ገንዘብ የዕሴት መለኪያ ሲሆን ሥውር ግልጋሎት
ይሠራል ። ይህም ማለት ፣ የሸቀጦችን ዕሴት ለመለካት
ገንዘብ (ካሽ) በእጅ እንዲኖር አስፈላጊ አይደለም ማለት
ነው ። እንደሽያጭና ግዥ ሥራ ሁሉ ፤ የሸቀጦች በገንዘብ
መለዋወጥ ፤ ብዙ ጊዜ ይደጋገማል ፤ ሺያጭና ገዥ በአእም
ሮአቸው በአንድ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ላይ (ወይም
ወርቅ) ከዕሴቱ ጋር በሚስማማ ሸቀጡን ያመጣጥናሉ ።



ሸቀጦች በገንዘብ እርዳታ ሲለዋወጡ ፤ የኋለኛው
እንደአዘዋዋሪ መሣሪያ ሆኖም ያገለግላል ። ይህን ተግባር
ለማከናወን ከሥውርነት ይልቅ ግልጽና ወዲያው በእጅ
የሚገኝ መሆን አለበት ። በማዘዋወር ጊዜ ገንዘብ በጅ ላይ
ሳያቋርጥ ይለዋወጣል ፦ ዛሬ አምራች ለሸቀጡ ሽያጭ
የተቀበለው ገንዘብ ፤ ነገ በሌላ አምራች የተመረተን ሸቀጥ
ለመግዛት ይውላል ። እንደአዘዋዋሪ መሣሪያ ገንዘብ ሊሠራ
የሚችለው በሸቀጦች ልውውጥ ውስጥ አማካይ በመሆን
ብቻና ሊተካ የሚችለው ደግሞ ያለምንም ጉድለት በዕሴት
ምልክቶች ወይም ወካዮች ፤ እንደወረቀት ገንዘብ ባሉት
ነው ። ዋናው ነገር ማንም ሰው እነኚህን የዕሴት ወካዮች
የሚቀበል ከእርሱም ወደሌላው ተቀባይነት የሚአገኙ
መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ፤ ለሌሎች ሸቀጦች ሲከፍል
ማለት ነው ። ለዚህ ነው መንግሥት የወረቀት ገንዘብ ሕጋ
ዊ ገንዘብ እንዲሆን የሚአውጀው ።

ለአዘዋዋሪነት የሚአስፈልገው የገንዘብ መጠን የሚ
ወሰነው በገንዘባዊ አከፋፈል በሚሠሩት የሸቀጦች ተመን
ድምር በአማካይ የመዘዋወር ቁጥሮች (Average number of
turnovers) ማካፈል ላይ ነው። ለምሣሌ፡-በአንድ አገር ውስጥ
በአንድ ዓመት የተሸጡት የጠቅላላ ዕቃዎች ተመን ጠቅ
ላላ ድምር 100,000 ሚሊዮን ገንዘባዊ አከፋፈል ቢሆንና
ገንዘባዊ አከፋፈሉ በዚያ ዓመት የአምስት ጊዜ አማካይ
መዟዟር ቢሠራ ፤ ለማዘዋወር አስፈላጊ የሆነው ገንዘብ
መጠን 20,000 ሚሊዮን ነው ። ገንዘባዊ አከፋፈሉ 10
የማዘዋወር አማካይ ከሠራ ፤ አስፈላጊው የገንዘብ መጠን

በ10,000 ሚሊዮን ላይ ብቻ ይቆማል ። ስለዚህ ፤ የገንዘብ
መዟዟር (መለዋወጥ) በፈጠነ ቁጥር ፤ ለማዘዋወር የሚያስ
ፈልገው ገንዘብ ያንሳል ።

በመዘዋወር ላይ ያለው የወረቀት ገንዘብ መጠን ሙሉ
በሙሉ በወርቅ ከተደገፈ የመግዛት ኃይሉ ከወርቅ እኩል
ይሆናል ። ይሁንና የካፒታሊስት መንግሥት ብዙውን ጊዜ
በተለይ በጦርነት ወቅት ፤ ኪሣራውን ለመሸፈን ፤ የንግድን
መለዋወጥ ፍላጉት ምንም ገንዛቤ ሳይሰጥ ትርፍርፉ የወጣ
የወረቀት ገንዘብ መጠን ያትማል ። ይህ ትርፍርፍ የወረቀት
ገንዘብ ሕትመት ወደ ገንዘብ ዝቅጠት ወይም ንረት ይመ
ራል ። ክፍያቸው (ደመወዛቸው) ከጨመረበት ጊዜእንስቶ
ለመኖር የሚአስፈልጉት ነገሮች ተመን ጋር ሲነጻጸር ወደ
ኋላ ስለሚጐተት ፤ ይህ በሠራተኛ ሕዝቦች በተለይም በፋ
ብሪካና በቢሮ ሠራተኞች ላይ ከባድ ሸክም ይሆንባቸዋል ።
ታናናሽ አምራቾች ፤ እንደገበሬዎች ያሉትም በተመን መና
ር ይሰቃያሉ ። አዘውትሮ ሳይሆን አለፍ ተቀደም የሚጉ
ዳው የካፒታሊስቱ መደብ ነው ፤ ታላላቅ ንግዶች ግን
ከዚሁም ትርፍ ያገኙበታል ።

የዋጋ መናር የካፒታሊስቱን ምጣኔ — ሀብት አደጋ
ላይ ለመጣል ሲጀምር ፤ መንግሥት ገንዘባዊ ሥርዓቱን
እርጋታ እንዲኖረው ርምጃዎችን ይወስዳል ። ሁሉም ዓይ
ነት ጥገናዎች ይቀርባሉ ፤ የመጀመሪያው ተመን ማውረድ፣
የወርቅን የገንዘባዊ ክፍያ ይዘት መቀነስ ይሆናል ።

<u>ገንዘብ እንደ ማከማቻ ወይም የዲናርና የልዩ ልዩ ሀብ
ቶች ማጠራቀሚያ ዘዴ ሆኖም ያገለግላል ። ይህ ግልጋሎት
ሊገኝ የሚችለው ገንዘብ ማንኛውንም ሸቀጥ መግዛት</u>



<u>ከመቻሉ ላይ ነው ።</u> ስለዚህ ፤ ገንዘብ የሀብት ሁለንታዊ
አያያዥና የማከማቻ ዘዴ ነው ። ይሁንና ፤ ከመዟዟር በመ
ውጣት ፤ ገንዘብ ሀብት ሊሆን የሚችለው ወርቅ ከሆነ ፤
ወይም ገንዘብ ወደ ወርቅ ፤ ብር (ማዕድን) እና ሌላ ውድ
ወደሆኑ ብረታ — ብረቶችና ድንጋዮች ከተለወጠ ነው ።

ገንዘብ ሁልጊዜ በካሽ መልክ አይደለም ። ሸያጭና
ግዥዎች ብዙውን ጊዜ የሚከናወኑት በዱቤ ነው ። ይኸውና
አንድ ምሣሌ ። አንድ ባለፋብሪካ ትራክተር ያወጣና በጥቢ
ወራት ለሽያጭ ያቀርባል ። ገበሬው እርግጥ በዚህ ጊዜ ትራ
ክተሩን ይሻዋል ፤ ግን እስከ በጋው እህል እስከሚሰበሰብ
ድረስ ገንዘብ አይኖረውም ። ስለዚህ ትራክተሩን እስከተ
ወሰነ የመጨረሻ ቀን ድረስ በማቆየት በዱቤ ይገዛል ።
በዚህ ዓይነት <u>ገንዘብ የመክፈያ ዘዴ ሆኖ ያገለግላል</u> ። በተ
ጨማሪም ይህንን ተግባር የሸቀጦችን እንቅስቃሴ ሳያስገ
ባም ፤ ግብር እንደመክፈል ባለው ክንዋኔ ሊሠራው
ይችላል ።

በሐገሮች መካከል ባሉት ምጣኔ — ሀብታዊ ግንኙነ
ቶች ፤ ገንዘብ ብሔራዊ የአለዋዋጭነት ልብሱን አውልቆ
እንደ ዓለማዊ ገንዘብ ያገለግላል ። በዚህ ሁኔታ እንደመ
ነሻ መልኩ ነው የሚአገለግለው ፡- እንደወርቅ ቡችላ
(የመጀመሪያ መልኩ ከመሠራቱ በፊት ያለው) ። የወርቅ
ክብደት በመንግሥታት መካከል በሂሣብ ማመዛዘኛ አደራ
ዳራነት ተቀባይነት አለው ።

## <u>የዕሴት ሕግ</u>

በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ የንብረት ባለቤቶች መገ
ልገያዎቻቸውን ለሕብረተሰቡ ጥቅም እንዲአውሉ ማንም

የሚአስገድዳቸው የለም ። ካፒታሊስቶቹ በምርት ላይ ሲሰ
ማሩ ፤ እያንዳንዳቸው ብዙውን ጊዜ የሚሠሩት በራሳቸው
ፋብሪካ ውስጥና በራሳቸው ኪሣራ ነው ። አንድ ዓይነት
ሸቀጦችን የሚአመርቱ ፋብሪካዎችን ቁጥር አስቀድሞ
በትክክል የሚያውቅ የለም ፤ ይህ ወይም 'ያ' ሸቀጥ
ምን ያህል እንደሚመረትና በዓመት ወይም በሁለት
ዓመት ገበያ ላይ እንደሚወጣ ፤ ወይም ደምበኛው
ምን ያህል ለመግዛት እንደሚችል አይታወቅም ። ይህ
ሁኔታ ወደ ምርት ሥርዓተ — አልባነት ይደርሣል — በካፒ
ታሊስቱ ምጣኔ — ሀብት በአጠቃላይ የድርጅትና የዕቅድ
እጥረት ይኖራል ። ምንም እንኳ ካፒታሊስቱ በራሱ ድር
ጅት ሁኔታ ላይ ቁጥጥር ቢኖረውም ፤ ሙሉ በሙሉ የገበያ
ጥገኛ ነው ፤ እናም የገበያው ምጣኔ — ሀብታዊ ሕጐች
ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ ናቸው ።

የምርት ሥርዓተ — አልባነት ከነጻ ውድድር ጋር በማይ
ነጣጠልሁኔታ የተያያዘ ነው — በምርትና በገበያ ላይ ጥቅም
ለመውሰድ በካፒታሊስቶች መካከል በሚካሄደው ኃይለኛ
ትግልና በትርፍ ሩጫ ላይ የተያያዘ ማለት ነው ።

አንድ ሰው ይህ ሥርዓት እንዴት ሊኖር እንደሚ
ችል ፤ ያም ይቅርና ፤ በማደጉ ይገረም ይሆናል ። መግለ
ጫው (ማብራሪያው) ፤ የካፒታሊስትን ምርት በግብታዊ
ሁኔታ ርጋታ የሚሰጠው ኃይል እንዳለ ነው ። ይህ ኃይል
የዕሴት ሕግ ነው ።

ከዚህ ሕግ ጋር በመስመር (መስማማት) ሸቀጦች እነ
ሱን ለማምረት ከሚወጣው የሕብረ ተሰብ አስፈላጊ
ጉልበት መጠን ጋር በሚስማማ ተመን ይለዋወጣሉ ፤ በን



ድፈ — ሀሳቡ የአንድ ሸቀጥ ተመን ከዕሴቱ ጋር ይጣጣማል ።
ግን የገበያ ተመን የሚመሠረተው በቀራቢነትና በተጠያቂ
ነቱ (የሸቀጡ) ተዕዕኖ በግብታዊ ሁኔታ ነው ። የዕቃዎች
ቀራቢነት ከተጠያቂነቱ ከአየለ ፤ ተመኑ ከዕቃዎቹ ዕሴት
በታች ይወርዳል ። ተጠያቂነት ከቀራቢነት እኩል ከሆነ ፤
ተመኑ ከዕሴቱ ጋር እኩል ይሆናል ። በተመን መዋለል ተጽ
እኖ ምክንያት ካፒታሊስቶች ገንዘባቸውን የዕቃዎች ተመን
ከዕሴታቸው በታች ከወረደበት ኢንዱስትሪ ከዕሴታቸው
በላይ ወደሆነበት ያዛውራሉ ።

የካፒታሊስትን የሸቀጥ ምርት ርጋታ ለመስጠት የሚ
አስችለው መሣሪያ በዕሴት አካባቢ በግብታዊነት የሚዋ
ልለው ተመን ብቻ ነው ። የተመን መዋለል በአንድ ኢንዱ
ስትሪ ውስጥ ያለን ምርት ከሌላው ኢንዱስትሪ የበለጠ
ወይም ያነሰ ትርፍ እንዲኖረው ማድረጉን ፤ ይህ ኢንዱስ
ትሪ ምርትን ያስፋፉ ወይም ያሳንስ እንደሆነ ይወስናል ።
ይህ ነው የዕሴት ሕግ ባሕሪ ። በካፒታሊዝም ውስጥ ይህ
ሕግ የሸቀጦችን መለዋወጥና የምርት መገልገያዎችን ማከ
ፋፈል እናም በኢንዱስትሪዎች መካከል የጉልበት መከፋ
ፈልን ያስተካክላል ።

በገበያ ላይ የተመኖችና በቀራቢነትና በተጠያቂነት
ያለ መዋለል በአምራቾች መካከል አለመመጣጠንን (ዕኩል
ያለመሆንን) ያሳያል ። አንዳንዶቹ ይራቆታሉ ፤ በአንጻሩ
ሌሎች ይበለጽጋሉ ። በዕሴት ሕግ አሠራር ውስጥ ይህ የማ
ይቀር ውጤት ነው ። አንድ ባለፋብሪካ በተወዳዳሪዎቹ
ከውድድር መስክ ውስጥ ተጨፍልቆ እንዲወጣ ሳይሆን
ለመኖር ከፈለገ ፤ ዕቃዎቹን ማርከስና የጉልበት አምራችነ

ትን በፋብሪካው ውስጥ መጨመርና የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎችን መጠቀም አለበት ።

እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ውድድር የአዲስ መሣሪያዎችን መተዋወቅንና ምርትን ዘመናዊ ማድረግን ያበረታታል ። በዚያው ጊዜ ፣ ውድድርና የምርት ሥርዓተ — እልባነት ለምርት ኃይሎች መበላሸት ምክንያት በመሆን ከዚህ በፊት ተደርጐ የማያውቅ ከባድ ሥራ በሠራተኞች ላይ ያመጣሉ ። ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል የጉልበት መበዝበዝ ሥልትን በምንተነትንበት ወቅት እናየዋለን ።

## ፪ የጉልበት በካፒታል (ወረት) መበዝበዝ

### ትርፍ ዕሴት

የካፒታሊስት ምርት ተግባር የካፒታሊስትን መደብ ማበልጸግ ብቻ እስከሆነ ድረስ ፣ ይህ በማን ኪሣራና እንዴት ሊገኝ እንደሚችል እስቲ እንመልከት ።

ሸቀጦች በገበያ ለመሸጥ ከመቻላቸው እና ለእነርሱም ገንዘብ ከመውሰዱ በፊት መመረት አለባቸው ። እናም አንድን ቁሳዊ ዕሴት የማምረቻ መንገድ (ዘዴ) ጉልበትና ጉልበት ብቻ ነው ። ካፒታሊስቱ ባሪያ — አሳዳሪ አይደለም ። ወይም መልከኛም አይደል ። እንደሚመኘው አድርጐ የሚአሰማራቸው ባሮች ወይም ገባሮች የሉትም ። ግን የምርት መገልገያዎች ባለቤት ነው ፣ እናም የከበርቴ ሕብረተሰብ ከነኝህ መገልገያዎች የተወገደ የወዝ-አደር መደብ አለው ። በደምቡ ፣ ሠራተኛው በካፒታሊስቱ ላይ ጥገኛ አይደለም ። ግን ለመኖር ሲል ከካፒታሊስቱ መቀጠ



ርን ይሻል ፣ የጉልበት ኃይሉን ለእርሱ ለመሸጥ መሆኑ ነው ። ካፒታሊስቱ ይህን ሲገዛው ፣ ቁሳዊ ጥቅም ሊአስገኝ የሚችለውን ልዩ ሸቀጥ (ጉልበት) ነው የሚአገኘው ።

እንደሸቀጥ የጉልበት ኃይል የተወሰነ ዕሴት አለው ። አሁን ሠራተኛው መሠረታዊ ፍላጐቶችን ካላገኘ ለመሥራት አይችልም ። ሁልጊዜ የተወሰነ የምግብ መጠን ከመፍጀቱም ሌላ ፣ ልብስና የመኖሪያ ቦታ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። በመሠረቱ ፣ ለካፒታሊስቱ አዲስ የጉልበት ኃይል የሚሆኑትን ቤተሰቡን ማለትም ልጆቹንም ይረዳል ። ስለሆነም ፣ የጉልበት ኃይል ዕሴት ለሠራተኛውና ለቤተሰቡ የሚአስፈልገውን የሕይወት መደጐሚያ ዕሴት እኩል ይሆናል ።

የጉልበት ኃይል ዕሴት ከአገር አገር ከዘመን ዘመን ይለያያል ። ጥገኛ የሚሆነው በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎችና በአንዲት ሀገር የዕድገት ጉዞ ላይ በሚገኘው የኑሮ ደረጃ ነው ።

ለምሣሌ የጃፓን ካፒታሊስቶች ፣ የጃፓን «ምጣኔ — ሀብታዊ ታምር » ምስጢሩ ምን እንደሆነ አይደብቁም ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የካፒታሊስት ኃይሎችን በኢንዱስትሪ ዕድገት የመጀመሪያውን ደረጃ ያገኘችው ይህች አገር ፣ ዋናው ምክንያት ከአውሮጳውያንና ከአሜሪካውያን ሠራተኞች ሲወዳደር የእርሷ ሠራተኞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ በመኖራቸውና ስለዚህም ፣ በጃፓን ውስጥ ባለው የጉልበት ኃይል ዕሴት ዝቅተኛነት ነው ።

ካፒታሊስቶች የጉልበት ኃይልን ዕሴት ባለበት ደረጃ ለማቆየት ምንም ያህል ፍላጐት ቢኖራቸውም ፣

እንዲያ ሊቀር ግን አይችልም ። በጉልበት ኃይል ላይ እን ደምርት ዕድገት ፣ የቴክኖሎጂ ርምጃ የመሳሰሉት ምጣኔ ሀብታዊ ምክንያቶች ተጽዕና ስለሚደርስበት ፣ በሌላ በኩል የጉልበት አምራችነት ማደግ የሠራተኞችን መደጐሚያ ዕሴት ዝቅ ስለሚአደርገውና ፣ በዚህም ምክንያት የጉልበት ኃይል ዕሴት ስለሚአሽቆለቁል ነው ። በሌላ መንገድ ፣ ከተሞች ሲአድጉ ፣ የትራንስፖርት እና እንደጋዜና ቴሌ ፎን ያሉት መጠቀሚያዎች ክፍያ ያአድጋል ። በባሕል አድማስም ውስጥ አዳዲስ ፍላጐቶች ይነሳሉ ። በአሁኑ ወቅት ወደፊት በቀደሙ የካፒታሊስት አገሮች ሠራተኛው

ያለጋዜጦች ፣ ያለሲኒማዎች ፣ ያለሬዲዮ ፣ ወይም ያለቴሌቪ ዥን ሊሠራ አይችልም ። የሠራተኛው ቤተሰብቦች ፍላጐት ሲአድግ ፣ የጉልበት ኃይልም ዕሴት ያድጋል። ።

ግን የጉልበት ኃይልን ዕሴት ተጽዕኖ የሚአደርስበት ዓይነተኛው ምክንያት ሁኔታውን ለማሻሻል ከካፒታሊስ ቶቹ ጋር የሚካሄደው የወዛደሩ የመደብ ትግል ነው ።

ካፒታሊስቱ የጉልበት ኃይልን በሚገዛበት ጊዜ በም ርት መገልገያ ባለቤትነቱ የሸቀጥና የዕሴት ትክክለኛ አም ራች እሱ መሆኑን ለማሳመን ሠራተኞችን ለማግባባት ይሞክራል ። ግን እርግጥ ነውን ?

ጉልበትና የምርት መገልገያዎች የተለያዩ ሚና ነው የሚጫወቱት ። የጉልበት ኃይል አዲስ ዕሴት ያስገኛል ፣ ግን የምርት መገልገያዎች ምንም አያስገኙም ። ጉልበት የምርት መገልገያዎችን ዕሴት ይጠብቃል ፣ ዕሴታቸው ሲአ ሽቆለቁል ደግሞ ይህን ዕሴት አዲስ ወደሚመረቱ ሸቀጦች ያሻግራል ። ስለዚህ ፣ የአንድ ማሽን ዕድሜው አሥር ዓመት



ቢሆንና እያንዳንዱ ዓመት የማሽኑን ዕሴት 1/10ኛ ቢቀንስ፣ ይህ ክፍል ወደ ሚመረተው ሸቀጥ ዕሴት ይተላለፋል ። ጥሬ ዕቃዎች ፣ ለምሣሌ ጥጥ ሙሉ በሙሉ የተፈበረከ በመ ሆን ላይ ወዳለ አዲስ ምርት ይጠቃለላል ፣ እናም የጥጡ ዕሴትም የተፈበረከው ዕሴት ክፍል ለመሆን ሙሉ በሙሉ ይተላለፋል ።

የአንድ ኮት ማቴሪያል ዕሴት (ከቁልፎች ፣ ገበር ፣ ወዘተ . . ጨምሮ) 20 ብር ቢሆንና ልብስ ሰፊው ለሥራው 10 ብር ቢጠይቅ ፣ ያለቀለት ኮት ዕሴት 30 ብር ይሆናል። የቀድሞው ዕሴት 20 ብር በልብስ ሰፊው ሥራ ተጠብቆ ወደኮቱ ተላለፈ ። በልብስ ሰፊው የተፈጠረው አዲሱ ዕሴት ፲ ብር ሆን ።

በሠራተኛው የተገኘው አዲስ ዕሴት በካፒታሊስቱ ምርት ጊዜ የእርሱን (የሠራተኛውን ) የጉልበት ኃይል ዕሴት ይበልጣል ።

ለምሣሌ ፦ ሠራተኛው ሁለት ብር የሚያወጣ አዲስ ዕሴት በአንድ ሰዓት ውስጥ ያስገኛል ፣ ግን የእርሱ የጉል በቱ የቀን ዕሴት ፲ ብር ይሆናል ብለን እንውሰድ ። በዚህ ሁኔታ የአምስት ሰዓት ሥራ በጠቅላላ የቀኑን ሥራ ዕሴት ይሸፍነዋል ። ሠራተኛው የጉልበት ኃይሉን ሸጧል ፣ ግን የተወሰነ የጉልበት መጠን አይደለም ። ይህም ማለት ለተወሰኑ ሰዓቶች ሳያቋርጥ መሥራት አለበት ነው ። የስ ምንት ሰዓት የሥራ ቀን ቢኖረው ፲፮ ብር የሚሆን አዲስ ዕሴት ይፈጥራል (ያስገኛል) ። ስለዚህ ፣ በማምረት ላይ ሠራተኛው ከእርሱ የጉልበት ኃይል ዕሴት በላይ የሆነ ዕሴት ያስገኛል ማለት ነው ።

ለሠራተኛው ምንም ካሣ ሳይሰጠው ካፒታሊስቱ የሚበዘብዘው ልዩነትና ለካፒታሊስቱ ብልጽግና ምንጭ የሆነው፤ ትርፍ ዕሴት ይባላል ።

ስለሆነም፤ የካፒታሊስት ብዝበዛ ባሕሪ የትርፍ ዕሴት ምርትና የዚሁ ዕሴት በካፒታሊስቱ መወሰድ ነው ። የምንዳዕ ጉልበት ሥርዓት የምንዳዕ ባርነት ሥርዓት ነው ።

የሥራ ቀኑ ሁለት ክፍሎች በውስጡ እንደያዘ እናያለን ፥— በመጀመሪያው ክፍል፤ አስፈላጊው የሥራ ሰዓት በሆነው፤ ሠራተኛው ከጉልበት ኃይሉ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዕሴት ያስገኛል፤ በሁለተኛው ክፍል፤ ትርፍ የሥራ ሰዓት በሆነው፤ ለካፒታሊስቱ ትርፍ ዕሴት ያመጣል ። ለማጠቃለል፤ ሠራተኛው ለራሱ ለመሥራት ብዙ ሰዓት በወሰደ ቁጥር፤ ለካፒታሊስቱ የሚሰራው ሰዓት አነስተኛ ይሆናል፤ እንዲህ እያለ ይለዋወጣል ። በዚህ ሁኔታ ካፒታሊስቱ ሁልጊዜ በተቻለ መጠን ትርፍ ሰዓት ለመጨመር ይጥራል፤ የሠራተኞችን መበዝበዝ ለማጠናከርና በተቻለው መጠን ከነሱ ጉልበት ብዙ ትርፍ ለመውሰድ ማለት ነው ።

ትርፍ ዕሴት ከካፒታሊስቱ ክንዋኔዎች በስተጀርባ ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል ነው ። ይባስ ብሎ የሚአመርተው ነገር ለእሱ ምኑም አይደለም — ለብሎት የሚሆኑ ጠቃሚ ዕቃዎች እንደምግብ ወይም ልብስ፤ ወይም የሞትና የጥፋት መግሪያዎች የመሣሰሉት ። የካፒታሊስቱ ዕርካታ ግን የጠቀሜታ ዕሴት ያላቸው ዕቃዎች ማምረት ነው፤ ምክንያቱም ይህ ትርፍ ዕሴት ለማስገኘት አስፈላጊ ነውና ።

የምንዳዕ ጉልበትን በመበዝበዝ የትርፍ ዕሴት ምርት የካፒታሊዝም ዋና ምጣኔ — ሀብታዊ ሕግ ነው ። በዚህ



ሕግ የካፒታሊስት ምርት ተግባርና ይህን ተግባር የማግኛ ዘዴዎች ግልጽ ይሆናሉ ።

ትርፍ ዕሴት የሚገኘው በቁሳዊ ምርት አካባቢ ስለሆነ፤ በመጀመሪያ ስናየው ኢንዱስትሪያሊስቶች በሙሉ የሚወስዱት ይመስለናል ። ይሁንና፤ በተግባር ግን በተከታታይና መራራ ውድድር አማካይነት ትርፍ ዕሴት በተለያዩ የካፒታሊስት ቡድኖች ነው የሚከፋፈለው ። መጀመሪያ ትርፍ ዕሴቱ በኢንዱስትሪያሊስቶች ይወሰዳል፤ ግን በኋላ ለነጋዴዎች፤ ባንከኞች ወዘተ . . . ማካፈል ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም ሸቀጦች ለመመረት ብቻ ሳይሆን ለመሸጥ ነው የሚመረቱት ። በደምቡ መሠረት ኢንዱስትሪያሊስቶች ምርቶቻቸውን ለደንበኛ (በላተኛ) ለሚሸጡ ነጋዴዎች በጥቅል (በብዛት) ይሸጣሉ ። ኢንዱስትሪያሊስቱ ራሱ ሸቀጦቹን መሸጥ ቢኖርበት (በችርቻሮ) ለሱቆች፤ የሱቅ ረዳቶች በመቅጠር፤ ለመጋዘኖች ወዘተ . . . . ተጨማሪ ገንዘብ ማጥፋት ይኖርበታል ። እነዚህን ተጨማሪ ክፍያዎች ለማስወገድ ለነጋዴው ዕቃውን እንዲሸጥ ይተውለትና ከትርፍ ዕሴቱ የተወሰነ ክፍል ለእርሱ መልቀቅ አለበት ።

ለማጠቃለል፥— በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ገንዘቡ ያልተወሰደ ገቢ ሁሉ በትክክል የትርፍ ዕሴትመልክ አለው ። ይህ የሚውለው በንግድና በንግድ ትርፎች፥ በወለዶች ወዘተ . . . ነው ። ይህ ያልተወሰደ ገቢ ምንጩ በማቴሪያል ምርት አካባቢ ከተሠማሩት ሠራተኞች ትርፍ ጉልበት ብቻ ነው ። ይህም ሠራተኞች የተበዘበዙት በቀጣሪያቸው ብቻ ሳይሆን ግን በአጠቃላይ በካፒታሊስቱ መደብም መሆኑን ነው ።

## ካፒታል ።

በካፒታሊስት ሕብረተሰብ የምርት መገልገያዎች ለገንዘብ ይሸጡ ይገዛሉ ፤ ማለትም የራሳቸው የሆነ ዕሴት ያላቸው ሸቀጦች ናቸው ። ምርት የሚጀምረው ካፒታሊስቱ የምርት ኃይልን መግዛት ሲጀምር ነው ። ወዲያውኑ አንድ ላይ እንደመጡ ፤ የሸቀጦች መመረት ይቀጥላል ። ታዲያ እነዚህ ሸቀጦች ደግሞ ካፒታሊስቱ በሚአወጣቸው ጊዜ ያጠፋውን መጠን በሚአስበልጥ የገንዘብ ድምር ይሸጣሉ ። ካፒታሊስቱ በአዲሶቹ ዕቃዎች ላይ ትርፍ ዕሴት የሚአገኘው፤የቅጥር ጉልበት ለመበዝበዝ ሲል ወጭ ያወጣል ።

የቅጥር ጉልበትን በመበዝበዝ ትርፍ ዕሴትን ለማስገኘት ወይም ለመፍጠር የሚችለው ዕሴት ካፒታል (ወረት) ተብሎ ይጠራል ።

የቡርዧ ርዕዮተ — ዓለማውያን ካፒታል (ወረት) የተገኘው በኢንዱስትሪ በመጥቅለቅ ፤ ካፒታሊስት በሆን አንዳንድ ግለሰቦች ጥንቃቄ (ቁጠባ) እና በሌላም ልግስና ነው ። በኋላ ቁጠባ የማያውቁና ሰነፍ ሰዎች ፤ ይልና ንድፈ—ሀሳባቸው ፤ ቅጥር ጉልበተኞች ሆኑ በማለት ያላዝናል ።

ግን የመጀመሪያው ካፒታል የተገኘው በሥራ ነበር ተብሎ ቢታሰብ እንኳ ባሕሪውን አይለውጠውም ። ከአጭር ጊዜ በኋላ ፤ የእንዲህ ዓይነት ካፒታል ጥፋቶች የብዝበዛ ውጤት በሆነው በትርፍ ዕሴት ተተክተዋል ፤ ይህ የሚሆነው ካፒታሊስቶች ላወጡት ወጭ ሁሉ ማስተካከያቸው ትርፍ ዕሴት በሚወስዱ ጊዜ ከሚአገኙት



ጥቅም ስለሚሆን ነው ። የቅጥር ጉልበት ብዝበዛ ባይኖር ኖሮ የመጀመሪያው ካፒታል በአጣዳፊ ጠፍቶ ባዶ እጃቸውን ያስቀራቸው ነበር ።

በአንድ የካፒታሊስት ድርጅት ውስጥ ጠቅላላ ድምሩ ፩፻ሺ ብር የሆነ ገንዘብ በአገልግሎት ላይ ዋለ እንበል ። ቅጥር ሠራተኞች ራቅ አርገን እንገምትና ፤ ካፒታሊስቱ ለግላዊ ፍላጎቱ ሙሉ በሙሉ የሚአጠፋው በዓመት ፳ሺ ብር ትርፍ ዕሴት ያምርቱ ። በዚህ ሁኔታ በአምስት ዓመት በካፒታሊስቱ የሚጠፋው ጠቅላላ ትርፍ ዕሴት ከመጀመሪያው ካፒታል (ወረት) ድምር ዕኩል ይሆናል ። በመጨረሻ ካፒታሊስቱ ቅጥር ጉልበት ሳይበዝብዝ ግን በመጀመሪያው ካፒታል (ወረት) ቢኖር ፤ ከአምስት ዓመት በኋላ ከገንዘቡ የሚቀረው በጣም ትንሽ ይሆናል ። ቀጣሪው ካፒታሉን (ወረቱን) ሊአቆይና ሊገነባ የሚችለው ከሠራተኞቹ ትርፍ ዕሴት በመጭመቅ ብቻ ነው ።

በተግባር ፤ ቀጣሪዎች ጠቅላላ ዕሴቱን አያጠፋትም ። የትርፍ ጥማት ምርትን ለማስፋፋትና ከገቢአቸው የተወሰነ ክፍል በእርሱ ላይ እንዲአጠፉ ይገፋፋቸዋል ። እናም ምርት ሲስፋፋና የሚበዘበዘው ሠራተኛ ቁጥር ሲጨመር ወደካፒታሊስቱ የሚሄደው ትርፍ ዕሴት መጠንም ይገራል ።

ከዚህ የሚወሰዱ ሁለት መደምደሚያዎች አሉ ፡— መጀመሪያ ማንኛውም ካፒታል (ወረት) የብዝበዛ ውጤት ነው ። ሠራተኛውን ሕዝብ በመበዝበዝ (ሁሉንም ግለሰቦችንና ጠቅላላ ብሔሮችን) ነው የሚቆየውና የሚጨምረው ። ሁለተኛ ፤ ብዛቱ ምንም ያህል ይሁን ፤ የገንዘብ

የምርት መገልገያ — ፋብሪካ
ድምር (መጠን) ወይም የምርት መገልገያ — ፋብሪካ
ድምር (መጠን) ወይም የምርት መገልገያ — በራሳቸው ዕውነተ
ጥሬ ሀብቶች ፤ ነዳጅና ማሺኖች — በራሳቸው ዕውነ
ጥሬ ሀብቶች ፤ ነዳጅና ማሺኖች — ካፒታል ሊአደርጋቸ
ውን ካፒታል (ወረት) አያስገኙም ። ካፒታል ሊአደርጋቸ
ውን ካፒታል (ወረት) የግል ባለቤት መደብ
የሚችለው የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤት መደብ
የጉልበት ኃይላቸውን እንደሸቀጥ የሚሸጡ የቅጥር ሠራ
ኞች መደብ የመኖር ሁኔታ ነው ። ለመደምደም ፤ ካፒታ
(ወረት) ፤ በካፒታሊስቶችና በሠራተኞች መካከል ያለ
የሕብረተሰብ ግንኙነት ነው የሚወክለው ፤ እናም ባሕሪ
የጉልበት ብዝበዛ ነው ።

የካፒታሊስቱ ሥርዓት ሲወገድ ፤ የምርት መገል
ዎች የሕዝብ ንብረት ይሆናሉ ፤ የጉልበት ኃይል ሸቀ
መሆኑን ያቆማል ፤ እና ካፒታልም እንደ ታሪካዊ ሪ
ሆኖ መኖርን ያቋርጣል ።

<u>የካፒታል ክምችትና የወዛደሩ ኑሮ እየከፋ መሄ</u>
እንዳየነው ፤ ትርፍ የካፒታሊስት የክምችት ምንጭ ነ
ከዚህ ትርፍ ዕሴት ውስጥ የተወሰነው ክፍል ለካፒታሊ
ግላዊ ፍላጐት ሲጠፋ ፤ ሌላው ክፍል ግን ምርትን ለ
ፋፋት ይውላል ። ይህ ክፍል እራሱ ወደካፒታል ይዞራ
ወይም ካፒታላዊ ይሆናል ። ታዲያ ሂደቱ ደግሞ የካፒታ
መከማቸት (መጠራቀም) ይባላል ።

የካፒታል መከማቸት ቀጣሪዎችን የበለጠ ምር
እንዲአስፋፉ ፤ ብዙ ሠራተኞ እንዲቀጥሩ ፤ በአዲስ መ
ያዎች አማካኝነትና የሰው ችሎታ እስከሚፈቅደው ወ
ድረስ ጉልበትን በማፈግ የጉልበት አምራችነትን ማላይ
ብዝበዛን እንዲጨምሩ ፤ እና በጣም በከፍተኛ ደረጃ
ዕሴት እንዲወስዱ ያስችላቸዋል ። በዚህ ምክንያት ፤ በ



በኩል ፤ የበዝባዥ መደቦች መንደላቀቅና ተባይነት ያድ
ግና ያ የሕብረተሰብ ክፍል እጅግ በጣም ከፍተኛ ሀብት
የግበሰብሳል ፤ በሌላ በኩል ፤ የወዛደሩ መበዝበዝ ይበልጥ
ይተባል ፤ ስለዚህ በሥራቸው የሕብረተሰቡን ሀብት በሚ
አፈሩትና የተፈራውን ሀብት በሚዘርፉት መካከል መለያ
የት ይፈጠራል ። ይህ ነው የካፒታሊስት ክምችት ሕግ ።
የሌሎችን ጉልበት በመበዝበዝ ካፒታሊስቶችን እን
ዲንፈላሰሱ ሲአበቃቸው ፤ ካፒታሊዝም ከሠራተኞች የተ
ወሰኑ ክፍሎችን ወደ ሥራ-አጥነት እና ድህነት ያወርዳቸ
ዋል ፤ እናም የሕይወት ማቆያቸውን እንኳ ይነሳቸዋል ።

ሥራ-አጥነት በምንም ዓይነት የካፒታሊዝም አጃቢ
ነው ፤ በሁሉም በማደግ ላይ ባሉና በተራመዱ የካፒታሊ
ስት አገሮች ሠራተኞች ላይ በካፒታሊስቶች የተጣለ
ምርገም ነው ። መጀመሪያውኑ እራሱን እንዲሰማ ያደረገ
በመጀመሪያው የካፒታሊስት ዕድገት ላይ ነው ። በቴክኖ
ሎጂ ዕድገት ምክንያት ብዙ የተሻሻሉ መሣሪያዎች እንደ
ታዩ የጉልበት ኃይል ተጠያቂነት አሽቆለቆለ ። ግን በመ
ጀመሪያ ደረጃ ሥራ-አጥነት ጊዜ እየጠበቀ ነበር ፤ ስለዚህም
ሥራ የሌላቸው ሰዎች ይነስም ይብዛ በአጭር ጊዜ ውስጥ
የገኙ ቢሆንም ፤ በኋላ ነቀርሳ ሆንና አረፈው ።

የሥራ አጥነት ዋና ሥር ምክንያቶች ምንድናቸው ?
ምናልባት ሰዎች ለእለት እንጀራቸው እንኳ በመከልከላ
ቸው ምክንያት አዲሱቹ መወገዝ ይኖርባቸው ይሆን ?
ሠራተኞች ፤ ሉዳውያን * ማሺኖች የሥራ — አጥነት

* ሉዳውያን በእንግሊዝ ከ 18 11 —16 ዓ. ም. የሠራተኛ ቡድን አባላት
ሆኑ ፤ ሥራ — አጥነትን የሚፈጥሩት ማሺኖች ናቸው በማለት አዲስ
ማሺኖችን ያወድሙ ናቸው — ከተርጓሚው

ማደግ ምክንያቶች ናቸው ብለው የሚአስቡበት ጊዜ ነበር ፡
ግን ፤ እርግጥ ፤ ማሺኖች በሥራ አጥነት ውስጥ ምንም የሚ
ሰሩት ነገር የለም ። የዚህ አስተማማኝ ማስረጃው የሚ
ጠው በሶሻሊስት አገሮች ነው ። ምንም አዳዲስ ማሺና
ችን ሳያቋርጡ በሰፊው በሥራ ላይ ቢአስማሩም ፤ ሥራ
አጥነት የለባቸውም ። ወይም ደግሞ ከዚህ አንዱ እን
ከካፒታሊዝም መርገሞች) በሶሻሊዝም ውስጥ አይኖርም ፡

በሌላ በኩል ግን ፤ ለምሣሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ
ርበ የሥራ-አጦች ቁጥር በሶስትና በስድስት ሚሊዮን መ
ከል ደርሷል ። ስለዚህ ፤ ካፒታሊስት ሕብረተሰብ ሥራ
የሌለው ትልቅ የሕዝብ ክፍል አለው ፤ ተጠባባቂ የሥራ
ኃይል ተብሎ የሚጠራ ።

የሥራ-አጥነት ምክንያት ሥሩ የሚገኘው በካፒታሊ
ስት ምጣኔ — ሀብታዊ ሥርዓት ውስጥ ነው ። የቴክኖሎ
ዕድገት በአነስተኛ ጥረት ከፍተኛ እሴት እንዲፈጠር ያ
ዳል፡፡ይሁንና ካፒታሊስቱ በአጠቃላይ ዕሴትን ሳይሆን ትር
እሴትን በመፍጠር ላይ ነው ዓላማው ። አዲስ መሣሪያዎች
ሲአቀርብ ፤ ሠራተኞቹን ለመርዳት ሳይሆን ፍላጎቱ ትር
ለማግኘት ነው ። ለሠራተኞች ሥራቸውን ሊአቃልልላቸ
ይቅርና ፤ እንዲያውም አንዳንዶቹን ከሥራ አላቆ የቀሩት
የበለጠ የጉልበት ኃይል እያፈሰሱ እንዲሰሩ ያስገድ
ዋል ። ይህን ለማድረግ የሚአስችለው ፤ ምክንያቱም እዚ
የነበሩት ብዙዎቹ ሰዎች ከሥራ ውጭ ስለሆኑና የተቀጠሩ
ይበልጥ ከሥራቸው ተጣብቀው ስላሉ ነው ። የሕይወ
ማቆያቸውን የማጣት ፍራት ከተቆጣጣሪያቸው ጅራ
የበለጠ ሹል አንካሴ ይሆንባቸዋል ። ስለዚህ ፤ ካፒታሊ



ቶች የሥራ አጥነትን ማስፈራሪያ የሚጠቀሙበት በተቀጠሩት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ነው ።

በማንኛውም አቅጣጫ ትርፍ እሴትን ለመጨመር ባላቸው ምኞት ፤ ካፒታሊስቶች የሕጻን ጉልበት ብዝበዛና የመጀመሪያ ደረጃ የደህንነት ሕጎችን መጣስ ደንባቸው አድርገውታል ። የካፒታሊስት የምርት አርኪነት (ብቁነት) የሚገኘው በመጀመሪያ በዕድሜ ወያልበሰለው ሠራተኛ የሚአመራውን ሥራ (ጉልበት) በማፈግ ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ አልፈው የሄዱ ብዙ ሠራተኞች ከ፵ እና ፶፭ ዕድሜ በኋላ ከአገልግሎት ውጭ ይሆናሉ ።

የወዛደሮች የኑሮ ሁኔታ እየከፋ መሄድ ቀጥ ያለ መስመር ወይም ደግሞ ተከታታይ(የማያቋርጥ)ሂደት አይደለም። በአንድ አገር ውስጥ ባለ ልዩ ሁኔታ በመንተራስ ከፍና ዝቅ ይላል ። ሠራተኞች ለመብታቸው ለመከላከል ካፒታሊስቶችን ይዋጋሉ ። ሰላማዊ ሰልፍና አድማን የመሳሰሉ ርምጃዎች በመውሰድ ፤ ሠራተኞች የተሻለ ክፍያንና የአጭር ሰዓት ሥራን በመሳሰሉት ረገድ በመደራደር ብዙ ድሎችን አግኝተዋል ። ግን ከነዚህ አንዱም እንኳ በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ የሠራተኞችን የመበዝበዝ ዕድገት አለወጠውም ።

ምርት ሲወድቅ ፡ የካፒታሊስት ዓለም በተለይ በሠራተኞች ላይ ከፍተኛ ችግር በሚአመጣ የምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ ይንቀጠቀጣል ። እንዲህ ዓይነት ቀውስ የሚፈጠረው ምክንያቱም ካፒታሊስቶቹ በሁለት—ትርፍ ለማግኘት መስገብገብና ውድድር—መንታ ፍላጎቶች ምክንያት ፤ ለሁልጊዜም ብዙ ብዙ ! ዕቃዎች ለማምረት ስለ

ሚጉብጡ (ስለሚአጕበድዱ) ነው ። ግን የበላተኛው (የተጠቃሚው) ገቢ የሚአድገው ቀስ ብሎ ነው እናም ሁሌም ጊዜ ጠብቆ ይሆናል ። ይህም ማለት የዕቃዎች ተስማሚ (አኳያ) ተጠያቂነት ከምርት ውጤቱ በስተጀርባ ይጐተታል ፤ በዚህም ምክንያት ግዙፍ የሽቀጥ ክምር ይወዘፋል ነው ። በዚህ ወቅት መካከለኛ ካፒታሊስቶችና የእርሻ ድርጅቶች ይራቆታሉ ፤ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ፋብሪኮች ይዘጋሉ ፤ ገበሬዎች ስብርብራቸው ይወጣል ፤ ሥራ አጥነት ያብጣል (ያይላል) ፤ እና ምንዳዕ ይቆረጣል (ይቀነሳል) ።

ይህ ሁሉ በምርት መትረፍረፍ ምክንያት የመጣ ይመስለን ይሆናል ። በእርግጥ ዕቃዎቹን የሚገዛ የለም ፤ ምክንያቱም ሰዎች የሚገዙበት ገንዘብ የላቸውም ፤ ግን ስለማይፈልጓቸው አይደለም ። ስለዚህ የፍጆታ (የብሉት) ሁኔታ የሚንተራሰው አንድ ሰው ባለው የገንዘብ መጠን ላይ ነው — ግን አንድ ሰው ምን ያህል እንደተራበ አይደለም ። በዚህ ምክንያት እንዲህ ዓይነት ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ክስት እንደረሀብና ሀብት መካከልያለ ሁኔታ ይታያል ። ሱቆችና መጋዘኖች በዕቃዎች ተሞልተዋል ግን ካፒታሊስቶች በዝቅተኛ ተመን ከመሸጥ ይልቅ እነሱን ማውደም የበለጠ ትርፍ ያለው ሆኖ አግኝተውታል ። ምንም ያህል ረጅም ጊዜ ቢሆን ተመናቸውን ከፍ እንዳለ ለማቆየት ይሞክራሉ ፤ ስለዚህ ኪሣራቸውን እንደገና ሊአሟሉ ይችላሉ ።

* በ፲፱፻፴፪ ዓ ም ለምሣሌ ፡ 2,400,000 ሰዎች በካፒታሊስቶች አገሮች ውስጥ በረሃብ ምክንያት ሞተዋል ። በዚያው ዓመት በዩናይትድ ስቴትስ ካፒታሊስቶች ከአ



ንድ ሚሊዮን በላይ የባቡር ፉርጐ ሙሉ እህል አውድመዋል — ፪ ሚሊዮን ሰዎች ለአንድ ዓመት ሙሉ በበቂ ሁኔታ ሊመግብ የሚችል መጠን ያለው እህል መሆኑ ነው ። 267,000 የባቡር ፉርጐ ሙሉ ቡና 258,000 ቶን ስኳር ፤ 26,000 ቶን ሩዝ ፤ 25,000 ቶን ሥጋ ፤ እና ሌሎች የምግብ ዓይነቶችም አውድመዋል ።

ቀውሶች የካፒታሊዝምን ሙሉ ዕውነታ ይገልጻሉ ። የምርት ኃይሎችን ዕድገት ወደኋላ እንደሚጉትትና ለሰው ልጅም እንኳ በተለያዩ መንገድ ጠላፊ ወጥመድ እንደሆነ ያሳያል ። ካፒታሊዝም ወደ ሕልውናው የመጨረሻ ደረጃ በሚሄድበት በአሁኑ ወቅት ይህ በተለይ ግልጽ ነው ።

## ፫. ኢምፔሪያሊዝም

## የካፒታሊዝም የመጨረሻ ደረጃ

ባለፈው ፲፱ኛው ምዕተ — ዓመት በስፓኝ — አሜሪካን እና አንግሎቦየር (በእንግሊዝና ደች) የጦርነት መድረክ በሆኑት ፤ የመካከለኛው አሜሪካ እና ደቡብ አፍሪካ ላይ የዓለም ዝንባሌ አተኩሮባቸው ነበር ። እነኚህ ሁለት ጦርነቶች የካፒታሊዝም ከፍተኛና የመጨረሻ ደረጃ የሆነውን ኢምፔሪያሊዝም መምጣት አስታውቀዋል ።

*

« ኢምፔሪያሊዝም » የሚለው ቃል የሚአመለከተው ፤ ሌሎች አገሮችን የመጨቆንንና የመስፋፋት ፖሊሲን ብቻ አይደለም ። የካፒታሊዝም ዕድገት በቡርዧው ሕብረተሰብ የምጣኔ ሀብት ፖለቲካዊ ሥርዓት ላይ ወደ መሠረታዊ ለውጥ አምርቷል ፤ ይህም ስለካፒታ

ሊዝም የመጨረሻ ደረጃ ለመናገር መረጃዎችን ያቀር
ባል ።

* እንዲሁም ፣ ኢምፔሪያሊዝም ከካፒታሊዝም የተ
ለየ የሕብረተሰብ ሥርዓት አይደለም ። በኢምፔሪያሊ
ሊስት ዘመን የምርት መገልገያዎች የካፒታሊስት ባለበ
ትነት የቡርዧዋው ሕብረተሰብ የምጣኔ ሀብት መሠረት
ነው ፣ ምንም ዓይነት ልዩ ጸባይ ይኑረው — የግል ፣ የሕ
ብረት ወይም መንግሥታዊ ካፒታሊስት — ይህ ባለበ
ትነት ቦታ አለው ። በካፒታሊስቱ የቅጥር ጉልበት ብዝ
በዛና የትርፍ ዕሴት መፈጠር የኢምፔሪያሊስት ምጣ
ሀብት የማዕዘን ደንጋይ ሆኖ ነው የሚቀረው ።

* ኢምፔሪያሊዝም እንደካፒታሊዝም ሁሉ በነዚያው
ሕጎች ነው የሚገዛው — በትርፍ ዕሴት ሕግ ፣ በካፒታ
ሊስት ክምችት ሁለንታዊ ሕግ ፣ በነጻ ውድድር ሕግ
ወዘተ . . . ።

ስለኢምፔሪያሊዝም ብስል ያለ ትንተና የሰጠው
ሌኒን ነበር ። እንዲህ ሲል ከፋፍሎታል ። መጀመሪያ
ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ፣ ሁለተኛ የበሰበሰ ወይም ደ
መጣጭ ካፒታሊዝም ፣ ሶስተኛ ፣ አርጅቶ ያፈጀ ሊወድ
የተቃረበ ካፒታሊዝም ብሎ ። ስለኢምፔሪያሊዝም ይበ
ልጥ አጠር ያለ መግለጫ ቢጠየቅ ሞኖፖሊ ካፒታሊ
ዝም በማለት እንደሚመድበው ተናግሯል ።

ሞኖፖሊዎች በአንድ ወይም በብዙ የኢኮኖሚ ክፍ
ሎች (ሴክተሮች) የበላይ ገዥነትን የአጠቃለሉ ካፒታሊ
ስቶች ግዙፍ ድርጅት ነው ። የምርት እና የካፒታል መ
ለብ የዚሁ ሎጂካዊ ውጤቶች ናቸው ።በኢንዱስትሪያዊ ካፒ



ታሊዝም ዘመን ነጻ ውድድር ትናንሽ ድርጅቶችን በት
ላልቆች የተዋጡትን ያጠፉል ። በጣም ግዙፍ በሆኑ ድር
ጅቶች ውስጥ ምርት ይደልባል ። ከትርፍ ዕሴቱ የተወሰነ
መጠን ወደ ካፒታል ስለሚጨመር ፣ በጣም ትልቅ ይሆ
ናል ፣ እናም ይደልባል ። ከዚህም በላይ ፣ ካፒታል ማዕ
ከላዊ ይሆናል ( centralized ) ። ይህ የሚሆነው
የካፒታሊስት ድርጅቶች ሲዋሃዱ ነው — በስምምነት
ወይም በግዴታ ። በስምምነት የሚዋሃዱት በጋራ ይዞታ
ድርጅቶች ሲቋቋሙ ፣ በግዴታ ደግሞ በነጻ ውድድር ጊዜ
ትናንሽ ተቋሞች ሲዋጡ ነው ።

በተለይ በታላላቅ ካፒታሊስቶች መካከል ያለ ውድድር
አጥፊና ጠንካራ ነው ። ግን አንዳንዴ ለመስማማት የሚ
ሞክሩበት ጊዜ አለ — ከተቻለ ፣ በምርት ውጤት ላይ ፣ ተ
ምን ወዘተ . . . ። በቁጥር አነስተኛ በመሆን ግዙፍ ድር
ጅቶች ከመቶና ከዚያም በላይ በሺ ከሚቆጠሩ አነስተኛ
የንግድ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ለመፍጠር ቀላል መን
ገድ ሆኖ ያገኙታል ። ካፒታልና (ወረት) ምርት ሲደል
ቡና ማዕከላዊ ሲሆኑ ፣ ለሞኖፖሊዎች ዕድገት ይሰጣሉ ።

* ግዙፍ የሞኖፖሊ ቡድኖች በጣም ባደጉ የካፒታ
ሊስት አገሮች ብቅ ያሉት ወደዚህ ምዕተ — ዓመት መጀ
መሪያ ላይ ነው ። ከሰል( የድንጋይ) ፣ ዘይት ፣ የአረብ ብረ
ትና ሌሎችም ግዛቶች ተከሰቱ ። በዩናይትድ ስቴትስ
ውስጥ ለምሣሌ ፣ የአረብ ብረት ኢንዱስትሪ በአምስት
ሞኖፖሊዎች ቁጥጥር ሥር ነው ። ከነኝህ ትልቆቹ የአ
ረብ ድርጅትና ቤተልሄም አረብ ብረት የሚባሉት ናቸው።
ከአሜሪካ የአረብ ብረት ጠቅላላ ውጤት 80%(ሰማንያ
በመቶውን) ይይዛሉ ። የዘይት ኢንዱስትሪ በዓለም ታላላ

ቅከሚባሉት ድርጅቶች አንዱ በሆነው የስታንዳርድ ዘይት ቁጥጥር ሥር ነው ። ዱፓንት ዲኒሞርት የተባለው የኬሚካል ኢንዱስትሪን ሲቆጣጠር ፣ ጀኔራል ኤሌክትሪክ የሚባለው ደግሞ የኤለክትሪካል ኢንጅነሪንግ የበላይ ነው ። የአውቶሞቢል ኢንዱስትሪ የሚገዛው በሶስት ታላልቅ ድርጅቶች — ጀኔራል ሞተር፣ ፎርድና ክራስለር በተባሉት ነው ።

* በምዕራብ ጀርመን ፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪ የሚታዘዘው በ አይ ጂ ፋርበን ኢንዱስትሪ ወራሾች ሲሆን ፣ ኢንጂነሪንግ ደግሞ በማኒስማን እና ክሉሽነር ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ፣ አረብ ብረት የፍሌክ ፣ ቲይስንና የሌሎች ኮርፖሬሽኖች ንብረት ነው ።

* በእንግሊዝ ፣ ቪከርስ ፣ የጦር መሣሪያ አምራቾች ብዙ ኢንዱስትሪዎችን ይቆጣጠራሉ ፤ የኢምፔሪያል ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች (I. C. I.) እና ሮያል ዳች ሼል (የደች ንጉሣውያን ቤተሰብ ሼል) የኬሚካልና የዘይት ኢንዱስትሪዎችን አጠቃለዋል ።

* በፈረንሳይ ፣ አራት ሞኖፖሊ ቡድኖች የአረብ ብረትን ጠቅላላ ውጤት ሰማንያ በመቶውን በእጃቸው አድልበዋል ፤— የፔቾኔት ኢውጌን ግዙፍ ድርጅት የአልሙኒየምን ሰማንያ በመቶ ምርት ፣ የቦሳክ የጥጥ ተቋም ሰባ በመቶ የጥጥ ምርት ውጤቶችን ይቆጣጠራል ።

* ትላልቅ ሞኖፖሊዎች ፋይናንስና ንግድንም ይቆጣጠራሉ ። በዩናይትድ ስቴትስ እፍኝ ሙሉ የፋይናንስ ቡድኖች ከነዚህ ዋና ታዋቂ የሆኑት ሞርጋንስ ፣ ሮኪፌለር ፣ ዱፓንትና ሚሎን ፣ ብሔራዊ ምጣኔ—ሀብትን ይቆ



ጣጠራሉ ፣ ፖሊሲዎችንም ይወስናሉ ። ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊዎች አሉ ። እነኝህ ከተለያዩ አገሮች በተገናኙ ካፒታሊስቶች ገበያንና የጥሬ ሀብትን ምንጭ በመካከላቸው ለመከፋፈል የተመሠረቱ ድርጅቶች ናቸው ።

ምንም እንኳ በኢምፔሪያሊስት ደረጃ ነጻ ውድድር ለሞኖፖሊ. መንገድ ቢሰጥም ፣ ከዚህ በኋላ (በላይ ምንም ውድድር የለም ማለት አይደለም ። አሁንም ቢሆን ብዛት ያላቸው መካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶችና ብዙ የትናንሽ ሸቀጥ አምራቾች ገበሬዎችና የእጅ ሙያተኞች አሉ ። እርግጥ ፣ በትላልቅ ሞኖፖሊዎች ሊጠቃለሉ አይችሉም እናም ስለዚህ የፍላጎታቸው ጥገኞች ናቸው ። በዩናይትድ ስቴትስ ለምሣሌ ፣ ብዙዎች ገበሬዎች ለትላልቅ የንግድ ኩባንያዎች በጅምላ የሚሸጥ ነው የሚአመርቱት ። በተራቸው እነሱ ደግሞ የእንደገና ሽያጭ አሠራር አላቸው ። ገበሬዎች የሞኖፖሊዎች ጥገኛ ስለሆኑ እነሱ የሚወስኑትን ተመን መቀበል ይኖርባቸዋል ። ሞኖፖሊዎች በዚህ በመጠቀም የጠቅላላ (የጅምላ ሺያጭን) ተመንን ዝቅ በማድረግ የእንደገና ሽያጭን ከፍ ያደርጋሉ ። በዚህ መንገድ በሺ. የሚቆጠሩ ገበሬዎች በየዓመቱ መራቆት ሲደርስባቸው እነሱ ግን ይህ ነው የማይባል የትርፍ መረብ ይሠራሉ ።

ይህ ምሣሌ የሚአሳየው ተመኖች ምን ያህል በሞኖፖሊዎች ቁጥጥር ሥር እንደሆኑ ነው ። በኢምፔሪያሊስት ዘመን ብዙዎቹ ዕቃዎች በግብታዊ የገበያ ተመን አይሸጡም ፣ ሞኖፖሊዎች ሠራተኛውን ሕዝብ በመዝረፍ ትርፍ ለማግኘት ከፍተኛ ተመን ይወስናሉ ።

ሞኖፖሊዎች ግዙፍ ትርፍ ካፒታል ሲአከማቹ ትርፍ በሚአስገኝ ጥቅም ላይ ለማዋል ይፈልጋሉ ። እራሳቸውን በሀገራቸው ውስጥ ባለው መዋዕለ — ንዋይ ሊወስኑ አይፈልጉም ፣ ስለዚህ በጉጉት ለክንዋኔአቸው አዲስ የሥራ መስኮች ይሻሉ ። በኢንዱስትሪያዊና በንግድ ሥራ ላይ መጠኑን በመጨመር ወደ ውጭ ካፒታልን ያስወጣሉ ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ካፒታል ይበልጥ ወደ ውጭ የሚወጣው ወደቅኝ ግዛቶችና በማደግ ላይ ባሉ ፣ በምጣኔ ሀብት ወደኋላ በቀሩ አገሮች ነበር ።

መዋዕለ — ንዋዩ ከፍተኛ ትርፍ የማግኘት ተስፋ ነበረው፤ምክንያቱም እዚያ ምንዳዕ ከአውሮጳ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ በጣም ዝቅተኛ ነበርና ።

እንዲህ አይነት መዋዕለ ንዋይ ለቅኝ ገዥ ኃይሎች ከሁሉም በፊት ለሞኖፖሊዎች ከአፍሪቃ የወርቅና የአልማዝ ፣ ዘይት ከቅርብና ከመካከለኛው ምሥራቅ ፣ ጎማ ከማሊያ ፣ መዳብ እና ፤ ቆርቆሮ ፣ ቡናና ፍራፍሬ ከደቡብ አሜሪካ በማይቋረጥ ሁኔታ መፍሰስን አስገኘላቸው ። ሌኒን እንዳስቀመጠው «ለኢምፔሪያሊዝም ፋሲካ ለዘገዩት ፣ ቅኝ ግዛት ያልነበራቸው አገሮች ፣ ከጊዜ ወደጊዜ የቅኝ ግዛታዊ የመዘረፍ ዕጣ እንዲደርሳቸው ተወሰኑ ።» ብሏል ። ይህ ሁኔታ ነው ዓለምን እንደገና ለመከፋፈል የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችን ያቀጣጠለው ።

ምክንያቶችን ይበልጥ ውስብስብ ለማድረግ ፣ ካፒታሊስት አገሮች ያልተመጣጠነ ዕድገት ነው ያላቸው ። ዕድገታቸው ፣ አንዳንድ ሯጮች ወደፊት ሲፈጥኑ ፣ ሌሎች ግን ወደኋላ ሲጐተቱ የሚታይበትን የረጅም ርቀት የሩጫ



ውድድር ይመስላል ። ትናንት በወታደራዊ ኃይልና በምጣኔ ሀብት በኩል ኃይለኞች የነበሩ አገሮች ዛሬ ለተወዳዳሪዎቻቸው ቦታ መስጠት ግዴታቸው ነው ። ነገ የኢምፔሪያሊስት ኃይል ገበያዎችን፤የተፅዕኖ አካባቢዎችንና በእርሱ ረዳትነት ሥር ያሉ ግዛቶችን እንደገና በመከፋፈል በሀገር ውስጥ ጥቅሙን የማስጠበቅ ደንብ ያወጣል ። ይህ ነው በሌኒን የተቀመረው በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ያልተስተካከለ የዕድገት ሕግ ። ይህ በተባ ቅራኔ ምክንያት የጦርነት አሸታች የሆኑ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን ቡድኖች ለግጭት ወደማምጣት ላይ ያደርሣል ።

በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ነጻ ውድድር በሞኖፖሊ የበላይነት ሲተካ ፣ በካፒታሊዝም ፖሊሲ ላይ ለውጥ ይፈጥራል ። ሌኒን ብዙ ጊዜ ሲጠቁም የኢምፔሪያሊዝም ልዩ ጸባዩ (ገጹ) ከዲሞክራሲ ወደ አድሃሪነት መለወጥ ነው ብሏል ። የሠራተኞች መበዝበዝ ሲአድግ ሞኖፖሊዎች ማንኛውንም ተቃውሞ በመጨቆን ብዙ ጊዜ የበለጠ የሽብር አገዛዝን ይጠቀማሉ ። የዚህ ሽብር ፈጣሪ አምባገነንነት ፍጹም ጽንፋዊ መልኩ ፋሺዝም ነው ።

ይሁንና ፣ እንዳጋጣሚ ጠቅላላ ሞኖፖሊዎች ሙሉ ለሙሉ ኃይለኛ አይደሉም ። የሽብር ፈጣሪ ገዥ ለማቋቋም ሁልጊዜም ሊሳካላቸው አይችልም ። ጉራቸው የሠራተኛውን መደብና የሌሎችንም የሕብረተሰብ ተራማጅ ክፍሎች—የአድሃሪውን ኃይል ለመለጉም ችሎታ ያላቸውን ኃይሎች—ተቃውሞ ለመቋቋም መሯሯጥ ነው ።

## « መንግሥታዊ—ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም »

የሞኖፖሊዎችን ከካፒታሊስት መንግሥት ጋር መ
ግማት የሚጠቁመው የመጀመሪያ ምልክት የታየው በዚ
ምዕተ—ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው ። ከነዚያ ምልክቶ
በመነሳት ሌኒን ፣ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወደ መንግ
ታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መለወጡን አሳይቷል ።

ይህን ዕድገት ለመረዳት ፣ በመጀመሪያ በቡርዧዎ
መንግሥትና በሞኖፖሊዎች መካከል ያለው ግንኙነ
ምን ለውጥ እንዳካሄደ መረዳት አስፈላጊ ነው ፣ ሁለተ
ደግሞ በኢምፔሪያሊስት አገሮች የመንግሥት ሚና እ
ዴት እንደተለወጠ መመርመር ያሻል ።

የቡርዧ መንግሥት ሁልጊዜም ቢሆን የካፒታ
ስቱ መደብ ገዥነት መሣሪያ ነበር ። ሁልጊዜም ቢሆ
የጠቅላላ የካፒታሊስቱን መደብ ምኞትና ዝንባሌ ነበ
የሚገልጸው ።

በነጻ ውድድር ዘመን የገዥው መደብ የተለያዩ ክ
ሎች የሠራተኞችን አብዮታዊ ንቅናቄ ለማዳፈን ከተነ
ኃይሎች ጋር በዝባዦች ለመቀላቀል በተገደዱ ጊዜ በ
መው ብቻ የሥልጣን ውጊያ ላይ ተሰማርተዋል ። ይ
ሁኔታ ካፒታሊዝም የኢምፔሪያሊዝምን ደረጃ ሲደር
አቆመ ። ምርት እየደለበና ካፒታል (ወረት) ማዕከላ
እየሆነ ሲሄድ ፣ ትላልቅ ሞኖፖሊዎች ሌሎች የቡርዧ
ክፍሎች ለፖለቲካ ሥልጣን ትግል ለመወዳደር በማ
ችሉበት ሁኔታ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ኃይል አግኝ
ዋል ።



በኢምፔሪያሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ የቡርዧ ዲሞ
ክራሲ በጥቂት ደርዘን ትላልቅ ሞኖፖሊዎች መካከል
ለብሔራዊ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ሥልጣን የሚደረግን ኃይ
ለኛ ትግል ለመደበቅ እንደተሠራ የጪስ ደመና ይሆናል።

ሞኖፖሊዎች ይበልጥ በብሔራዊ ምጣኔ — ሀብት
ላይ መተሳሰራቸውን ባጠበቁ ቁጥር ፣ መንግሥታዊ መሸ
ከርከሪቱን ሙሉ በሙሉ የእነሱ ጥገኛ ለማድረግ እና
በሀገሪቱ ውስጥ ሊከፋፈል በማይችል ኃይል ለመጠቀም
ያላቸው ፍላጎት ይበልጥ ግልፅ ይሆናል ። በመጀመሪያ
ትላልቅ ድርጅቶች ዋናው የሚሠሩት በወኪሎቻቸው
አማካይነት ፤ ለፓርላማ አባሎችና ለመንግሥቱ ሚኒስት
ሮች ገንዘባዊ ድጋፍ በመስጠት ፣ እናም የፖለቲካ ፓርቲ
መሪዎችን ጉቦ በመስጠት ነው ። ይሁንና ፣ ጊዜ እያለፈ
ሲሄድ ፣ የሞኖፖሊ ባለቤቶች የለበሱትን ካባ ይጥሉና
ለራሳቸው ወይም ለእነሱ ታማኝ ሰዎች ቁልፍ የመንግ
ሥት ሥልጣን ለመውሰድ ሲሉ በግልጽ ይቀርባሉ ።
ይህ በተለይበቅርቡ እየተስፋፋ ሄድዋል ።

በመንግሥቱ መዋቅር ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን ከወ
ሰዱ በኋላ ፣ ሞኖፖሊዎች በዓለም አቀፍ ደረጃና በሀገር
ውስጥ ግባቸውን ለመምታት በከፍተኛ ጥረት እንዲአገ
ለግላቸው ሊአለማምዱት ይፈልጋሉ ።

ከሁሉም በፊት ለካፒታላቸው(ወረት) የማያቋርጥ
መዟዟርን ለማረጋገጥ ፣ የድሮውን ለማቆየትና አዲስ የጥሬ
ሀብት ምንጭና ገቢያ ለማግኘት ፣ ቀውስን ለማስቀረት
በመካከላቸው ግንኙነቶችን ለማስተካከል ፣ እናም በሠ
ራተኛው የሚፈጸመውን የተቃውሞ ርምጃ ለመከላከል
ይታገላሉ ።

ምንም እንኳ የካፒታሊስት መንግሥት በሠራተኛው
ሕዝብ ላይ ከተጣለው ታክስ ይህ ነው የማይባል ብዙ ገን
ዘብ ቢሰበስብም ፣ ከዚህ ውስጥ ትምህርት ፣ ጤናንና ሌሎ
ችንም ሕዝባዊ አገልግሎቶችን በገንዘብ ለመደገፍ የሚ
ጠቀመው በጣም ጥቂቱን ብቻ ነው ። ከወጭው ብዙውን
ክፍል የሚይዘው ለወታደራዊ ሁኔታዎች የሚወጣው
ነው ።

እናም ሠራተኛው ሕዝብ ነው የወታደራዊ ወጭውን
ሸክም የሚሸከመው ፣ መንግሥት ለወታደራዊ መጠገ
ኛዎች የሚከፍለው ገንዘብ ወደ ታላላቅ መሣሪያ ኮርፖ
ሬሽኖች የገንዘብ መጋዘን ይፈሳል ።

በነጻ ውድድር ዘመን የቡርዧዋው መንግሥት የግል
ድርጅቶች ነጻ እጅ እንዲኖራቸው በመፍቀድ ፣ አልፎ
አልፎ በምጣኔ — ሀብት ውስጥ ጣልቃ ይገባል ። የአ
ሁኑ ዘመን የኢምፔሪያሊስት መንግሥት ፍጹም ልዩ ነው፤
ንቃት ባለው ሁኔታ በምጣኔ ሀብት ክልል ውስጥ ጣልቃ
በመግባት በብሔራዊ ደረጃም የምጣኔ ሀብት ዕድገት
ፕላን ለማውጣት ይሻል ። ምርምርን በገንዘብ ይደግፋል፤
የብሔራዊ ገቢውን የተወሰነ ክፍል ያከፋፍላል ፣ እናም
የተወሰነ ክፍል ይወስዳል ፣ አንዳንዴ በጣም ትላልቅ
ምጣኔ-ሀብታዊ ክልሎችንም (ሴክተሮችን) ማለት ነው፤

በመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ውስጥ የመ
ንግሥት ንብረት ዕድገት አለ ፣ ይህም በሶስት ዓይነት
መንገድ የሚታየው ነው ፡— በባጀት ዕርዳታ ድርጅቶ
ችን (በተለይ የጦር መሣሪያ ፋብሪኮችን) በማቋቋም ፣
በግል ኩባንያዎች ድርሻ (አክሲዮን) በመግዛት ፣ እናም
ፋብሪካዎችን በመውረስ፣ ካስፈለገም ሙሉ ኢንዱስትሪ



ዎችን የመንግሥት በማድረግ ማለት ነው ። ብዙ ጊዜ
ከፍተኛ ማዋዕለ—ንዋይ የሚጠይቀው እንደ አቶም ኢን
ዱስትሪ ፣ ወይም ብዙ ትርፍ ሊአስገኙ የማይችሉት እንደ
ከሰል ማዕድንና የኃይል ማመንጫ የመሳሰሉት በመንግ
ሥት በመወሰዳቸው የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ንብረ
ትን ያስፋፋሉ ።

* በእንግሊዝ ለምሣሌ ፣ መንግሥት የከሰል ኃይልንና
የጋዝ ኢንዱስትሪን ይቆጣጠራል ። በመንግሥት የተያ
ዙት ድርጅቶች ከሃገሪቱ ፋብሪኮችና የቢሮ ሠራተኞች
ሃያ በመቶውን ይሆናሉ ። በፈረንሣይ ፣ ከብሔራዊው
አጠቃላይ ውጤት አሥራ አምስት በመቶውን የመንግ
ሥቱ ሴክተር (ይዘት ያጠቃልላል ። መንግሥት ሰማኒያ
በመቶውን የአውሮፕላን መገጣጠሚያ ኢንዱስትሪና ሁሉ
ንም ለማለት ባያስደፍርም የከሰልና የኃይል ኢንዱስት
ዎችን ይቆጣጠራል ። በኢጣልያ ፣ በመንግሥት የተያ
ዙት ድርጅቶች የፋብሪካና የሃገሪቱን የቢሮ ሠራተኞች
ሃያ በመቶውን ቀጥሯል ።

በመጀመሪያ አመለካከት ፣ እነኚህ ሁሉ የሕብረተ
ሰብ ዕድገትን ፍላጐት የሚስማሙ ናቸው ። እርግጥ ፣
የጊዜአዊ ምርት ሕብረተሰባዊ ጸባይ በአጣዳፊ ዕቅድ
ይፈልጋል ፣ ይህ ደግሞ የመንግሥቱን አርጊ ሚና የተ
ፅዕኖ አስከባሪነት ሳይጨመር ሊገኝ የሚችል አይደለም ።
ግን ፣ መንግሥታዊ መሽከርከሪትና ሞኖፖሊዎች እንደ
ተዋሃዱ ለመጀመሪያና እስከ መጨረሻ የመንግሥት በም
ጣኔ-ሀብታዊ ሁኔታዎች ጣልቃ ገብነት የሚአገለግለው
ለትላልቅ ድርጅቶች ዝንባሌ ነው ።

የመንግሥት ንብረት ተብለው የሚ
በመደብ ባሕሪያቸው የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ንብረቶች
ጠሩት ሁሉ በእውነቱ የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ንብረቶች
ናቸው ። ይህም የሚባልበት ምክንያት እነዚህ ንብረቶች
የሚያዝባቸውና የሚቆጣጠራቸው መንግሥት በመጀመ
የሚያዝባቸውና የሚቆጣጠራቸው መንግሥት በመጀመ
ሪያ ተቀዳሚ ታላላቅ ድርጅቶችን ስለሚንከባከብ ነው ፣

የዛሬው የካፒታሊስት መንግሥት በጉልበትና በካ
ፒታል ግንኙነት መካከል ጣልቃ ሲገባ የሚለፍፈው
የማያዳላ ዳኛና የሁሉንም ክፍሎች ጥቅም ወይም ዝንባሌ
በዕኩል ለማስጠበቅ የቆመ መሆኑን ነው ። በትክክለ
ኛው መንገድ ግን ፣ ምንም ቢሆን የመንግሥቱ ሙሉ ኃይ
ልና ሥልጣን የካፒታሊስቶችን ዝንባሌ በመከተል የሚ
ከናወን ነው ። ስለዚህ የቡርዧ መንግሥት ተመኖችእን
ዲንሩ ሲፈቀድላቸው አድማዎችን ለመከላከል ፣ ምንዳ
እንዲአሸቀለቁል ያልሆኑ ሕጎችን ያሳልፋል ።

ሌላው የመንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም መለ
የሚሆነው ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊ ማኅበሮች እንደ የ
ውሮጳውያን የምጣኔ-ሀብታዊ ማኅበረ — ሰብ የጋ
ገበያ የመሳሰሉት መከሰት ነው ።

ስለዚህ ፣ የካፒታሊዝምን ዕድሜ ለማራዘምና የ
ላልቅ ድርጅቶችን ቦታ ለማጠናከር ፣ መንግሥታዊ ሞ
ፖሊ ካፒታሊዝም የሞኖፖሊዎችን ኃይል ከመንግሥ
ኃይል ጋር ያዋህዳል ። ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወደ መ
ግሥታዊ-ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሲአድግ ፣ ከኢምፔ
ሊዝም ልዩ የሆነ ሌላ የመሸጋገሪያ ደረጃ አለ ማለት አ
ደለም ። ያው አሮጌው ካፒታሊዝም በኢምፔሪያሊዝ
ዕድገቱ ላይ ያለው ነው ።



ዓላማው በትላልቅ ሞኖፖሊዎች መካከል ውድድርን
ሥርዓት ለማስያዝ የሆነው የካፒታሊስት ዕቅድ ፣ በም
ንም መንገድ ከሶሻሊስት ምጣኔ — ሀብታዊ ዕቅድ ጋር
እኩል ሊሆን አይችልም ። በካፒታሊስት መንግሥታት
ምጣኔ — ሀብታዊ ፕሮግራሞች ለግል ኩባንያዎች አስ
ገዳጆች አይደሉም ፣ መምሪያዎችና ጥቆማዎች ናቸው ።
የግል ድርጅቶች ወይም የሞኖፖሊ ቡድኖች በመንግሥት
ውሱን የሆነ የምርት ዓላማ አይሰጣቸውም ፣ እናም እርስ
በእርሳቸው ስለሚወዳደሩ ፣ ክንዋኔአቸውን ዕቅድ ባለው
መንገድ ለማቀናጀት ወይም ተመጣጣኝ ምጣኔ-ሀብታዊ
ዕድገት ለመሥራት አይችሉም ።

ሠራተኛው መደብና የኮሚኒስት ፓርቲዎች ፣ የመ
ንግሥታዊ ሞኖፖሊን ንብረት ካፒታሊስታዊ ባሕሪ ሲአ
ጋልጡ ፣ የቁልፍ (ዋና) ኢንዱስትሪዎችን የግል ካፒታል
ባለቤትነት ለማስቀረት ይታገላሉ ። ይህ ትግል ከሁለተ
ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ባለው ዕድገት ውስጥ ፣ በእ
ንግሊዝ እና በፈረንሳይ ብዙ ኢንዱስትሪዎች ሲወረሱና
በኢጣልያ መንግሥት የኃይል ኢንዱስትሪን በ፲፱፻፷፪
ዓ. ም. ሲወስደው ፣ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ። ባሁኑ
ወቅት አብዛኞቹ የኮሚኒስትና ሠራተኛ ፓርቲዎች ፕሮ
ግራሞች የውርስን ጥያቄ ይዘዋል ። ግን ኮሚኒስቶች
እንዲያው ብቻ የኢንዱስትሪዎች በመንግሥት ከመወሰዳ
ቸው ይበልጥ የሚፈልጉት ሌላም ነገር አለ ። ብቃት ያለው
ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በመንግሥታዊ ድርጅቶች ላይ እን
ዲኖር ይገፋፋሉ ።

## ፬. የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውሶች—በካፒታሊ-ዝም ውስጥ የቅራኔዎች መትባት ።

በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል
ያለው ግጭት ከአንድ ሥልተ—ምርት ወደሌላው የሚአ
ሸጋግር የታሪካዊ ዕድገትና ለሕዝባዊ አብዮት የምጣኔ
ሀብት መሠረት ለሆነው ዋና መመንጫ ነው ። ዋናው
የንጥቡ መነሻ ፣ በሕብረተሰብ ምርት አፈጣጠርና በካ
ፒታሊስት ግላዊ ንብረት አስተባሰብ መካከል ያለው
ቅራኔ ነው ። ይህ ነው የካፒታሊስቱ ሥርዓት ዋና ቅራኔ፤
እናም ይኸውና ዛሬ ተብቶ እናየዋለን ።

ካፒታሊዝም ሲአድግ ፣ የሥራ ሕብረሰባዊ እየሆነ
የመሄድ ደረጃ የማያቋርጥ ይሆናል ። ጊዜን ጠብቆ የሚ
ሸጠው ምርታቸውና በማያቋርጥ መንገድ የጥሬ ሀብት
መፍሰስ ውስጥ የካፒታላቸውን (ወረት) መዟዟር ለማረጋ
ገጥ (ዋስትና ለመስጠት) ፣ እና ይህን ካፒታል ይበልጥ
ትርፍ ወደሚአስገኙ የምጣኔ—ሀብት ቅርንጫፎች ለማ
ሸጋገር እንዲችሉ በመቶ የሚቆጠሩ የንግድና የኢንዱስ
ስትሪ ድርጅቶችን ፣ ሆቴሎችና የመዝናኛ ቤቶችን ፣ ብዙ
ባንኮችን ፣ የማዕድኖችን ፤ የዘይት ጉድጓዶችን ግዙፍ ሞና
ፖሊዎቹ ያዋህዳሉ ፤ የምርምር ተቋሞችን በገ
ንዘብ ይረዳሉ ፣ በጋዜጦች ፤ መጽሔቶችና በማተሚያ
ቤቶች ላይ ሙሉ ቁጥጥር ይወስዳሉ ።

ካፒታሊዝም በከፍተኛ ደረጃ ጉልበትን ሲአደልብ ፣
የምርት ሂደት ሶሻላዊ ይሆናል ። ይሁንና ፣ የግላዊ መልክ
ብዝበዛ ፣ ካፒታሊስቶች የምርት መገልገያዎችንና የሥራ



ውጤቶችን እስከአዘዙባቸው ድረስ እንዳለ ይቆያል ።
ይህ የግል ባለቤትነት የምርት ዕድገትን ይጉትታል ፣
የምርት ኃይሎችንም ርምጃ ያዘገያል ።

በጣም የዳበሩ የካፒታሊስት አገሮች ምንም እንኳ
ከፍተኛ ደረጃ የምጣኔ—ሀብት ዕድገት የደረሱና ችሎታ
ያላቸው ቢሆኑም የምርታቸው ዕድገት የዝግታ
ርምጃ ነው ። እንዲያውም ርምጃ የማይታይበት ዓመትም
አለ ። የድርጅቶች የቀነሰ የአሠራር ችሎታ ፣ የኤኮኖሚ
ሥራ አጥነትና ወታደራዊነት ለዛሬው ካፒታሊዝም ልዩ
ባሕሪዎች (ገጾች) ናቸው ።

በምርት ሕብረተሰባዊ መሆንና በግላዊ ሥልት የም
ርት ማካበት መካከል ያለው ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ
በተለይ አሁን በጣም ተብቷል ።

የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች ከብዙ ጊዜ ጀ
ምሮ ከምርት ኃይሎች ጸባይ ጋር መስማማት አቁመው
ወደ ቅራኔ ገብተዋል ።

መንግሥታዊ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊ
ዝም የሚያሸጋግሩ ሁሉንም ቅድመ—ሁኔታዎች አዘጋጅ
ቷል ። ባለሙሉ ኃይል ኢንዱስትሪያዊ መሠረቱና
በተለይም በከፍተኛ ደረጃ የምርት ሕብረተሰባዊነት
ለመጠቀ የምርት ኃይሎች ከፍተኛ ዕድገት አስተማማኝ
ሂደቶች ናቸው ፤ የምጣኔ—ሀብታዊ ሥርዓተ—አልባነት
ንና ቀውሶችን ዕድሜ ያሳጥራል ፤ እናም በአጠቃላይ
በሕብረተሰቡ የገንባሌ ዕቅድ መሠረት ምጣኔ—ሀብታዊ
ዕድገትን ያረጋግጣል ። ግን ይህ እንዲሆን ለማድረግ ፣
የምርት መገልገያዎችን የግል ባለቤትነት ማስወገድ

በዝባዦችን ትርፍ እሴት የማጋበስ መብታቸውን መካድ አስፈላጊ ነው ፣—በሌላ አባባል ፣ የካፒታሊስት ሥርዓትን መጠራረግ ።

ኢምፔሪያሊዝምን አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም ብለን ስንገልፅ በሠራተኛው መደብ በሚመራው ያለሕዝቡ ትግል ፣ እራሱ በራሱ ይሞታል ለማለት አይደለም ። ሌኒን ኢምፔሪያሊዝምን ሲገልጸው አርጅቶ ያፈጀ ካፒታሊዝም በማለት ብቻ ሳይሆን የሶሻሊስት አብዮት ዋዜማም እንደሆነ ነው ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዲያው ዝም ብለው ሞኖፖሊ ካፒታሊስቶች በደምብ ይንበረከካሉ ተብሎ አይጠበቅም ። እንዲያውም ፣ ያላቸውን ምቾትና ሥርዓት ለማቆየት ማንኛውንም ዓይነት ጥረት ያካሂዳሉ፤ ግን ሊቀር የማይችለውን ሁኔታ ሊገቱ አይችሉም ፣ የካፒታሊዝም ቅራኔዎች እሚፈነዱበት ደረጃ ደርሰዋል ፣ እናም የሚጨማተርበትን ጊዜ ያቀርቡታል ።

የሠራተኛው መደብ በሞኖፖሊ ቡርዧዎች የተጠናከረበትን ብዝበዛ የመቋቋም ኃይሉን ይጨምራል ። የሠራተኞች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ኃይል እየጨመረ ይሄዳል ፣ ሠራተኛው ሕዝብ ከካፒታሊስት ጭቆና ራሱን ነጻ ለማውጣትና ሕብረተሰቡን እንደገና በሶሻሊስት መስመር ለመገንባት ይዋጋል ።

ሞኖፖሊ—ካፒታል (ወረት) የቅኝ ግዛትና የጥገኛ ሀገሮችን ሕዝቦች ባሪያ ሲአደርግ ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩትን ወደዘላለም ጥፋት ያደርሳቸዋል ። የተረገጡት ሕዝቦች አንድ አማራጭ ብቻ አላቸው — ነጻነት ማግኘት ወይም መሞት ። ስለሆነ ፣ ኢምፔሪያሊዝምን በመጻረ



እያደገ የሚሄደው የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ሞገድ ተነሣ ።

ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም የፋሺስት አምባገነናዊነትን ይደግፋል ፣ እናም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሚገደሉባቸውን ፣ በጉልበት አማካኝነት ለብዙ ምዕተ—ዓመት በሕዝቦች የተገኙት ሀብቶች የሚወድሙባቸውን ጦርነቶች ያጭራል ። ስለሆነ ፣ በየቦታው ለሰላምና ለዲሞክራሲ እያደገ የሚሄድ እንቅስቃሴ ይታያል ።

እንደ አንድ ጅረት በመሆን ፣ እነዚህ ኃያል ኃይሎች ኢምፔሪያሊዝምን ያጥረገርጋሉ ። የካፒታሊስት ሥርዓት ደረጃ እየወረደ መሄድና ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ ዘመን ወቅት መምጣት የማይቀር ነው ።

በተለያዩ አገሮች የካፒታሊዝም ዕድገት ያልተሟላ ስለሆነ ፣ ይህ ሽግግር በሁሉም አገሮች በአንድ ጊዜ ሊሆን አይችልም ። የካፒታሊዝም መጨማተርና የሶሻሊዝም መንሰራፋት ራሱን የቻለ ዘመን ሂደት ነው ። የካፒታሊዝም የአጠቃላይ ቀውሶች ዘመን የሚባል ።

## የካፒታሊዝም አጠቃላይ የቀውስ ደረጃዎች

በካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውሶች ጊዜ ፣ የተለያዩ አገሮችን በራሱ ግዛት ሥር ለማቆየት እንዳይችል ውስጣዊ ቅራኔዎቹ በጣም ከፍተኛ ይሆኑበታል ። በውስጡ የነበሩ አገሮች አንድባንድ ከካፒታሊስት ሥርዓት ፊታቸውን እያዞሩ ወደሶሻሊዝም ጉዳና ያመራሉ ። በተጨማሪም ፣ የሶሻሊስት ማኅበረ — ሰብ የመምጣት ዕውነ

ትና እያደገ የሚሄደው ኃይሉ የኢምፔሪያሊስትን ማጎ
በረ — ሰብ መበታተን እያጣደፈው ይመጣል ።

የመጀመሪያው ደረጃ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀ
ውስ የተጀመረው ከአንደኛው የዓለም ጦርነትና ከ፲፱፻
፲፯ቱ ዓ ም የሩሲያ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ጋር ነው።

የካፒታሊስት ሥርዓት ከብዙዎቹ ደካማ ጉኖቹ ባ
ንዱ በኩል ተሰባበረ ። የሠራተኞችና የገበሬዎች መንግ
ሥት የመጀመሪያዎች አሥር ዓመቶች ሕልውናው ጊዜ
ከዚህ በፊት ታይቶ ያልታወቀ የጉልበት አምራችነት
የዕድገት ደረጃ ያሳየውን የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች
ጥቅም ምን እንደሆነ አሳይቷል ።

የጥቅምት የሶሻሊስት አብዮት በዓለም የሠራተኛ
መደብ ላይና በብሔራዊ የአርነት ዕንቅስቃሴዎች ውስጥ
ከባድ ተፅዕኖ አሳድሯል ፣ እናም ከኢምፔሪያሊስት ሥር
ዓት ሲወዳደር በብዝበዛ ላይ ሳይሆን ለሁሉም አባሎች
ነጻና እኩል የሆነ ሥራ ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ ደረጃ
ያለው አዲስ ሥርዓት—ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ዕድገት
ሙሉ ኃይልና እንቅስቃሴ የሆነውን — ሰጥቷል ።

የሩሲያውያን ሶሻሊስት አብዮት ለተጨቆኑ የም
ሥራቅ አገሮች የአርነት ትግል ዕድገት ከፍተኛ አስተዋ
ፅኦ አድርጓል ። በእስያ በብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴው
ውስጥ አብዮቱ የፈጠረው ስሜታዊ ሞገድ ለሞንጎሊያ
ሕዝባዊ አብዮት ድልና ለቱርክ በከማል ለተመራው አብ
ዮት መንገዱን ጠርጎለታል ፤ በተጨማሪም በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም.
በእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ላይ ድል ለመጎናጸፍ በአፍጋኒ
ስታን የብሔራዊ አርበኞችን ኃይል ረድቷል ።



የሩሲያ ሠራተኞች ድል በእስያ አገሮች በብሔራዊ
የአርነት እንቅስቃሴ ውስጥ የጸረ — ኢምፔሪያሊስትና
የዲሞክራሲያዊ አዘንባዮችን አንድነት በመፍጠር ብቻ
ሣይሆን የረዳው ፣ በተጨማሪም በእስያ የማርክሲስት
ሌኒኒስት ሀሳቦችን አሠራጭቷል ። በሁለቱ የዓለም ጦር
ነቶች መካከል በተለያዩ የእስያ አገሮች ፣ በተለይ ቻይና ፣
ሕንድና ኢንዶኔዥያ ውስጥ ማርክሲስቶች ፣ የበለጠ የተ
ራመደውን የወዛደር ክፍል ፣ ሠራተኛ ገበሬ እና ተራማጅ
ምሁራንን በሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ በተወደዱትና በተ
ደገፉት የኮሚኒስት ፓርቲዎች ውስጥ በማሳተፍ ግባቸ
ውን መተዋል ። በዚያው ዘመን የኢንዱስትሪ አድማዎ
ችና ርምጃዎች የውጭ ጭቆናን በመጻረር በቱርክ በኢ
ራን ፣ በሲሎን ፣ በሕንድ ፣ በኰሪያና በፊሊፒን ሰፋትና
ጥልቀት ነበራቸው ።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የካፒታሊዝምን ጠቅ
ላላ ቀውስ ጥልቀት ሰጠው ፣ አባባሰውም ። የዚህን ቀውስ
ሁለተኛውን ደረጃ በታሪክ በማስመዝገብ ፣ ብዙ አገሮች
በአውሮጳና በእስያ ከካፒታሊስት ዓለም ሰብረው ወጡ ።
የኰሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክና የቬየትናም
ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መመሥረት ፣ እንዲሁም የቻ
ይና አብዮት ድል ፣ በአውሮጳና በእስያ ሶሻሊዝም ከአንድ
ሀገር ድንበር አልፎ መሠራጨቱን ፣ እና የዓለም የሶሻሊ
ስት ሥርዓት ወደሕልውና መምጣቱን አሳይቷል ። እነኛ
ዓመቶች ለሕብረተሰብ እና ብሔራዊ ነጻነታቸው የእስ
ያውያን ሕዝቦች ትግል ውስጥ መጠቅ ያለ ዕድገት አይ
ተዋል ። በሕንድ የጸረ — ቅኝ ግዛት ንቅናቄ ከዚህ በፊት
ያልታዩ ዕድል አግኝቷል ፣ የሲሎን የሠራተኛና ዲሞክ

ራሲያዊ እንቅስቃሴ ፣ ኮሚኒስት ፓርቲው በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም በተመሠረተበት ፣ ይህ ነው የማይባል ድል ተጐናጽፉል ፣ የኢንዶኒዥያ ፣ የፊሊፒን ፣ የኢንዶ ቻይና እና የማለያ የአርነት ኀይሎች ከጃፓን ወራሪዎች ጋር ባላቸው ውጊያ እንደ ብረት ተቀጥቅጠውና ጠንክረው ነበር ። በብሔራዊ የእርነት ትግል ውጤት ምክንያት በቀድሞዎቹ ቅኝ እና ግማሽ ቅኝ ግዛቶች ነጻ መንግሥታት ታዩ ።

በ፲፱፻፶ ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ሶስተኛ ደረጃውን ገባ ። በመሠረቱ ፣ ይህ ደረጃ በዓለም ጦርነት አይደለም የመጣው ። ቀድሞ ካፒታሊዝም ጠንካራ ነበር ፣ እናም የሠራተኛ ሕዝቦችን የሶሻሊስት ንቅናቄ እና በሰላም ጊዜ በባርነት ተጠምደው የነበሩትን ሕዝቦች የብሔራዊ አርነት ትግል ለመጫን ይችል ነበር ፤ የነጻነት እንቅስቃሴዎች ትግል ብዙ ድል እያገኙ ሲሄዱ ለማገድ ያልቻለው ካፒታሊስት አገሮች ኢምፔሪያሊዝም ባጫረው የዓለም ጦርነት እና ጥፋት በሚአደርሱት ግጭቶች በመድከማቸው ብቻ ነው ። የቅኝ ግዛት ሥርዓትን በኃይል በመበታተን የተካሄደውን ፣ ዛሬ እንደዚያ ለማድረግ (ንቅናቄን ለማገድ) በሰላም ጊዜ እንኳን አይቻልም።ግን ሞኖፖሊ—ካፒታል (ወረት) ያለ ውጊያ ቦታውን አይሰጥም ። ጸረ — አብዮትንና ፋሺዝምን ለመርዳት ፣ እናም የሶሻሊስትን የዕድገት ጐዳና መርጠው አዲስ ነጻ የወጡ መንግሥታትንና ሶሻሊስት አገሮችን በመጻረር የሚውጠነጠኑ ክንዋኔዎችን ለመምራት ከፍተኛ ገንዘብ ይረጫል ። ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎችንና የብሔራዊ አርነት ትግሎችን ለማፈን ጥቅም የተከፈላቸውን ወኪሎቹን እንደ አድሃሪገዥ ዎችና በጠላላ አገሮችን ፣ ለምሣሌ እንደ እሥራኤል ፣ ደቡብ ኮሪያና ታይዋን የመሳሰሉትን ይጠቀማል ። ይሁንና ፣ አድሃሪ ኀይሎች ምንም ያህል ተለዋዋጭ ድል ቢአገኙ ፣ የታሪክ ወደፊት መቀጠል ሊታጠፍ የማይችል ነው ፣ እናም ኢምፔሪያሊዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳያቋርጥ መሬት እየለቀቀ ይሄዳል ።



የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ አንዳንዴ ከሚደርሱት ምጣኔ—ሀብታዊ ቀውሶች (ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት) ጋር ሊምታታ አይገባውም ። የካፒታሊዝም ቀውስ « አጠቃላይ » ተብሎ የተገለጸበት ምክንያቱም ከካፒታሊስት ሕብረተሰብ የምጣኔ—ሀብት አድማስ ክልልም አልፎ ፖለቲካ፡ና ርዕዮተ—ዓለማዊ አድማሱንም ስለሚጨምር ነው ። በፖለቲካዊው አድማስ የሞኖፖሊ ካፒታሊስቶች ራሳቸውን በሥልጣን ለማቆየት በጦር ኃይል ዕርዳታ ላይ የበለጠ ያተኩራሉ ፤ በርዕዮተ — ዓለሙ አድማስ ግን የሕዝብ ድጋፍ የሚአጡበትን ጦርነት ነው የሚአካሂዱት ። ብዙ የአፍሪቃና የእስያ አገሮች የኢምፔሪያሊዝምን « ርዕዮተ ዓለማዊ ጠቀሜታ » በግልጽ ተቃውመው የሶሻሊስት ሕብረተሰብን መገንባት እንደግባቸው አድርገው ማወጃቸውን ማንሣቱ አስፈላጊ አይደለም ።

## <u>በእውር ጭፍን</u> <u>(ያለ ሃሳቦች)</u>

የቡርዧ ርዕዮተ — ዓለም የካፒታሊስት ሕብረሰብ ርዕዮተ ዓለም ነው ።

• የቀድሞዎቹ ቡርዣዎች ለሥልጣን በሚዋጉበት ጊዜ፣ ነጻነት ፣ ወንድማማችነትና እኩልነት በሚሉት መፈክሮች

የሕዝብን ድጋፍ አግኝተው ነበር ። አሁንም እነኚህ መፈክሮች የቡርዧዋው ሕገ መንግሥት ማስዋቢያ ናቸው ። ነገር ግን ሠራተኞች እውነተኛ ጠቃሚእቸውን አውቀዋል ። የእነሱ « ነጻነት » ማለት ሠራተኞችን ለመበዝበዝ የካፒታሊስቶችን ነጻ መሆን ፣ ፖለቲካዊ ክህደቶችን ለመፈጸም ለአድሃሪያዎች ነጻነት ፣ እናም በጋዜጦች አምድ ላይ የጦርነት መንስኤዎችን ለማማሰል ነጻነት ማለት ነው ። ሠራተኞች አንድ ዓይነት ነጻነት ብቻ ያላቸው ፤— ለካፒታሊስት ጌቶቻቸው የመሥራት «ነጻነት» በኮሚኒስቶች አባባል ፣ ከብረት አጥር በስተጀርባ የመኖር « ነጻነት » ተረጋግጦላቸዋል ፤ ፖሊሶች ግን የሰላም ደጋፊዎችን በዱላዎቻቸው የመቀጥቀጥ ነጻነት ተሰጥቷቸዋል ።

* እርግጥ ፣ ቀደም ብሎ ቡርዧዎች ለነጻነትና ለእኩልነት ጥሪ አድርገዋል ፤— ካፒታሊስቶቹ ነጻነትን የፈለጉት ለግል ድርጅት ሲሆን የሕብረተሰብን እኩልነት ደግሞ የመሳፍንታዊ አገዛዝን ከደረቡ በኋላ ብቻ የፖለቲካ የበላይነት ለማግኘት ነው ። እንዳንዱ ዓላማቸው አድርገው ወንድማማችነትን አወጁ ፣ ምክንያቱም ያለ ሠራተኛው ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ ሊአሸንፉና ሥልጣን በእጃቸው ሊአስቀሩ ስለማይችሉ ነበር ።

* ይሁንና ፣ ለበዝባዡ ነጻነት ማለት ምንም አይደለም ፣ ግን ለተበዝባዡ ባርነት ነው ። የቡርዧ ዲሞክራሲ ምዕድቅና የይስሙላ መብቶችን ለሁሉም በማስፋፋት የተሞሉ ናቸው ፤ ለሁሉም ለሚጠቀሙበትና ለማይጠቀሙበትም ሰዎች ጭምር ።



* እም ፣ ሠራተኛው ራሱን ነጻ አድርጐ እንዲወስድ መብት አለው ፣ ግን ይህን መብቱን በተግባር ለማዋል ቢፈልግና ብዝበዛን በመቃወም ርምጃ ቢወስድ የምርት ቀጣሪው ይባረራል ፤— መብቱን በሁሉም ዘንድ ለይስሙላ ይደሰቱበታል ።

* ከሥራ ከወጣም በኋላ እንኳ ፡ ሠራተኛው ራሱን ከአንድ ባለብዙ ሚሊዮን ባለጸጋ እኩል የመቁጠር ሙሉ መብት አለው ። ግን ባለጸጋው እራሱን በሀገሪቱ ሕጋዊ አካሎች ባንዱ ተመዝግቦ ቢአገኘው ፣ ሠራተኛው ፣ በወንድማማችነት አባባል ፣ ከምርጫ ስብሰባዎች በፊት ፣ እጁን ለመነቅነቅ እርግጠኛ ከፍተኛ መብት አለው ። ግን ከመመረጥ አያስቀረውም ፤ ነፃነቱ የይስሙላ ነውና — ከተርጓሚው

የዘመናችን ቡርዧዎች ፣ ካፒታሊስቶች ፣ በሰንደቃቸው ላይ ያስተጋቡአቸው የነበሩትን አሳቦች ሙሉ በሙሉ አጥፍተዋቸዋል ወይም ከእግር ሥር አውለዋቸዋል ። በደንብ የተሟሉት ትላልቅ የፕሮፓጋንዳ ተቋሞችና ማዕከሎች ምንም እንኳ አዲስ « ሀሳቦች» ለመፈልሰፍ እየሞከሩ ቢሆንም ከነኛ ሀሳቦች ጥረት ምንም አይገኝም ። በዘመናችን የካፒታሊስቶች « ነጻ ዓለም » ፕሮፓጋንዲስቶች ፣ በተበዝባዦች ርዕዮተ — ዓለም የዲሞክራሲን መርህ በግብር ባዋሉትና « ለነጻነት » ፣«ለእኩልነት » «ለወንድማማችነት» ተገቢ ትርጉማቸውን ባስገኙት የሶሻሊስት አገሮች ሁለ—ገብ ድል ምክንያት በዝባዦችን ስለተቋቋመ ተግባራቸው ተወናብደባቸዋል ። በዚህ ምክንያት ነው ዘመናዊ ቡርዧ በሙሉ ኃይሉ ኮሚኒዝምን የሚአጠቃው ። ጸረ—ኮሚኒዝም በርዕዮተ—ዓለም

ክልል የካፒታሊዝምን አዳጊ ቀውስ በግልፅ የሚጠቁም
ነው ። ሶሻሊስት አገሮችን በመጸረር ከታለመ የማጥቃት
ዘመቻ ሌላ ፣ ኢምፔሪያሊስቶች ከዚያም ዘለው በሀገራ
ቸው ውስጥ ያሉ ኮሚኒስት ፓርቲዎችን እያጠቁ ናቸው።
የኮሚኒስት ፓርቲዎችና አባሎቻቸው ከመብት ሁሉ የታ
ገዱ ስለሆነ በብዙ ሀገሮች ፓርቲዎቹ ሕገወጥ ሆነዋል ።

አንዳንድ ካፒታላዊ የሆኑ የእሲያ አገሮች ቡርዧ
መንግሥታት የኮሚኒስት ፓርቲዎችን ከንዋኔዎች መገ
ደብ ወይም ከዚያም አልፎ ፓርቲዎቹን ማገድ የሕብረ
ተሰብን ዕኩልነትና የብዝበዛን መወገድ ሀሳቦችን በመ
ጻረር በቡርዧ ርዕዮተ — ዓለም አማኝነት የሚካሄደውን
ሊታረቅ የማይችል ትግል ነው የሚአንጸባርቀው ። ከነዚህ
መንግሥታት አንዳንዱ የመንግሥታቸውን ፖሊሲ ጸረ
ኮሚኒስት አድርገዋል ። በግልፅ ፣ እንዲህ ዓይነት ርም
ጃዎች ኮሚኒስቶች ላይ ሽብር መፍጠር የመሳሰሉት ከነ
ዥው ክፍል ጥንካሬ ይልቅ የፖለቲካና የርዕዮተ — ዓለም
ድክመቱን ነው የሚአመለክተው ።

የቡርዧ ርዕዮተ — ዓለም ቀውስ በተጨማሪ የግ
ከሰተው በባሕል ማሽቆልቆል ነው ። « የግለሰብ ነጻነት »
እንደ መንፈሳዊ አስተሳሰብ ሆኖ በቡርዧ ፕሮፓጋንዳ
ይስተጋባል ። እስከዚህ ድረስ ፣ የቡርዧ ርዕዮተ — ዓለም
እስከተቻለው መጠን የግለሰብ አቋም የሚቀረጸው በሕ
ልውናው ፣ በሕብረተሰብ አካባቢው ፣ ወይም በዕውነታ
ላይ ባለው ሂሣዊ አመለካከቱ ሁኔታዎች ሳይሆን ፣ ግ
በሀሳባዊ ስሜቶች ፣ በአእምሮአዊ ፣ በንቃት ጥገኛ ደመ
ነፍሱ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ይፈልጋል ።



ስሜትን ከምክንያት እና ግለሰቡን ከሕብረተሰቡ
በማወዳደር ፣ ቡርዧዋው ከሚአውጃቸው አስተሳሰቦች
ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆኑ ግቦችን ለማግኘት ይጥራል።
ሕዝብን ለመከፋፈል ያልማል ፣ በመካከላቸው የሕይወት
አስፈላጊ ልውውጦችን እርስ በእርስ መረዳዳት ፣ መከባ
በርና ሕብረት ላይ የተመሠረቱትን ማለት ነው ያግዳል ፣
ከሕዝብ የተገኙ ሀሳቦችን በማጥፋት እና የሕብረተሰቡን
እያንዳንዱን አባል በባለ ሥልጣኖች የሚነገረውን ፕሮ
ፓጋንዳ ብቻ እንዲሰማ ያስገድዳል ።

የመጻሕፍት መሸጫዎች ፣ ቲያትር ፣ ሲኒማና ቴሌ
ቪዥንን ጭካኔን ፣ ኃይልንና ጋጠወጥነትን ፣ በማድነቅ
እና መሠረታዊ ደመ — ነፍስነትን በማጉላት በዝቅተኛ
ደረጃ ምርቶች ይጥለቀለቃሉ ። በቅብ በኩል ስሜት የማ
ይሰጡ የመስመሮች ጥርቅምና የሰውን አእምሮ ምስጢር
(ታምር) ድብቅ ለማድረግ ቀለሙ ወይም ቅቡ ይህ ነው
የማይባል ንድፍ መሥራት የጊዜው ፋሽን ሆኗል ። በሙ
ዚቃ ፣ ጣፋጭ ሙዚቃዎችና ዜማዎች በጭርቅርቃቸው
በወጡ የሆያሆዬ ዘፈኖች ተተክተዋል ። በጥርብ (የድን
ጋይ ፣ የእንጨት) ፣ ያልተመጣጠኑ ፣ ለዐይን የሚአስለቹ
ስሜት የሚፈጥሩ ቅጥ ያጡ ቅርጾች መድረኩን አጣበ
ውታል ።

ድርሰት ፣ ግጥም ፣ ሙዚቃ ፣ ቅብ እና ድራማ
ሁሉም ለአንድ ግብ ያገለግላሉ ፤— ሰዎች እንዴት እን
ደሚአስቡ ለማስረሣት ፣ አስተሳሰብን « በስሜቶች » እና
ቃላትን (ነጥቦችን) « በማኅበሮች » ለመተካት — እውነ
ተኛ ኑሮን በማይለወጡ ሀሳቦች ለመለወጥ (በሽክላ ተቀ
ድቶ የተቀመጠ ለማድረግ ) ነው ሥራቸው ።

የሞኖፖሊ ቡርዧዎችና መንግሥታቸው ጠንካራ የፕሮፓጋንዳ ዘዴን የዜና ማሠራጫዎችን — ሬዲዮ ፣ ሲኒማ ፣ ቴሌቪዥን ጋዜጣና መጽሔቶችን — ለዓላማቸው ይጠቀሙባቸዋል ። ሶሻሊዝምን ለማጥላላትና ፣ የዛሬውን የካፒታሊስት ሕብረተሰብ ልዩ የሆነ የሠራተኞች ገነት ፤ የነጻነት እና የብልፅግና ዓለም አስመስሎ ለማቅረብ ከመስመራቸው ይወጣሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም በአዳጊ አገሮች ውስጥ የርዕዮተ ዓለም መስፋፋት ለማግኘት ሲል ብዙ መንገዶችን በንቃት ይከታተላል ። በእነዚህ አገሮች ውስጥ የመጻሕፍት ኪዎስኮች በምዕራብና በምዕራባውያን ታምራዊና ወንጀለኛ ታሪኮች የተጥለቀለቁ ናቸው ፣ በማያቋርጥ ሁኔታም በሲኒማ ሠሌዳዎች ላይ ይለጠፋሉ ። የሀገር ውስጥ ስቱዲዮችንና ማተሚያ ቤቶችን በመጨቆን ጠንከር ባለ መንገድ የብሔራዊ ድርሰቶችና ኪነቶችን ዕድገት በእነዚህ አገሮች ውስጥ መገታት ብቻ ሳይሆን ፣ የሀገር ውስጥ ጸሐፊዎችንና የኪነት ሰዎችን ብሔራዊ አባልነታቸውን ከምዕራብ ለሚመጡት ፋሺኖችና በእነዚህ ፋሺኖች ሠሪነት የአገር ውስጥ ገበያ ጥየቃ ራሳቸውን መስዋዕት እንዲአደርጉ ያስገድዳቸዋል ። እላይ ከተጠቀሱት « የኪነት ሥራ » ጋር ኢምፔሪያሊዝም ለአዳጊ አገሮች የኃይል ከኔ በላይነትንና የግለሰብ ተዋጊነትን ፤ የወጣቶች ሥራ ጥላቻን ፣ አጉራ ዘለልነትን በወጣቶች መሐል እንዲሠራጭ ያቀርብላቸዋል ።

ሰራተኛውን ሕዝብ የሕይወት ዋናው ሀሳብ ገንዘብ ማጠራቀምና ራስን ለድሎት ማዋል ነው በሚል ዓላማ በሚአግባቡ ፣ በኑሮ ጥሩ ነገሮች ላይ ማመን የመ



ሳሰሉት በጥንቃቄ በሰዎች ውስጥ ሥር እንዲሰዱ ተደርገዋል ።

የኢምፔሪያሊስት ፕሮፓጋንዳዎች በዩናይትድ ስቴትስ ፤ እንግሊዝ እና በተለያዩ የአደጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያለውን የኑሮ ደረጃ በተለይ አንድ መልኩን ብቻ በማቅረብ ወይም በማሳየት በኩል ንቁ ናቸው ።

• በእነዚህ አገሮች ውስጥ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች በከፍተኛ ግዥ ወይም የቀስ በቀስ ፕላን መሠረት መኪና ወይም ቤት እንዲኖራቸው መቻላቸው ከፍተኛ ጩዋታ ተሰርቷል ። በዚህ ሥርዓት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ነገሮችን በማግኘት ፣ ሰራተኛው ለብዙ ዓመታት ዕዳ ይገፈግፋል ። ለተጠቃሚው «ከፍተኛ ግዥ» ምቹና ጠቃሚ ሆኖ ይገኝ ይሆናል ። ይሁንና ፣ ካፒታሊስቱ ይህን ዘዴ የሚጠቀምበት ለተጠቃሚዎቹ እርዳታ ለመስጠት ተመኝቶ ሳይሆን ፣— የገበያ መጥበብና የዕቃዎች ጠያቂ ማጣት እንዲህ እንዲአደርግ ስለሚአስገድደው ነው ። ከፍተኛ ግዥ ለሁሉም የሚሰጥ አይደለም ። ይህም ዋስትናው ጥብቅ በሆነ መንገድ ነው ፣ አንድ ሰው የሚቀጥለውን ክፍያ ሳይከፍል ቢቀር ፣ ዕቃውን ያጣል እና ምንም ይቅርታ አይደረግለትም — ከሥራ የመውጣትም እንኳ ቢሆን ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ከሠራተኞች የተወሰኑቱ ከሌሎቹ ሲነጻጸር ከፍተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው ከፍተኛ ድሎት እንዳላቸው እውነት ነው ። ግን ለመኖሪያ ከሚአገኙት ሌላ ፣ የካፒታሊስት አገሮች ፣ ይበልጥ የተራመዱት እንኳ ፣ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሚሊዮን

የሚቆጠሩ ሥራ አጦች አሏቸው ። ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ሠራተኞች ጐን ልምድ የሌላቸው ሠራተኞች ፣ የእርሻ ተቀጣሪዎች አሉ ፣ እና ይህ በግልፅ ሁኔታውን ምን እንደሆነ ያሳያል ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለአንድ ዓይነት ሥራ ከነጭ ሠራተኞች ያነሰ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ የሚከፈላቸው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ጥቁሮች ሜክሲኮአውያንና ፖርቶሪካውያን ሰራተኞች አሉ ። አሜሪካውያን ባለሥልጣኖች የፎርድ አውቶ—ሥራ ተቀጣሪዎችን ምቾት ያላቸው ቤቶች ለቱሪስቶች ለማሳየት በጣም ይሾራሉ ። ግን ወደ ሐርሊም ኒውዮርክ ውስጥ ብዙ ጥቁር አሜሪካውያን የአይጥ ትርምስምስ በበዛባቸው ጥቅጥቅና ሽርን ቁሉ ቤቶች ውስጥ በድህነት ጭንቀት የሚኖሩበትን ለጐብኝዎች ለማሣየት አይፈልጉም ።

የቡርዧን ባሕል ማሽቆልቆል ስናነሳ ፡ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ለጥሩ ነገሮችና ለፍትህ በታማኝነት አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልጉ ትሁት አርቲስቶች እንዳሉ መርሳት የለብንም ። ነጥቡ ፣ ሥራቸው ሙሉ በሙሉ የቡርዧ ባሕል ተብሎ ሊቆጠር እንደማይገባ ነው ። ኑሮ ራሱ የካፒታሊዝምን መጥፎ ገጾች እንዲአጋልጡና ይህ የአረጀና የአፈጀ ሥርዓት ብሔሮችን የሚጉትትበትን ሰንሰለት ሰብሮ ለመውጣት የሚአስችል መንገድ እንዲፈልጉ ያስገድዳቸዋል ። በባሕል አካባቢ ዓይነተኛ የሆኑ ሰዎች የኮሚኒስት ሀሳቦች ታላቅ እንደሆኑ መገንዘባቸው ያለ ነገር ነው ። ይህም ሮማን ሮላንድን ፣ ቴዎድሮስ ድሬይሰርን ፣ ቶማስ ማንን ፣ ሂንሪክ ማንን ፣ ፍሬድሪክ ጁሊየት ኩሬይን ፣ ጳውሎስ ላንጊቪን ፣ ጆርጅ በርናርድ ሾውን ፣ ፓብሎ ኔሩዳን ፣ እና ኒኮላስ ጊዮሉንን



የመሳሰሉትን ይይዛል ። ተራማጅ ምሁራኑ የካፒሊታሊስት ዓለምን ጥሰው ጥረታቸውን ለኮሚኒዝም ድል ሥራ መስዋዕት አድርገዋል ።

የካፒታሊዝምን ነዋሪ ጸባዮች የሚደብቅ የፕሮፓጋንዳ ስብከት አይገኝም ፤ በብዝበዛ ላይ የአለንና የነበረ ሥርዓትን ፣ በውስጡ ብሔሮች የሚጨቆኑበት ሥርዓትን ፣ እኩልነት የሌለበት ሥርዓትን ማለት ነው ። ታሪክ ኢምፔሪያሊዝምን ቀድሞ አድርጐ ነው ያወገዘው ። ተወግዟል ፣ ስለሆነም—የሕብረተሰብን ዕድገት የሚገዙት ነባራዊ ሕጐች በዚህ ምዕተ — ዓመት አጀንዳ ላይ ወደ ሶሻሊዝም የአብዮታዊ ሽግግር ዘመንን አስቀምጠዋል ።

## ምዕራፍ ፫

## ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር

በሩሲያ የ፲፱፻፲፯ ዓ ም ታላቁ የጥቅምት አብዮት ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም አብዮታዊ የሽግግር ዘመንን በመላው ዓለም ከፍቷል ። ይህ ሽግግር የሚከናወነው መራራ በሆነ የመደብ ትግል ነው ። በዓለም መድረክ ላይ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች መካከል ፣ በተራማጅና በአድሃሪ ኃይሎች መካከል የመፋጠጫ ጊዜ ነው ።

አብዮታዊ ኃይሎች ምንም ያህል ችግርን መወጣት ይኑርባቸው ፣ አዳዲስ ደረጃዎችን እየወጡና በማንኛውም አቅጣጫ በአድሃሪ ኃይሎች ላይ ግፊታቸውን እያሳረፉ በቆራጥነት ወደፊት ይጓዛሉ ። የዓለም ዕድገቶች የማርክሲስት—ሌኒኒስት ሀሳቦችን ትክክለኛነት የሚአረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች አበርክተዋል ፤ በዛሬው ጊዜ በጣም

ኃይለኛ ንቅናቄዎች መሪ ስለሆነው የኮሚኒስት ንቅናቄ
ማለት ነው ።

የአብዮታዊው የማርክሲስት — ሌኒኒስት ትምህ
ርት መንሰራፋት በዛሬው ዘመን ባሉት ሶስት ዋና አብ
ዮታዊ ኃይሎች ውስጥ ጠንከር ያለ ማብራሪያ ያስፈልገ
ዋል — በዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ፣ በሠራተኛው መደብ
እንቅስቃሴ እና በብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴ ውስጥ
ማለት ነው ።

### ፩. የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት

ከ፪ተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ የአውሮጳና
የእስያ አገሮች የሶሻሊስት አብዮት ድል ማድረግ ለዚህ
ምዕተ — ዓመት ከጥቅምቱ ፲፱፻፲፯ቱ ዓ. ም. አብዮት
አስከትሎ ፪ተኛው ውጋጋን ነበር ። ሶሻሊዝም ዓለማዊ
ሥርዓት ሆነ ። የዕድገት ታሪኩ ማለትም የሌኒን ትምህ
ርት በሁሉም አገሮች ተቀባይነት አገኘ አለውም። ምክን
ያቱም ለሁሉም ብሔሮች ሶሻሊዝም የሚገነባበትን መን
ገድ ይጠቁማል ፣ ያሳያል ።

### የአጠቃላይ ሕጐች ሁለንታዊነትና የቅርጾች መለያየት

በካፒታሊዝም ውስጥ አገሮች በተመጣጠነ መልክ
ስለማያድጉ ፤ ወደሶሻሊስት አብዮትም የሚቀርቡት በዕ
ድገታቸው የተለያዩ ደረጃ ነው ። አንዳንዶቹ በምጣኔ
ሀብት ወደፊት የመጠቁ ሲሆኑ ፣ ሌሎች ደግሞ ኋላ—ቀር
ናቸው ። አንዳንዶቹ ነጻ ናቸው፣ለብዙ ዓመታትም በዚህ
መልክ ኖረዋል ፣ ሌሎቹ በቅርብ ነጻ የወጡ ሆነው ፣ እስ



ከቅርብ ጊዜ ድረስ ቅኝ ወይም ግማሽ ቅኝ ግዛቶች ነበሩ ።
ቸው ፡— በአንዳንዶቹ ብዙው ሠራተኛ ገበሬ ነው ፣ በሌ
ሎቹ ግን አብዛኛውን ክፍል የሚይዘው የኢንዱስትሪ
ሠራተኛው ነው ። አንዳንዶቹ የራሳቸው ብሔር ምሁራን
ሲኖራቸው ሌሎቹ ግን ምንም የላቸውም ። በእነዚህ አገ
ሮች ውስጥ የቡርዧ ይዞታ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ
በሚወስነውም ላይ ይለያያሉ ፡— በካፒታሊስት ግንኙ
ነቶች የዕድገት ደረጃና በውስጣቸው የመልከኛው ቅሬታ
ሕልውና ስፋት ላይ ያለውን ማለት ነው ። የታሪካዊ ዕድ
ገት ፣ የብሔራዊ ጸባይና ለነጻነት ያለው እምነት ልዩነቶ
ችና አብዮታዊ ትግልም ሊጠኑ የሚገባቸው ናቸው ።
ውጫዊ ምክንያቶች ፡— በዓለም የኃይሎች ዝምድና
ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ፣ በአንድ ሀገር ውስጥ የአብዮታዊ
ዕድገት ላይ ጥልቀት ያለው ተፅዕኖ ያሳድራሉ ።

በመሠረቱ ፣ ሶሻሊዝምን ለመገንባት መነሻ ሁኔ
ታዎች የተለያዩ ስለሚሆኑ ፣ የሶሻሊስቱ ሽግግር ቅር
ጾች ፣ ዘዴዎችና ርምጃዎች ተመሳሳይ ሊሆኑ አይችሉም ፤
መሆንም የለባቸውም ። ስለዚህ ድል አድራጊው ሠራተኛ
መደብና ፓርቲው ፣ የማርክሲዝም — ሌኒኒዝም
አጠቃላይ መርሆዎችን (ብሂል) ከሀገራቸው ልዩ ሁኔታ
ጋር ማስማማት አለባቸው ። እኛም ከፍተኛ ድል ለማግ
ኘት እና በአነስተኛ ጥረት ለመጠቀም እና ግባቸውን ለመ
ምታት የማአበቃቸውን አዲስ ሕብረተሰብ ለመገንባት
ዘዴዎችንና መንገዶችን መፈለግ ይኖርባቸዋል ። አብዮ
ታውያን ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ ወንድማማች የሆኑ
አገሮች ሰፊ ገጠመኝ በቁጥጥራቸው ሥር ነው ፣ ግን

ዝምብለው ብቻ ያንን አይገለብጡም ። ለአንድ ሀገር
ተስማሚ የሆነው ለሌላው አገር ተፈላጊውን ውጤት እያ
ስገኘ ይሆናል ። ስለዚህ ፣ ዋናኑቱ ፣ የሌሎችን ገጠመኝ
በመምረጥና በመፍጠር ጸባይ ላይ ፣ የሀገሪቱን ልዩ ገጾች
(ባሕሪዎች) እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ቦታ መገን
ዘብ አስፈላጊ መሆኑ ነው ።

ሌኒን ፣ ታሪክ ለሶሻሊዝም ሽግግር በጣም ብዙ የተ
ለያዩ ቅርጾችን መምጣት ቦታ እንደሚሰጣቸው የተረጋ
ገጠ ነው ብሏል ። ይህን ቅድመ — ሁኔታ የተናገረው ሶሻ
ሊዝም የአንድን አገር ድንበር አልፎ ከመሄዱ ከረጅም
ጊዜ በፊት ነው ፣ እናም ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠ ከሁለ
ተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሶሻሊዝም ዓለማዊ ሥርዓት
በሆነበት ጊዜ ነው ። የሶሻሊዝም አብዮት ግቡን ከመታ
ባቸው አገሮች መካከል በኢንዱስትሪ የገፉ መንግሥታት
በእርሻ ኢኮኖሚ ላይ ያሉ ፣ እና የቀድሞ ቅኞችና ግማሽ
ቅኝ ግዛቶች አሉባቸው ። ለዚህ ነው ሶሻሊዝምን ለመገን
ባት የተለያዩ ቅርፅና ዘዴ ይኖራል የምንለው ።

* በአብዛኞቹ በእነዚህ አገሮች አብዮቱ ድል ያገኘው ፣
በሰራተኛው መደብና በግምባር ቀደም ተዋጊው የኮሚኒ
ስት ፓርቲ መሪነት ፣ የገበሬዎች ፣ የከተማ ንዑስ ከበር
ቴዎች ፣ የምሁራንና ከመካከለኛው የብሔራዊ ቡርዧዋው
መደብ የአርበኝነት ጸባይ ያላቸው ሰዎች ሕዝባዊ ዲሞክ
ራሲያዊ የግንባር አንድነት ተፈጥሮ ፣ ኃያል የሆነ ጸረ
ፋሺስት እንቅስቃሴ ከፍተኛውን ደረጃ በደረሰበት ጊዜ
ነው ። ወደሶሻሊዝም ለመሸጋገር ይህ ዓይነተኛ ተፅዕኖ
ነበረው ።



* በዚህ ምክንያት ፣ በብዙ አገሮች የሠራተኛው መ
ደብ በሰላማዊ መንገድ ያለ ትጥቅ ትግል ወይም ያለ ሕዝ
ባዊ ጦርነት ሥልጣን መውሰድ ችሎ ነበር ። በቼኮዝሎ
ቫኪያ በየካቲት ፲፱፻፵፰ ዓ ም በፕራግ ውስጥ ሰፊ የሠ
ራተኛው መደብ ሰላማዊ ሰልፍ ፣ የአገሪቱን ሕዝቦች አብ
ዮታዊ ፍላጎት መግለፅና ፣ የአድሃሪ ኃይሎችን ወደኋላ
እንዲአፈገፍገ የማስገደዱ ሁኔታ ይህ እላይ ባየነው ምክ
ንያት ነው ። ያ በኮሚዩኒስት የሚመራ መንግሥትን ሥል
ጣን ላይ አወጣ ።

* በእርግጥም ፡ የሕዝብን አገዛዝ መጠናከር ወደኋላ
ለመጐተት በሞከሩ ጸረ — አብዮተኞች ላይ የሶሻሊስት
ለውጦች ጠንካራ ትግል አካሂደዋል ። ግን ይህ ትግል
ወደ ሕዝባዊ ጦርነት አላመራም ፣ ምክንያቱም የሶቪዬት
ሕብረት የወጣት ሶሻሊስት መንግሥታትን የኢምፔሪያ
ሊስት ጥቃት ተከላክላ ስለነበር ነው ። በእነዚህ አገሮች
ውስጥ ትላልቅ ቡርዧዎች ያለውጭ ግልጽ ድጋፍ የሠ
ራተኛ ሕዝቦችን አገዛዝ ለመዋጋት ብቁ ጥንካሬ አልነበ
ራቸውም ።

* ስለዚህ ፣ ለሶሻሊስት ለውጦች በተግባር መዋልና
መከወን የተለያዩ ቅርፅና ጊዜ እንዳለ የሚአሳዩ ልዩ ባሕ
ሪዎች ነበሩ ። የተደረቡት በዝባዥ መደቦች አባላት በከ
ፊል ከፖለቲካ መብታቸው ሲገለሉ ፣ በአንዳንድ አገሮች
ደግሞ እንዲያውም ምንም አልተገለሉም ። የቡርዧዋው
መንግሥት መሽከርከሪት ቀስ በቀስ ተበታተነ — በአንድ
ጡጫ ግን እፈር ዲቤ አልበላም ።

* የድሮው መንግሥት ብዙ ተቋሞችና መሠረቶች
በፍጹም አልጠፉም ። ተሸጋገሩና አዲስ የመደብ ይዘት

ተሰጥቷቸው የእዲሱ ሕዝባዊ ዲሞክራሲ መንግሥት አካል
ሆኑ ። በብሔራዊ ምጣኔ — ሀብት ውስጥ ከአርጌው አገ
ዛዝ ውስጥ ልምድ ያላቸው ግለሰቦች በሰፊው ተቀጥረው
ስለነበር ፣ ዋናው የምጣኔ ሀብት መስባበር ተወግዶ ነበር።
በብዙ የሶሻሊስት አገሮች በኮሚኒስት የተመሩ መንግሥ
ታት የገበሬዎችን ፣ የምሁራንን ወዘተ . . . ክፍሎች የሚ
ወክሉ ፓርቲዎችንም በውስጣቸው ይዘው ነበር ። ትላ
ልቅ መሬት የያዙ ኩዳዶች ሲወገዱ ፣ በመጀመሪያ ለገበ
ሬዎች የመሬት በግል መያዝ ተጠበቀ ። መሬት ወደ
ሕዝብ ንብረትነት የተዛወረው ቀስ በቀስ ሆኖ ፣ ገበሬዎች
የሕብረት ሥራ ሲአቋቁሙ ነው ። በብዙ ሀገሮች ካፒታ
ሊስቶች ለተወሰደባቸው የምርት መገልገያ ካሣ ተከፍ
ሎአቸው ነበር ። ማርክስ በአንዳንድ ሁኔታዎች ካፒታ
ሊስቶችን ማምረቻዎቻቸውን እየገዙ ማባረር ለሠራተ
ኛው መደብ ጠቃሚ የሚሆንበትንም መንገድ በተመለ
ከተ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ነገር በልዩ መንገድ ጠቁሞ
ነበር ።

በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችና ጥገኛ ሀገሮች ውስጥ አብ
ዮቱ ልዩ ቅርፅ ነው የያዘው ። የሶሻሊስት አብዮቶች በቻ
ይና ፣ በኮሪያና በቬየትናም ውስጥ የነጻነት ሕዝባዊ ጦርነ
ቶችን ወልደዋል ። የትጥቅ ትግል በኪዩባ ፣ የዩናይትድ
ስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም ግማሽ ቅኝ በነበረችው ፣ የተ
ጀመረው ኋላም የግራናን የሽምቅ ውጊያ ባስከተለው ፣
በፊደል ካስትሮ በሚመራ ጀግና አብዮታውያን ቡድኖች
በምንካዳ ጦር ሰፈር ውስጥ በተካሄደው ቁራጥ አመፅ ነው።
ምስቅልቅሉ የወጣው አገዛዝ በገበሬዎችና ሠራተኞች
በተደገፈው የአርበኞች ጡጫ ስብብሩ ወጣ ።



ይሁንና ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሀገር ወይም የአ
ገሮች ቡድን ወደ ሶሻሊዝም የሚሄደው በራሱ መንገድ
ነው ፣ የራሱ የሆነ « ብሔራዊ » ሶሻሊዝም ዓይነት
ይገነባል ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል ። ሩሲያዊ ወይም
ቻይናዊ ፣ ጀርመናዊ ወይም ፖላንዳዊ ዓይነት ሶሻሊዝም
የለም ። በዋና ባሕሪው ሶሻሊዝም የሚገልጸው የሕብረ
ተሰብ ዕድገትን ነባራዊ ፍላጐቶች እስከሆነ ድረስ ፣
እነዚህ ባሕሪዎች ለሁሉም አገሮችና ሕዝቦች አንድ
ናቸው ።

በዚህም ምክንያት የሶሻሊስት ሽግግሮች ፣ በቅርፅና
በዘዴ ካላቸው መለያየቶች በቀር ፣ በማያጠራጥር ሁኔታ
ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚአሸጋግሩት አጠቃ
ላይ ሕጐች ነው የሚገዙት ።

እነዚህ አጠቃላይ ሕጐችን በመከተልና ከልዩ ባሕ
ሪዎች ጋር የሚሰምሩ የተለያዩ ምጣኔ — ሀብታዊና ፖለ
ቲካዊ ቅርጾችን በማገናኘት ፣ ወደ ሶሻሊስት ጐዳና ያመ
ሩት ብሔሮች በአገሮቻቸው ውስጥ አጠቃላይ የሕብረተ
ሰቡን ሥርዓት ሥር ነቀል ለውጥ አምጥተውላቸዋል ።
የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ንብረትነት በሶሻሊስት
ማኅበረ — ሰብ አገሮች በጠንካራ ሁኔታ ተመሥርቷል ፣
በአብዛኞቹ በሶሻሊስት መስመር የእርሻ እንደገና መደ
ራጀት ተጠናቋል ። ከሶሻሊስት አገሮች አንዳንዶቹ የሶ
ሻሊዝምን መሠረት ጥለዋል ፣ ሌሎቹ ግን መጠቅ ያለ
የሶሻሊስት ሕብረተሰብን መገንባት ጀምረዋል ።

ሶሻሊዝም ከአንድ አገር ድንበር አልፎ ሲሰራጭና
ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ሲሆን ፣ የኮሚዩኒስትን ንቅናቄ በማ
ይገሰሱ የሶሻሊስት መንግሥታት መካከል ምን ዓይነት
ግንኙነት መኖር እንዳለበት የመወሰን ፕሮብሌም ገጠ
መው ።

የዚህ ፕሮብሌም መፍትሔ ቅድመ — ዝግጅቶች
ግልፅ ነበሩ ። የሶሻሊዝምና የኮሚዩኒዝም ከዋና ዓላማዎች
አንዱ በሕዝቦች መካከል ያለውን ጥርጣሬና ጠላትነት
ማጥፋትና ዘላለማዊ የሆነ የሰላምና የወንድማማችነት
መተሳሰር በነጻ ብሔሮች መካከል መመሥረት ነው ። ስለ
ዚህ ፣ በሶሻሊስት አገሮች መካከል የግንኙነቶች ጠቅላላ
ሥርዓት እነዚህን ዓላማዎች ማገልገል እንዳለባቸው ግል
ጽ ነው ።

እነዚህ ዓይነት ግንኙነቶች በኮሚዩኒስት አስተሳሰ
ቦች ውስጥ ብቻ መቅረት የለባቸውም ። የሶሻሊስትን
መንገድ ለሚከተሉ ብሔሮች ነዋሪ የሆነ ሕብረት ነባራዊ
አስፈላጊነት አለው ። ይህ በንድፈ — ሀሳብና በተግባር
ተረጋግጧል ። ወዲያው ከመጀመሪያውኑ የሶሻሊስት
አገሮች የኢምፔሪያሊስት የወረራ አደጋ ገጥሟቸው ስለ
ነበር ፣ አብዮታዊ ሁኔታን ከጠላት ለመከላከልና ሶሻሊ
ዝምን ያለ እንከን ለመገንባት እንዲችሉ ጥረታቸውን
ማሳሳብ (ማያያዝ) ዋና ተግባር ነው ። በካፒታሊስት አገ
ሮች አሥራጊነት የሚፈጠረውን የኢኮኖሚ ከበባ ውጤተ
አልባ ለማድረግ ፣ በካፒታሊስት ገበያ በኃይል መልክ
የንግድ ንግሡትን ለማስወገድ ፣ እና ፈጣን ምጣኔ ሀብ



ታዊ ዕድገት ለማግኘት በቂ ዕርዳታ እርስ በእርሳቸው እን
ዲሰጣጡ ለማድረግም ሕብረት ያስፈልጋቸዋል ። የመ
ጨረሻው (ግን አነስተኛው አይደለም) የውጭ ፖሊሲዎ
ቻቸውን በሚአስተባብሩበት እና በአለም መድረክ ላይ
የሕብረት ግንባር በሚፈጥሩበት ጊዜ ፣ የሶሻሊስት አገ
ሮች በዓለም ከዊን — ነገሮች (events) አቅጣጫ ላይ
ተፅዕኖ ለማሳደር ባላቸው ችሎታና ክብር ላይ አድናቆት
ንም ይጨምርላቸዋል ።

አንድ ዓይነት የሕብረተሰብ ምጣኔ — ሀብታዊ ሥር
ዓት ፡ አንድ ዓይነት የማርክሲስት — ሌኒኒስት ርዕዮተ —
ዓለም ፣ እና የቅርብ የፖለቲካ ዝንባሌዎች ተመሳሳይነት
እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሶሻሊስት አገሮችን ሕብረት
በቅድሚያ ይወስናሉ ። የብዙ መንግሥታት ሕብረት ከማ
ለት ዘለቄም የሚሰጠው ብዙ ጥቅም አለው ። ይህ ሕብ
ረት የሚአመለክተው አዲስ ዓይነት የዓለም አቀፋዊ ግን
ኙነቶችን መሠረታዊ ዕድገት መቋቋምን ነው ። ለዚህ
ግሩም የሆነው ምሣሌ በሶቪየት ሕብረት የሶሻሊዝምን
ኢኮኖሚ ለመገንባት ለቬትናምና ዲሞክራሲያዊ ሬፑብ
ሊክ የቀረበው ሁለገብ የሆነ የወንድማማችነት መረዳዳት
ነው ። በሁለቱ አገሮች በተፈረሙት ስምምነቶች መሠ
ረት የሶቪየት ሕብረት የኢንዱስትሪ ዕቃዎችን ፣ የእርሻ
መሣሪያዎችን ፣ የመገናኛ አገልግሎቶችን ፣ የሕክምና
ዕቃዎችና መድሐኒቶችን ለቬትናም ዲሞክራሲያዊ ሬፑ
ብሊክ ትልካለች ፣ እናም በጂኦሎጂ ምርመርና የእርሱ
ንም የኃይል ምንጭ በመገንባት ትረዳለች ። በሁለቱ
የእስያ ሶሻሊስት አገሮች — የሞንጎሊያ ሕዝብ ሬፑብ
ሊክና የኮሪያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መካከልና

በሶቪየት ሕብረት ጠበቅ ያለ የጓደኝነት ፣ የሕብረትና የወንድማማችነት መተሳሰር አለ ።

ማርክስ ፣ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የአንድ መንግሥት ማትረፍ ለሌላው መክሰር ነው ብሏል ። ከተግባርና ከንድፈ — ሀሳብ በመነሳት ፣ በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ የአንዱ ማትረፍ ለሁሉም ነው ማለት እንችላለን ።

እርግጥ ፣ አዲሶቹ ዓይነቶች ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች በአንድ ምሽት ተከውነው የሚመጡ አይደሉም ። አጠቃላይ የሆነ የምጣኔ — ሀብት ፣ የፖለቲካና የባሕል መተሳሰር በሶሻሊስት አገሮች መካከል መመሥረት አስፈላጊ ነው ። አዲሶቹ የዓለም ግንኙነቶች ለተወሰነ ጊዜ ቅርፅ እየያዙ ናቸው ፣ እናም ይህ ዕድገት ለመጠናቀቅ ብዙ ይቀረዋል ። ከዊን — ነገሮች የአዲሶቹ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች በተለያዩ የሶሻሊስት አገሮች መካከል መቋቋም አንዳንድ ጊዜ ተመጣጣኝ ወደሆነ ችግር እንደሚአመራ አሳይተዋል ፣ ግን እነኝህ ችግሮች አላፊ ጠባይ ያላቸው ከመሆናቸው ሌላ በዓለም መድረክ ላይ በካፒታሊስት መንግሥታት መካከል ካለው ኃይለኛ ውድድር ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም ።

* በደምብ እንደሚታወቀው የሶቪዬት ሕብረት አዲሶቹን ዓይነት ዓለም — አቀፋዊ ግንኙነቶች በመቅረፅ ከፍተኛ ሚና ትጫወታለች ። የሁለተኛው የዓለም ጦርነትን በማስከተል በተለያዩ አገሮች የሶሻሊስት አብዮት ድል ሶቪዬት ሕብረት አድኅሪ ኃይሎችን በማደንዘዟ ምክንያት በቀላሉ ተፈጽሟል ። የውጭ ጣልቃ ገብነትን ተከላክላለች



የወጣት ሶሻሊስት አገሮችን የመከበብ ዕቅድ አከሸፋለች ፣ እናም የራሳቸውን ኢንዱስትሪ እንዲገነቡ ረድታለች ።

* ከጦርነት በኋላ ባሉ የመጀመሪያ ዓመታት የሶቪየት ሕብረትና የሶሻሊስት አብዮት ድል የአገኙባቸው ሌሎች አገሮች የምጣኔ — ሀብት ስምምነቶችና የሕብረት ውሎች እንዲሁም በወረራ ላይ የእርስ በእርስ መረዳዳት ውሳኔ ላይ ደረሱ ። ከናቶ (N.A.T.O.) የኢምፔሪያሊስት ከበብ መመሥረት በኋላ የአውሮጳ ሶሻሊስት አገሮች በግንቦት ፲፱፻፵፰ ዓ ም የዋርሶ ቃል ኪዳንን አቋቋሙ ። ይህ የመከላከያ ድርጅት በጥምር አዛዥነት የሚመራ ጭምር የጦር ሠራዊት አለው ። የተቀናጀው መከላከያ የሶሻሊስት አገሮችን ፣ በተለይም የሶቪየት ሕብረትን የኑክሌር ሚሳይል ጥንካሬ ፣ ሶሻሊዝምን ለመጠበቅ ብቁ መሆኑን ይመጥናል ፣ እና በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ጦርነት አሸታች ክበቦችን እርምጃ ይከታተላል ።

ይሁንና ፣ የዓለም ሶሻሊስት አገሮች ሕብረትና አንድነት በከመቅፅበት ነው የመጣው ብሎ መገመት (ማሰብ) የዋህነት ይሆናል ። አዲሶቹን ግንኙነቶቻቸውን የገነቡት ለብዙ ምዕተ — ዓመታት ጠላትነትና አለመተማመን እና ብሔራዊ ጥላቻን መሥርቶ በነበረው መሠረት ላይ ነው ። ካፒታሊዝም ብዙ ጊዜ በመንግሥታት መካከል የውዝግብ ውርስን ነው የሚተውላቸው ። አንዳንድ ጊዜ ፣ የተለያዩ አገሮች በቅርብ ብሔራዊ ዝንባሌዎች ላይ ስማሙ ይችላሉ ። የእነዚህ ዓይነት ችግሮች ስፋት በመካከላቸው ካለው የወንድማማችነት ሕብረት ተፅዕኖ ጋር ሲወዳደሩ ዋናነት ባይሰጣቸውም ፣ አሁንም ቢሆን እነ

ዚህን ችግሮች ለመወጣት ከባድና የማያቋርጥ ጥረት ያስፈልጋል ።

በአሁኑ ሁኔታ ፣ ስለዚህ ፣ ለኮሚኒስትና ሠራተኛ ፓርቲዎች ትክክለኛ የሆነ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፖሊሲ መሥራትና የሀገሮቻቸውን ብሔራዊ ዝንባሌ ከመላው የሶቪየት ማኅበረ—ሰብ ማዋሃድ ዓይነተኛ ነው ። ለዚህ ነው የኮሚዩኒስትና ሠራተኞች ፓርቲዎች ምክርና ንግግር፣ መልዕክተኞችን መለዋወጥ ፣ እና በጋራ ዝንባሌዎች ላይ ግልፅ ፣ ጓዳዊ ውይይቶች ማካሄድ የሚኖርባቸው ።

በሶሻሊስት አገሮች መካከል ጤነኛ የሆኑ ጓደኝነት ግንኙነቶችን ለመጠበቅ በተለይ ጊዜ የአረጋገጣቸውን መርሆዎች፣ (time-tested principles) በኮሚዩኒስት ንቅናቄ መገብ ላይ የተመዘገቡትን፣ማጤን ዓይነተኛ ነገር ነው ። እነዚህም ፦— ዕኩልነት ፣ የአንዱን ነጻነትና ብሔራዊ የማይገሰስ ክብር የማክበር ፣ እና በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት ናቸው ። እንዲሁም ስለተባለ በሶሻሊስት አገሮች መካከል ያሉት ግንኙነቶች ከእነዚህ መርሆዎች (ብሒል) የተከለከሉ አይደሉም ፦— በሶሻሊስት ዓለም — ዓቀፋዊነት የተመሠረቱ ናቸውና ።

ይህ በዓይነት አዲስ የሆነ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነቱ ነው ። መርሆው ፣ በሃገራቸው ውስጥ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች ከተቋቋሙ በኋላ በሠራተኛው ሕዝብ ንቃተ — ሕሊና ውስጥ ሥሩን ይተክልና ይዳብራል ። ከሶሻሊዝም መንሰራፋት በኋላ የዓለም አቀፋዊነት ሀሳቦች የወንድማማችነትና የዓለም ሠራተኞች በሙሉ የእርስ በእርስ መረዳዳት — አዲሱን ሰው ለመቅረፅ ወሳኝ የሚ



ሆኑ ሞራላዊ ደረጃና መሠረታዊ መርሆች በመሆን ተቀባይነት ይኖራቸዋል ።

የሶሻሊበት ዓለም — አቀፋዊነት ዋነኛው ክፍል ሶሻሊስታዊ አርበኝነት ነው ፣ ይህም ለሶሻሊስትና ለኮሚዩኒስት መርሆዎች ታማኝነትና ሶሻሊስት ሥርዓትን የሠራተኞችን ኃይል ፣ በአንድ ሀገር ብቻ ሳይሆን ግን በሁሉም የሶሻሊስት ማኅበረ—ሰቦች ለመንከባከብ ዝግጁ መሆን ማለት ነው ። የሶሻሊስት ዓለም አቀፋዊነት ፅንሰ ሃሳብ የሚአመለክተው የሶሻሊስት ማኅበረ — ሰብዕን ጥንካሬ የሚአዳብረውን ትልቅና ዙሪያ — ገባ መረዳዳት በሙሉ ነው ። የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት በትክክለኛ ሁኔታ እንዲአድግና ጥንካሬ እንዲአገኝ ዋስትና የሚሰጠው የዓለም አቀፋዊነት ታማኝነት ነው ። በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊነት የሚአመለክተው ከወዝ አደሩ ተቃራኒ የሆነውን የቡርዧ ርዕዮተ—ዓለም ብሔረተኝነትን በመጻረር የማያወላውል ትግል ማካሄድን ነው ።

የቡርዧ ብሔረተኝነት የታየው ብሔሮች በመጡበት ጊዜ ነበር ። ይህም የብሔራዊ—ቡርዧዋው ፍልስፍና ነው ። በትግሉ ፣ በመልከኝነት ዘመን የግዛት መከፋፈልን በመጻረር እና ብሔራዊ ገበያን ለመገንባትና ለማጠናከር በወሰደው ጥረት ፤ በተጨማሪም ዝንባሌዎቹን ከመልከኛ መኳንንትና ከጐረቤት አገር ቡርዧዎች ለመከላከል ፣ ብሔራዊ ቡርዧዋው የሠራተኛውን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ይታገላል ። የሰራተኛ ሕዝቦች ለሀገራቸው ፣ ለቋንቋቸውና ባሕላቸው ያላቸውን ስሜት በመጠቀም ፣ የቡርዧ ርዕዮት — ዓለምአውያን የመደብ አመጣጣቸውን ሳይሆን ፣ ባለው አስተሳሰብ ሕዝብን ለማንቀሳቀስና ሕብ

ረት ለመፍጠር የሚረዳውን « የብሔራዊ ስሜትን » ሀሳብ በሕዝቡ ፊት የመጣሉ ። በከፍተኛ ልምድ በሚሠሩት ሕዝባዊ ኪነቶች ውስጥ ሠራተኛው ሕዝብ ባለው ተፈጥሮአዊ ክብር ላይና ከሕዝቡ መካከል በወጡት ብሔራዊ ጀግኖች ላይ በማትኮር ፣ ቡርዧዎች ፣ ሠራተኞች የእነሱ ብሔር የበላይነትንና የዘር ጥራት እንዳለው በማነብነብ ለማግባባት ይሞክራሉ ። ስለዚህ ፣ የቡርዧ ብሔረተኝነት ሠራተኛ ሕዝቦች ለመብታቸው የሚወስዱትን እርምጃ በመጻረርና ከሌላ ብሔር ቡርዧ ጋር በሚአካሂዱት ጠንካራ የውድድር ትግል ቡርዧዎች የሚጠቀሙበት ዋና አማካይ ነው ።

አንድን ብሔር በመገንባት (በመሥራት) ላይ ግን ፣ በተለይም የቅኝ ግዛት ሥርዓትን በሠብታተን ጊዜ ፣ ብሔረተኝነት ጸረ — ቅኝ ግዛት ከዚያም ይበልጥ ወይም ጸረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት በመውሰድ ፣ ትክክለኛ ተራማጅ ሚና ሊጫወት ይችል ይሆናል ፣ የብሔር አርነት ትግሉ ኃይል በሚሰበሰብበት ጊዜ ለሠራተኞችና ለድሀ ገበሬዎች የፖለቲካ ንቃት ጊዜ ይሆናል ።

* የብሔረተኝነት ታላቁ አደጋ የሚንተራሰው የቡርዧዊው ርዕዮተ — ዓለም በመሆኑ — በግል ባለሀብቶች፣ በንዑስ ከበርቴዎች መካከል በቀላሉ ተቀባይነት ያገኛል፣ ከሠራተኛው መደብ ሌላ ፣ ገበሬው እና የከተማው ንዑስ ከበርቴ በሶሻሊስት ንቅናቄ ውስጥ ይሳተፋሉ ። የጥቂት ባለንብረቶች ዘዴአማ ስግብግብነት (egoism) በብሔራዊ ደረጃ የተስፋፋ ብሔራዊ ስግብግብተኝነት ይሆናል ፣ በሌላ በኩል በራስ ሀገር ውስጥ ከውጭው ዓለም እራስን አጥሮ የማስቀመጥ ምኞት እና በሌላ መንገድ ፣ የራስን



ብሔር ከሌላው ብሔር ሁሉ በላይ አድርጎ ለማስቀመጥና ሥልጣኑንና የአስተሳሰብ ዘዴውን በዚሁ ውስጥ ለማስገባት ፤ ለማሥረግ እና በእነሱ ለመሥራት ነው ። ከላይኛው ጋር በቅርብ የተያያዘው « ጠንካራ ስብዕዊነት » (strong personality) ወደሚል ከኔ በላይ የማለት አዘንባይነትና የብሔርን ኃይል ክብር ለማረጋገጥ (ዋስትና ለመስጠት ) ችሎታ አለው ተብሎ የሚታመንበት « ምንም ስህተት የማይሠራ » መሪን ማምለክ ነው ።

* ከወዛደሩ ቁልፍ ተግባሮች አንዱ የሕዝቡን የንዑስ ከበርቴ ክፍል በወዛደራዊ ትክክለኛነት ፣ በማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም ፣ ዓለም አቀፋዊ አመለካከት በመስጠት ማግባባት ፣ እና በሳይንሳዊ ኮሚኒዝም መንገድ መምራት ነው ። ሌኒን የዚህን ተግባር ዋናነት ደጋግሞ አፅንዖት ሰጥቷል ፣ በተለይም አብዛኛው ሕዝብ ገበሬ በሆነባቸው አገሮች ። የንዑስ — ከበርቴ ብሔራዊ አመለካከቶች በተለይ የሶሻሊስት አብዮት ተካሂዶ ሥልጣን በወሰደበት አገር በፓርቲ፡ እየተመሩ ከተብራሩ አደገኛ ናቸው ። ይህ ሁኔታ አንድን ሀገር በሚመለከት መንገድ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ጥያቄዎችና ሀሳቦች ከማወገርገር ሌላ በዓለም መድረክ ላይ የሶሻሊስት ዓለም — አቀፋዊነትን መርሕ ወደመጣሱ ይመራል ። ብሔራዊ ጥላቻዎች ጸረ — ሶሻሊስት አዝማሚያዎችን ያራባሉ ፣ እናም እነኝህ ሶሻሊዝምን በሚአመጡት ሁኔታዎች ላይ መቃብራዊ ጥፋት ያደርሳሉ ።

የተለያዩ የቡርዧ ብሔረተኝነት መልኮችን በመዋጋት ፣ የማርክሲስት—ሌኒንስት ፓርቲዎች የሶሻሊስት አገሮችን ሕብረት ለማጠንከር ይሠራሉ ። በዚህ ጥረት ውስጥ

አንዳንድ ጊዜ ያልተጠበቀ የታሪክ መታጠፍ ይገጥማቸዋል ። ግን አዲሶቹን ዓይነቶች ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች የመገንባቱ ሥራ ምንም ያህል አስቸጋሪና ውስብስብ ይሁን ፣ ግቡን ይመታል (ይከናወናል)። ምክንያቱም በዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት ዕድገት ጊዜ የሚነሱትን ነባራዊ ፍላጐቶችና በሞላ የአበላት አገሮች ዝንባሌዎችን ስለሚስማማ ነው ።

## የዓለም ሶሻሊስት ምጣኔ — ሀብታዊ ሥርዓት

በሶሻሊዝም የተገኙት የአዲሶቹ ዓይነቶች ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች ጥቅም በግልፅ የሚታየው በሶሻሊስት አገሮች መካከል በሚደረገው የምጣኔ — ሀብታዊ ሕብረት ክልል ነው ።

የእያንዳንዱ ሶሻሊስት አገር ሕዝቦች የወንድማማች አገሮች ሕዝቦች በኢንዱስትሪና በእርሻ ፈጣን ዕድገትና የኑሮ ደረጃቸውን እጥፍ እንዲያደርጉ ይፈልጋሉ ። እናም የሁሉም ከግባቸው መድረስ በብዙው ጥገኛ የሚሆነው ባላቸው የምጣኔ-ሀብታዊ የእርስ በእርስ መረዳዳት ላይ ነው ። ይህ መረዳዳት ብዙ መልኮች ይይዛል ፡— እንደ እርስ በእርስ የመጠቃቀም ንግድ ፣ ዱቢዎችና ብድሮች ፣ ፋብሪካዎችን የመገንባት ዕርዳታ ፣ ሳይንሳዊ—ቴክኒካዊ ዕውቀት የመለዋወጥ ፤ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ።

ማንም እንደሚጠብቀው ሁሉ ፣ እንዲህ ዓይነት ዕርዳታ በመጀመሪያ የሚመጣው በጣም ከዳበሩ አገሮች ነው። ለምሣሌ ፡ ሶቪዬት ሕብረት ሌሎች ወንድም ሶሻሊስት አገሮችን የኢንዱስትሪ ድርጅቶቻቸውን በመገንባት ረዳ-



ታለች ፣ ዱቤዎች ፣ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርት ለማስገኘት የሚአስችል ቴክኒካዊ ዕርዳታና እንዲሁም ፕላን ሰጥታለች ። ልዩ ባለሙያዎችን በማሰልጠንም ትረዳለች።

ይበልጥ የተራመዱቱ የሶሻሊስት ማኅበረ - ሰብ አባላት ለሌሎች ወንድም አገሮች ለሚሰጡት ዕርዳታ ጥቅም አይጠይቁም ። ግን ይህ ዕርዳታ በተፈጥሮው «መፅዋችነት» አይደለም ። የሶሻሊስት አገሮች «በመፅዋችነት» እና «በተመፅዋችነት» የተከፋፈሉ አይደሉም። እያንዳንዱ ሀገር የሀብት ምንጩን በመጀመሪያ ደረጃ ፤ አዲስ ሕብረተሰብን ለመገንባት ያንቀሳቅሳል ። ግን እንዲህ በሚአደርግበት ጊዜ ፣ ከሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ጋር ይተባበራል ፣ እና በዓለመው ነገር ግቡን ከመታ ፣ የአገኘውን ነገር ምስጢር አድርጎ አይጠብቅም ። እንዲያውም ፣ ከሌሎቹ ጋር ይካፈላል ። ይህ ነው በኮሚዩኒስት ማኅበረ — ሰብ የጓዳዊ መረዳዳትን ሁለገብ ግንኙነቶች ልዩ የሚአደርገው ።

ለምሣሌ ፡— ቼኮዝሎቫኪያ ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችን የማሺን መሣሪያ እንዱስትሪዎቻቸውን እንዲአሳድጉ ትረዳለች ። የጀርመን ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ በከፍተኛ ደረጃ (አንደኛ) የብርሃን መሣሪያዎችን የማምረት ሰፊ ገጠመኝ ታካፍላለች ፣ ፖላንድ ደግሞ የማዕድን ዕቃዎችን የማምረት ገጠምጇን ትሰጣለች ። በተጨማሪም የሶሻሊስት አገሮች የብሎት ዕቃዎችንም በመጨመር ፣ የተፈበረኩ ሸቀጦችን ይለዋወጣሉ ። የሶቪየቱ ተጠቃሚ የቼኮዝን ጫማ ፣ የፖላንዱን መቀመጫ የቡልጋሪያን ሲጃራ ፣ እና የሁንጋሪን ሐር እንደተዘጋጀ ሲገዛ ፣ በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ግን በሶቪየት የተፈበረኩ ሰዓ

ቶች ፣ ካሜራዎች (መቅረጸ — ትርኢቶች) እና ሌሎች ዕቃዎች ከባድ ተጠያቂነት አላቸው ።

የሶሻሊስት አገሮች በምጣኔ — ሀብታዊ ሕብረቱ፡ የሚቀርቡትን ነገሮች በተቻለ መጠን ከበፊቱ፡ በበለጠ መልክ በጥቅም እንዲያውሉ እያደረጉ ናቸው ። ለምሣሌ ፣ የበለጸገ የከሰልና የዘይት ምንጭ ያላቸው ፣ ወይም እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የማሺን መሣሪያ ያላቸው (ኢንዱስትሪ) ፤ እነዚህን እንዱስትሪዎች የሚአሳድጓቸው የራሳቸውን ፍላጐት ለማርካት ብቻ ሳይሆን ግን እነዚህን ምርቶች ለወንድም አገሮችም ለመላክ ነው ። እነዚያ ደግሞ በተራቸው ሌሎችን የእነሱን ልዩ ምርቶች ያቀርቡላቸዋል ። ይህ ልውውጥ ብዙ ጥቅሞች ያስገኛል ። እያንዳንዱ ሶሻሊስት አገር ሁሉንም ነገር ማምረት አያስፈልገውም ። እነዚያኑ አይነት የእርሻና የኢንዱስትሪ ክልሎች (ሴክተሮች) ማሳደግ ይችላሉ ፣ ምክንያቱም የበለጠ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ (አመችነት) ስላላቸውና የበለጠም ገጠመኝ ስለሚኖራቸው ።

በታሪካዊ መልኩ፣በአገሮች መካከል ግዛታዊ የዓለም የሥራ ክፍፍል ተደረገ ። ይህም ማለት የተወሰኑ ዕቃዎችን በማምረት ጠበብት የሆኑ አገሮች ዕቃዎቻቸውን በዓለም ገበያ በመሸጥ የሌላቸውን እንዲገዙ ይሆናሉ ። በእርግጥ፣ዓለም አቀፋዊ የሥራ ክፍፍል በብዛት የጉልበት አምራችነትን ስለሚአሳድግ ተራማጅ ነው ። ይሁንና በካፒታሊዝም ውስጥ ለትርፍ ማመንጫና ያልዳበሩ አገሮችን የምጣኔ — ሀብት የመበዝበዣ መንገድ ሆኗል ።

ኢምፔሪያሊስቶች ቅኝ ግዛቶቻቸውንና ጥገኛ ሀገሮችን በአንድ ወይም በሁለት ምርት ብቻ ጠበብት እንዲ



ሆኑ አደረጓቸው ። በዚህ ምክንያት ፣ እነኝህ አገሮች ሙሉ በሙሉ ለኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጥገኛ ሆኑና ያለ ርኅራሄ ወደሚአስበዘብዛቸው የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ሆነው ቀሩ ። ዛሬም እንኳ ፣ ለምሣሌ በቆርቆሮና በተፈጥሮ ጐማ አምራችነት ጠበብት የሆነችው ማላያ ፣ ይህን የመጀመሪያ ደረጃ (ጥሬ ዕቃ) ምርት በደህና ተመን ለመሸጥ ሳትችል ብትቀር ጠቅላላ ምጣኔ ሀብቷ ይሰባበርና አገሪቷ ጥፋትና ረሀብ ይገጥማታል ። ኢምፔሪያሊስቶች እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ እንዴት እንደሚብዘብዙ ያውቃሉ ።

በሶሻሊዝም ግን ሁኔታው ፍጹም ልዩ ነው ። በሶሻሊስት አገሮች መካከል ዓለም — አቀፋዊ የሥራ ክፍፍል ከካፒታሊስቶች መርገም ነጻ ነው ፣ ሶሻሊሊዝም የአንድን ሀገር በሌላው መበዝበዝን እንዲአከትም ያደርግና በዚህ ዓይነት ክፍፍል እኩልነትን ያመጣል ። በአገሮች መካከል ተቃራኒነት ይወገዳል ፣ እናም በዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት የሁሉም አገሮች የስምምነት ምጣኔ — ሀብታዊ ዕድገት ሁኔታዎች ቀስ በቀስ ይፈጠራሉ ። በዚህም ምክንያት የዓለም ሶሻሊስት ምጣኔ ሀብት በመዋደድ ሕብረትና እኩልነት ላይ የተመሠረተ ፣ አዲስ ዓይነት ዓለም አቀፋዊ የሥራ ክፍፍልን ያሳድጋል ። የሁሉንም የሶሻሊስት ማኅበረ — ሰብ አባላትን የምጣኔ — ሀብት ዕድገት (ርምጃ) ያገለግላል ።

ዓለም አቀፋዊው የሶሻሊስት የሥራ ክፍል ቅርፅ መያዝ ከጀመረ ብዙ ጊዜ አይደለም ። አሁንም ቢሆን በደምብ አልዳበረም ፣ ምክንያቱም የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት የአንድ ምዕተ—ዓመት እንድ አራተኛ ዕድሜ ነው ያለው፣ እናም በሃገሮች መካከል ሕብረትና ጠበብትነትን ( Spe-

Cialization) ለመመሥረት ጊዜ ይወስዳል ። ስለዚህ ፣ ብዙ ጥቅም የተገኘ ቢሆንም ፣ ዓለም አቀፋዊ የሶሻሊስት የሥራ ክፍፍልን ጥቅሞችና ሁኔታዎች በሙሉ ለመጠቀም ብዙ የሚሠሩ ነገሮች ይቀራሉ ። የአውሮጳ ሶሻሊስት አገሮች የምጣኔ — ሀብት ሕብረትን ውስብስብ ተግባር የእርስ በእርስ የምጣኔ — ሀብታዊ መረዳዳት በሚባለው ድርጅት (C. M. E. A.) አማካኝነት ያካሂዳሉ ።

በ ሲ. ኤም. ኢ. ኤ አገሮች (የእርስ በእርስ የምጣኔ ሀብታዊ መረዳዳት) የተባበረ ጥረት አማካኝነት ብዙ ትላልቅ የምጣኔ ሀብት ፕሮጀክቶች ተመስርተዋል ወይም እየተሰሩ ናቸው ።

ለምሣሌ ፣ የ፭ ሺህ ኪ ሜ የዘይት ቧንቧ መስመር ፣ የጓደኝነት ቧንቧ መስመር ተብሎ የሚጠራው ፣ ከ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ነው ። የቮልጋን ረግረግና ዩክሬንን ከቼኮዝሎቫኪያ ፣ ከፖላንድ ፣ ከጀርመን ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክና ከሁንጋሪያ ያገናኛል ። በካፒታሊስት ሞኖፖሊስቶች ከተሰሩት ሁለት ታላላቅ የቧንቧ መስመሮች ይረዝማል ፤ በአሜሪካ ቢግ ኢንች (ትልቁ ኢንች) እና በመካከለኛው የትራንስ አረቢያን የቧንቧ መስመር የሚባሉትን ። በ፲፱፻፸፫ እና በ፲፱፻፸፭ የጓደኝነት የቧንቧ መስመር ሶሻሊስት አገሮችን ፫፻፹፮ ሚሊዮን ቶን ዘይት መግቧቸዋል ። የተፈጥሮ ጋዝ ከሳይቤሪያ ለቼኮዝሎቫኪያ ፣ ለፖላንድ ፣ ለጀርመን ዲሞክራቲክ ሬፑብሊክ ፣ ለቡልጋሪያ እና ለሁንጋሪ የሚመግብ ሌላ ትልቅ የቧንቧ መስመር እየተዘረጋ ነው ። የአውሮጳውያን ሶሻሊስት አገሮች ሚር (ሰላም) ተብሎ የሚጠራ የኤሌክትሪክ ኃይል ማሠራጫ ኬብልም አላቸው ፣ ይህ የኤሌክትሪክ ውስብስብ ከመቶ



ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላቸውን ግዛቶች ያገለግላል ። ይህ ንኑ የሚአሳድጉ ለወደፊቱ ከ፲፭ — ፳ ዓመት ድረስ አጠቃላይ ፕሮግራሞች ተነድፈዋል ። ይህም የዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል በትክክል እንደሚዳብር ያሳያል።

ሌኒን የዓለም የምጣኔ-ሀብት አዝማሚያ እንደ አንድ ሆኖ እንደሚአድግና በሁሉም አገሮች ወዛደሮች ቁጥጥር ሥር በአንድ የጋራ ፕላን መሠረት እንደሚዳብር ጠቁሟል ። ይህ አዝማሚያ በሶሻሊስት አገሮች እንደተረጋገጠው በጣም ይበልጥ ትክክለኛነቱን አሳይቷል ። መተባበር የሕብረት ከፍተኛው ደረጃ ነው ። እንደ (የእርስ በእርስ የምጣኔ ሀብታዊ መረዳዳት) አባል አገሮች መሠረት ፣ የተባበረ መዋዕለ — ንዋይ በብዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የጥሬ ሀብት ምርት ፣ ነዳጅ ፣ አንዳንድ ዐይነት ማሺኖች ፣ ወዘተ . . በማስገባት ፣ ይበልጥ ጠበብትና ትልቅ ሕብረት እንዲኖረው በማድረግ ፣ እና በተቀራረበ የኢኮኖሚ ዕቅድ ቅንጅት መሠረት ፣ ምጣኔ — ሀብትን ይበልጥ እያቀራረቡ ማያያዝን ነው የሚአመለክተው ። መተሳሰር የእያንዳንዱን ሀገር የምጣኔ — ሀብት ዕድገትና የሶሻሊስት አገሮችን ሃያልነት ያሸጋግራል ፣ ያሳድጋል ።

ይሁንና ፣ የዓለም ሶሻሊስት የምጣኔ-ሀብት ሥርዓት ዕድገት ፣ የሶሻሊስት አገሮች ራሳቸው ከሌላው የዓለም ክፍል ተቆራርጠው በብቸኝነት ይኖራሉ ማለት አይደለም ። እንዲያውም ፣ ከምጣኔ ሀብት ሥርዓታቸው በቀር ከሁሉም አገሮች በምጣኔ ሀብት ሕብረት እርስ በእርስ የመረዳዳትን ጥቅም ይሻሉ ።

## መሪው አብዮታዊ ኃይል

የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት የዛሬው ዘመን መሪ አብዮታዊ ኃይል ነው ። ይህ የተረጋገጠው ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በሶሻሊስት ምሣሌ ተፅዕና ነው ። የሰዎችንና የአገሮችን መበዝበዝ የሚያስወግደውን አዲስ ሕብረተሰብ በመገን ንባት ላይ ፣ የሶሻሊስት አገሮች የሶሻሊስት ሥርዓትን ታላቅ ጥቅም ያሳያሉ ። ከፍተኛ ደረጃ የምጣኔ — ሀብት ዕድገት አሳይተዋል ፣ እናም ሥራ አጥነትንና ሌሎች የሕረተሰብ መርገሞችን (በካፒታሊስት ሥልተ—ምርት ውስጥ የሚገኙትን) አስወግደዋል ። እያንዳንዱ ሶሻሊስት አገር ሰፊ የሆነ የሕብረተሰብ ደህንነት ሥርዓትና ፍጹም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የትምህርት ሥርዓት አለው ። በሶ ሻሊዝም ውስጥ ሳይንስና ባሕል በደንብ ያድጋሉ ። እነ ዚህ ሁሉ የሶሻሊዝም ድሎች የማርክሲስት—ሌኒኒስት ሀሳቦችን መሠራጨት ሲረዱ በሶሻሊስት መስመር የሕብ ረተሰብን እንደገና መቅረፅንም ያበረታታሉ ።

የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት የኢምፔሪያስት ኃይሎ ችንም ወደዚሁ እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል ። በዚህ ምክን ያት ፣ ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ። የሶሻሊስት አገሮች ፣ በዕድገት ላይ ባለው የምጣኔ-ሀብትና የፖለቲካ ተፅዕኖ ኃያልነት በመንተራስ የኢምፔሪያሊስቶችን የጸረ — አብዮት ኃይል ከቦታ ቦታ የማስተላለፍን ይከላከላሉ ፣ እናም በጣም አድሃሪና ጠብ አጫሪ የኢምፔሪያሊስት መምሪያዎችን አሸክላ (ሴራ) — የኒውክሌር ጦርነት ለማስነሳት -የሚፈልጉትን— ያከሽፋሉ ። የሶሻቪየት ሕብረት የኑክሌር ሚሳይል ጥን



ካሬ የኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች ወደኋላ እንዲአፈገፍጉ በማድረግና የዓለም ሰላምን ለማጠንከር ያገለግላል ።

በሶቪየት ሕብረትና እና በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ሰላምንና ጣልቃ ያለ መግባትን ለመጠበቅ የተወሰደ ውን ጠንካራ አቋም የእስያ አገሮች በተደጋጋሚ የማየት ዕድል ገጥሟቸዋል ። የአንድን ሀገር የማገይሰስ ክብርን በሚመለከት ረገድ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የውጥረትን ማደግ ስለሚከላከል ዋና ነጥብ ነው ። ለዚህ ነጥብ ምሣሌ የሚሆነው በሕንድና በፓኪስታን መካከል የነበረውን ግጭት ለማስቀረት ሶቪየት ሕብረት የተጫወተችው ሚና እና የመካከለኛውን ምሥራቅ ቀውስ መፍትሔ ለመስጠት ያደረገችው የአጠቃላይ ጥረት አስተዋፅኦ ነው ።

በተጨማሪም ፣ የሶሻሊስት አገሮች ሁል—ገብ የሆነ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ለአብዮታዊ ንቅናቄ ዎች ይሰጣሉ ፣ ለብሔራዊ ነጻነትና የራሳቸውን መዳረሻ የመወሰን መብት በማስከበር ለሚታጋሉ ሕዝቦች ማለት ነው ። ይህ ዕርዳታ ወታደራዊ እርዳታን (ካስፈለገ) ለምሣሌ በቬየትናም እንደነበረው ይጨምራል ።

### ፱. የወዝአደሩ አብዮታዊ እንቅስቃሴ፦ እያደገ የሚሄደው የኮሚኒስት ፓርቲዎች ተፅዕኖ

የካፒታሊዝም ቅራኔ ሲተባ ፣ የወዝ አደሩ የመደብ ትግል ትልቅ ስፋትና ጥንካሬ ያገኛል ።

የሠራተኛው መደብ እድማዎችና ሌሎች የተቀነ ባበሩ ድርጊቶች ለዝንባሌዎቹና ለመብቶቹ ለመዋጋት ያለውን የቆራጥነት ዕድገት ያሳያል ። በተለይም ዋና

የሚሆነው ነገር ሠራተኞች በብዙዎቹ አድማዎች ፖለቲካዊና እንዲሁም ምጣኔ — ሀብታዊ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ ።

በጃፓን ሠራተኛው መደብና ገበሬዎች አገሪቱን የዩናይትድ ስቴትስ የኑክሌር መሞከሪያ የማድረግን ማውጠንጠን እየተዋጉ ናቸው ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለጥቁር አሜሪካውያን የመብት ጥያቄ ሰልፎች ይካሄዳሉ ። በላቲን አሜሪካም ወዛደሩና ሌላው የሠራተኛው ሕዝብ ክፍል በጣም ንቁ እየሆኑ ሄደዋል ፤— በዚያ የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ዋና ጥያቄዎች አንዱ የሰሜን አሜሪካን ሞኖፖሊዎችን የገዥነት ዕድሜ ማሳጠር ነው ።

የኢንዱስትሪ ሠራተኞችና ሌሎች የሠራተኛው ሕዝብ ክፍሎች የፖለቲካዊና የኤኮኖሚ ክንዋኔዎች የሚአሳዩት ይበልጥ እየተደራጁና የፖለቲካ ንቃታቸው ከፍ እያለ መሄዱን ነው ። የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ አዲስ ደረጃ እየገባና የጥያቄው ደረጃም እያየለ ነው ። ለከፍተኛ ደመወዝና ለአጭር የሥራ ሰዓቶች ፥ ለተሻለ የሕብረተሰብ ደህንነትና ለጡረታ ስምምነት ከመጠየቅ ሌላ ፥ ሠራተኞች ምርትን የመምራትና የማቀናጀት ተሳትፎ መብት እየተዋጉ ናቸው ፤ ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅላቸውና ለባሕላዊ ዕድገትና የተሻሉ ትምህርት ሁኔታዎች እንዲፈጠሩላቸው ይጠይቃሉ ። ሰፊ ሕዝባዊ መብቶችና ዲሞክራሲያዊ ነጻነቶችን መብት ያቀርባሉ ። እነዚህ ድርጊቶች የታቀዱት የሞኖፖሊን ገዥነት በመጻረር ነው ። አመሠራረቱን ቀስ በቀስ በማዳከም የካፒታሊስቱን ሥርዓት ይበልጥ ደካማ ያደርጉታል ። ዛሬ በአንዱ



ነገ በሌላው የካፒታሊስት አገር ትብ የሕብረተሰብ — ፖለቲካዊ ቀውሶች ያልፈነዱበት ዓለም የለም ። እነዚህ ከዊነ — ነገሮች የመደብ ትግሉን አዲስ ደረጃ እንዲወጣ ሲአደርጉት ፥ እናም ካፒታሊዝምን ከመጀመሪያ ሕልውናው ጀምረው ባላቸው ጠንካራ ይዞታ ይቋቋሙታል ።

የሠራተኛው መደብ ትግል የሚመራው በኮሚኒስት ፓርቲው ነው ። የኢምፔሪያሊስቶችን የገዥ ክበብ አድሃሪ ፖሊሲዎችን ያለመሰልቸት ያጋልጣል ፤ በተጨማሪም ተራማጅ ኃይሎችን ለሰላም ፥ ለዲሞክራሲ ለሶሺሊዝም እንዲዋጉ ያስተባብራል ።

በዓለም ወደ ዘጠና በሚጠጉ አገሮች ውስጥ ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች አሉ ፤ አጠቃላይ የአባላት ቁጥርም ወደ ፶ ሚሊዮን ይጠጋል ።

በብዙ የካፒታሊስት አገሮች የኮሚዩኒስት ፓርቲዎች ይታገዳሉ ሽብር ይካሄድባቸዋል እናም ጸረ—ኮሚዩኒስት ፕሮፓጋንዳ ይሠራጫል ። ይህ ለክንዋኔአቸው አስቸጋሪ ሁኔታን ሲፈጥር ዕድገታቸውን ይጐትተዋል ። ስለዚህ ብዙ ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች በከፊል ሕጋዊ ወይም ሙሉ በሙሉ ሕቡዕ ሆነው (ለምሣሌ ፥ እንደኢንዶኔዥያ ፥ ቱርክ እና ኢራን ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች) ለመሥራት ይገደዳሉ ፥ ይሁንና ፥ በብዙ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ የኮሚዩኒስት ፓርቲዎች በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ሕዝባዊ ድርጅት ለመሆን እያሰቡ ናቸው ። ከዚህ በፊትም በፈረንሣይ ከ፶ሺ አባላት በላይ ፥ በሕንድ ፪፻፳ አባላት አካባቢ ፥ በጃፓን ወደ ፫፻ሺ አባላት ያሏቸው ሕዝባዊ ኮሚዩኒስት ፓርቲዎች አሉ ።

የኮሚኒስት እንቅስቃሴ ድል የሚለካው በፓርቲ
አባላት ብዛት ብቻ ሣይሆን ፣ ግን የኮሚኒስት ፓርቲዎች
በሠራተኛ ሕዝቦች ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነት ማግ
ኘትም ጭምር ነው ። በብዙ የካፒታሊስት አገሮች ኮሚ
ኒስት ፓርቲዎች በትላልቅ የሙያ ማኅበር ድርጅቶች
ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው ። በምርጫ ላይ ብዙ
ሕዝብ የሚመርጠው ኮሚኒስቶችን ነው ፣ እናም ይህ የሚ
አሳየው የኮሚኒስት ፓርቲዎች ፖለቲካዊ ተፅዕኖ እያደገ
መሄዱን ነው ።

አሁን በካፒታሊስት አገሮች የኮሚኒስት ፓርቲዎች
እራሳቸውን እንዴት እንደሚአደርጉ ያሏቸውን ዓላማዎች
እንመልከት ።

## ሠራተኛው መደብ — ለሰላምና ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል መሪው ኃይል

የኮሚኒስት ፓርቲዎች ዋና ግብ የነበረውና ወደፊ
ትም የሚሆነው ፣ ካፒታሊስት ሕብረተሰብን ወደሶሻሊ
ዝም ማሸጋገርና ኮሚኒዝምን መገንባት ነው ። ይህ ዓላማ
የዛሬውን ዘመን የኮሚኒስት ንቅናቄ፣ስትራቴጅና ታክቲክ
ይወስናል ።

እንደብጥብጥ ወይም መፈንቅለ — አገዛዝ ሳይሆን
የሶሻሊስት አብዮት በሕብረተሰብ ዕድገት ሕጐች የሚገዛ
ሂደትና በካፒታሊዝም ማደግና በቅራኔዎች መትባት ምክን
ያት ቀድሞ የሚወሰን ነው ። ሶሻሊስት አብዮቶች ለሥርዓት
(ለትዕዛዝ) የተሰሩ አይደሉም ፣ ግን ከነሱ የሕብረተሰብ
ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ሲበስሉ (ሲጋምሩ) ብቻ ፣ የወዛደሩ
የንቃተ ሕሊና ደረጃና የድርጅት ጥንካሬው ደረጃ በቂ



ሆና ሲአይል ፣ እናም አብዮታዊ ርምጃዎችን ለመውሰድ
ብቁ መስዋዕትነት ሲአሳይና ሰፊውን ሕዝብ ካፒታሊዝ
ምን ለማጥቃት ሲመራው የሚመጡ ናቸው ። ነገሮችን
ማጣደፍና ከዊን — ነገሮችን ማስገደድ በሠራተኛው
መደብና በኮሚኒስት ፓርቲው መካከል አደገኛ የገደል
ውጤትን ያሳያል ።

በአብዮታዊው ሠራዊትና በተዋጊው ወታደር መካ
ከል ይህ ዓይነት አጉል ጀብደኝነት የሥርዓተ — አል
በኞች ፣ የትሮትስካይቶችና የሌሎች ጽንፋውያንና የአፈ
ንጋጭ አብዮተዋያን ጸባይ ነው ፤ ግን ለማርክሲስት —
ሌኒኒስቶች ተጻራሪ ነው ።

ይሁንና ፣ የሠራተኛ ሕዝቦች አብዮታዊ ግንባር ቀደም
መሪ የእንቆይ እና እንየው «ፖሊሲ» ያውጣ ማለት አይ
ደለም ። እንዲያውም ፣ ዋና ዓላማዎቹ ሠራተኛውን ሕዝብ
ማስተባበር ፡ ለፖለቲካዊ ግንዛቤው እንክብካቤ ማድረግ፣
ድርጊቱን ማሻሻል እና የኮሚኒስት ሀሳቦችን ማስፋፋት
ነው ። ሰፊውን ሕዝብ በሥትራቴጅና ታክቲክ ወደ አብ
ዮቱ ጥያቄ ለመምራት ብቁ ነው የምንለው ማርክሲስት —
ሌኒኒስት ፓርቲ እጅግ መጥፎ ጊዜ በሆነበት እንኳ ፣ ለወ
ደፊቱ ወሳኝ ጦርነት ዝግጁ በመሆን ኃይሉን በትዕ
ግሥት ለማንቀሳቀስ ሲችል ነው ። ይህ ዓላማ በትክክል
የሚገኘው በብሔራዊ የነጻነት ትግል ውስጥና የሕዝብ
መብቶችና ነጻነቶችን በማስጠበቅና በማስፋፋት ፡ እናም የም
ጣኔ-ሀብትን ወታደራዊነት ፣ ፋሺዝምንና ጦርነትን በመቃ
ወም ትግል ውስጥ ነው ። ሌኒን እንደጠቆመው ፣ የፖለ
ቲካ ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲ መለወጥ ለሶሻሊስት መን
ገድ ጠርጓል ። መሠረቱን በማስፋትና የንውስ ከበርቴ

ውን አዲስ ክፍሎችና ሰፊውን ግማሽ ወዛደር ወደሶሻሊዝም ትግል ውስጥ እያቀረበ እምጥቷቸዋል ። ስለዚህ ለዲሞክራሲ ትግል ለሶሻሊዝም ትግል ነው ።

በዛሬው ዘመን የካፒታሊስት ሕብረተሰብ የዲሞክራሲ ዋና ጠላት ከሰፊው ሕዝብ በተጻራሪ ራሳቸውን የሚአስተምጡት ሞኖፖሊዎች ናቸው ። የተቃውሞውን ንቅናቄ በየጊዜው ሕዝቡ እየተዳበለው (እየገባበት) በሄደ መጠን የሞኖፖሊዎችን የበላይነት ቅዋሜ እያየለና እየናረ ይሄዳል ። የትላልቅ ድርጅቶች ከንዋኢ የትንናሽ ገበሬዎችንና የከተማ መካከለኛ መደብን (ትናንሽ ባለድርጅቶችን ፣ ነጋዴዎችን ፣ የእጅ ሙያተኞችን ፣ እና እንዳንድ የቢሮ ተቀጣሪዎችን) ዝንባሌ ይጨፈልቀዋል ። ወይተራቆች እለዚያም የሞኖፖሊዎችና የባንኮች ሙሉ ጥገኛ ይሆናሉ ። ስለዚህ ፣ ይበልጥ ዝንባሌአቸውን ለመጠበቅ ንቃት ይኖራቸዋል ።

በዘመናችን የአእምሮ ሠራተኞች ቁጥርም ሆነ ተፅዕኖ በሳይንስና በባሕል ፈጣን ዕድገትና በትምህርት ሥርዓት መስፋፋት ቀጥታ ውጤት ምክንያት በፍጥነት እያደገ ነው ። ቀድሞ ፣ እንዲህ ዓይነት ሠራተኞች በካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ ለተለያዩ ሁኔታ ከፍተኛ ዕድል ነበራቸው ። ብዙዎቹ በሕብረተሰቡ ውስጥና ባመለካከታቸው ያላቸው ደረጃ ከቡርዧዊው በጣም የተቀራረበ ነበር ፣ እናም የቡርዧዊውን ዝንባሌ ነው የአገለገሉት ። ይሁንና ፣ ዛሬ በቁጥር እየጨመሩ የሄዱት ምሁራን ምንዳዕና ደመወዝ ተቀባዮች እየሆኑ ናቸው ። ትላልቅ ድርጅቶች እንደ ኢንዱስትሪ ሠራተኞች ሁሉ ያለርህራሄ ይበዘብዟቸዋል ፣ እናም ዝንባሌአቸው ከሠራተኛው መደብ



ጋር በትርብ ተያይዟል ። የትላልቅ ድርጅቶች ለናረ ትርፍ መሯሯጥ የሳይንቲስቶችን ፣ የምሁራንን ፣ የኪነት ሰዎችን የባሕላዊ ሠራተኞችንና የምሁራንን የመፍጠር ችሎታና ከፍተኛ ፍላጎት ላይ እግር ብረት ሆኗል ። ከካፒታሊስት ሕብረተሰብ መንፈሳዊ ቀውስ ጥልቀት እና የሶሻሊስት ሀሳቦች ይበልጥ ማራኪ እየሆኑ መሄድ ጋር ፣ በተራማጅ ምሁራንና በሞኖፖሊዎች መካከል ያለው ግጭት ይበልጥ እየናረ ነው ።

ካፒታላዊ የእስያ አገሮች መንግሥታት ፣ ብሔራዊ ምጣኔ ሀብታቸውን በዕቅድ መሠረት ለመምራት እንዳልቻሉ በተግባር ተረጋግጧል ፣ ሌላ ምሳሌ ሳያስፈልግ ፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየጨረሱ የሥራ — እጥንትን ትርጉም በመማር ላይ ያሉትን መመልከት በቂ ነው ። ስለዚህ በጸረ — ኢምፔሪያሊስት ትግሉ ውስጥ የእንጉል ሠራተኞች ከጉልበት ሠራተኞች ኃይል ጋር እየተዳበሉ ናቸው ፣ እናም ይህ የሁለቱን ቡድኖች የጠንካራ ሕብረት ቆራጥ ዕድል ያስገኛል ።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የካፒታሊስቱ ዓለም «የወጣት ብጥብጥ » ተብሎ በሚጠራው ተፋጠ ነበር ። ወጣት ሠራተኞች ፣ ተማሪዎችና ሌላው የወጣቱ ክፍሎች በሞኖፖሊ በሚገዛ ሕብረተሰብ ውስጥ ስለ ወደፊቱ ምንም ተስፋ አይታያቸውም ። ለውጥን ነበር የሚጠይቁት ። እርግጥ ተቃውሟቸው ግብታዊ ነው ፣ እናም አንዳንድ ጊዜ በሥርዓት — አልበኞችና በሌሎች ሀሳዊ — አብዮታዊያን (pseudo-revolutionaries) ዝንባሌዎችና ሀሳቦች ድንበር ለቀው ይመሩ ነበር ። ይሁንና ከንዋኤአቸው (ተግባራቸው) ከኢንግዲህ ወዲያ በተጠናከረው ዘመናዊ ካፒ

ታሊዝም የአየር ክልል ውስጥ ለመኖር እንደማይሹ ያሳያል ። ስለሆነም ወጣት ሰዎች ወደ ሠራተኛው መደብ ንቅናቄ እና ለሀሳቦቻቸው ሞኖፖሊዎችን በመጻረር እንዴት እንደሚታገሉ ሊአሳያቸው ከሚችለው የኮሚኒስት ግንባር ቀደም ጋር አቀራርቦ ለማሰለፍ አመቺ ሁኔታ አለ ።

የጸረ-ሞኖፖሊዎችን ትግል ብዙ ሕዝቦች በየጊዜው በተጻበሉት ቁጥር ፣ የትላልቅ ድርጅቶች ሶሻላዊ መሠረት ይጨማተራል ። ይህም ለሁሉም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችና ለሕብረተሰቡ ክፍሎች የአገር ውስጥ አድሃሪዎችና የውጭ ኢምፔሪያሊስት ወራሪ ፖሊሲዎችን በመቃወም ለሚአደርጉት የፖለቲካ ሕብረት ጥረታቸውን ለማሳሳብ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ። በዚህ መንገድ የተራማጅ ኃይሎችን ሕብረት ለመፍጠርና እነሱንም የጸረ — ሞኖፖሊ ጥምረት (anti-monopoly coalitions) ጥንካሬ እንዲኖራቸው ለማድረግ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ንቁ ናቸው ።

በዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ሚና በመጫወት ሠራተኛው መደብ የፋሺዝምን ክንዋኔ ለመከላከልና ከቡርዧ ዲሞክራሲያዊ ጥገናዎች ጋር ውጭ ያሉ ለውጦችንና ለሶሻሊስት አብዮት ድል ለመዋጋት ቀላል መንገድ የሚከፍቱትን ለማስገኘት ብቁዕ ነው ። ከዚህ በማስከተል በኮሚኒስት ፓርቲዎች የተደመደመው ሰፊውን ሕዝብ በመያዝ ሞኖፖሊስት ካፒታሊስቶችን ከፖለቲካ በማግለል ፣ እና ጠቅላላ የሥርዓቱን ግንኙነቶች (የሕብረተሰቡን) በሶሻሊስት መስመር እንደገና ለመገንባት ወደሚመሩ ሥር-ነቀል ዲሞክራሲያዊ ጥገናዎችን በማካሄድ በሰላማዊ መንገድ ወደሶሻሊዝም መሸጋገር የተረጋገጠ ይሆናል ።



ግን በዝባዥ መደቦች በሕዝቡ ላይ በኃይል በሚነሳሱበት ጊዜ ፣ ወደሶሻሊዝም ለመሸጋገር ያለው ዕድል በትጥቅ ትግል እንደሆነ መጤን አለበት ።

የኮሚኒስትና ሠራተኞች ፓርቲዎች ማርክሲዝም — ሌኒኒዝምን በጥሩ መንገድ እየገነቡ ናቸው ። በማንኛውም ደረጃ የዓለምን የኮሚኒስት ንቅናቄ ስትራቴጂና ታክቲክ እየቀመሩና በማያወላውል ሁኔታ ተቀልባሾችንና (Revisionists) ቀኖናውያንን ፣ ሁሉንም ቀኝ — ክንፍ እና «ግራ» አድርባዮችን እየተዋጉ ናቸው ። የቀኝ ክንፍ አድርባይነት ተከታይ ዝንባሌዎች ፣ በተለያዩ ጥያቄዎች ላይ ፣ ከቡርዧ ርዕዮተ — ዓለማውያን ጐን የሚሰለፉና ብዙ ጊዜም ስለጥገና የሚሟገቱ ፣ ማለትም ፣ ከመዛደሩ እና ከሌላው ሠራተኛ ሕዝብ የመደብ ጠላት ጋር እርቅ የሚፈልጉ ናቸው ። « የግራ » አድርባይነት ደግሞ የሚገለጸው ፣ በአብዮታዊ ፅንፋዊነት ፣ ለሶሻሊስት አብዮት ዝግጅት የሚአስፈልጉትን ሁኔታዎች በመዘንጋት ወይም ባለማጤንና በትጥቅ ትግልና በአመፅ ብቻ ላይ የሚደገፉ ናቸው ። በመጀመሪያ አመለካከት ሁለቱ አዝማሚያዎች ተቃራኒዎች ይመስላሉ ፣ ግን ማርክሲዝምን በማቃወም ኃይሎቻቸውን ያስተባብራሉ ። እናም አንድ ዓይነት የንዑስ ከበርቴ አመጣጥ ነው ያላቸው ።

ማንኛውንም ዓይነት አድርባይነት በተከታታይ መታገል የወንድማማች ማርክሲስት ፓርቲዎች ዋና ተግባር ነው ።

በፕሮግራማቸው ፣ የኮሚኒስት ፓርቲዎች የአጭርና የረጅም ጊዜ ዓላማዎቻቸውን በሀገራቸው የውስጥና የ

ውጭ ሁኔታዎች ላይ ጠንካራ ትንታኔ በመመሥረት ይቀምራሉ ። በመሠረቱ ፣ ሁኔታዎች ከአገር አገር ስለሚለያዩ የድርጊት ፕሮግራሞቻቸው ሙሉ በሙሉ አይጣሙም ። ይሁንና ፤ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ሁሉም የኮሚኒስት ፓርቲዎች ለሠራተኛው መደብ ከንዋኔ ሕብረት በመሥራትና እንደ መጀመሪያ ተግባራቸው አድርጎ በመውሰድ በኩል አንድ ናቸው ።

## የወዝ አደሩ ሕብረት ለድሉ ዋስትና ነው ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ የሶሻሊስትና የሶሻል — ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች በተወሰኑ የሠራተኛው መደብ ክፍሎችና በሌሎች ቡድኖች ላይ ሊዘነጋ የማይገባው ተፅዕኖ አሳድረዋል ። በምርጫ ላይ ብዙ ድምጾችን ያዝዛሉ ፣ በፓርላማ ከፍተኛ ግንዛቤ ሊሰጠው የሚችል ብዙ መቀመጫ ያገኛሉ ፣ እናም በብዙ አገሮች ተወካዮቻቸው መንግሥትን ይመራሉ ።

በሶሻል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ውስጥ ለመሪነት ቦታቸው እንከን የሚፈጥሩ ብዙ አዝማሚያዎች እያደጉ ናቸው ። ብዙዎች መሪዎች ወደ የጥገናዊነት አዝማሚያ ጢሎሽ በማለት ለብሔራዊ ቡርዧ ዝንባሌዎች ታማኝ ይሆናሉ ። ግን አንዳንዶቹ ለሰላምና ለዕድገት በሚደረገው ትግል ውስጥ የሠራተኞችን ምጣኔ — ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እንዲጤኑ ለማድረግ ያዘነብላሉ ። በሶሻል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ውስጥ የግራ ክንፍ ኃይሎች በጸረ — ኢምፔሪያሊስት ትግል የጋራ ግንባራቸው ላይ የሶሻሊስትና የሶሻል — ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ቦታቸውን እንዲይዙ የሚአስችል መንገድ ለማግኘት ይሞክራሉ ። እርቆ ተመልካች የሶሻል ዲሞክራሲ መሪዎች



ድልን ለማግኘት ከሁሉም ፓርቲዎች ይበልጥ ለሠራተኞች ጥቅም በመዋጋት ጠንካራ ወደሆኑት የኮሚኒስት ፓርቲዎች ይበልጥ መጠጋት እንዳለባቸው ተገንዝበዋል ።

ኮሚኒስቶች ለሠራተኛው መደብ ንቅናቄዎች ሕብረት ከፍተኛ ሚና ይሰጣሉ እናም ተራማጅ ፣ ዲሞክራሲያዊ ገዥ ለማቋቋም (እንደ አጭር ጊዜ ፕሮግራም) በኋላም የሶሻሊስት ሕብረተሰብን ለመገንባት (እንደ ረዥም ጊዜ ዕቅድ) ፣ የሶሻሊስቶችንና የሶሻል ዲሞክራሲዎችን ሕብረት ጥሪ ያደርጋሉ ። ኮሚኒስቶች እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት ለመመሥረት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ።

ይሁንና ፣ ሁለትነት ፣ መዋለልና ጠንካራ አቋም ማጣት ሁልጊዜም ቢሆን የሶሻል ዲሞክራቶች ጸባይ ነው ፣ ስለዚህ ወደሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ሕብረት የሚአመራው መንገድ እንዲህ ቀላል ነው ተብሎ አይጠበቅም ። ብዙ እንቅፋቶች መታለፍ አለባቸው ፣ እናም ብዙ አሽክላዎች እንደሚኖሩ በተጨማሪ እንገንዘብ ። ኮሚኒስቶች እስከመጨረሻ ድረስ ጠንካራ መሆን እንዳለባቸውና ግን ይህ ሥራም እጅግ (ፍጹም) አስፈላጊ እንደሆነ እርግጥ ነው ።

ካፒታሊዝም ሊኖር የቻለው ዋናው በሠራተኛው መደብ ሕብረት ማጣት ነው ብሎ መናገር ማድነቅ አይደለም ። ግን ይህ ሕብረት ከቀን ቀን እያደገ ሊሄድ የሚችለው የካፒታሊዝምን መጨማተርና የሶሻሊዝምን ጥቢ በማፋጠን ነው ።

## ፫· ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴ

### የቅኝ ገዥነት መጨማተር ፤

ብሔራዊ — የአርነት እንቅስቃሴዎች በካፒታሊስት የጭቆና ሥርዓት መሠረት ላይ ደምሳሺ ጡጫ እያነዘሩ ናቸው ።

የካፒታሊስት ሥርዓት የሚወገዝበት ቅኝ ገዥነት ፣ ለሰው ልጆች ክብር የሌለው ነው ። ይህ ሥርዓት ነው እፍኝ ሙሉ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን የዓለምን ሰፊ ሕዝብ ባሪያ ለማድረግ ያስቻላቸው ።

በሩሲያ የጥቅምቱ ፲፱፻፲፯ ዓ ም የሶሻሊስት አብዮት የምሥራቅ ሕዝቦችን በመቀስቀስ ጨቋኞቻቸውን ለመዋጋት ገፋፋቸው ። ይህ ትግል በተለይ ኃያል የሆነው ከናዚ ጀርመንና ከወታደራዊት ጃፓን የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ድል በኋላ ነው ። የቻይና ፣ የኮሪያና የቪየትናም ሕዝቦች ጨቋኞቻቸውን ካባረሩና ሶሻሊዝምን መገንባት በጀመሩበት ጊዜ ፣ ድላቸው ለቅኝ ግዛት ሥርዓት ደቋሸ ጡጫ ነበር ። ሕንድ ፣ ኢንዶኒዥያ ፣ በርማ እና ሌሎች ብዙ የእሲያ አገሮችም ነጻነታቸውን አገኙ ። እንደኛው ከአንዱ በመከተል የምሥራቅ ቅኝ አገሮች በፖለቲካ ነጻ ሆኑ ።

የቅኝ ገዥነት መጨማተር በታሪክ ውስጥ የመለኪያ ደንጋይ ነው ። ለዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት መምጣት ብቻ ዋናነቱ ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ ፣ የካፒታሊዝም እጠቃላይ ቀውስ ትብ በሆነ መንገድ በማባባስ በኩል ከዓይነተኛ ምክንያቶች አንዱ ነው ።



## የብሔራዊ እርነት አብዮቶች

በቅኞች ውስጥ ያሉ የተጨቆኑ ሕዝቦች በራሳቸው መሪነት ባላቸው ጉልበት ሁሉ ኢምፔሪያሊዝምን ወግተዋል ። ይሁንና ፣ ቅኝ ገዥዎች ይበልጥ ጠንካራ ስለነበሩ ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ተጭነዋል ። በዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት ብቻ ነው ኢምፔሪያሊስቶች በዓለም ያላቸውን ገዥነት ለዘላለም የሚአጡትና የጭቁኖች ድል ግቡን የሚመታው ። የአፍሪቃና የእሲያ አዲስ ነጻ መንግሥታት መታየት ለኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት መበታተን ከብሩኃዊ ማረጋገጫ በላይ ነው ፣— የማይገሰስ ክብራቸውን በመጠበቅ ፣ በመጀመሪያ ይዞታቸው በነበሩት መንግሥታት መካከል ለትክክለኛ ምጣኔ ሀብታዊ ግንኙነቶች በመታገል ፣ እናም እርስ በእርሳቸው በፖለቲካ እና በምጣኔ — ሀብት በመረዳዳት ፣ ኢምፔሪያሊዝም በዓለም ያለውን ኃይል ይበልጥ ያዳክሙታል ።

ዛሬ ብሔራዊ — የአርነት አብዮቶች የተጨቆኑ ሕዝቦች የአርነት ትግል ከሌሎች ሁለት ዋና የዛሬው አብዮታዊ ኃይሎች ጋር የሚወሳሰቡበት የአንድ ዓለም አብዮታዊ ሂደት ክፍል ነው ፤— የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓትና በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ።

ብሔራዊ የአርነትአብዮቶች የሚአድጉባቸው አዲስ ሁኔታዎች እመጣጣቸውን ፣ እንቅሳቃሽ ኃይላቸውንና ዓላማቸውን ይወስናሉ ። እንደ ደምብ ሆኖ ፣ የቀድሞ ቅኞችና ግማሽ ቅኝ ካፒታሊስቶች ፣ ሌላው ይቅርና ሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶችን አላሳደጉም ። ስለዚህ ፣ የዛሬው ዘመን

ብሔራዊ — የአርነት አብዮቶች በመጀመሪያ ደረጃ ጸረ—ኢምፔሪያሊስትና መልከኛ አብዮቶች ናቸው ፣ የመጀመሪያ ጥያቄአቸው ነጻነትና ሁለተኛው ደግሞ የመሬት ይዞታ መሻሻል ነው ። ዕድገታቸው ጥገኛ የሚሆነው በብሔራዊ — የአርነት እንቅስቃሴ ውስጥ በመደቦች ኃይል ፤ ዝምድናና ትግል ነው ።

የብሔራዊ — የአርነት አብዮት ብዙውን ጊዜ የሕብረተሰብን ኃይሎች ሰፊ ጥምረት ፣ የወጣት ሠራተኛ መደብ ፣ የገበሬ ፣ የከተማ ንዑስ ከበርቴ ፣ እና በአጠቃላይ ከብሔራዊ ቡርዧው የአርበኝነት ጸባይ ያላቸው ክፍሎች የሚባሉትን ይጠይቃል ፣ ያሳትፋል ። የዚህን ሕብረት ፖለቲካዊ መመሪያ የሚአከናውነው ከሁሉም ይበልጥ ዋናው ነው ።

በፖለቲካ ንቁ የሆኑ የሰራተኛ መደብና ኮሚኒስት ፓርቲዎች — ሕዝቡን በትግላቸው ውስጥ የመምራት ችሎታ ያላቸው — ባለው ሀገር ውስጥ የብሔራዊ — አርነት አብዮቱ ወደ ሶሻሊስት አብዮት ያድጋል ። ሠራተኛ መደብ በሌለበት ፣ ወይም በፖለቲካ ደካማ በሆነበት ፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች በሶሻሊስት ምሣሌ ተፅዕኖ ሥር የብሔራዊ — አርነት እንቅስቃሴዎችን በትክክል ሊመሩ ይችላሉ ። እነዚህ ፓርቲዎች የተመሠረቱት በሀገር ውስጥ ተራማጅ ምሁራን ፣ በቢሮ ሠራተኞች ፣ በወታደሮች ነው ። በዚህ መልክ አብዮቱ ውስብስብ በሆነ መንገድ የሚአድግ ቢሆንም ፣ ሶሻሊስታዊ የሆነ ሃሳብ ሊአቀርብ ይችላል ።



የቡርዥ አባላት አብዮቱን በሚመሩበት አገር ውስጥ ፣ የብሔራዊ አርነት ችግርና የመልከኛን ርዝራዥ ማስወገዱ ጠንካራ ያልሆነና ግማሽ — ልብ እርምጃ ነው የሚኖረው ። እንዲህ ዓይነት አገሮች አብዮቱን በካፒታሊስት ክልል ውስጥ የማቆየት አዝማሚያ ነው ያላቸው ።

የፖለቲካን ነጻነት ከማሸነፍ ባሻገር የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴውን ማን ይምራው ? የሚለው ጥያቄ በተለይ አንገብጋቢ ይሆናል ።

## ትግሉ ይቀጥላል ።

የቅኝ ገዥነት ሥርዓት መጨማተር ቅኝ ገዥነት ሙሉ በሙሉ ተደምስሷል ማለት አይደለም ። ኢምፔሪያሊስቶች በቅኝ ግዛቶች ላይ ያላቸውን ይዞታ ለመልቀቅ በመቃወም ፣ አዲስ የተሻሻሉ ዘዴዎችን አዲስ ነጻ በወጡ አገሮች ላይ ዝርፊያን ለማካሄድ ያውላሉ ።

ከሁሉም በፊት ኢምፔሪያሊስቶች በአዲሶቹ መንግሥታት ውስጥ የነሱን ታማኝ አገልጋዮች — ከእነሱ ፍላጐት ጋር ለመሥራት ጥገኛ ሊሆን የሚችል — በሥልጣን ላይ ለማውጣት ይሻሉ ። እናም ይህን ግባቸውን በመቱበት ፣ የነጻነቱ መታወጅ በሕዝቡ ኑሮ ላይ ምንም ለውጥ አያመጣም ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ኢምፔሪያሊስቶች የቀድሞ ቅኞቻቸውን ወደ ጠብ አጫሪ ክልል ውስጥ ለማስገባት ጥረዋል ። «ኮሚኒዝምን ለመከላከል» በሚለው የሀሰት ሽፋን ፣ በእነዚህ አገሮች ግዛት ውስጥ ወታ

ያራዊ ሰፈሮችን ይሰራሉ ፣ ወታደሮቻቸውን ያስገቡና
አማካሪ ይሏችዋል ፣ እነዚህን አገሮች ያለማቋረጥ በጦር
መሣሪያ ይመግቡና የቅርብ ጊዜ ጸረ — ሽምቅና ጸረ —
ንቅናቄ የውጊያ ሥልቶችን ያስተምራሉ ፤ ኢምፔሪያሊ
ስቶች « ሕዝቡን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል » የሚ
ረዳቸውን የሕዝቡን « በሕዝባዊ ወታደራዊነት ሥር »
እና « በአገር ውስጥ ጥበቃ ኃይሎች » እና በሌላ ወታደ
ራዊ አመሠራረቶች ውስጥ መመዝገብ ያበረታታሉ ።
በዚህ መንገድ በጥንት ቅኞቻቸው የበላይነታቸውን እን
ዲአቆጠቁጥ ይፈልጋሉ ።

ኢምፔሪያሊስቶች በቀድሞ ቅኞቻቸው ላይ ፖለቲካዊ
ጥንካሬአቸውን ለመጠበቅ በማይችሉበት ጊዜ እንኳን ፡
ሰፊውን ሕዝብ በመበዝበዝ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት
ባላቸው ዓላማ ጠንካራ ምጣኔ — ሀብታዊ ይዞታ በእነሱ
ለማቆየት ይቀጥላሉ ። የምዕራባውያን ሞኖፖሊስቶች
አዳጊ አገሮችን በመበዝበዝ የዓመት ትርፋቸው ወደ ብዙ
ሺ ሚሊዮን ዶላር እያደገ ነው ።

ከቅኝ ገዥነት ጋር ያለው ትግል ገና ብዙ ይቀረ
ዋል ። አዳዲስ (ወጣት መንግሥታት ከኢምፔሪያሊስ
ቶች ጠንካራ የምጣኔ — ሀብት ትብትብ ለማምለጥ እና
የብሔራዊ ሀብታቸውን የመዘረፍ ዕድሚ ለማሳጠር ያላ
ቸው መንገድ ፣ የራሳቸውን ኢንዱስትሪ መገንባት ፣ የራ
ሳቸውን ጠበብት ማሰልጠን ፣ እና የካፒታሊስት ሞኖፖ
ሊዎችን ማባረር ብቻ ነው ። እነዚህን አገሮች የሚገጥ
ማቸው ዋና ዓይነተኛ ተግባር የምጣኔ — ሀብት ኋላ ቀርነታ
ቸውን መወጣትና የራሳቸውን ነጻ ምጣኔ — ሀብት መገ
ንባት ነው ።



የቀድሞ ቅኞች ነጻነታቸውን ለማጠንከር በሚወስ
ዱት ጥረት የጓደኞቻቸው ድጋፍ አላቸው — ሶቪዬት
ሕብረትና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ። ስለዚህ ፣ የሶቪየት
ሕብረት በሕንድ ፣ ቢሕላይ ትልቅ የአረብ ብረት ሥራ
እና በግብፅ ደግሞ የአስዋን ግድብ በመሥራት ረድታለች።
ሶቪዬት ሕብረትና ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ኢንዱስት
ያዊ ድርጅቶችን ፣ መንገዶችን ፤ ሆስፒታሎችን እና ተቋ
ሞችን በሕንድ ፡ በበርማ ፣ በአፍጋኒስታን ፣ በብዙ
ወጣት የአፍሪቃ መንግሥታትና በሌሎች አገሮች እንዲ
ገነቡ ፡ ረድተዋል ። በእነዚሁ አገሮች ዩኒቨርስቲዎች በተ
ለያዩ ሙያ ጠበብት ሆነው ያገራቸውን ምጣኔ ሀብትና
ባሕል ለማሳደግብ የሚማሩ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች
የመጡ ወጣቶችም ይገኛሉ ።

ነጻ የወጡት መንግሥታት አሁንም ቢሆን ብዙ
ችግሮችን መወጣትና ብዙ ውስብስብ ፕሮብሌሞችን
ማስወገድ ይኖርባቸዋል ።

የነጻነት ጦርነት በሚካሄድበት ጊዜ ፣ የተለያዩ መደ
ቦችና የሕብረተሰብ ቡድኖች የጋራ ጠላታቸውን ኢም
ፔሪያሊዝምን ለመዋጋት አንድነት ይሰራሉ ። ወዲያው
ነጻነት እንደተገኘ ፣ ተጻራሪ የመደብ ዝንባሌዎች ፊት
ለፊት ይደቀናሉ ። በሠራተኛው መደብ ፣ በገበሬው እና
በሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች መካከል ያለው ግጭት
በሌላ በኩል ፣ ይበልጥ እያየለ ይሄዳል ። የቡርዧ ከበቦች
በሕዝቡ አሸናፊነት የተገኘውን ነጻነት ለመጨበጥ የራ
ሳቸውን የሥልጣን ኃይል ለማቋቋም ይሻሉ ። ሠራተ
ተኞችንና ገበሬዎችን በመበዝበዝ ላይ የተመሠረተ ካፒ
ታሊስት ሥርዓትን ለማጠናከር ባላቸው ፍላጐት በሠ

ራተኛ ሕዝቦች ኪሣራና ጉልበት ከኢምፔሪያሊስቶችና
ከመልከኞች ጋር ለማበር ኢያወላውሉም ።

በኋላ ፣ የካፒታሊስትን ጉዳና የተከተሉ በማደግ
ላይ ያሉ አገሮች ገጠመኝ እንዳሳየው ፣ ካፒታሊዝም ነጻ
ለወጡት መንግሥታት ፕሮብሌም ምንም መፍትሔ ሊሰጥ
አልቻለም ። እንዲያውም የበለጠ ሥቃይና ከአስፈላጊ
ነገሮች መወገድን ብቻ ነው የሚአመጣው ፣ እናም ሕዝ
ቦች የአለመደሰታቸውን ድምፅ ሲአሰሙ ፣ የሀገር ውስጥ
አድሃሪዎች የመጨቆኛ እርምጃዎችን መውሰድና የዲሞክ
ራሲያዊ ነጻነቶችን መታፈን ያስፋፋሉ ። በተጨማሪም
የጐሣና የሃይማኖት ብጥብጥ እንዲነሳና የተቻላቸውን
ያህል የጸረ — ኢምፔሪያሊስቱ ሕብረት እንዲሰባበር
ያደርጋሉ ፣ ስለሆነም የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴውን
ድሎች አደጋ ላይ ይጥላሉ ።

ለዚህ ምሣሌ በጣም ዕውቅ የሆኑት በሕንድ የሞና
ፖሊ ተከታይ ኃይሎች ሕብረት የሆነው ሲንዲኬት ያው
ጠነጠናቸው ሴራዎች ፣ የመንግሥቱን ተራማጅ ፖሊሲ
ዎች የተዋጋው ፣ እና በእነዚህ ዓይነት አድሃሪ የብሔረ
ተኝነት ድርጅቶች የተወሰደው ሚና እንደ ጃና ሳንግና
ስዋታንራ ያሉት ዘረኝነትና የሃይማኖት ብጥብጥ በሀገ
ራቱ ውስጥ ያስነሱት ናቸው ። እንደነዚህ ዓይነት ቀኝ
አክራሪ የእስላም ፓርቲዎች በኢንዶኔዥያ እንደማሹሚ
(አሁንም በግልፅ ሕገ — ወጥ ናቸው ) እና በፓኪስታን
ጀማቲ ኢስላሚ በጣም አደገኞች ናቸው ።

የሶሻሊስት አገሮች ገጠመኝ የቀድሞ ቅኞችንና
ግማሺ ቅኞችን የብሔራዊ ንቃትንና የሕብረተሰብ ዕድ



ገትን ጉዳና ይመራቸዋል ። በዚህ ጉዳና ለመጓዝና በደ
ንብ ለመከተል ፣ አንዳንድ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያስፈል
ጋሉ ።እጅግ ወደኋላ ቀር በሆኑ አገሮች ውስጥ በሕብረተሰ
ብም ምጣኔ እነዚህ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ በጣም
ችግር ነው ። አዲስ ነጻ የወጡ መንግሥታት ብዙ ችግሮች
ያጋጥሟቸዋል ። ኢምፔሪያሊስቶችና የአገር ውስጥ አድሃሪ
ዎች የጥንት ዘዴአቸውን ለመጠበቅና ወጣቶቹ አገሮች
ከካፒታሊስት ሥርዓት ሰብረው እንዳይወጡ ለመከል
ከል ኃይላቸው እስኪፈቅድላቸው ድረስ የሆነውን ነገር
(ለጥፋት) ከማድረግ አይቆጠቡም ።

አንዳንድ አዲስ ነጻ የወጡ አገሮች ካላቸው ገጠመኝ
በመነሳት የጸረ አብዮተኞች ክንዋኔ ግልፅ ሆኖላቸዋል ።
አድኃሪ ኃይሎችን በፍርሃት ለማስዋጥና እርምጃን ወደኋላ
ከመጐተት ለመከላከል ፣ ጸረ — ኢምፔሪያሊስት ፤ ጸረ —
መልከኛ እና ዲሞክራሲያዊ አብዮቶችን ወደትክክለኛ
ግብ ለማድረስ የሚዋጉትን ተራማጅ እና አገር ወዳድ
ኃይሎች ሕብረት መገንባት አስፈላጊ ነው ።

በብዙ አገሮች ፣ ላለፉት ጥቂት ዓመታት ፣ በተግባር
የብሔራዊ አርነት ትግል ወደ ጸረ — ብዝበዛ ላይ በተመ
መሠረቱ ግንኙነቶች ትግል ማደግ ጀምሯል ። በብዙ የነ
ጻነትን ዕድገት በተከተሉ አገሮች ገዥ ፓርቲዎችና የፖ
ለቲካ መሪዎች ፣ ዓላማቸው ሶሻሊዝምን መገንባት እን
ደሆነ ገልጸዋል ። እነዚህ አገሮች የሕብረተሰብ መሻሻ
ሎችን በተለያዩ ደረጃ (ስፋት) እያካሄዱ ናቸው ። በኢ
ምፔሪያሊስት ሞኖፖሊዎች የተያዙትን የምርት መገል
ገያዎችን ወረሱ ፣ የምጣኔ — ሀብት ሴክተሩን (ክልሉን)
አቋቋሙ ፣ የመሬት ይዞታን መሻሻል አራመዱ ፣ ገበሬ

ዎች የሕብረት ሥራ እንዲአቋቁሙ አበረታቱ ፣ ወዘተ . . ።
እነዚህ ለውጦች በተግባር የዋሉት ሁልጊዜ አንድ (ነዋሪ) ባልሆኑ የሕብረተሰብ ዕድገት ፕሮግራሞች ነው ፣ እናም በብዙ መንገዶች የሶሻሊስት እስተሳሰቦችን ካሉት የን ውስ ክበርቱ እና የሃይማኖት አመለካከቶች ጋር ያምታቷ ቸዋል ።

የራሳቸውን መንገድ እንደሚከተሉና የሶሻሊልት ሕብረተሰብን የሕዝቦቻቸውን የውርስ (የታሪክ) ይዘት በመከተል እንደሚገነቡ ሲገልጹ ፣ የእነዚህ አገሮች መሪ ዎች አፅንዖት የሚሰጡት በተለያዩ መንገድ የሶሻሊስት አገሮችን ምሣሌና ገጠመኝ በማቅረብ ነው ። ይህም የሰው ልጅ ወደሶሻሊዝም እንደሚጓዝና የማይቀርም እንደሆነ በተጨማሪ ያሳያል ። የሶሻሊስት አገሮች ያሏቸውን ገጠ መኞች በወጣት መንግሥታት ውስጥ እያስገቡም ፤ ሁለ ገብ የሆነ ዕርዳታ ይሰጧቸዋል ፣ ግን በእነሱ የውስጥ ይዞ ታ ጣልቃ አይገቡም ። ንድፈ — ሀሳብ ለዉጣት መንግሥ ታት የብዝበዛን መወገድና በዕውነተኛ ነጻነት ላይ የተ መሠረተ ሕብረተሰብን መገንባት ፣ ለሁሉም አባላት እኩ ልነትና ወንድማማችነትን መፍጠር ፣ ዘዴን እንደሚሰ ጣቸው ዕድገቶች ያሳያሉ ።

## ፩. የጊዜአችን ዋና ጥያቄ ፤

በአሁኑ ዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት የሕብረተሰብ ሥርዓቶች አሉ ፦ — የሶሻሊስት እና የካፒታሊስት ሥር ዓት የሚባሉ ። የሁለቱን የዕድገት መስመሮች በማነጻጸር እንደሚታየው ፣ በሁለቱ ተጻራሪ ሥርዓቶች መካከል ያለው ውድድር በሶሻሊዝም ድል ማድረግ ያከትማል ።



ይሁንና ፣ ያለሕዝቡ ትግል ምንም ዓይነት የሕብረ ተሰብ ዕድገት አዝማሚያዎች ድል አያደርጉም ።

የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ትጥቃቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየጨመሩ ናቸው ። ወታደራዊ ጠብ አጫ ሪነትን በማውጠንጠንና በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ ኃይልንና ደንብ ጣሽነትን በመጠቀም ጣልቃ ይገባሉ ። በዚህ ዓይነት ነው የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓትንና የብሔ ራዊ — አርነት እንቅስቃሴዎችን የሚዋጉበትን ዘዴ የሚአቀርቡት ። ስለዚህ ፣ ሌላ የዓለም ጦርነት አደጋን ! . .

አሁን ፣ ካፒታሊዝም እየወደቀ ሶሻሊዝም እየጠነ ከረ በሚሄድበት ጊዜ ፣ ሚቹ ሥርዓት የብዙ መቶ ሚሊ ዮን ሕዝቦችን ሕይወት ወደ መቃብር ለማውረድና በብዙ ትውልዶች ጉልበት የተፈጠሩትን መጠናቸው ይህ ነው ተብሎ ሊገመት የማይችሉ ንብረቶችን ጥፋት ውስጥ ለመክተት ሽር ጉድ ይላል ።

ዛሬ ፣ የሰላምና የጦርነት ጥያቄ ለዓለም በጣም አስ ፈላጊ ነው ።

## የሰላም ደህንነት የሕዝቦች ኃላፊነት ነው

በ፲፯ኛው ምዕተ-ዓመት ጦርነቶች የ፫ ሚሊዮን ፣ በ፲፰ ኛው ምዕተ-ዓመት 5.5 ሚሊዮን ፣ እና በ፲፱ኛው ምዕተ ዓመት የ፲፮ ሚሊዮን ሕዝቦች ሕይወት ጠፍቷል ። በዚህ ምዕተ — ዓመት የአንደኛው ዓለም ጦርነት ፲ ሚሊዮን እና የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ከ፶፩ ሚሊዮን ሕይወት በላይ ማጥፋቱ ታውቋል ።

በ፲፯ኛው ምዕተ — ዓመት መስኬት እና ሽጉጥ ነበሩ ዋና የጦር መሣሪያዎች ። መድፍ በመጀመሪያ ረ

ዳት መሣሪያ የነበረው ፣ በ፲፰ኛው እና በ፲፱ኛው ምዕተ—
ዓመት ወሳኝ መሣሪያ ሆነ ። በዚህ ምዕተ—ዓመት በሁለቱ
የዓለም ጦርነቶች መድፍ ዋና ቦታውን ከታንክና ከአየር
ኃይል ጋር ተካፈለ ። በኋላም ለከፍተኛ ጥፋት መገልገ
ያነት የኑክሌር መሣሪያዎች ተጨመሩ ። እና አሁንም የጦር
ትጥቅ እየጨመረ ነው ። በዚህ ጦርነት ውስጥ ምን ዓይ
ነት መሣሪያ መጠቀም እንደሚአስፈልግ አልበርት አይ
ንስታይን ሲጠየቅ ፣ ስለሶስተኛው ምንም እንደማያውቅ
ሲናገር ፣ ግን ቀስትና ፍላፃ በአራተኛው ላይ በተግባር
እንደሚውሉ እርግጠኛ ነበር ።

ጦርነት መቆም አለበት ፣ ማንኛውም በትክክለኛ
አመለካከቱና የዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የአጥፊነት
ኃይል የአወቀ ሁሉ ይህን ይገነዘበዋል ። የመጀመሪያው
አቶም ቦንብ የፈንጅነት ኃይል ከ፳ሺህ ቶን (ቲ. ኤን. ቲ.)
ጋር እኩል ነበር ፤ ዛሬ ፤ መቶ ሚሊዮን ቶን በላይ
ኃይል ያላቸው የሃይድሮጅን ቦንቦች አሉ ። የኑክሌር
መሣሪያዎች የአጥፊነት ኃይል በዚህ የሚአቆም አይ
ደለም — የሕይወት ማጥፋት ችሎታ ያለው ጨረርም
አለው ። ከታላላቅ ሳይንሳዊ አሰሳዎች አንዱ ፣ ለሰው
ልጅ ይህ ነው የማይባል ኢኒርጂ የሚሰጠው ፣ በምትኩ
ዓለምን በሞትና በጥፋት ይበጠብጣል ፣ እናም ሙሉ
በሙሉ መወገዝ የአለበት ኢሰብአዊ የሆነው የካፒታሊ.
ስት ሥርዓት ነው ።

በነሐሴ ፣ ፲፱፻፵፭ ፣ ጃፓን እጅዋን ከመስጠቷ ከጥ
ቂት ቀናት በፊት ፣ የዩናይትድስቴትሱ ፕሬዚዳንት ትሩ
ማን የሆሮሽማንና የናጋስኪን በአቶም ቦንብ መደብደብ
አዘዙ ። በሆሮሺማ በፈነዳው ፈንጅ ሁለት መቶ ሺህ



ሰዎች ተገለዋል ፣ ወይም ለጨረር በሽታ ተጋልጠዋል ፤
ከተማይቱ ወደ አመድነት ወርዳለች ።

ወታደራዊ አስፈላጊነት ሳይኖረው ፣ ለምንድነው ዩና
ይትድ ስቴትስ የአቶም ቦንብን የተጠቀመችው ? የዩናይ
ትድ ስቴትስ የገዥ ቡድኖች የሶቪየት ሕብረትን እና
ሌላው የዓለም ክፍልን ለማስፈራራት ኃይላቸውን ለማ
ሳየት ስለፈለጉ ነው ።

ግን ተስፋቸው ተዳምጧል ፡— ሶቪየት ሕብረት ፡ A
ቦንብ (ኤ. ቦንብ) ፣ እናም ሃይድሮጅን ቦንብ ፣ አህጉር አቋ
ራጭ ሚሳይሎችና በዓለም ላይ የትኛውንም ኢላማ በተ
ለዩ ትኩረት (ማነጣጠር) ሊመታ የሚችል ሉላዊ ሮኬት
አዳብራለች ።

አዲስ የዓለም ጦርነት ሊቀር ይችላልን ? በተፈጥሮው
ኢምፔሪያሊዝም ጦርነትን እንደሚአራባ እናውቃለን —
ታሪክ ለዚህ አናት የሚመታ ማረጋገጫ ሰጥቶናል ።
እናም የኢምፔሪያሊዝም ተፈጥሮ ስላልተለወጠ ፣ በሕ
ልውና እስካለ ድረስ ፣ የጦርነት አደጋ ይኖራል ።

ይሁንና ፣ ልዩ ሁኔታዎች (ጸባዮች) ወይም የተለወጡ
ታሪካዊ ወቅቶች ማጤን ሳይደረግ በተግባር ላይ የሚውል
ምንም ዓይነት ንድፈ — ሀሳብ የለም ። ኢምፔሪያሊዝም
አሁንም ጦርነቶችን ይፈለፍላል ፣ ግን በዓለም ውስጥ
ሌሎች ኃይሎች አሉ ፣—ኢምፔሪያሊዝምን የማ ለጉሙና
የጠብ አጫሪነት ማውጠንጠንን የማአግዱ ፣ የሚከለክሉ
ኃይሎች ። በሌላ አባባል ፡ እላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ
ለመመለስ ፡ የጦርነት ኃይሎችንና የሰላም ኃይሎችን
የዘመኑን ሚዛን ማስተንተን አስፈላጊ ነው ።

የሰላም ኃይሎች ፣ በኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች ላይ ደምሳሽ ጡጫ ሊሰጡ የሚችሉት ከሁሉም በፊት የሶቪየት ሕብረትና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ናቸው ። ከገለልተኛ ናቸው ጦርነት የማይፈልጉና ብሔራዊ ንቅናቄዎቻቸውን ለማግኘት ሰላምን የሚፈልጉ ብዙ ሶሻሊስት ያልሆኑ አገሮች አሉ ። የዓለም ሠራተኞች ሰላምን ወደ ላይ ከፍ አድርገው ይዘውና ሰፋ ያለ ጸረ — ኢምፔሪያሊስት ትግል እያዘጋጁና በማዘጋጀትም ላይ ናቸው ።

ዋና የትጥቅ ግጭቶችን በሰላም ኃይሎች የተባበረ ጥረት አማካኝነት ማስወገድ እንደሚቻል ዕድገቶች አሳይተዋል ። በአሁኑ ወቅት የዓለም ጦርነትን ለመከላከል በቂ ጥንካሬ አላቸው ።

እርግጥ ፣ የዓለም ዕድገቶች ቀጥታ መስመር ተከትለው አይሄዱም ፣ እናም ሰላምን ለመጠበቅ ያለው መንገድ በዓለም መድረክ ላይ ካለው አጠቃላይ የኃይሎች ሚዛን ከመ — ቅፅበት የሚመጣ አይደለም ። የጦርነትና የሰላም ጥያቄ የሚወሰነው በምንም አይነት መንገድ ይሁን የወረራ ፖሊሲውን ከሚተወውና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች አደገኛ ሁኔታዎች ለመፍጠር ከሚቀጥለው ኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚደረገው ትብ ግጭትና መቋቋም ነው ። ዛሬ የዓለም አቀፍ ሁኔታ የውቅያኖስ ሞገድን ወደየብስ መፍሰስና መመለስ ነው የሚመስለው ። ዲቴንቲ ( Detente ) የተገኘው በወራሪ ኢምፔሪያሊስት ድርጊቶች ምክንያት በዓለም ላይ እየጨመረ በሄደው ውጥረት በሰላም ኃይሎች ጥረት ቅንጅት ነው ።

ለዚህ ምሣሌ የሚወሰደው ነጥብ የዩናይትድ ስቴትስ የቬየትናም ወረራ ነው ። በዓለም ውስጥ ያሉ የሁሉንም እውነተኛ ሰዎች ቁጣ አስነሳው ። ሶቪዬት ሕብረትና ሌሎችም ሶሻሊስት መንግሥታት ፣ ዓለም አቀፋዊ ተግባራቸውን የሚሰሩት ፤ ለቬየትናም ሕዝቦች ሰፋ ያለ ምጣኔ — ሀብታዊና ወታደራዊ ዕርዳታ ሰጥተዋል ። ጀግኖቹ የቬዬትናም ሕዝቦች ፣ በዚህ ዕርዳታ እና በዓለም አቀፍ አንድነት በመደገፍ ፣ ጦርነት ለማቆምና ሰላምን እንደገና በቬየትናም ውስጥ ለማቋቋም አስችሏቸዋል ። ለአረቦችም እስራኤልን ለመቋቋም ሲባል ከእነኚህ አገሮች ዕርዳታ ተደርጓል ።

ኮሚኒስቶች ሁል ጊዜምና አሁንም ለጸረ — ኢምፔሪያሊስት የጦርነት የወረራ ፖሊሲ ፣ ለሕዝቦች የሰላምና የጓደኝነት ትግል ግንባር ቀደም ናቸው ። የኒውክሌር ሙከራዎችን ዕድሜ ለማሳጠር ባላቸው የመከላከል ጥረት ምክንያትና በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. እንደነዚህ ዓይነት ሙከራዎችን በሶስት አማካዮች ለማገድ — በመሬት ላይ ፣ በአየር ውስጥ ፤ ከባሕር በታች — ዓለም አቀፋዊ ስምምነት ተፈረመ ። የኒውክሌር መሣሪያዎችን መራባት ለማገድ በ፲፱፻፷፱ ዓ ም ስምምነት ተደረሰ ። የኒውክሌር ጦርነትን አደጋ ለመቀነስ የተወሰደው ዋና እርምጃ በግንቦት ፲፱፻፸፪ ዓ ም በሞስኮ የተፈረመው ፣ የጸረ አህጉር አቋራጭ ሚሳይል መጠን የመወሰን ውልና በአንዳንድ ሁኔታዎች ስትራቴጅያዊ የማጥቂያ መሣሪያዎችን ለመወሰን በሚመለከት ረገድ የተደረሰው ጊዜያዊ ስምምነት ነው ። እንግዲህ ሶቪዬት ሕብረት እላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ለመቋቋምና ለመግታት ሲባል (ኢምፔሪያሊስቶችን) የሰላም ፕሮግራም አውጥታለች ።

## መደምደሚያ ፤

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ሰዎች ያለ መርገም ፣ ያለ ጭቆና ያለ በሽታ ፣ ያለ ረሃብና ያለ ኃይል የሚመራ ኑሮ ሲአልሙ ነበር ። ከነዚህ ሕልሞች የተወለዱት ስለገነት ሃይማኖታዊ እምነት ፣ እና ያለፈው « ወርቃማው ጊዜ » በማለት የማሰብ ዝንባሌ ፣ እናም ደፋሩ ግን የዋሁ አስተሳሰብ ፣ ቆንጆውን ፣ ብሩሁን የወደፊቱን ሕብረተሰብ በዓይነ ሕሊና መማተር ነበር ።

ከነዚህ ሕልሞች የማይመሳሰለው ፣ ስለኮሚኒስት ሕብረተሰብ የማርክሲስቶች ሀሳብ ፣ በሳይንሳዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ። የኮሚኒስት ሕብረተሰብ ሊደርስበት የማይችል ራቅ ብሎ ስለወደፊቱ ያልታቀደ ሀሳብ አይደለም — በመሠረቱ የሚአድገው ከሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች ነው ፣ በአዲስና ከፍተኛ መልክ ባለው የጉልበት ድርጅትና የሕብረተሰብ ኑሮ ከሚተካው ነው ።

## ሰ ላ ም

ጦርነት ፣ ማለትም ፣ በመሣሪያዎች በመጠቀም የሚገኝ ኃይል ፣ ሁልጊዜም ቢሆን የመጨቆኛ መሣሪያ ነበር። ሚሊዮን ያህሉን ለመርገጥ በሺ. የሚቆጠሩትን መግደል የጦርነት ተግባር ነው ።

ሁሉንም ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ በማስወገድ ኮሚኒዝም ጦርነትን ያስወግዳል ፡— ጭቆና በሌለበት ሕብረተሰብ ውስጥ የመሣሪያ ኃይል — ጦርነት — ጊዜው ያለፈበትና ቂልነት ነው ።



ለዘመኑ ሰው ዓለምን ፣ ያለ አቶም ቦንብና ያለወታደራዊ ጦር ሰፈር ፤ ያለ ሰራዊት ፣ ያልተከፋፈሉ ድርጅቶችና ፣ ያለ ወታደራዊ ምስጢሮች፤ ያለ ጥብቅ ቁጥጥር ወሰኖችና ግዛታዊ ባሕሮች ፣ ያለሰላዮች ድርጅትና ያለሰላዮች ለማለም በጣም ችግር ነው ። ማለትም በሌላ አባባል ፣ ስለዓለም ያለነዚያ ነገሮች ሁሉ የሚአስደንቅ ወይም ዕውነት ያልሆነ ምንም ነገር የለም ። ሶሻሊዝም በዓለም በሙሉ ከመንሰራፋቱ በፊት እንኳ ጦርነትን ማስቀረት እንደሚቻል እንተማመናለን ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ ባለው የረጅም ጊዜ ታሪክ ያሳለፈው የሥቃይና ፣ የጥፋት ዘመን አሁን የእፎይታ እስትንፋስ ሊተነፍስ ይችላል ። የጥፋት መሣሪያዎችን በመሥራት ለትርጉም የለሹ የሰዎች ጥረት ብልሽት ዕድሜው የሚአጥርበት ቀን ይመጣል ። በሁሉም አገሮች ያሉ በሺ የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች፤ አሁን የጥፋት መሣሪያዎችን የሚያመርቱት ፣ የሰዎችን ዕለታዊ ፍላጎት ማርኪያ ዕቃአዎችን ወደማምረቱ ይሰማራሉ ።

አዲስ ፣ ሰፊ — አስተያየት ለሳይንስ ይከፈታል ። በአሁኑ ወቅት በምርምር ሥራ ላይ ከዋሉት $^{2}/_{3}$ኛዎቹ አዲስ ዓይነት መሣሪያዎች እና እራሳቸውን የመከላከያ ዘዴ በመሥራት እረፍት የላቸውም ። ጥረታቸውን ለአዲስ ዓይነት ኢነርጂና ማቴሪያል ወደፊት ያውሉታል ። የሰውን ልጅ ኑሮ ተወዳጅና ቀላል ለማድረግ ማሺኖች ይሠራሉ ። እናም ሰውን ለብዙ ዘመን እንዲኖር በሽታ የሚጠፋበትን መንገድ ይሻሉ ።

በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ በጣም አስቸጋሪ የሆኑ ፕሮብሌሞችን ለመወጣት ካሉት ኃይሎች ጋር ይተባበራል ። በሕብረተሰቡ ውስጥ ተደብቆ ያለው ግዙፍ ችሎታ እንዲህ ላሉት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ለመፈለግ ያስችላል ። እንደምግብ እና ውሃ ፣ ምድረ በዳን እንደመለወጥ ፣ ረግረግና ሜካውን ፣ የአካባቢ መከላከሉን (ከቁር ፣ ከሐሩር ፣ ከበረድ ፣ ወዘተ...)፣ በውቅያኖስ ውስጥ ስላለው ይህ ነው ስለማይባለው ሀብት የመጠቀም የመሳሰሉ ችግሮችን መወጣት ማለት ነው ።

በአሥር ዓመታት (In decades) ውስጥ የአንዳንድ ሀገሮች ባሕላዊ ወደኋላ መጐተትን ማስወገድ ይቻላል ። « ለዘላለም ማስወገድ » ማለት በካፒታሊስቶች የተፈጠረውን የዓለም ሕዝብን ለመቀነስ ወረርሽኝና ጦርነት ያስፈልጋል የሚለውን ሐሳብ አስተያየት ያለውን ኢሰብአዊ ንድፈ — ሀሳብ ይሆናል ፣ ትርፍ ጉልበትን ማስወገድ ለሠራተኛ ሕዝቦች ደህንነት ከመሥራት ይበልጥ ጥቅም አለው የሚለውን ማለት ነው ።

የሕዝብ ብዛት ችግር የሚኖረው በኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር ሥር ነው ። በአገሮች መካከል ያለው የምጣኔ—ሀብት አለመመጣጠን ወዲያው እንደተወገደ ፣ ረሃብ ፣ ድህነት ፣ መልከኛና ቅድመ — መልከኛ የሕብረተሰብ ግንኙነቶች ሲጠፉ ፣ ሴቶች ነጻ ሲወጡና አዲሱ ትውልድ የብሔራዊ ጥንቃቄ ሲቋቋምለት ፣ በሶሻሊስት አገሮች እንደሆነው ሁሉ የሕዝብ ብዛት ችግር እራሱ በራሱ ይወገዳል ፣ ይሞታል ።



በመሬት ላይ ለሁሉም በቂ የመኖሪያ ቦታ ፣ ምግብና ውሃ አለ ፣ ይህም ሊሆን የሚችለው የሁሉም ጥረት ፣ የፈጠራ ሥራ በሰላም ላይ ከተከማቸ ፣ ከተወሃደ ነው ።

## ሥራ

በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ውስጥ የሥራን ባሕርይ በአጭሩ እንመልከት ። ባለፉት ሕብረተሰቦች ሁሉ ሰው ከሁሉም በፊት የሚሠራው ለራሱና ለቤተሰቡ ምግብና ልብስ ለማቅረብ እና እራሱን በእርጅና ጊዜ የመጠበቅና ልጆች የመውለጃ ዘዴን ፣ ማለትም ዋና አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ነው ። ሰው ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራና ያለ ጉልበቱን በዚያ ላይ እንዲአጠፋ ተገዷል — ለመኖር ሲል ። ሥራውን የማጣት ፍርሃት አለበት ፣ አንዳንዱም ለማረፍ ሲፈልግ ሥራውን ያማርራል ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ሰዎች ስለሥራ ያላቸው አስተያየት ሙሉ በሙሉ ይለወጣል ። ሁለተኛ ላይ መለስ ሥራ አጥነት ድራሹ ይጠፋል ። ሁለንታዊ የሆነ ትምህርት እያንዳንዱ ሰው የሥራ ሥምሪቱን እንዲመርጥ ያስችለዋል ። የሶሻሊስት መንግሥት በጤና አገልግሎት ፣ በትምህርት ፣ በሕጻናት እያያዝና በሕብረተሰብ ደህንነት የሚአጠፋው ብዙ ገንዘብ ፣ የሠራተኛውን ሰው የወደፊት ሥጋትና ስለልጆቹ ያለውን ሀሳብ ያስወግድለታል ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ሰዎች የሚሠሩት በረሃብ ፍርሃት እየተተነኮሱ ሳይሆን ፣ ግን ምክንያቱም ደህንነታቸው ፣ ድሎታቸው መሻሻል የሚመጣው በሁሉም የሕብረተሰቡ አባላት በተባበረ የፈጠራ ጥረት(Creative effort)

መሆኑን ስለሚገነዘቡ ነው ፣ እናም ምክንያቱም የሚሠ
ሩት ሥራ እራሳቸው የመረጡትና ደስ የሚላቸው ስለሆነ
ነው ። በሶሻሊዝም ውስጥ ያሉ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ
የሆኑ ሰዎች ፣ ከጨዋታዎች ፣ ወይም ከስፖርቶች ፣ ወይም
ከሌላ ዓይነት መዝናኛዎች ሁሉ ይበልጥ ሥራ ደስ ይላቸ
ዋል ። ይህ ሊሆን የቻለው የሥራ ሁኔታ ስለሚለወጥ ነው።
ይበልጥ ውስብስብ ፣ እንደ አንድን ነገር የመፍጠር ሃሳ
ብና ምናብ ብዙ የጡንቻ ኢነርጂ የማይፈልግ ስለሚሆን
ነው ።

ሳይንስ ቀጥተኛ የምርት ኃይል እየሆነ መጥቷል ፣
ግን ዛሬ ለሱው የሚሰጠው ጥቅም ወደፊት ከሚአስገ
ኘው በጣም ቅንጣት ያህሉን ነው ። በአባሎች የተባበረ
ጥረት ፣ ሕብረተሰብ ሰውን ለሕይወት ዋና አስፈላጊ የሆኑ
ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን ነገሮች እንዲአገኝ የሚአረ
ጋግጡ ሰፊ የምርት ኃይሎች ዕድገት ይገኛል ።

የኮሚኒዝም ዋና መርሕ — ለእያንዳንዱ እንደች
ሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጐቱ — በተግባር ይው
ላል ፣ ይህም ለሕብረተሰቡ ሙሉ እኩልነት ማለት ነው።

## እ ኩ ል ነ ት

ሕብረተሰብ ለሁሉም አባሎቹ በእኩልነት ሁኔታ
ሁሉንም የሚፈልገውን ሊአረካ ይችላልን ? ጸረ — ኮሚ
ኒስቶች ይህ ሊሆን እንደማይችል ያናፋሉ ። ዓለምን የሚመ
ለከቱት ከዘመናዊ ካፒታሊስት ሕብረተሰብ ውስጥ በመ
ሆን — የግል ባለቤትነት ከሰፈነበትና የሰው ጠቃሚነትም



የሚወሰነው ባለው ቁሳዊ የንብረት መጠን ነው ከሚለው —
ስለሆነ እነርሱ የሚሉትን ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም።
ግን እስቲ ለጥቂት ጊዜ ብዙው ቁሳዊ — ሀብት የሕብረ
ተሰቡ የሆነበትን ሕብረተሰብ እንመልከት ፣ አንድ ሰው
ይህን ሀብት የሚጠቀምበት አስፈላጊዎቹን ነገሮች ለማ
ግኘት ነው — በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ደረጃ ለመ
መሥረት አይደለም ።

በሰፊው የሥራ ውጤት እየጨመረ ከመሄድ ጋርና
በምርት መገልገያዎች ፍጹም የሕዝብ ንብረትነት መስ
ፈን ፣ ለሕብረተሰቡ እያንዳንዱ አባል ፍላጐት መርካት
በጣም አስቸጋሪ ተግባር አይመስልም ይሆናል ። ኮሚኒ
ዝም በሕብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ ፍትሕ ይመ
ሠርታል ፣ እያንዳንዱ አባል የቻለውን ያህል ለሕብረተ
ሰቡ ፣ ሕብረተሰቡ በተራው ለእሱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮ
ችን ሁሉ ማርካት ይላል ።

የኮሚኒስት እኩልነት በገጠርና በከተማ ያለን የሕ
ብረተሰብ የምጣኔ — ሀብታዊ ልዩነት በማስወገድና እን
ዲሁም በገጠርና በከተማ በባሕላዊ ደረጃና በኑሮ ሁኔታ
ያሉ ልዩነቶችን በማጥፋት ይታያል ። የእርሻ ሥራ ከኢ
ንዱስትሪ ሥራ ተመሳሳይ ይሆናል ፤— ምንም ዓይነት
ልዩነት አይኖረውም የተለያዩ የሥራ መስኮች ከመሆና
ቸው በቀር ።

አንድ የሆኑ የኮሚኒስት የምርት መገልገያዎች ባለ
ቤትነት መቋቋም እና የመደብ ልዩነቶች መወገድ በመ
ደብ አልባ ሕብረተሰብ መታየት ከፍተኛውን ደረጃ ይደ
ርሳሉ ። እርግጥ ፣ ሰዎች በችሎታቸውና በገጠመኞቻ

ቸው ይለያያሉ ፣ እናም የሕብረተሰቡ ፍትሕ በችሎታና በገጠመኝ እኩል ያደርጋቸዋል ማለት አይደለም ፣ ግን ለእያንዳንዱና ለሁሉም ለመናገርና በደንብ (በፈጠራ) ለመሥራት በጣም አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ ማለት እንጂ ።

## ነጻነት

ነጻነት ከእኩልነት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ነው የሚሄደው ፣ ምክንያቱም ነጻ የሆኑ ሰዎች ናቸው እኩል የሚሆኑት ፣ እናም እኩል የሆኑ ሰዎች ናቸው ነጻ የሚሆኑት ።

የሶሻሊስት አብዮት ሠራተኛ ሕዝቦችን ከብዝበዛ ነጻ አውጥቷል ። የሕብረተሰብ ተከታታይ ዕድገት የታለመው ሰው ነጻ በሆነ መንገድ የመፍጠር ችሎታውን በተግባር ላይ እንዲአውልና እንዲአሳድግ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ነው ።

ከፍተኛ የትምህርትና ባሕላዊ ደረጃዎች ከዋናው ሥራቸው በላይ የሥራ መስካቸውን እንዲአስፋፉ ያስችላቸዋል ። ሌሎች ችሎታዎች ለማሳደግና በተግባር ለማዋል ይችላሉ ። በሌላ አነጋገር ፤ በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለ ሰው ያለምንም ተፅዕኖ ያድጋል — ጤናማ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሞራላዊ ፣ በጥሩ ሕብረተሰብ የተቀረጸ ሰው ።

ነጻነትን በሚመለከት ረገድ ለአንድ ግለ — ሰብ ዕድገት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ የእያንዳንዱ ሰው በኮሚኒስት የሕዝብ የራስ — አገዛዝ ውስጥ ያለው ተሳትፎ ነው ።



በኮሚኒዝም ውስጥ ሥራ የአንድ ሰው ዋና አስፈላጊው ነገር ይሆናል ። ለሕዝባዊ አገልግሎቶችም እንደዚሁ ነው ።

በራስ አገዛዝ ውስጥ የሁሉም ተሳትፎ ፣ እና ከፍተኛ ደረጃ የንቃት ዲሲፕሊን አንድነት በመሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ የአጠቃላይ መዋቅሩን ያለ እንከን መሥራትና መካሄድ ያረጋግጣል ። ይህ ነው የነጻነት ክብረ ሕሊናዊ ጐን የሚመጣበት ። አንዳንድ ሰዎች ነጻነትን ድንበር የለሽ አድርገው ይገነዘቡታል ። ማንኛውንም የፈለጉትን ነገር የማድረግ ነጻነት ፣ ከሕግና ከሥርዓት ወጭ የሆነና ከቀረው ማኅበረ — ሰብ ዝንባሌ ባፈነገጠ ሁኔታ ማለት ነው ። ሁሉም በዚህ ሁኔታ የሚሠራ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ነጻነት ሳይሆን ሥርዓተ — አልባነት ነው ።

ነጻነት በሕብረተሰቡ ውስጥ ማለት ከሕብረተሰቡ ነጻ መሆን ማለት አይደለም ። እውነተኛው ነጻነት ማለት ግለሰቡ አስተሳሰቡን እና ድርጊቱን ከማኅበረ — ሰቡ ጋረ የሚአስተባብርበት ነው ። ግለሰባዊና ማኅበራዊ ዝንባሌዎች በሰዎች አእምሮ ውስጥ አንድ ሲሆኑ ፣ ከሕብረተሰቡ ጥቅም ሌላ የሚአስቡት ነጻነት ሊኖር አይችልም ። በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ውስጥ የሚንሰራፋው የኮሚኒዝም ገንቢዎች የነጻነት ፅንሰ ሀሳብ ይህ ነው ።

## ወንድማማችነት

ዕኩልነትና ነጻነት ባሉበት ፣ የሁሉም ሠራተኞችና አገሮች ወንድማማችነትም የኑሮ መንገድ ለመሆን ይተባበራሉ ። ስለወንድማማችነት ግንኙነቶች ስንናገር ፣

እነዚህ ከጓደኝነት እና ከጓዳዊ ግንኙነቶች ይበልጥ እንደ ሆኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው ። በሕዝቦች መካከል የከፍተኛ መተሳሰርና መረባዊ መወሳሰብ መልኮች ናቸው ። የወንድማማችነት ፅንሰ — ሀሳብ ያለ እሱ ኮሚኒዝም ሊገኝ የማይችልበትን በሰዎች መካከል ዕውነተኛ ሰብዓዊ ግንኙነቶችንና ጥብቅ መተማመን የማሸፍን ነው ።

እነዚህ ግንኙነቶች በጋርዮሻዊ ፣ በሕብረትና በእርስ በርስ መረዳዳት መንፈስ የተጠቃለሉ ናቸው ። በጋርዮሽ ውስጥ ፣ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ጥገኛ ናቸው ፣ እናም የጋራ ግባቸው የሚመጣው እያንዳንዱ በሚአወጣው ጥረት ነው ።

ወደ ኮሚኒዝም በመሸጋገር ጊዜ ፣ የጋርዮሻዊ መንፈስ ፣ በሕዝብ ንብረትንነት መቋቋም የሚመጣው ፤ በማያቋርጥ ሁኔታ ለማደግ ይተሳሰርና አዲስ መልክ ይይዛል ።

ኮሚኒዝም በተናጠል ሊገነባ አይችልም ፣ ይህ መሪ የሆኑት በአንዳንድ ምክንያት ወደኋላ የቀሩትን በመርዳት በተባበረ ጥረት ብቻ ነው የሚሠራው ። ይህ ነው ማርክሳዊ መርሆ ። ሁሉም ሶሻሊስት አገሮች አዲስ ነጻ የወጡ ፣ አዳጊ የእስያ ፣ የአፍሪቃና የላቲን አሜሪካ አገሮችን በሚረዱበት ጊዜ የታዩ የመለኪያ ጠባይ ነው ።

## ደስታ ፤

ኮሚኒዝም ማለት እኩልና ነጻ የሆኑ እራሳቸውን ወንድማማች አድርገው በሚወስዱና በሚኖሩ ፣ ለማያቋርጥ የሰላም ሁኔታ የሚሰሩ ሰዎች ጥበባዊና ዕቅዳዊ ሥራ የሰፈነበት ሥርዓት ነው ።




ምናልባት በመላው ዓለም በትክክል አንድ ዓይነት የሆነ የደስታ ሀሳብ ያላቸው ሁለት ሰዎች አይኖሩም ይሆናል ። አንዱ የሚተረጉመው በዕለታዊ ጥቃቅን ነገሮች ላይ ምንም ጊዜ ሳያጠፋ እራሱን በራሱ በግል ሥራው ላይ የሚገዛበት መንገድ ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ ያለ ሕዝባዊ ግልጋሎትና ክንዋኔ ደስታ የለም ብሎ ይወስደዋል ። እንደገና ሌላው ለከፍተኛ ቁሳዊ ደረጃዎች ፣ ለጥሩ ምግብና ላማሩ ልብሶች ያደርገዋል ። ብዙዎች ስፖርትን በማንሳት እርግጠኛ ናቸው ፣ እናም እርግጥ ፍቅርን ፣ ቤተሰብ መመሥረትንና ወላጅ መሆንን ሁሉ — ሁሉም እንደዕድሚውና እንደተፈጥሮው ይመለከተዋል ። በኮሚኒስት ሕብረተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ የኑሮ መደሰቻዎችን በሙሉ ድርሻውን ሊካፈል ይችላል ።

እርግጥ ፣ በኮሚኒዝም ማንም ለግላዊ ደስታው የሚሯሯጥ የለም ። የሕዝቦች ኑሮ በብዙ መንገዶች የተቀረጸ ነው ። የዘላለም ሥቃይንና ያለመርካት ፣ የተስፋ መቁረጥ ፣ የምቀኝነትና የአልፎ ሂያጅ ፍቅር (Un requited love) ግጭቶችን ማቆም ይቻላል ። ስለዚህ ኑሮ ለጸሐፊዎች የኮሜዲ ፤ የድራማና የትራጀዲንም ቢሆን ሰፊ ሜዳ ይሰጣቸዋል ። የሀሳብ ደካማነትን የሚገልጽ ጹሑፍም አይቀር — ሰው ያለበትን ችግር ለመወጣት ሁልጊዜ ወደሳቅ ያመራል ።

ሰው ሁልጊዜ ወደፊት ይጓዛል ። ምናልባት ፣ የዚህ እንቅስቃሴ አካል መሆናቸው ፣ ርምጃቸውን ከጊዜአቸው ጋር የሚወጥኑ መሆናቸውን ከመገንዘብ ደስታ በቀር ሌላ የሚአስደስታቸው የለም ።

Proudly Brought to you
By
www.binyamhk.wordpress.Com



ዋጋ 2.25 ብር